*Ronald Dunn*

# የጸሎት ኀይል

## የምልጃ ጸሎት አስደናቂ ኀይል

ተርጓሚ

ጳውሎስ ፈቃዱ

"Don't just Stand there, Pray Something"
ከተሰኘው የሮናልድ ደን መጽሐፍ የተተረጐመ፡፡

የካቲት ፳፻፭ ዓ.ም  የመጀመሪያ እትም

ተርጓሚና አሳታሚ  ጳውሎስ ፈቃዱ

ይህንን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ በማንኛውም ዐይነት መንገድ ለማባዛት በቅድሚያ ከተርጓሚው ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

Copyright© 2013 Paulos Fekadu

*በዚህ መጽሐፍ ከሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡-*
አ.መ.ት የሚለው በ1993 ዓ.ም ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣
የ1997 ትርጉም የሚለው በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ ከታተመው አዲስ ትርጉም፣
ሕያው ቃል የሚለው ደግሞ በ1988 እ.ኤ.አ ከታተመው ሲሆን፣
የቀሩት በሙሉ ከቀኃሥ ትርጉም (1954 ዓ.ም) የተወሰዱ ናቸው፡፡

የሽፋን ሥዕል - ልዑል ገብርኤል

የተርጓሚው አድራሻ
የመ.ሣ.ቍ. 6394
አዲስ አበባ

e-mail: paulosvictory@yahoo.com
paulosvictory@gmail.com





ለሚጸልዩልኝ ሁሉ

# ስጦታ

ለ________________

________________

________________

________________

________________

ከ________________



# ስለምትጸልዩት ነገር ተጠንቀቁ ...

ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርኩ ለማገልገል አሰቤ በ1975 እ.ኤ.አ የመጋቢነት አገልግሎቴን ስለቅ፣ የትኛውንም የአገልግሎት ጥሪ በገንዘብ የተነሣ እንደማንሰርዝ ከሚስቴ ከካዬ ጋር ተስማምተን ነበር፡፡ ብዙም ሳልቆይ ግን ኑሮዬ ከእጅ ወደ አፍ መሆን ጀመረ፡፡

በአንድ የ“ሚሲዮናዊነት” ጉባኤ ላይ እንድንሳተፍ ጥሪ ቀረበልን፡፡ ካዬም ሆነች እኔ እግዚአብሔር የዚያ ስብሰባ ተሳታፊ እንድንሆን እንደሚፈ ልግ በጣም ተሰምቶናል፤ ችግሩ ግን ጠቅላላ ወጪው ወደ 1,000 ዶላር ገደማ ይደርሳል - ይህ ደግሞ በእጃችን ካለው ገንዘብ በ990 ዶላር ይበልጣል፡፡ ቢሆ ንም ገንዘቡን የጸሎትና የእምነት ጉዳይ አድርገን ጥሪውን ለመቀበል ወሰንን፡፡

በርካታ ወራት ዐለፉ፡፡ ዕለቱ ዓርብ ነበር፤ ወደ ጉባኤው ለመሄድ ዕቅድ የተያዘው በቀጣዩ ቀን ነው፡፡ ገንዘቡ ግን አሁንም የለም፡፡ የዚያን ቀን ሽመታ ስናካሂድ ቈየንና እኩለ ቀን አካባቢ መኪናችንን ወደ ቤታችን መግቢያ አካባቢ አቆምን፡፡ በአጥሩ በር በኩል ዐልፌ ወደ ኋላው በር ስጓዝ የሆነ ነገር አደናቀፈኝ፡፡ በነጭ ሸራ የተሠሩ እንግዳ ከረጢቶች ደጃፋችን ላይ በሥርዐት ተሰድረው አየሁ፡፡ በየከረጢቶቹ ላይ ዴንቨር ሚንት፣ 50 ዶላር፣ የ1975 ዝርዝር ሳንቲም የሚል ጽሑፍ ታትሞባቸዋል፡፡

በችኮላ ከረጢቶቹን ቈጠርኳቸው - ሃያ! ያም የ1,000 ዶላር ዝርዝር ነው፡፡ እነዚህ ከረጢቶች ከየት እንደ መጡ ባላውቅም፣ በፍጥነት የሆነ ነገር ማድረግ ነበረብኝ፡፡ በየከረጢቶቹ ሥር በቀኝ በኩል የአካባቢው ባንክ ስም ይታያል፡፡ ስልክ ደወልኩ፡፡

“ሳውዝዌስት ባንክ፡፡ ምን ልርዳዎት?”

“እህ፣ ሄሎ፣ እህ፣ ይኸውላችሁ፣ እህ፣ የሆኑ ዝርዝር ሳንቲሞች ጠፍተዋችኋል?”

“ምን አሉኝ?”

በመጨረሻ ከአንዲት ሴት ጋር አገናኙኝና ታሪኬን ስነግራት፣ የጠፋ ገንዘብ ስለ መኖሩ ምንም የምታውቀው ነገር ባይኖርም፣ የባንካቸው ስም በከረጢቶቹ ላይ ስለ ተጻፈ ሰው ልኮ እንደምትወስዳቸው ነገረችኝ፡፡

"አይሆንም፤ እንዲህማ አታድርጊ" አልኩ የሆነ ነገር ድንገት ትዝ ብሎኝ። "አሁን ከየት እንደ መጡ ሳላውቅ አልቀረሁም።"

አመከንዮ። ሳንቲሞቹ የተገኙት እኔ በር ላይ ነው። ሆን ተብለው በሚያምር መልኩ ተደርድረዋል። አንድ ሺህ ዶላር። የእኔ ገንዘብ። የእኔ ጸሎት።

አንድ ልዩ ጓደኛ አለኝ። መክፈል እንዳለብኝ የማላምንበትን ክፍያ እንደ ተጠየቅሁና ይህንንም በጥሬ ገንዘብ - በዝርዝር ሳንቲም ለመክፈል እንዳሰብኩ ከጥቂት ወራት በፊት ሰምታ ነግሬው ነበር። በዚህ መካከል አሁን ስለሚያስፈልገኝ ገንዘብ አንዳችም የማያውቀው ይህ ወዳጄ አንዳንድ ነገሮችን ሸጠና ለአገልግሎቴ 1,000 ዶላር ስጦታ ለመስጠት ወሰነ። ክፈል የተባልኩትን ገንዘብ በዝርዝር ሳንቲም ስለ መክፈል የተናገርኩትን አስታውሶ 1,000 ዶላር በዝርዝር ሳንቲም ከዴንቨር ማርት ድረስ ተጭኖ እንዲመጣ ከአካባቢው ባንክ ጋር ዝርዝር ዕቅድ አዘጋጀ።

ከረጢቶቹ እኔ ዘንድ የደረሱት እንዲህ ነው። ምን እንደምትጸልዩ ተጠንቀቁ ... እግዚአብሔር ይመልሰው ይሆናልና እንደ ማለት ነው። በእኛ ጉዳይ እግዚአብሔር ጸሎታችንን ብቻ አልሰጠንም - በጥሩ ሁኔታ ነው የመለሰው።



## ማውጫ


መግቢያ - በመጀመሪያ .............................. 9

### ክፍል አንድ: የእግዚአብሔር ታላቅ ሐሳብ

፩ - በቃ አድርጉት .............................. 13
    ጸሎት የሚጠይቀው የእምነት ዐይነት
፪ - እንደ እኛ ዐይነት ሰዎች .............................. 23
    ኢየሱስ ለታላላቅ ሥራዎች የሰጠው ተስፋ እንዴት እንደሚፈጸም
፫ - "ለመንግሥታዊ ጉዳይ ብቻ" .............................. 35
    በኢየሱስ ስም መጸለይ
፬ - እግዚአብሔር ጸሎትን ለምን እንደሚመልስ. .............................. 43
    ታላቁ ምክንያተ ጸሎት

### ክፍል ሁለት: የምስጢራዊው መንግሥት ምስጢራዊ የጦር ዕቃ

፭ - የዓለማቱ ጦርነት .............................. 51
    እውነተኛው ፍልሚያ ያለበት ስፍራ
፮ - ሦስት ኀናዊ ጸሎት .............................. 60
    ከደፋር፣ ግትር ምልጃ የሚገኝ ትምህርት
፯ - ይዞታውን ማግኘት .............................. 70
    የምልጃ ጸሎት ልብ
፰ - ለሌሎች መጸለይ .............................. 78
    የቅዱሳን ጸሎት ኀይል
፱ - የእግዚአብሔር የጸሎት ዝርዝር .............................. 87
    ጸሎት ላይ ላሉን አንዳንድ ጥያቄዎች የሚሆኑ መልሶች
፲ - ለጠፉት መጸለይ .............................. 98
    ለኢአማንያን እየጸለያችሁ ነው?

## ክፍል ሦስት: የሚጸልይ ሕይወት

፲፩ - ሁለት ሁኔታዎች ........................ 113
*ጸሎቱንና ጸላዩን መመልከት*

፲፪ - በእርሱ መኖርን መማር........................ 117
*ፍሬ ማምረት ሳይሆን፣ ማፍራት*

፲፫ - የእርሱ ቃሎች፣ የእኛ ፈቃድ ........................ 126
*በእግዚአብሔር ቃል ቁጥጥር ሥር መሆን እና መንጻት*

፲፬ - ጾም፡- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥናት........................ 133
*ለመጸለይና ጌታን ለመፈለግ ዐይነተኛው ሁኔታ*

## ክፍል አራት: የሚያደምጥ ሰማይ

፲፭ - እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚመልሰው ጸሎት ........................ 147
*አንዳንድ የጸሎት ለምኖች እና አንዴቶች*

፲፮ - ዝምታ በሰማይ ........................ 162
*የእግዚአብሔር ሉዐላዊነት ምስጢር*

፲፯ - እግዚአብሔር ጸሎትን እንዴት እንደሚመልስ........................ 168
*አንዳንድ መንገዶቹ ላይ ምልከታ*

፲፰ - እስከ መቼ? ........................ 179
*ጸሎትን መቼ ማቆም እንዳለብን መወሰኛ ሦስት መንገዶች*

፲፱ - የምትጸልይ ቤተ ክርስቲያን በአረማዊ ዓለም........................ 184
*የቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ ኀይል መመልከት*

፳ - ቤተ ክርስቲያን ስትጸልይ ........................ 195
*የሪቫይቫል "ምስጢር"*

ምስጋና ........................ 207

የተርጓሚው ሌሎች ሥራዎች ........................ 208



# በመጀመሪያ

በ1972 እ.ኤ.አ በመጋቢነት የማገለግልባት ቤተ ክርስቲያን በሳምንት ሰባት ቀናት ለሃያ አራት ሰዓት ምልጃ የሚካሄድበት የጸሎት አገልግሎት ጀመረች፡፡ እግዚአብሔር ለተወሰኑ ጊዜአት ለጸሎት ሲቀሰቅሰን ቈይቶአል፡፡ ሳምንቱን ሁሉ በምሳ ሰዓት ወይም ከምሽቱ ቀደም እያሉ የተለያዩ ሰዎች ለጸሎት ይሰባሰቡ ነበር፡፡ ለሦስት ወራት ያህል ስለ ምልጃ ጸሎት ሳስተምር ቈይቼ ነበርና ማክተሚያው የጸሎት አገልግሎታችን ተመርቆ መከፈት ሆነ፡፡ አዲስ የጸሎት አገልግሎት ለመፍጠር አላዋቀርንም፤ ቀድሞውንም የተፈጠረውን አገልግሎት አዋቀርን እንጂ፡፡

የምልጃ ጸሎቱ የተጸለየላቸውን ሰዎች ሕይወት በከፍተኛ ደረጃ ለውጧል፤ ጸሎቱን ሲያካሂዱ የነበሩትንም ሰዎች እንደ ለወጠ አምናለሁ፡፡

ደግሞም፣ አንድ መጽሐፍም መኖር ነበረበት፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያውን ረቂቅ በ1973 ጨረስኩ - ከዚያም ለዐሥራ አምስት ዓመት ያህል አስቀመጥኩት፡፡

ከዚያም እያንዳንዱ የሰበክሁት ነገር እየተፈተነ በተለያዩ ቀውሶች መካከል በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ የኖርኩባቸው ዓመታት መጡ፡፡ ስሰብከው የነበረው እውነት እንደ ሆነ ተረዳሁ - ቀለል አድርጌ ሰበክሁት እንጂ፡፡ ይህን መጽሐፍ ለመጨረስ እስካሁን በመጠበቁ ደስተኛ ነኝ፡፡

# ክፍል አንድ

# የእግዚአብሔር ታላቅ ሐሳብ

## ፩ - ጸሎት የሚጠይቀው የእምነት ዐይነት

# በቃ አድርጉት

ጸሎት ማለት ...

*ኢይደለም፣ እንደገና ጀምር፡፡*

ጸሎት ማለት ...

*እንዴ! ትኩረትህን ሰብስብ!*

ጸሎት ማለት ...

ይቅርታ - ተገቢውን የጸሎት ምስል በሐሳቤ ለማምጣት አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞኛል፡፡ ስለ ጸሎት ሳስብ ምን ዐይነት ምስል እንደሚመጣልኝ ታውቃላችሁ? ከልጅነቴ ጀምሮ ነው ይህን የማስበው፡፡ ትዕይንቱ በምድረ በዳ የሚገኝ ትንሽዬ የሚሲዮን ጣቢያ ነው፡፡ ከፊት ለፊቱ ጠጕራቸውን የተላጩ፣ ከርዳዳ ቡናማ ቀሚስ ለብሰው (ሞቃት መሆኑን ማሰቡ ራሱ ያሳክከኛል) ወገባቸውን በረጅም ገመድ የታጠቁ መነኩሴ ቆመዋል፡፡ በጸሎት እንደ ተዋጠ ሰው እጆቻቸውን አጋጥመዋቸዋል፤ ሲታዩ ትሑትና ዐቅመ ቢስ፣ ከዚህ ዓለም ያልሆኑ፣ ያልተወሳሰቡ እና የተመጣጠነ ምግብ ያላገኙ (ምናልባት ከጾም የተነሣ) ይመስላሉ፡፡ እዚያ ሆነው፣ ተወጥሮ ከተያዘው ልጓማቸው የተነሣ ከአፍንጫቸው ነበልባል እየወጣ በሚያሽካኩና እየተትጎለጎለ በሚነሣ የአቧራ ዳመና መካከል በእግራቸው መሬቱን በሚፎግሩ ፊት ለፊታቸው ያሉ ፈረሶች ላይ በተቀመጡ ፈረሰኞች ላይ አትኩረዋል፡፡ ፈረሰኞቹ (ልባቸው ንጹሕና ፍርሀት የማያውቃቸው ይመስላሉ) በኮስታራ ፊታቸው ላይ ቍርጠኝነት እየተነበበ የጦር መሣሪያቸውን መዘዙ፡፡

መነኩሴው አብረዋቸው ስለ መሄድ የሆነ ነገር ተናገሩ፡፡

“እርስዎ ብርቱ ሰው ኖት አባ” አለ ፊቱን በጭምብል የሸፈነው ሰው፤ “ነገር ግን አደገኛ ነው የሚሆነው፡፡ ሰላማዊ በሆነው ቦታ እዚሁ ቢቈዩ ይሻላል፡፡”

"ቢሆንም መርዳት እፈልጋለሁ" መለሱ መነኩሴው::

ጠንካራው፣ ነገር ግን ደጋግ ዐይኖች ያሉት ባለ ጭምብሉ ሰውዬ ዐይኖቹን በእኚህ የእግዚአብሔር ሰው ላይ ተከለ:: "መጸለይ ይችላሉ::"

ድንገት ግዙፉ ነጭ ፈረስ በኋላ እግሮቹ ቆሞ የፊት እግሮቹን ወደ ላይ አነሣ:: ጋላቢውም ባርኔጣውን በእጆቹ ብድግ አድርጎ "ሄይ፣ ሆ፣ ሃ" እያለ ታማኙን ባልደረባውን አስከትሎ ወደሚጠብቃቸው አደጋ ጋለበ::

የአእምሮዬ ካሜራ ካህኑ ሲጸልዩ ለማየት ወደ ሚሲዮን ጣቢያው አልተከተላቸውም:: ፈረሰኞቹን አሳድዶ እየተከተለ ነው:: ድርጊያው ያለው እዚያ ነው::

## የጸሎት አሳዛኝ ምስል

እስቲ እንጋፈጠው:: ጸሎት ዙሪያውን ከከበቡት አከብሮቶች በተቃ ራኒ በአሳዛኝ ምስል (ገጽታ) ይቸገራል:: አንዳንዶች ጸሎትን የተግባር ደካማ አማራጭ - ምንም ላለመሥራት የሚቀርብ ማመካኛ አድርገው ያጣጥሉታል:: ለአንድ ሰው "እጸልይልሃለሁ" ማለት ከማይመች ሁኔታ ራስን ለማግለል ለዛ ያለው ሰበብ የማቅረቢያ መንገድ ተደርጎ ብዙ ጊዜ ይወሰዳል፤ የመውጫ መንገድ ነው:: ጸሎት ሴቶች የሚያደርጉት ነገር፣ የተግባር ሰዎች ወጣ ብለው ሥራውን ሲፈጽሙ፣ ይበልጥ ዐቅም የለሽ የሆኑ ቅዱሳን እንዲሳተፉበት የተተወ ነገር ነው::

ሆኑሉሉ ከተማ ውስጥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ሳገለግል እንደ ነበር አስታውሳለሁ:: የጋበዙኝ በተለይ ስለ ጸሎት እና በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምልጃ አገልግሎት እንዴት ማደራጀት እንደሚቻል እንድናገር ነበር:: ቤተ ክርስቲያን ለእያንዳንዱ ነገር መርሐ ግብር እንዳላት - የምስክርነት መርሐ ግብር፣ የደቀ መዝሙርነት መርሐ ግብር፣ የባላደራነት መርሐ ግብር - ነገር ግን የጸሎት መርሐ ግብር ያላቸው ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ መሆናቸውን ጠቆምኳቸው:: መጽሐፍ ቅዱስ ለጸሎት ከሚሰጠው ትልቅ አጽንዖት ጋር ሲነጻጸር ይህ ምጸት ይመስላል::

የጠዋቱን ስብሰባ እንደ ጨረስን፣ ከተለያየ ቦታ ተወክለው ከመጡት ሰዎች መካከል የአንድ ቤተ እምነት የወንጌል ሥርጭት ክፍል ኀላፊ የሆነው ሰው ትከሻዬን መታ መታ አደረገኝና የሌሎች ጥቅሻ እያሳየ ወደ ጎን ወሰደኝ::

"ታውቃለህ?" አለ በሹክሹክታ፣ "ይህ የጸሎት ጉዳይ ትልቅ ሐሳብ እንደ ሆነ አስባለሁ፤ ነገር ግን ከቍጥጥር ውጭ እንዳይወጣ እፈራለሁ::"



"ምን ማለትህ ነው?"

"እንግዲህ" በማለት መለሰ፤ "ሰዎች በጸሎት ተጠምደው ምንም ላይ ሠሩ ይችላሉ::"

"ሌላ ነገር" አይደለም ያለው:: "ምንም" ነው ያለው፤ አራት ነጥብ:: ሰውዬው የምሩን እንደ ነበር ሲገባኝ፣ እጅግ አብዝታ ከመጸለይዋ የተነሣ ጸሎትን ቸላ እንድትል ሊነገራት የሚያስፈልጋት አንዲትም ቤተ ክርስቲያን እስከ ዛሬ እንዳላጋጠመችኝ አረጋገጥኩለት:: ጉዳዩ ሲሆን እናነሣዋለን:: እስካሁን ግን ይህን የሚመስል ጉዳይ አልተከሰተም::

ጸሎት የሥራ ምትክ ወይም የሥራ ዝግጅት ብቻ አይደለም:: *ሥራ ነው::*

ሌላኛው አሳዛኝ የጸሎት ምስል ይህ ነው፤ የጥንት ቅዱሳን በጨፍጋጋው ክረምት በማለዳ እየተነሡ፣ እጅግ ደረቅ በሆኑ ቀዝቃዛ ወለሎች ላይ ተንበርክከው ወደ ጌታ አብዝተው ሲጮኹ:: በዚህም ጸሎት የምር ጉዳይ መሆኑን ይነግሩናል፤ እዚህ ጋ መጃጃል የለም:: ይህንንም በትክክል ለመፈጸም ጥብቅ ሥነ ሥርዐት ይፈልጋል::

## መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ የሚያስፈራራው ቃል

አሳሳቢነቱ ሲታይ ጸሎት በክርስቲያኖች መዝገበ ቃላት ውስጥ በጣም ከሚያስፈሩ ቃላት መካከል አንዱ ነው:: "ዛሬ ብዙ የምሠራው ነገር ስላለ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ሰዓታት በጸሎት ማሳለፍ አለብኝ" በማለት የተናገረውን ማርቲን ሉተርን የመሰሉ የቀደሙ መንፈሳዊ ሰዎች ንግግር፣ ጸሎተኛው ሀይዲን (የሕንዱን ሚሲዮናዊ)፣ ወይም በዙሪያው ያለው በረዶ እስኪቀልጥና እርሱም በኒሞኒያ በሽታ ተይዞ እስኪሞት ድረስ እስከ ጉልበት በሚደርስ የበረዶ ክምር ላይ ለረዥም ጊዜ በብርቱ ሲጸልይ የነበረውን ዴቪድ ብሬይነርድን የመሳሰሉ የጸሎት ጦረኞች ታሪክ ሁላችንንም ተስፋ ሲያስ ቈርጠን ቈይቷል:: ትውፊት እንደሚነግረን አብዝቶ በጸሎት ከማሳለፉ የተነሣ ጉልበቱ ደድሮና ጉጥ አውጥቶ የግመልን ጉልበት በመምሰሉ "የግመል ጉልበት" የሚል ቅጽል ስም የወጣለትን ሐዋርያው ያዕቆብንም አንዘነጋም::

እነዚህ ቅዱሳን አያት ቅድመ አያቶቻችን በሁላችንም ራስ ላይ የበደለኝነት ክምር ከምረውብናል:: ስለዚህ አብዛኞቻችን ቀኑን ከመጀመራችን በፊት ከሌሊቱ 10 ሰዓት ተነሥቶ "በጸሎት የመጋደል"ን ሥርዐት መከተል እንደሚኖርብን እጠረጥራለሁ::

“ልፋት ከሌለ፣ ትርፍ የለም” የሚለው የጸሎት መመሪያ ይመስላል:: ጸሎት የአካላዊ ጽናት ፈተና ለምን እንደሚሆን ፈጽሞ ሊገባኝ አልቻለም:: እኔ ከማለዳው ጸሎት ይልቅ በምሳ ሰዓት የሚደረግን ጸሎት እመርጣለሁ::

ስለዚህም ጸሎት *ሥራ መሆኑን*፣ ወይም ግላዊ መሥዋዕትነት፣ ደም፣ ላብ እና እንባ እንደሚጠይቅ ሲነገር እናጣጥላለን - ይህን የምናደርገው ግን ስለ ጸሎት ሲሆን ብቻ ነው:: መሥዋዕትነት እና ጠንክሮ መሥራት ማራቶን ከመሮጥ ጋር ተያይዘው ሲቀርቡ ግን አድናቆት ይቸራቸዋል::

እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነውንና ስለ ጸሎት ያለኝን ጠቅላላ ሐሳብ የለወጠውን ነገር እስከገነዘብ ድረስ (የእናንተንም ይለውጠው ይሆን?)፣ በውስጤ ያለው የጸሎት ምስል ይህ ነበር (የእናንተም ይኸው ነበር?)::

ጸሎት ሃይማኖታዊ ልምምድ እንዳልሆነ ተገንዝቤአለሁ፤ ሰብአዊ አስፈልጎት (need) እንጂ::

በዚህም ሆነ በዚያ መንገድ፣ ለዚህኛው አምላክም ሆነ ለዚያኛው፣ እኛ ሰብአዊ ፍጡራን ስሙን ጸሎት አልነውም አላልነው ሁልጊዜም ስንጸልይ ኖረናል:: ከራሳችን ውጭ የሆነን፣ ከምንደርስበት በላይ የሆነን፣ መንፈሳዊ ወይም ልዕለ ተፈጥሮአዊ የሆነን ነገር፣ ሮጠን የምናመልጥበትን፣ በትንሹም ቢሆን የምናለቅስበትንና ያለንበትን አስቸጋሪ ሁኔታ የሚገነዘብልንን አካል በመፈለግ መንምነናል:: እየደፈጠጠን ካለው ዕጣ ፈንታና ነገር ሁሉ እንደ ተወሰነና እንደማይለወጥ ከሚሰማን ስሜት ሁሉ ለማምለጥ እንናፍቃለን:: አዎን፣ ጸሎት ከሃይማኖታዊ ልምምድ በእጅጉ ይልቃል:: ሰብአዊ አስፈልጎት ነው::

## የክርስቲያን ምስጢራዊ ጦር መሣሪያ

ጸሎት ማለት “ላደርግ የምችለው አንድም ነገር የለም” በጭራሽ አልልም ማለት ነው:: ሁሌም ማድረግ የምችለው፣ ጌታ ኢየሱስም ያደረገው ትልቅ ነገር አለ:: እንዲያውም የበለጠ ማድረግ እችላለሁ:: ዝም ብዬ መቆም የለብኝም - የሆነ ነገር መጸለይ እችላለሁ::

ጸሎት የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢራዊ ጦር መሣሪያ መሆኑንም ተረድቻለሁ:: ልክ በምድር ላይ ወዳለ ወደ የትኛውም ቦታ ሊተኮስ፣ ሳይታወቅና ሳይገኝ በሐሳብ ፍጥነት ሊጓዝና በየጊዜው ዒላማውን ሊመታ እንደሚችል ሚሳይል ነው::

ካስፈለገም ጊዜውን ጠብቆ የሚፈነዳ ነገርም ሊገጠምበት ይችላል:: ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ 17 ባደረገው ጸሎት፣ “የምለምንህም ስለ እነዚህ ብቻ



ሳይሆን፣ የእነዚህን ምስክርነት ሰምተው ስለሚያምኑብኝ ሁሉ ነው” ብሏል (ዮሐ. 17፥20 - ሕያው ቃል):: ጸሎቱ በክፍለ ዘመናት ሁሉ ላይ ተዘርግቶ ያመኑትን ወይም ገና የሚያምኑትን ሁሉ አቅፏል:: የሆነ ሰው ወደ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ሁሉ የጌታ ኢየሱስ ጸሎት እንደገና መልስ ያገኛል - ዕድሜው ሁለት ሺህ ዓመት ሆኖአል፤ ግን አሁንም እየተመለሰ ነው::

አንድምታው አስደንጋጭ ነው:: እኛም ብንሆን ገና ስለሚሆኑ ነገሮች፣ ለምሳሌ በልጆቻችን እና በእነርሱ ልጆች ሕይወት ስለሚሆኑ ነገሮች መጸለይ እንችላለን:: በምልጃ እጆች ሸፍነን የሲኦልን እሳት አሳልፈን ወደ ሰማይ ደጆች ልናደርሳቸው እንችላለን:: ለልጆቻችን ልንተውላቸው የምንችለው ውርስ ይህ ነው - የጸሎት ውርስ፣ ልጆቹ ከመወለዳቸው በፊት ወደ እግዚአብሔር ከፍ የተደረጉ ጸሎቶች፣ እኛ ካለፍን ከብዙ ጊዜ በኋላ መልስ የሚያገኙ ጸሎቶች::

ገና ብዙ አለ:: ሰይጣን ይህንን ጦር መሣሪያ የሚከላከልበት ነገር የለውም፤ ጸረ ጸሎት ሚሳይል የለውም:: ለምሳሌ አንድ ኢአማኒ የወንጌል ሥርጭት ጥረታችንን የሚቃወምበት በርካታ መከላከያዎች አሉት:: ቤተ ክርስቲያን አልመጣም ሊል ይችላል፤ በአጋጣሚ ቢመጣም የኮርኒሱን ስንጥቆች ሲቈጥር ውሎ ሊሄድ ይችላል:: ወደ ቤቱ ልትሄዱ ትችላላችሁ፤ ግን አላስገባም ይላችኋል:: መንገድ ላይ ትራክት ትሰጡታላችሁ፤ ሊወረውረው ይችላል:: በቴሌቭዥን በኩል ስበኩት፤ ጣቢያውን ይቀይረዋል:: ስልክ ደውሉለት፤ ጆሮ አችሁ ላይ ይዘጋዋል:: ነገር ግን ከምልጃ ጸሎታችሁ የተነሣ ጌታ የልቡን በር እንዳያንኳኳ መከልከል አይችልም:: በሌላ በምንም ነገር ልንደርሳቸው የማንችላቸውን ሰዎች በጸጋው ዙፋን በኩል በጸሎት ልንደርሳቸው እንችላለን::

## አንድ ነገር ልናደርግ እንችላለን - አሁን!

ሌላ ልናደርግ የምንችለው ነገር በማጣት እንዲሁ የምንጸልይ አይደለንም:: የምንጸልየው ማድረግ የምንችለው ምርጡ (የተሻለው) ነገር በመሆኑ ነው:: ዝም ብለን እዚያ መቆም የለብንም - የሆነ ነገር ልንጸልይ እንችላለን:: ይህች የልጅ እናት እንዳደረገችው::

በአንድ የቤተ ክርስቲያን የምልጃ ጸሎት አገልግሎት በተዘጋጀ የእራት ግብዣ ላይ እየሰበክሁ ሳለ ነበር በቅርቡ ያገኘችውን የጸሎት ምላሽ ያካፈለችን:: ከጥቂት ቀናት በፊት ነው፤ ስልኩ የጮኸው ልትጋግር የነበረውን ነገር ወደ ማብሰያው ለማስገባት እየተዘጋጀች ሳለ ነው:: ከትምህርት ቤት ነበር የተደወለው፤ ልጇ በከፍተኛ ትኩሳት ተይዟል፤ መጥታ ልትወስደው ትችላለች?

እናትየው መኪናዋን እየነዳች ትምህርት ቤት ደርሳ ለመመለስ ስንት ጊዜ እንደሚፈጅባትና የምትጋግረው ነገር ለመብሰል ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈልግ አሰበችና በቂ ጊዜ እንደሚኖር ገመተች፡፡ ምግቡን ማብሰያው ውስጥ ጨመረችና ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ወጣች፡፡ እዚያ ስትደርስ ግን የልጇ ትኩሳት እንደ ተባባሰና ወደ ሐኪም ይዛው ብትሄድ እንደሚሻል ተነገራት፡፡

ልጇ እንደዚያ ሆኖ ማየቱ - ትኩሳቱ ጉንጩን አቅልቶት፣ ገላው በላብ ተጠምቆ ይንቀጠቀጣል - እያርበተበታት ወደ ሐኪም የቻለችውን ያህል ይዛው በረረች፡፡ እዚያም ከደረሰች በኋላ ሐኪሙ ልጇን ይዞ ከገባበት የምርመራ ክፍሉ እስኪወጣ ድረስ እየተርበተበተች ስትጠብቀው፣ ከትንሽ ቈይታ በኋላ ቍራጭ ወረቀት ይዞ ወደ እርሷ መጣ፡፡

"ወስደሽ አስተኚውና" አለ በእጁ የያዘውን የመድኀኒት ማዘዣ እየሰጣት፤ "ይህንን መድኀኒት አሁኑኑ አስጀምሪው፡፡"

ቤት ደርሰው ልጇን መኝታ ውስጥ አስገብታ ወደ ገበያ አዳራሽ ስትሄድ ከመርበትበትም ዐልፋ ተጨንቃና ዝላ ነበር፡፡ ማብሰያው ውስጥ ያለውን ምግብ ፈጽሞ ረስታዋለች፡፡ የገበያ አዳራሹ ውስጥ መድኀኒት ቤቱን አግኝታ የታዘዘለትን መድኀኒት ከገዛች በኋላ እየተጣደፈች ወደ መኪናዋ ተመለሰች፡፡

ተቈልፏል፡፡

አዎን - ቍልፎቿ ደግሞ እዚያው መኪና ውስጥ እንደ ተንጠለጠሉ ተቈልፎባቸዋል፡፡ ወደ ገበያ አዳራሹ ሮጣ ወደ ቤት ስልክ ደወለች፡፡ ልጇ ሲያነሣው፣ "ቍልፎቹን መኪናው ውስጥ ቈለፍኩባቸው!" በማለት ዘከዘከች፡፡

ልጁ በደንብ መናገር አልቻለም፤ ብቻ በጎርናና ድምፅ፣ "የልብስ መስቀያ ሽቦ ፈልጊ እማዬ፡፡ በእርሱ መከፈት ትችያለሽ" አላት፡፡ ከዚያ ስልኩ ተዘጋ፡፡

ወደ ገበያ አዳራሹ ተመለሰችና የልብስ መስቀያ ሽቦ መፈለግ ጀመረች - ቀላል ሥራ አልነበረም፡፡ ከዕንጨትና ከፕላስቲክ የተሠሩ መስቀያዎች ገበያውን ሞልተውታል፤ የሽቦ መስቀያ መጠቀም ትተዋል፡፡ ደርዘን ያህል መደብሮችን ካዳረሰች በኋላ የሽቦ መስቀያ የሚጠቀም አንድ ኋላ ቀር ሱቅ አገኘች፡፡

በዕፎይታ እየፈገገች ከሱቁ ተጣድፋ ወጣች፡፡ ልክ የመጨረሻውን ደረጃ ስትወርድ ግን ቀጥ አለች፡፡ ከሽቦ የተሠራው ልብስ መስቀያ ላይ አፈጠጠች፡፡

"በዚህ ምን እንደማደርግ አላውቅም!"



ልክ በዚህ ጊዜ ማብሰያው ውስጥ የተጣደው ምግብ ትዝ አላት፡፡ እስካሁን ያሳለፈችው መርበትበት ሁሉ ተሰብስቦ መጣባትና ማልቀስ ጀመረች፡፡ ከዚያ መጸለይ ጀመረች፡፡ "ጌታ ሆይ፤ ልጄ ታሟልና ይህ መድኀኒት ያስፈልገዋል፤ በዚህ ላይ ማብሰያ ውስጥ ምግብ ጥጄ ነው የመጣሁት፤ ቍልፎቼ ደግሞ መኪና ውስጥ ተቈልፎባቸዋል፤ እናም ጌታ ሆይ በዚህ ልብስ መስቀያ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፡፡ ጌታ ሆይ በዚህ መስቀያ ምን መሥራት እንዳለበት የሚያውቅ ሰው ላክልኝ፤ ይህም በእርግጥ አሁኑኑ ነው የሚያስፈልገኝ፣ ጌታ ሆይ፤ አሜን!"

አንድ የተገሜጨ መኪና ኩርባውን ዞሮ ፊት ለፊቷ ሲቆም እንባዋን እየጠራረገች ነበር፡፡ ዕድሜው በሃያዎቹ ውስጥ ያለ የሚመስል፣ ቲ ሸርትና የነተበ ጂንስ የለበሰ ወጣት ከመኪናው ወጣ፡፡ መጀመሪያ ያስተዋለችው ነገር ቢኖር እንደ ሲባጎ የረዘመውን ጠጕሩን ሲሆን፣ ከዚያም የአገጩን ደቡባዊ ክፍል የሸፈነውን ጢሙን ነው፡፡ ወደ እርሷ ነበር የሚመጣው፡፡ ወደ እርሷ ሲቃረብም ፊቱ ተጋረጠችና የሽቦውን መስቀያ ዘረጋችለት፡፡ "የእኔ ልጅ" አለችው፤ "ይህን ተጠቅሞ፣ የተቈለፈ መኪና እንዴት መከፈት እንደሚቻል ታውቃለህ?"

አፉን ከፍቶ ለአፍታ ተመለከታት፤ ከዚያም መስቀያውን ስቦ ወሰደ፡፡ "መኪናው የታለ?"

በዚያ የእራት ግብዣ ላይ ስትናገር፣ እንዲህ ዐይነት ነገር ከዚህ በፊት በፍጹም ዐይታ እንደማታውቅ ነገረችን - አቤት ልጁ መኪናውን እንዴት በቀላሉ እንደ ከፈተው! በሩንና መስኮቱን እንዴ ፈጠን ብሎ ተመለከተ፤ የልብስ መስቀያውን ሽቦ ሁለቴ አዟዟረ - በቃ፡፡ በዚህ ብቻ በሩ ተከፈተ!

በሩ መከፈቱን ስታይ እጆቿን ዘርግታ ተጠመጠመችበት፡፡ "እፎይ" አለች፤ "ጌታ ነው የላከህ! አንተ ጥሩ ልጅ ነህ፡፡ ክርስቲያን ነህ መቼም፡፡"

ወደ ኋላ ሸሸት አለና፣ "አይደለም እናቴ፡፡ ክርስቲያን አይደለሁም፤ ጥሩ ልጅም አይደለሁም፡፡ ከማረሚያ ቤት ገና ትናንት መውጣቴ ነው፡፡"

ዘልላ ወጣችበትና እንደገና አቀፈችው - በኀይል! "እግዚአብሔር ይባረክ!" ጮኸች፡፡ "ባለሞያ ነው የላከልኝ!"

ዝም ብላ አልቆመችም - የሆነ ነገር ጸልያለች፡፡

ያች ሴት ስለ ጸሎት ትልቅ ምስል አላት፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሉቃስ 18፥1 ላይ የተናገረውን - "ሳይታክቱ ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው" - እሱኑ ነው ያደረገችው፡፡

## ማዘጋጃ ቤትን መፋለም

ይህንን ነጥቡን ለማስረገጥ ጌታ ኢየሱስ ምሳሌ ነገራቸው:: ምሳሌውም እግዚአብሔርን ስለማይፈራና ሕዝቡንም ያን ያህል ስለማይጠቅም ዳኛ፣ ብሎም ፍትሕን ፍለጋ ወደ እርሱ ስለምትመላለስ ያልታደለች መበለት ታሪክ ነው::

ጡረታ፣ የሕክምና ዋስትናና ሌሎች የማኅበራዊ ዋስትና መርሓ ግብሮች ባልነበሩበት በጥንት ጊዜ አንዲት መበለት ከፍጥረታት ሁሉ የባሰች አሳዛኟ ነበረች:: ባሏ ሲሞት መጋቢዋንና ጠባቂዋን (አስተዳዳሪዋን) አጥታ የሚቸረው ብዙም ነገር በሌለው በማኅበረ ሰቡ ምሕረት ሥር ትወድቃለች:: አንዲት መበለት የድኾችና የመጠጊያ አልባዎች ምሳሌ ነበረች፤ ጌታ ኢየሱስም በትረካው ውስጥ የዐቢይ ገጸ ባሕርይ ሚና የሰጣት የባለታሪኳን ምስኪንነትና ረዳት የለሽነት የተቻለውን ያህል አጽንዖት እየሰጠው ነበር::

እስቲ ለአፍታ ቆም እንበል:: ምሳሌውን በሆነ ጥንታዊ፣ የሻገተና ጊዜ ያለፈበት መዝገብ ውስጥ እንደ ተጻፈ አፈ ታሪክ አድርጋችሁ ማሰባችሁን አቁሙ:: አሁን ነው የተፈጸመው:: ብዙዎች የማይቋቋሟቸውን የሰዎችን ዕጣ ፈንታ የሚወስኑ ኀይላት ፍትሕን ጥየቃ እየተፋለመች ያለች አንዲት የተገፋች፣ የተገለለች፣ ብቸኛና ከሁሉ የባሰች ምስኪን ሰው አለች:: ይህች ሴት ማዘጋጃ ቤቱን እየተፋለመች ነው::

የምታውቁት ዐይነት ታሪክ ይመስላል? አዎን፣ ሁላችንም ጠንቅቀን የምናውቀው ታሪክ ነው፤ አይደል?

በመሠረቱማ የእያንዳንዳችን ታሪክ ሊሆን ይችላል:: ሕይወት ፈታኝ ናትና ኢፍትሐዊ ከሆነው ዓለም ጥቂት ፍትሕ ጨምቀን ለማውጣት ስንታገል ራሳችንን ብዙ ጊዜ እናገኛለን - ዕድል ባያግዘንም::

ነገር ግን በተስፋ መቍረጥ ቡጢ ከመጨበጥ ያለፈ ነገር ማድረግ እንችላለን:: መበለቲቱ ያደረገችውን - መጸለይ:: ጸሎት በእውነት ለውጥ ያመጣልን? እስቲ፣ በመበለቲቱ ጉዳይ ለውጥ ስለ ማምጣት አለማምጣቱ እንይ::

መበለቲቱ አንዳች ተጽዕኖ፣ ገንዘብም ሆነ ዳኛው እንዲደግፋት የሚያደርግ ዋጋ ያለው ምንም ነገር እንደሌላት አስታውሱ - የምትሻውን ነገር ያለ ማቋረጥ ከማሳወቅ በቀር:: በመጨረሻ ዳኛው እንዲህ አለ፤

> ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ፣ ሰውንም ባላፍር፣ ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ሁልጊዜም እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ:: (ሉቃስ 18፥4-5)



ትርጕሙ ግልጽ ነው:: ሳንታክት ሁሌ መጸለይ አለብን:: ምክንያቱም የሚከተለው ነው፤

> ዐመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ:: እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? (ቍጥር 6-7)

ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ትክክለኛ ካልሆነው ዳኛ ጋ እያወዳደረ አይደለም፤ ሁለቱን *እያነጻጸረ* እንጂ:: ከትንሹ ተነሥቶ ስለ ትልቁ እየተከራከረ ነው:: በሌላ አገላለጽ፣ የዳኛው እስከፊነት ይበልጥ በጨመረ ቍጥር የአምላካችን መልካምነት ይበልጥ ይታየናል:: የኢፍትሐዊነት ቁልል የሆነ አንድ ዳኛ የአንዲትን ችግረኛ መበለት ጥያቄ ከፈቀደ፣ በፍቅርና በጽድቅ ፍጹም የሆነው የሰማይ ዳኛ ጩኸታችንን ሰምቶ አይፈርድልንምን?

ከዚያም ጌታ ኢየሱስ ጥያቄውን ፈጥኖ ያስከትለዋል፤ “ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆን?” (ሉቃስ 18፥8):: የጥያቄው አወቃቀር የአሉታዊ ምላሽ አንድምታ አለው፤ ግን አይደለም::

ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ የሚፈልገው የተለየ ዐይነት እምነትን ነው:: በግሪኩ እምነት የሚለው የተለየ ዐይነት እምነት መሆኑን የሚያስረዳ መግለጫ ይዟል፤ ቃል በቃል “ይህ ዐይነቱን እምነት”:: ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ፣ ያለ ማቋረጥ የሚጸልይን እምነት እና ተስፋ መቍረጥን እምቢ ብሎ “ሁልጊዜ በመምጣት” ሽልማቱን የሚያገኘውን ዐይነት እምነት ያገኝ ይሆን?

ይህ መጽሐፍ ስብከት ቢሆን ኖሮ ሕዝቅኤል 22፥30 ምንባቤ እንዲሆን እመርጠው ነበር፤

> ቅጥርን የሚጠግን፣ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፤ ነገር ግን አላገኘሁም::

እግዚአብሔር ሁልጊዜም ማላጆችን፣ በፈረሰው ቅጥር በኩል ስለ ምድሪቱ በፊቱ የሚቆምን ሰው ይፈልጋል፤ እነርሱን ማግኘት ግን አስቸጋሪ ሆኖበታል:: በሕዝቅኤል ዘመን እግዚአብሔር በእርሱና በእስራኤል መካከል ኀጢአት በቀደደው ሸንቁር በኩል የሚቆምን ሰው ፈልጎ ነበር:: ማንንም አላገኘም:: ኢሳይያስም እግዚአብሔር ሰውን መፈለጉን፣ ነገር ግን አለ ማግኘቱንና “ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ” መረዳቱን ይነግረናል (ኢሳ. 59፥16)::

እግዚአብሔር አሁንም እየፈለገ ነው፤ ጌታ ኢየሱስም ሲመጣ የሚማልድን፣ "ያን ዐይነት እምነት" ያለውን ሰው መፈለጉን ይቀጥላል፡፡ ይህን መጽሐፍ የምጽፈው እርሱ ሲመጣ እናንተና እኔ "በፈረሰበት በኩል በፊቱ ቆመን" እንዲያገኘን ተስፋ በማድረግ ነው፡፡ የሆነ ነገር ስንሠራ፡፡ ስንጸልይ፡፡



## ፪ - ጌታ ኢየሱስ ለታላላቅ ሥራዎች የሰጠው ተስፋ እንዴት እንደሚፈጸም

# እንደ እኛ ዐይነት ሰዎች

አንዳንዶቻችሁ ምን እያሰባችሁ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ፡፡ "እርግጥ ስለ ጸሎት ማውራት ለዚህ ሰው ቀላል ነው፡፡ ስለ አስደሳች የጋብቻ ሕይወት እና ስለ ስኬታማ ወላጅነት፣ እንዲሁም ገጽታን በጥሩ ሁኔታ ስለ መገንባት መጻሕፍትን እንደሚጽፉ ሰዎች ሁሉ ነገር ተከናውኖለታልና" በማለት ነው የምታስቡት፡፡

"ዝነኛ ሰዎች"ን እንዴት በፍቅር ስሜት እንደምናገንናቸው አስደናቂ ነው፡፡ የፊልም ተዋንያንን፣ አቀንቃኞችን፣ አትሌቶችን፡፡ "የሕይወታቸውን ጥቃቅን ጉዳዮች - ስለሚለብሱት ልብስ፣ ስለሚመገቡት ምግብ፣ ስለ ሚያዘወትሩት አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ስለሚወዷቸው ሰዎች፣ ስለሚጠቀሙት የጥርስ ሳሙና ሁሉ እየተከታተልን እንሸቆጠቆጥላቸዋለን፡፡"[1]

ክርስቲያኖችም ሃይማኖታዊ ጸሓፊዎችንና ሰባኪዎችን በሚመለከት ተመሳሳይ ነገር ይፈጽማሉ፡፡ ይህን አለማድረግ እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ እስቲ መጽሐፉን ተመልከቱት፤ አዲስና አንጸባራቂ ነው፤ ሽፋኑ ተስፋ በሚሰጡ ቃላት ተሞልቷል፤ ቀለሙን አሽትቱት፡፡ ከጀርባ ስትመለከቱት ደግሞ ጸሓፊው/ዋ እጆቿ/ቹን በትዳር ጓደኛው ላይ አድርጎ/ጋ (የትዳር ጓደኛው/ዋም ጸሓፊና ታዋቂ ሰባኪ ነው/ናት) ከጀርባ በተለያዩ ተክሎች የተሞላ ቤትንና የሚያምር ፍርግርግ አጥርን የሚያሳይ ፎቶ ታያላችሁ፡፡ ደስታ የሚነበብባቸው የእነዚህ ሁለት ሰዎች ፈገግተኛ ፊት ሁሉ ነገር እንደ ተሳካላቸው ያሳያል፤ በዚህ ላይ ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸው - አንዱ ሐኪም ሲሆን ሌላኛው የሕግ ባለሞያ ነው፤ ሁለቱ ሴቶች ልጆቻቸው ደግሞ (ታናሺቱ የቁንጅና ውድድር አሸናፊ ናት) አስደናቂና ወጣት አገልጋዮችን አግብተዋል፡፡

አንድ ቀን ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጉባኤ የመዝጊያ መርሐ ግብር በኋላ አንዲት ሴት ምን ዐይነት ሳምንት እንዳሳለፈች ልትነግረኝ ወደ እኔ መጣች፡፡ ከዚያም ወደ ኋላ ቀሸሸት በማለት፣ እጆቿን ደረቷ ላይ አጣምራ፣ ራሷን ዝቅ አደረገችና ዐይኖቿ መኳኳት እየተነበበባቸው፣ "በጣም ምርጥ

ሚስት አለችህ፤ በጣም አስደሳች ጥንዶች ናችሁ - መላው ሕይወታችሁ ውብ ነው" አለችኝ፡፡

በዚያን ቀን ማለዳ እኔና ሚስቴ ስላሳለፍነው አለመግባባት ልነግራት ይገባ እንደ ነበር አሰብኩ፡፡ ከሰብከቶቼ ሁሉ ይልቅ ይህ ያበረታታት ነበር፡፡

አድምጡኝ፤ መጻሕፍቱን የሚጽፉትንና ቪዲዮዎቹን የሚያዘጋጁትን ብዙ ሰዎች ዐውቃለሁና ለእናንተ የሚሆን ዜና አለኝ፡፡ ከእናንተ የተሻለ ድርጊት የሚፈጽሙ ሰዎች አይደሉም!

የራሳቸው የቤተ ሰብ ዋይታና የትዳር ጭንቀት ድርሻ አላቸው፤ በዐመፀኛ ልጆቻቸው ያለቅሳሉ፤ ስለ ገንዘብ ይጨነቃሉ፤ ፍርሀትና ሥጋትን እየታገሉ እንቅልፍ አልባ ምሽቶችን ያሳልፋሉ፡፡ በድብታ አዘቅት ውስጥ መዘፈቅ ምን ማለት እንደ ሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ከኀዘንና ስብራት ጋር ይተዋወቃሉ፡፡

ለመናገር የፈለግሁት እነዚህ ሰዎች ወደ ሰማይ ሄደው አምላክ የሚሆኑበትን ተራ ቁጭ ብለው የሚጠብቁ፣ ምስጢሩን ደርሰውበት እኛንም ለማካተት እየጋበዙ ያሉ መንፈሳዊ ሊቃውንት አለመሆናቸውን ነው፡፡ በመንገዳቸው የተመለከቱትን የሚያካፍሉ አብረው ተጓዦች፣ በምድረ በዳው ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡ ሰዎች የውሃ ጉድጓድ የሚቆፍሩ ናቸው፡፡ እንደ እኔና እንደ እናንተ ዐይነት ሰዎች ናቸው፡፡

## የ"ኮከብ" ሥርዐት

ሆሊውድን የገደለው የ"ኮከብ" ሥርዐት እንደ ሆነ ይነገራል፡፡ ይኸው የኮከብ ሥርዐት በቤተ ክርስቲያንም ይህንኑ እየፈጸመ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ዝነኛ የሆኑ ባለተሰጥዖ እና ባለስጦታ ከዋክብት አሉት፡፡ እነዚህ ጥቂቶቹ ተዋንያን ሆነው፣ የቀረነው ተመልካቾች ሆነናል፡፡

ፊሊፕ ያንሲ ስለዚህ ኮከብ/አገልጋይ ደዌ ምልክቶች ጽፏል፤

> የዝነኛ ክርስቲያኖችን (ከዋክብትን) ቅሌት ከሚመለከቱ ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ ከአገልጋዮቹ ይልቅ ከዋክብቱ ላይ ትኩረት ለማድረግ በመለማመድ የእግዚአብሔር መንግሥትን ማዛባታችን ነው፡፡

ከዚያም ሄነሪ ኖዌይን ይጠቅሳል፤

> ድንጋዩን ዳቦ የማድረግ፣ ከከፍታ ስፍራዎች ራሱን የመወርወር ወይም በጊዜያዊ ትልቅ ኀይል የማስተዳደር ግብዣ



> ሲቀርብለት እምቢ ያለው ጌታ ላይ ዐይኖቻችሁን አድርጉ፡፡ "ድኾች፣ የሚያዝኑ፣ የዋሆች፣ ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዐን ናቸው፤ ልበ ንጹሖች፣ የሚያስተራርቁ፣ ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዐን ናቸው" በማለት የተናገረው ሰው ላይ ዐይኖቻችሁን አድርጉ፡፡[2]

እንዲህ ዐይነት ሰዎች ብፁዐን ናቸው፡፡

ማርቲን ሎይድ ጆንስ ስለ ጸሎት የተናገሩትን አስታውሳለሁ፤

> ይህንን ርእሰ ጉዳይ በተመለከተ ሁልጊዜም ሳመነታ ኖሬአለሁ፡፡ ከተዘጋጀሁበት ሌላ ነገር ጋር ተያይዞ ሲመጣ ብቻ ነው ስለ ጸሎት የሰበከሁት፤ ነገር ግን የጸሎት ርእሰ ጉዳይን በሚመለከት በመጽሐፍ ይቅርና ትንንሽ መጣጥፎችን እንኳ ለማዘጋጀት በፍጹም ሐሳቡ አልነበረኝም፡፡[3]

ይህም "ጠቢባን ፈጽመው በማይደርሱበት ስፍራሞኞች እየተጣደፉ ይገቡበታል" የሚባለውን አባባል የሚያረጋግጥ ይመስለኛል፡፡ ሆኖም ከጸሎት በፍርሀት እንድንርቅ የሚያደርገን ዝንባሌም ይኸው ነው፡፡ እርሱን መንካት እንፈራለን፡፡ ጸሎት አይነኬ አይደለም፡፡ በዚያ ዐይነት አክብሮታዊ ፍርሀት እንድንይዘው አይደለም እግዚአብሔር ያሰበው፡፡

ጸሎት የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው፡፡ በኀጢአት ለደከሙ፣ በቃላቸው እና በውሳኔአቸው ለመጽናት ለሚቸገሩ፣ አንዳንድ ጊዜአት ደግሞ በጥርጥር ለሚዋጡ፣ ብዙውን ጊዜ ተስፋ ለሚቈርጡ፣ ግራ ለሚጋቡ፣ ከሞላ ጎደል ሁሌም ስለ ሕይወት ለሚጨነቁ ሰዎች ነው የፈጠረው፡፡

ይህ ደቀ መዛሙርቱን በጥሩ ይገልጣቸዋል፡፡ አንዳችንም ልዕለ ቅዱሳን በማለት የምንጠራቸው አይደሉም፤ ሆኖም ጌታ ኢየሱስ ጸሎትን በሚመለከት ታላቅ ትርጒም ያለው ነገር የተናገረው ለእነዚሁ ደቀ መዛሙርት - ከጥቂት ሰዓት በኋላ፣ ጥርግርግ ብለው ጌታቸውን ትተው ለሚሄዱ ሰዎች ነው፡፡ እስከ ሞት ድረስ የፈሩትን እነዚህን ሰዎች ለብቻ መተው አይቻልም፡፡

ጌታ ኢየሱስ ወደ መስቀሉ ከመሄዱ በፊት በነበረው የመጨረሻ ሰዓት፣ "ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም" በማለት ቃል ገብቶላቸዋል (ዮሐ. 14፥18)፡፡ የፈሩትም ይህንኑ ነበር - እንደ መጠጊያ አልባ እጓለ ማውታን መሆን፡፡ በተለይ በኋላ ደጋግሞ የሚያነሣውን ትቶአቸው የመሄድ ሐሳብ መቋቋም አቅቷቸዋል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ስለ መስቀሉ ባነሣ ቍጥር ርእሰ ጉዳዩን ለማስቀየር ይሞክራሉ፡፡ *ከእርሱ ጋር ሆነን እንዲህ ፍሬ ቢስ ከነበርን፣*

*ያለ እርሱማ ምን ልንሆን ነው?* በማለት ሳያስቡ አልቀሩም፡፡ የእኛው ዐይነት ሰዎች ናቸው፡፡

"እንዴ፣ ጴጥሮስስ?" ትሉ ይሆናል፤ "እርሱ እኮ አልፈራም"፡፡ በእርግጥ አልፈራም - ነገር ግን ቢፈራ ነበር የሚሻለው፡፡ ሁሉ ነገር በቍጥጥሩ ሥር እንደ ሆነ የሚያስበው ይኸው ደቀ መዝሙር ነው ከሁሉ የበለጠ የመውደቅ ድምፅ ያሰማው፡፡ እዚህ ጉዳይ ላይ ፍርሀታችሁና መንቀጥቀጣችሁ ድካሞቻችሁ አይደሉም፤ ጥቅሞቻችሁ ናቸው፡፡

ለእንደኛ ዐይነት ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ምንድን ነው ያለው? የታላላቅ መሪዎች የመጨረሻ ቃላት ሁሌም ትልቅ ቁም ነገር እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ታዲያ የጌታ ኢየሱስ የመጨረሻ ቃላት ምን ነበሩ? የንግግሩ ፋይዳስ ምን ነበር?

## ጌታ ኢየሱስን ጆሮ መጥባት

እስቲ ጌታ ኢየሱስ ከመስቀሉ በፊት አብሮአቸው ባሳለፈው የመጨረሻ ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንሁንና ንግግራቸውን ማድመጥ እንችል እንደ ሆነ እንይ፡፡

ጊዜው እኩለ ሌሊት ገደማ ሲሆን፣ ጌታና ደቀ መዛሙርቱ የመጡት የፋሲካን እራት ከበሉበት ሰገነት ላይ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ትንሹን ቡድን በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች እየመራ በምሥራቁ ደጅ በኩል ሲወጡ ተከተልናቸው እንበል፡፡ የት ይዟቸው እየሄደ እንደ ሆነ አግራሞት ይዞናል፡፡ አሃ፣ የቄድሮንን ፈፋ እየተሻገረ ነው፡፡ አዎን፡፡ ከሚወዳቸው መደበቂያዎች አንዱ ወደሆነው በደብረ ዘይት ተራራ ግርጌ ወደሚገኘው ጌቴሴማኒ እየመራን ነው፡፡

እያዘገምን ሳለ ጌታ ኢየሱስ ሰገነቱ ላይ የጀመረውን ሰፊ ገደ ቢስ ንግግር ቀጥሎአል፡፡ ደብዛዛው የጨረቃ ብርሃን ሰዎቹ ፊት ላይ የሚነበበውን ግራ መጋባት ያጋልጣል፡፡ ሰዎቹ እያንዳንዱን ቃል ለመስማት በመጨናነቅ እርስ በርስ ተጠጋግተዋል፡፡ አስሸባሪ ምሽት ነበር፡፡ አብሮአቸው ደቀ መዝሙር በነበረው ይሁዳ እንግዳ ጠባይ እና በእርሱና በጌታ ኢየሱስ መካከል ሲካሄድ በነበረው ምስጢራዊ ውይይት ተጨንቀዋል፡፡

ጌታ ኢየሱስ እንቈቅልሽ ነው የሚናገረው - እኛም ከደቀ መዛሙርቱ ግራ መጋባት ጋር አንድ ላይ ነን፡፡ አሁን ጌታ ኢየሱስ እኛን ትቶ ስለ መሄድና ስለ አባቱ ቤት የሆነ ነገር ተናገረ፡፡



ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንዲህ አለ፡፡ ፊሊጶስ ሳይሆን አይቀርም፡፡ "ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል" (ዮሐ. 14፥8)፡፡

*ጥሩ ጥያቄ፣ ፊሊጶስ! የሚያስፈልገን እርሱ ነው - ይበልጥ ግልጽ የሆነ ቃል፣ አስተማማኝ ርእይ፡፡ እስቲ በእምነት ብቻ ሳይሆን በዐይናችንም እንይ፡፡ ይህ በቂ ነው - እርሱ ትቶን ቢሄድም እንኳ፡፡*

ጌታ ኢየሱስ መለሰ፤

> እኔን ያየ አብን አየ፡፡ ... እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረ ውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል፡፡ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ፡፡ (ዮሐ. 14፥9-11)

ፊሊጶስ እስካሁን በፍጹም አይቶት እንደማያውቅ "አብን አሳየን" ቢልም ጌታ ኢየሱስ ግን "አይተኸዋል" ነው የሚለው፡፡ አላወቀም እንጂ፤ ጌታ ኢየሱስ ለምጻሞችን ሲፈውስ በሚመለከትበት ጊዜ ሁሉ አብን ነበር የሚመለከተው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር በሚያደምጥበት በእያንዳንዱ ጊዜ አብን ነበር ሲያደምጥ የነበረው፡፡

ደቀ መዛሙርቱ አሁን ባያስተውሉትም፣ ጌታ ኢየሱስ በእነዚህ ቃላት የሕይወቱንና የሥራውን ምስጢር እንደ ገለጻላቸውና ይህም በቅርቡ የእነርሱም ሕይወትና ሥራ ምስጢር እንደሚሆን በኋላ ያስተውላሉ፡፡

## የጌታ ኢየሱስ ምስጢር

ጌታ ኢየሱስ በምላሹ ውስጥ፣ "የኀይሌ ምንጭ እኔ አይደለሁም፡፡ የምናገራቸውና የማደርጋቸው ነገሮች ከእኔ የመነጩ አይደሉም፡፡ ከአብ እንጂ" እያለ ነበር፡፡

ጌታ ኢየሱስ በተናገራቸው ቃሎችና በፈጸማቸው ሥራዎች ክብሩ የእርሱ እንዳልሆነ እየተናገረ ነው፡፡ ይህም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ሐሳብ ለመረዳት ያግዘናል፤

> እውነት እላችኋለሁ፤ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያደርጋልና፡፡ (ዮሐ. 5፥19 - አ.መ.ት)

እንደገናም ቍጥር 30 ላይ፤

እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ፤ ፍርዴም ቅን ነው፤ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።

ምስጢሩ ዮሐንስ 8፥28 ላይም ይታያል፤

ስለዚህም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "የሰው ልጅን ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ፣ ያ ያልሁት እርሱ እኔ እንደሆንሁና አብ ያስተማረኝን እንደምናገር፣ በራሴም ፈቃድ ምንም እንደ ማላደርግ ታውቃላችሁ። (አ.መ.ት)

እንደገናም፤

እኔ ከራሴ አልተናገርኩምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ። (ዮሐ. 12፥49)

ጌታ ኢየሱስ ሲያደርገው የነበረው ተአምራትና ሲናገራቸው የነበሩ ቃላት በእግዚአብሔር ዘንድ ነው የሚገኙት። እነዚህን እግዚአብሔር ነው ያደረጋቸው - በኢየሱስ በኩል - ነገር ግን እርሱ ነው ያደረጋቸው።

"ይኸውልህ ፊሊጶስ፣ የሥራዎቼ ምስጢር አካላዊ *መገኘቴ (ሀልዎቴ)* አይደለም፤ እናም ምስጢሩ አካላዊ መገኘቴ ካልሆነ ደግሞ በአካል *አለመኖሬም* ምንም ልዩነት አይፈጥርም።

"ለነገሩማ፣ እምነታችሁን በእኔ ላይ ካደረጋችሁ እኔ ያደረግኋቸውን ሥራዎች ማድረግ ትቀጥላላችሁ፤ እንዲያውም እኔ ካደረግኋቸው የበለጡ ሥራዎችን ታደርጋላችሁ።

"የእኔ መሄድ የሥራዎቼ ፍጻሜ እንደሚሆንና ነገር ሁሉ አስቸጋሪ እንደሚሆንባችሁ ታስባላችሁ። ነገር ግን ወደ አብ ቀኝ ከፍ ማለቴ፣ እኔ ከሠራኋቸው የሚልቁ ሥራዎችን በእኔ ምልጃ በኩል እንድትፈጽሙ ያስችላችኋል። እኔ በሰማይ ያለኝ ህልዎትና በእናንተ ውስጥ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ህልዎት ትልቅ ኀይልና ትልልቅ ሥራዎች እንዲኖሩ ማረጋገጫ ነው።"

ጌታ ሊሄድ ነው። መሄዱ ግን ሥራዎቹን አያፈራርሳቸውም።

## አስደናቂ የተስፋ ቃል

ከዚያም ጌታ ኢየሱስ ለማመን እስኪያስቸግር አስደናቂ የሆነ ተስፋ ለደቀ መዛሙርቱ - እና ለእኛ - ሰጠ።



እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል። (ዮሐ. 14፥12)

"ለእኛ" ያልኩት፣ ተስፋው "በእኔ የሚያምን" ስለሚል ሲሆን፣ ይህ ደግሞ እኛን ይመለከታል።

በእርሱ ለሚያምኑ ጌታ ኢየሱስ ሁለት ነገር ቃል ገብቷል፤ **አንደኛ፣** የእርሱን *ሥራ የሚመጣጠን* ይሠራሉ፤ **ሁለተኛ፣** እርሱ ከሠራው የሚበልጥ ያደርጋሉ። ይህን ቃል ከገባ አምሳ ቀናት በኋላ እርሱ በተሰቀለባት በዚያችው ከተማ የእርሱን ሥራ የሚስተካከል እና የሚበልጥ ሥራ ደቀ መዛሙርቱ ፈጸሙ። በሰገነቱ ቤት ውስጥ ዐሥር ቀን ከቆዩ በኋላም ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ውስጣቸው ተሞልቶ ወጡና በጴጥሮስ አጭር ስብከት ሦስት ሺህ ሰዎች ገና ባልጠናችው ቤተ ክርስቲያን ተጨመሩ።

ማስታወስ እንደምችለው ከሆነ ይህንን ደግሞን ለመፈጸም እየሞከርን ቢሆንም፣ ጰንጠቆስጤአዊው ኀይል መጥፋቱ እንደ ቀጠለ ነው። ቤተ ክርስቲያን በዮሐንስ 14፥12 የተስፋ ቃሏ መሠረት እየኖረች እንደ ሆነ የሚናገሩ በርካታ ክርስቲያኖችን አላውቅም። ስለዚህ ጥያቄው፣ "ለምን አልሆነም?" የሚል ነው።

ይህን ጥያቄ ለመመለስ መጀመሪያ ጌታ ኢየሱስ *የሚበልጥ ሥራ* ሲል ምን ማለቱ እንደ ሆነ መረዳት አለብን።

ምናልባት እውነተኛው ቍልፍ ያለው ብዙውን ጊዜ ችላ በምንለው ሐረግ ውስጥ ይሆናል፤ "እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና" በሚለው። የሚበልጡ ሥራዎች መሟላት የሚችሉት እርሱ ወደ አብ ከተመለሰ ብቻ መሆኑን ጌታ ኢየሱስ ግልጽ አድርጎታል። ለምን? ደቀ መዛሙርቱ ይህንን የተስፋ ቃል መገንዘብ ከመቻላቸው በፊት እርሱ ወደ ሰማይ ማረጉ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው? ማረጉ አካላዊ ተአምር ለማድረግ መሠረታዊ አልነበረም። ይህንን ለሦስት ዓመታት ሲፈጽሙት ኖረዋል።

በግልጽ ጌታ ኢየሱስ የሆነ የተለየ ነገር፣ የላቀ ደረጃ ያለው ነገር፣ አዲስ ደርዝ ያለው ነገር እየተናገረ ነው።

ጌታ ሲያርግ መንፈስ ቅዱስን ይልካል (ዮሐ. 7፥39፣ 16፥7)። የደቀ መዛሙርቱን (እንደ እኛው ዐይነት ሰዎች መሆናቸውን አስታውሱ) ጸሎት የመስማትና መልስ የመስጠት የምልጃ ስፍራውን ራሱ ጌታ ኢየሱስ ይይዛል። የሚበልጡ ሥራዎችን መሥራት የሚያስችለው ይህ ነበር።

ጌታ ኢየሱስ በአካል ቢለያዩም እንኳ በእርሱና በደቀ መዛሙርቱ መካከል ለሚኖረው ኅብረት አጽንዖት እየሰጠ ነው:: እርሱ መሄዱ ነው - ነገር ግን አብሮአቸው ይቈያል፤ የጀመረው ሥራም ይቀጥላል፣ ይጨምራልም:: አካላዊ መለየቱ ሥራውን አይቀንሰውም - ይጨምረዋል:: ባርናባስ ሊንደርስ እንደሚለው፣ "ሥራዎቻቸው የኢየሱስ ሥራዎች እንደ መሆናቸው፣ የኢየሱስ ሥራዎች በእግዚአብሔር የሚፈጸሙ እንደ ነበሩት ሁሉ የእነርሱም እንደ ዚያው በዓለም ውስጥ የሚፈጸሙ የእግዚአብሔር ተግባራት ናቸው::"[4]

"ሥራዎች" እና "የሚበልጡ ሥራዎች" የደቀ መዛሙርቱን ልዩ እና ነጠላ ተግባራት የሚያመለክቱ አይደሉም፤ ይልቁኑ የሚያደርጓቸው ነገሮች ሁሉ ራሱ ኢየሱስ በእነርሱ ውስጥ የሚፈጽማቸው የመሆኑን እውነታ እንጂ::

## በሻምፒዮኑ እጅ ውስጥ

ቴኒስ መጫወት አዘወትራለሁ:: ብዙም ጎበዝ ባልሆንም ችሎታዬን የሚያሻሽልኝን ነገር ሳገኝ ለመቀበል ሁሌም ዝግጁ ነኝ:: አንድ ቀን በቴሌቪዥን የሚተላለፍ ውድድር እየተከታተልኩ ሳለ የዊልሰን ቲ-2000 ራኬት ማስታወቂያ ሲተላለፍ አየሁ:: ዝነኛው የቴኒስ ሻምፒዮን ጂሚ ኮኖርስ አስገራሚ ስንዘራዎችን እያደረገ ሳለ ስውሩ ተራኪ "ዊልሰን ቲ-2000:: የዊምበልደንን እና የፎረስት ሂልስ ውድድሮችን በአንድነት ለማሸነፍ የሚሆን ብቸኛው ክብረት የተሠራ ራኬት" በማለት ተናገረ::

ችግሬ ይሄ ነበር! ይህን ሁሉ ጊዜ ከዕንጨት በተሠራው የዳንሎፕ ማክስፕሊ ራኬት ነበር የምጫወተው:: ዊልሰን ቲ-2000 የዊምበልደንን እና የፎረስት ሂልስ ውድድሮችን ማሸነፍ ከቻለ በእርግጠኝነት የእኔዎቹን ትንንሽ ውድድሮችማ ያጠናቅቃቸዋል::

ያንን ክረምት በሙሉ በዚያ አዲስ ራኬት ስጫወት ከረምኩ:: ክረምቱን ሙሉ ተሸነፍኩ:: ያ ራኬት ምንም አልፈየደልኝም:: የዊልሰን ስፖርት ቁሶች ኩባንያ የተሳሳተ ማስታወቂያ በማስተላለፍ ተጠያቂ ነው::

እውነቱ ግን ዊልሰን ቲ-2000 ራኬት የዊምበልደንንም ሆነ የፎረስት ሂልስን ውድድር አላሸነፈም - ውድድሩን ያሸነፈው ስፖርተኛው ነው - የዊልሰን ቲ-2000ን ራኬት ተጠቅሞ:: ቲፎዞዎቹ የዚያን ቀን ከግጥሚያው ስፍራ ሲሄዱ ዊልሰን ቲ-2000 ምን ዐይነት ታላቅ ራኬት እንደ ሆነ እየተነጋገሩ አልነበረም፤ ሲነጋገሩ የነበረው ጂሚ ኮኖርስ ምን ዐይነት ታላቅ ተጫዋች እንደ ነበር ነው:: የሽልማቱ ገንዘብ ቼክ የተጻፈውም ለተጫዋቹ ጂሚ ኮኖርስ እንጂ ለሌላ ቁስ አልነበረም::



አሁን ለቴኒስ ውድድር ራኬት መሠረታዊ ነው፤ ውድድሩን የሚ ያሸንፈው ግን ራኬቱ አይደለም:: ራኬቱን ተጠቅሞ ውድድሩን የሚያሸንፈው ተጫዋቹ ነው:: ሥራዎችን እና የሚበልጡ ሥራዎችን የሚፈጽመው ሻምፒዮን ኢየሱስ ሲሆን፣ እኛ በእጁ ውስጥ ያለን ራኬቶች ነን::

የጌታ ኢየሱስ "መሄድ" የደቀ መዛሙርቱ "የሚበልጡ ሥራዎች" ማለት ነው:: ዕርገቱም የመንፈስ ቅዱስ ኀይል መውረድና የክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ ምልጃ ጅማሮ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ወንጌልን የማዳረስ ተል እኮዋን እንድታሟላ የሚያስችል ነው:: ጄ. ሲ. ራይሌ እንዲህ ያብራሩታል፤

> የሚበልጡ ሥራዎች ማለት የብዙ ሰዎች መዳን ነው:: ከአንዲት ነፍስ መዳን የሚልቅ በላጭ ሥራ ሊኖር አይችልም::[5]
>
> ጌታ ኢየሱስ የተናገረው ምን እንደ ሆነ በሐዋርያት ሥራ ትረካ ውስጥ ማየት እንችላለን:: ጥቂት የፈውስ ተአምር ብቻ ሲኖር፣ አጽንዖቱ ለታላቁ ሰዎችን የማዳን ሥራ ነው:: በጴንጠቆስጤ ዕለት ብቻ እንኳ በጠቅላላው የጌታ ኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ከዳኑት ሰዎች በእጅጉ የሚበዙ አማኞች በዚያ አነስተኛ ቍጥር ባለው የአማኞች ስብስብ ላይ ተጨም ረዋል:: በዚህ ስፍራ "ከዚህም የሚበልጥ" የተባለው ቃል በቃል ሲፈጸም እናያለን:: የእግዚአብሔር ልጅ በምድራዊ ሕይወቱ የነበረው ተጽእኖ በአንጻራዊ ሁኔታ በአነስተኛ አካባቢ የተወሰነ ነበር:: ከእርሱ መሄድ በኋላ ግን ተከታዮቹ በስፋት በተሰበጣጠሩ ስፍራዎች ለመሥራትና ትልቅ ቍጥር ባላቸው ሰዎች ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ቻሉ::[6]

ይህም፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በዚህ የሚበልጡ ሥራዎች ተስፋ የማይኖሩበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ወደ መረዳት ያመጣናል::

መልሱን ለማግኘት የተሻለው ስፍራ ተስፋው ራሱ ነው:: ጌታ ኢየሱስ የተስፋውን ፍጻሜ እንዴት እንድንገነዘበው ነው ያሰበው? ለሚበልጥ ሥራ በዮሐንስ 14፥12 የተገባልን ቃል ቍጥር 13 ላይ ሌላ ተስፋ ተከትሎታል፤ "አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ::"

## ምሳሌአችን የሆነ ጥቅስ

እስቲ ቍጥር 12 ላይ ቧምንቆም አያይዘን ቍጥር 13 ድረስ እንዝለቅ:: "እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፤

እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና [ቍጥር 12]፡፡ … በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ" (ቍጥር 13)፡፡

የቍጥር 12 የሚበልጡ *ሥራዎች* በቍጥር 13 ጸሎት የሚከናወኑ ናቸው፡፡ ቍጥር 13 ምሳሌአችን የሚሆን ጥቅስ ሆኖአል፡፡

የሐዋርያት *ሥራ* መጽሐፍ በጸሎት ጉባኤ የተሞላ ነው፤ ቤተ ክርስቲያን ወደ ፊት ለመግፋት የምትወስደው እያንዳንዱ እርምጃ በጸሎት የተነከረ ነበር፡፡ የጰንጠቆስጤ ቀኗን ቤተ ክርስቲያን እንደ ተጨማሪ ምሳሌ ውሰዱአት፡፡ ለዐሥር ቀናት ጸልየው በዐሥር ደቂቃ ስብከት ሦስት ሺህ ሰዎች ዳኑ፡፡ ዛሬ ለዐሥር ደቂቃ ጸልየን ለዐሥር ቀናት እንሰብክና የሚድን ሰው ከተገኘ እንፈነድቃለን፡፡

ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ እኛ የምናደርገው እርሱ ባደረገበት መንገድ እንደሚሆን መናገሩን አስታውሱ፤ የእርሱ ምስጢር የእኛም ምስጢር ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ይጸልይ ነበር? ይህስ የሕይወቱ ጉልህ ክፍል ነበር? ጌታ ኢየሱስ ከአብ የሰማውንና ያየውን ብቻ መናገርና ማድረግ ከቻለ፣ በመስማትና በማየት ረጅም ጊዜ ማሳለፍ አለበት፡፡ እንደዚያም ነው ሲያደርግ የነበረው፡፡ በኢየሱስ ሕይወት የሚስተዋል ስልተ ምት አለ፤ ለማሰላሰልእና ለጽሞና ብቻውን ገለል ይላል፤ ከዚያ ሊያገለግል ይወጣል፡፡ አሁንም አሁንም ይህ አካሄድ (ሁኔታ) ራሱን ይደግማል፡፡ የጌታ ኢየሱስ የአደባባይ ሕይወት ከአባቱ ጋር በነበረው የግል ሕይወት የተደገፈ ነው፡፡

አሁን በሕይወት የሌሉትና በዓለም ዙሪያ እግዚአብሔር በሰፋት የተጠቀመባቸው የሙዲ መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ መጋቢ አላን ሬድፓዝ ለጥቂት ዓመታት እጅግ የከፋ የደም መርጋት ደረሰባቸው፡፡ በኋላ እያገገሙ ሳለ፣ "ጌታ ኢየሱስ ከሁሉም ነገር በላይ ይህንን ነገር እንዳስተማረኝ አምናለሁ፤ *በእምነት ጸሎት ሊሸፈን ከሚችለው በላይ ክርስቲያናዊ ሥራዎችን በፍጹም አትጀምር፡፡* እያንዳንዳችን ከአገልግሎታችን ጋር በተያያዘ ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ ለመረዳት በግል ተሞክሮአችን ልንደርስበት ይገባል፤ ሆኖም ይህ ለሁላችንም ዘላቂ መርሕ እንደሚሆን አምናለሁ፡፡ ይህን ማድረግ አለ መቻል ማለት በእምነት ሳይሆን በድፍረት መንቀሳቀስ ነው፡፡"[7]

ወደ ጸሎት ቤታችን የመጣውን የመጀመሪያ የጸሎት ጥያቄ አስታውሳለሁ፡፡ በድንገት ለዐሥራ አራት ሳምንት ስለ ምልጃ ጸሎት ከተካሄደ ስብከት በኋላ ሁለት መቶ እጅግ የተነቃቁ ማላጆችን መዘገብንና ውቧ ጸሎት ቤታችን በመጨረሻ ዝግጁ ሆነች፡፡



ስልክ ተደወለ፤ የአገልግሎቱን መከፈት አመልካች ሆነ፡፡ *ሥራ* ጀምረናል፡፡ አባሎቻችን ከነበሩት እናቶች አንዷ ናት፤ የሁለት ዓመት ዕድሜ ያለው ልጇ ከገባበት ሐኪም ቤት ነው የምትደውለው፡፡ እንዴት እንደ ሆነ እንጃ ትንሹ ልጅ የመኪና ሞተር ማጽጃ እጁ ይገባል፡፡ እርሱም ክዳኑን ይከፍትና ከመርዛማው ፈሳሽ የተወሰነ ያህል ይጠጣል፡፡ ወደ ድንገተኛ ክፍል አጣድፈው ሲወስዱት እየጮኸና እየተንዘፈዘፈ ነበር፡፡

ሐኪሙ ስለ ልጁ መትረፍ ምንም ተስፋ አልሰጠም፡፡ አንድን ጎልማሳ ለመግደል የሚበቃ መርዝ ነው ውስጡን እየበላው ያለው፡፡ የሆነ ትንሽ ተስፋ ቢኖር እንኳ ምናልባት ዐይነ ስውር ሆኖ ሊተርፍ ይችላል፡፡

እናም የምልጃ ጸሎት አገልግሎታችን ተጀመረ፡፡

ልናዘዝ፡፡ መቀበሉን ብጠላውም፣ ወዲያውኑ ከመጡልኝ ሐሳቦች አንዱ ይህኛው ነው፤ *አሁን ይህን የጸሎት ጥያቄ ለማላጆቻችን እሰጣቸዋለሁ፤ እነርሱም እንደሚሻለው ከምር አምነው ለሕፃኑ መትረፍ ይጸልያሉ - እርሱ ግን ይሞታል (ሐኪሙ ያለው ይህንን ነው፤ እውነቱን የሚያውቀው ደግሞ እርሱ ነው)፤ ስለዚህ ተስፋ ይቈርጣሉ፡፡*

ለዐሥራ አራት ሳምንታት እነዚህን ሰዎች ስለ ምልጃ አስደናቂ ኀይል ስሰብካቸው ቈይቻለሁ፤ እነርሱም እያንዳንዱን ቃል አምነው ተቀብለውኛል፡፡ ቋምጠዋል፤ ጥርሳቸውን ነክሰዋል፤ ሲኦልን በሌላ ሳይሆን በጸሎት ለመጋፈጥ ተዘጋጅተዋል፡፡ ከቀላሉ ጒዳይ ጀምረን ወደ ከባዱ እንደምንሄድ ነበር ተስፋ ያደረግሁት፡፡ አሁን ትልቅ ውርደት እንደሚገጥመን ዐውቄአለሁ፡፡

የጸሎት ጥያቄው ለማላጆቹ ተሰጣቸውና መጥተው ጸለዩ፡፡ እነዚህ ጀማሪዎች ክህነታቸውን በተግባር ለመግለጽ፣ የእግዚአብሔርን የጸጋ ዙፋን ለመከበብ፣ ስለ ወንድማቸው ነፍሳቸውን ለመስጠት ለሃያ አራት ሰዓት ወደ ጸሎት ቤቱ ገቡ፡፡

የመጀመሪያውን ጥሪ ከተቀበልን ከሃያ አራት ሰዓት በኋላም የስልኩ ድምፅ የጸሎት ቤቱን ጸጥታ አደፈረሰው፡፡ እናትየው ነበረች ዳግመኛ ከሐኪም ቤት የምትደውለው፡፡ እያለቀሰች፣ እየሣቀች፣ እግዚአብሔርን እያመሰገነች ነበር፡፡ ሐኪሙ ሊገባው አልቻለም፤ ነገር ግን ልጇ እያገገመ ነው፤ በዐይኖቹም ሆነ በሌሎቹ ወሳኝ የአካል ክፍሎቹ ላይ የደረሰ ጉዳት የለም፡፡ ይህ አስደናቂ አይደለምን? ተአምር መሆን አለበት፡፡

ደግሞም ነበር፡፡ የምልጃ አገልግሎታችንን ከሚቻለው ጀምሮ ወደማይቻለው መሄዱ የተሻለ እንደሚሆን ነበር ያሰብኩት፡፡ እግዚአብሔር ግን ከማይቻለው ጀመረና አስደናቂውንና አስፈሪውን የጸሎት ኀይል ገለጠ፡፡

ጸሎት የጌታ ኢየሱስ ምስጢር ነው:: ይህንንም ለእኛ አስተ ላልፎልናል፤ ነገር ግን የተቀበሉት ሁሉም ክርስቲያኖች አይደሉም:: የሚበልጡ ሥራዎችን ምስጢር የሚቀበሉት፣ "እግዚአብሔር በጸሎቴ በኩል የሚበልጡ ሥራዎችን እንደሚሠራ አምናለሁ" ማለት የሚችሉ ብቻ ናቸው::

ይህ የጌታ ኢየሱስ ምስጢር ነው - ለእኛ ዐይነት ሰዎች::

ማስታወሻ

1. Philip Yancey, *I Was Just Wondering* (Grand Rapids: Wm. B. Eerdmans Publishing Co., 1989) 94.
2. Ibid., 95.
3. D. Martyn Lloyd-Jones, *Preaching and Preachers* (Grand Rapids: Zondervan Publishing House, 1971) 169.
4. Barnabas Linders, *The New Century Bible, The Gospel of John* (Grand Rapids: Wm. B. Eerdmans Publishing Co., 1972) 475.
5. Quoted by Leon Morris, *The New International Commentary, The Gospel of John* (Grand Rapids: Wm. B. Eerdmans Publishing Co., 1971) 646.
6. Ibid., 646.
7. From an interview, February 1969.



## ፫ - በኢየሱስ ስም መጸለይ

# "ለመንግሥታዊ ጉዳይ ብቻ"

አንድ ቀን አንድ ሰው ወደ ቢሮዬ መጣና ስለ አሳሳቢ የንግድ ችግር አወራኝ:: ሁኔታውን ካብራራልኝ በኋላ፣ "ለመሆኑ ጸልየህበታል?" በማለት ጠየቅሁት::

የተናደደ መሰለ፤ "በእርግጥ አልጸለይኩበትም::"

"ለምን?"

"እንዴ! ይህ'ኮ ንግድ ነው" አለኝ:: "ስለዚህ መጸለይ አልችልም::"

ለዚህ ጠያቂዬ ጸሎት "ለመንግሥታዊ ጉዳይ ብቻ" የሚውል ሲሆን፣ መንግሥታዊ ማለት ደግሞ "ሃይማኖታዊ" ማለት ነው:: ሆኖም በጸሎት ጊዜ ሁሉ ነገር እንደ መንግሥታዊ ጉዳይ ይቈጠራል:: ስለ ምን መጸለይ ነው ያለብኝ? ለሚለው ጥያቄ ጌታ፣ "ስለ ማንኛውም ነገር" በማለት መልሷል:: ጌታ ስለ ማንኛውም ጉዳይ መጸለይ እንደምንችል የተናገረው ምሳሌአችን በሆነው በዮሐንስ 14፥13 ብቻ ሳይሆን፣ በዮሐንስ 15፥7 ላይም ነው:: "በእኔ ብትኖሩ፣ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፣ የምትለምኑትን ማንኛውንም ነገር ለምኑ ይሰጣችኋልም" (ኢ.መ.ት):: ስለ ማንኛውም ነገር እንድንጸልይ መጽሐፍ ቅዱስ ያበረታታናል::

### አትወስኑኝ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጸሎት ሲናገር "ትልቅ"፣ ገደብ የለሽ ቃላት ነው የሚጠቀመው:: ኤርምያስ 33፥3፣ "ወደ እኔ ጩኽ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኀይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ" ይላል:: "ኀይለኛ ነገር" የሚለው ሐረግ በቁሙ ሲተረጐም፣ "ስውር ነገሮች፣ የማይደረስባቸው ነገሮች፣ የታጠሩ ነገሮች" ማለት ነው::

ልጅ ሳለሁ አንድ ዝነኛ የነበረ "አትገድቡኝ" የሚል የፈረሰኞች ዘፈን ነበር:: ጸሎትም የሚለው እንደዚሁ ነው፤ "አትገድቡኝ":: ጸሎት አጥሮቹን

አፈራርሶ ነገሮችን በቀላሉ የሚደረስባቸው ያደርጋቸዋል፤ እንዲህ ባይሆን ኖሮ ነገሮቹ አጥር ውስጥ ተቀምጠው የማይደረስበት ርቀት ይኖራቸው ነበር:: ከጸሎት የመድረሻ ክልል ውጭ የሚሆን አንዳች ነገር የለም፤ ሥልጣኑ ድንበር የለውም::

ጸሎት ሁልጊዜም ተገቢ ነው:: በሰው ልብ አሳሳቢ የሆነ ነገር በእግዚአብሔር ልብም አሳሳቢ ነው:: አስታውሱ፤ ጭንቀት ውስጥ እስከንገባ ድረስ የገዘፈ ነገር፣ ግዝፈቱ ወደ ጸሎት የሚወስደን መሆን አለበት::

ሐዋርያው ጳውሎስም ስለ አንዳች እንዳንጨነቅ ይናገርና ስለ ነገር ሁሉ እንድንጸልይ ይመክራል (ፊልጵ. 4፥6):: "ስለ አንዳች - ስለ ነገር ሁሉ":: ጸሎት የሕይወታችንን ሁለቱንም ጽንፍ ይነካና በመካከል ያለውን እያንዳንዱን ነገር ይሸፍናል::

ቀደም ብለን እንዳየነው ቤተ ክርስቲያን እርሱ ካደረገው የሚበልጡ ሥራዎችን እንደምታደርግ ጌታ ኢየሱስ ተናግሮአል፤

> እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገ ውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል:: (ዮሐ. 14፥12)

እነዚህ ትልልቅ ሥራዎችም በጸሎት እንደሚደረጉ ተናግሮአል::

እነዚህ ቃላት አስደናቂ በመሆናቸው ጌታ ኢየሱስ ደግሟቸዋል፤ ፊታቸው ላይ የጥርጣሬ ሽውታ የተመለከተ ይመስል:: "ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ"::

ከሞቱ በፊት በነበረው በዚህ የመጨረሻ ስብሰባ (ዮሐንስ 14-17) ጌታ ኢየሱስ እነዚህን ቃላት ለደቀ መዛሙርቱ ስድስት ጊዜ ደግሟቸዋል፤ "ብትለምኑ ... አደርገዋለሁ":: ዶክተር ከርቲስ ሚቸል እንዲህ ይላሉ፤

> *ጸሎት የእግዚአብሔርን መርሐ ግብር በምድር ላይ ለማከናወን ወሳኝ ሰብአዊ ድርሻ እንደ ሆነ ተደርጎ በዚህ ቀላል ዐረፍተ ነገር ተቀምጧል:: መለኮታዊ ድርጊት በእምነት በሚደረግ ጸሎት ላይ እንደሚመሠረት ክርስቶስ በሆነ ምስጢራዊ መንገድ በአስገራሚ ድፍረት ይናገራል:: ስለዚህ ጸሎት የአማኙ ዋነኛ ሥራ ተደርጎ ተቀምጧል፤ ጥያቄ ማቅረብ ኀላፊነቱ ነው:: ማከናወን ደግሞ የእግዚአብሔር ኀላፊነት ነው::*[1]



ስለ ጸሎት ብቁና አጥር ምጥን ያለ ፍች የሚሰጥ አንድ ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ መምረጥ ቢኖርብኝ ምርጫዬ ዮሐንስ 14፥13 ነው የሚሆነው:: "አብ በወልድ እንዲከብር፣ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ" (አ.መ.ት)::

በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 2 የክርስቶስን የሚበልጡ ሥራዎች ተስፋ ዐይተናል:: አሁን ደግሞ እነዚህ የሚበልጡ ሥራዎች የሚፈጸሙባቸውን የጸሎት ዐይነቶች እናያለን::

## በስሜ

በዚያ ዐረፍተ ነገር ውስጥ እጅግ ትርጉም ያዘለው ሐረግ "በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ" የሚለው ነው:: በእነዚህ በሰገነት ላይ የተካሄዱ ምዕ ራፎች (ዮሐንስ 14-17) ጌታ ኢየሱስ ቃላቱን ለበርካታ ጊዜአት ይጠቀማቸዋል፤

"በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ" (14፥13)::

"ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ" (14፥14)::

"አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ" (15፥16)::

"አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ" (16፥23)::

"እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ፤ ትቀበሉማላችሁ" (16፥24)::

"በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ" (16፥26)::

*በስሜ* በሚለው ቃል ጌታ ኢየሱስ በቤዝዎታዊ (redemptive) ሥራው ውስጥ አዲስን እርከን፣ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ላለው ግንኙነትም አዲስን ወርድና ስፋት ያመለክታል:: "እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና" በማለት የሚበልጡ ሥራዎችን እንደሚፈጽሙ ቃል ገብቶላቸዋል:: ወደ አባቱ እስኪሄድ ድረስ፣ የመዋጀት ሥራው አልተጠናቀቀም ነበር፤ የገባው ቃል ተፈጻሚ የሚሆነው በሰማይ በግርማው ቀኝ ሲቀመጥ ብቻ ነው:: በራሱ ለኀጢአታችን መንጻትን ካስገኘ በኋላ መካከለኛና ኪዳኑን በሥራ ላይ የሚያውል (ፈጻሚ) ይሆናል:: ሥልጣንን በእጁ ያስገባል (ዕብ. 1፥3)::

"ተቀመጠ" - የተጠናቀቀ ሥራ እና የተጀመረ ሥራ:: የመስቀሉ ሥራ፣ ዕፍረቱ፣ ሥቃዩ እና መሥዋዕትነቱ ተጠናቋል:: የዙፋኑ ሥራ፣ ምልጃና መካከለኛነት ተጀምሯል:: አሁን ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የሚመጡት በጌታ

ኢየሱስ በኩል ነው። *መሥዋዕት* በሆነው በእርሱ በኩል እንጂ በ*መሥዋዕቶች* በኩል *መሆኑ* አከትሟል። በምድራዊ ካህናት በኩል *መሆኑ* አከትሟል፤ በሰማይ ባለውና በእግዚአብሔር ፊት በሚታይልን በታላቁ ሊቀ ካህናታችን በኩል እንጂ።

በአካል ያለ መኖሩን ክፍተት ለመሙላት ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሦስት ነገሮችን ቃል ይገባላቸዋል፤ *ሰላሙን* (ዮሐ. 14፥27)፣ *አጽናኙን* (ዮሐ. 14፥16)፣ እና *በስሙ መጸለይን* (ዮሐ. 16፥23፣ 24)። በጌታ በኢየሱስ ስም መጸለይ ጸሎትን በሚመለከት ሙሉ በሙሉ አዲስ ትምህርት ሲሆን፣ የሚገኘውም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው።

## ስሙ ውስጥ ምን አለ?

በጌታ ኢየሱስ ስም መጸለይ ምን የተለየ ነገር አለው? በስሙ መጸለይ ብቻም ሳይሆን በስሙ መኖርስ? ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት" በማለት ያዛል (ቈላ. 3፥17)።

የጌታ ኢየሱስ ስም ሲጠቀሙበት ምትሀታዊ ኀይል ያለው አይደለም። እግዚአብሔርን እንዳሻን የምናንቀሳቅስበት መሣሪያም አይደለም። በጌታ ኢየሱስ ስም መጸለይ ማለት "በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን"፣ "ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመስማማት"፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ተቀድሶ" መጸለይ ማለት ነው። በስሙ የመጸለይ መብት የሰጠንም ተወካዮቹ (ወኪሎቹ) በመሆናችን ምክንያት ሲሆን፣ በእርሱ ወኪልነታችን ጥያቄ የምናቀርበውም የምናካሂደው የእርሱን ሥራ በመሆኑ ነው።

በሉቃስ 9፥48 ላይ ጌታ ኢየሱስ፣ "ማንም ይህን ሕፃን በስሜ የሚቀበል፣ እኔን ይቀበላል፤ የሚቀበለኝም ሁሉ የላከኝን ይቀበላል" በማለት ተናግሯል። አንድን ሰው በኢየሱስ ስም መቀበል ራሱን ጌታ ኢየሱስን መቀበል ነው። ጌታ ኢየሱስ ከስሙ ጋር ሙሉ በሙሉ አንድ ሆኖ ይታወቃልና ስሙን ማወቅ ማለት እርሱ ማን እንደ ሆነና ምን እንደ ሠራ በሙላት ማወቅ ነው።

እስቲ ለምሳሌ ሮሜ 10፥13ን እንመልከት፤ "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና"። ይህ "የሮሜ የድነት ጎዳና" አካል ነው። ለጠፉ ሰዎች ለመመስከር ብዙ ጊዜ ተጠቅሜበታለሁ። ጥቅሱ ግን፣ "ክርስቶስ እንዲያድናችሁ ብትጣሩ ያድናችኋል" ከማለት ያለፈ ትርጒም አለው። ይህ ዐረፍተ ነገር ለጸሎት ብቻ የተወሰነ አይደለም። *መጥራት* የሚለው ቃል እዚህ ጋ ጥቅም ላይ የዋለው መጀመሪያ ለአድናቆት ሲሆን፣ ቀጥሎ ልመና ለማቅረብ ነው።[2]



"የጌታን ስም መጥራት" ኢየሱስ ስሙ እንደሚለው መሆኑን አምኖ መቀበል ነው - ጌትነቱን። ቊጥር 9፣ "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር [ከቊጥር 13 ጋር አነጻጽሩት]፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና" ይላል። ስሙ ጌታ ነው፤ እርሱም ስሙ እንደሚለው ነው - ጌታ። ስሙን በመጥራት ጌትነቱን አምነው የሚቀበሉ ሁሉ ደግሞ ይድናሉ።

አሁን እስቲ እናጠቃልለው። በጌታ ኢየሱስ ስም መጸለይና ማድረግ ማለት በእርሱ ሥልጣንና ስምምነት የጸለይንበትን ጒዳይ መፈጸም ማለት ነው። የምንጸልይበትና የምናደርገው ነገርም በስሙ ከተገለጠው የእርሱ ማንነት ጋር ይጣጣማል ማለትም ነው። በጌታ ኢየሱስ ስም መዋሸትና መስረቅ አትችሉም፤ ይህ ከስሙ ጋር የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ እርሱም ስሙን በዚህ ሁኔታ እንድትጠቀሙበት ፈጽሞ አይፈቅድላችሁም።

እናም በጌታ ኢየሱስ ስም መጸለይ ማለት እንደ ፈቃዱ፣ እንደ ስምምነቱ፣ ከባሕርዩ፣ ከጠባዩና ከዕቅዱ ጋር የሚጣጣም ጸሎት ማቅረብ ማለት ነው። ስለዚህ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ጥያቄውን ያቀረበ ያህል ነው። ሥልጣናችን ይህ ነው።

## ላብ ሳይሆን፣ ደም

እስቲ እነዚህን ሁለት አጋጣሚዎች በመጠቀም ላብራራው። በወጣትነቴ በከተማ ዳር የምትገኝና በፍጥነት በማደግ ላይ የነበረች የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሳለሁ ለግል ጸሎቴ የሚመቸኝ ምርጥ ጊዜ እኩለ ሌሊት ነበር - ለሁሉ ሰው የእንቅልፍ ጊዜ ስለሆነ የስልኩም ሆነ የበሩ ደወል አያስቸግረኝም። አንድ የተለየ ቀን ግን ባልተለመደ ሁኔታ ግርግር የበዛበት ሆኖ ዋለ። ሥራ በዝቶብኝ ዋልኩ። ለመጸለይም ሆነ መጽሐፍ ቅዱሴን ለማንበብ ጊዜ አላገኘሁም። እንዳችም "መንፈሳዊ" ነገር አላደረግሁም። አስፈላጊ የሆኑ ደብዳቤዎችን ጽፌአለሁ፤ ስልኮችን አነጋግሬአለሁ፤ ስብሰባ አዘጋጅቻለሁ፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ ዕለታዊ ዕቅድ መሠረት ሥራዎችን ሠርቻለሁ - አንድም መንፈሳዊ ሥራ ግን አልሠራሁም።

የእኩለ ሌሊት የጸሎት ሰዓቴ ሲደርስም አለመብቃት እየተሰማኝ ወደ ጸሎት ስፍራዬ መጣሁ። ከአንደበቴ የወጡት የመጀመሪያዎቹ ቃላት፣ "ጌታ ሆይ፤ ዛሬ ማታ አንተን አንድም ነገር የመጠየቅ መብት እንደሌለኝ ዐውቃለሁ" የሚሉ ሲሆን፣ ለመጸለይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ ወይም ለመመስከር - አንድም መንፈሳዊ ነገር ለማድረግ ጊዜ እስካጣ ድረስ ባተሌ ለመሆኔ ይቅርታ ጠየቅሁ። እየተሸማቀቅሁ ነበር ስጸልይ የነበረው።

ድንገት ጌታ የተናገረኝ መሰለኝ፤ "እሺ ይሁንልህና በርካታ 'መንፈሳዊ' ነገሮችን ስታደርግ - ለአራት ሰዓታት ስትጸልይ፣ መጽሐፍ ቅዱስን (ተንበርከ ከህ) ለአራት ሰዓታት ስታነብ እና ዐሥር ሰዎችን ወደ ጌታ ስታመጣ ዋልክ እን በል፡፡ ታዲያ ለመጸለይ ከአሁን ይልቅ ልበ ሙሉነት ይሰማሃል ማለት ነው?"

"አዎን፤ ይሰማኛል!"

"እሺ፤ ስለዚህ በራስህ ስም ነው የምትጸልየው ማለት ነው! ከቅድስናህ የተነሣ እንደምሰማህ ታስባለህ፡፡ ብዙ መልካም ሥራዎችን ከሠራህ አንተን ይበልጥ የመስማት ዝንባሌ እንዳለኝ ታስባለህ፡፡ ብቁ ባልሆንው የገዛ ስምህ ነው የምትቀርበኝ፡፡ ዛሬ ለስምንት ሰዓት ብትጸልይ፣ እንዲሁም ተንበርክከህ ለስምንት ሰዓት መጽሐፍ ቅዱስ ብታነብና አምሳ ሰዎችን ወደ ጌታ ብታመጣም አሁን ካለህ የበለጠ የመጸለይ ሙብት አይኖርህም!"

አቀርቅሬ የእግዚአብሔርን ዙፋን ከፍል ወለል ሳየው የተረጨው በእርሱ ደም እንጂ በእኔ የመልካም ሥራዎች ላብ አለመሆኑን አየሁ፡፡

ጴጥሮስና ዮሐንስ ያንን ሽባ ሰው መልካም በምትባለው ደጅ ሲፈውሱት ጴጥሮስ፣ "በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ" በማለት ነው የተናገረው (የሐዋ. 3፥6)፡፡

የቤተ መቅደሱን አካባቢ አጨናንቀው መዋል የሚያዘወትሩ ሰዎች "መደነቅና መገረም ሞላባቸው" (ቍጥር 10) እና ወደ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሮጡ፡፡ እናም ...

> ጴጥሮስም ይህን ባየ ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ "የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤ በዚህ ለምን ትደነቃላችሁ? ደግሞም በእኛ ኀይል ወይም በእኛ ጽድቅ ይህ ሰው ድኖ እንዲመላለስ እንዳደረግነው በመቍጠር፣ ለምን ወደ እኛ አትኩራችሁ ትመለከታ ላችሁ? ..." (የሐዋ. 3፥12 - አ.መ.ት)

የፈውስ ኀይል ስለ ጽድቃቸው የተሰጣቸው ሽልማት አልነበረም፡፡ "ይህ ... ሰው የበረታው በኢየሱስ ስም በማመን ነው" (የሐዋ. 3፥16 - አ.መ.ት)፡፡

እግዚአብሔር እኛ በፈጸምነው ሥራ ምክንያት ወደ ጸጋው ዙፋን አይጋብዘንም፤ ክርስቶስ በፈጸመው ሥራ ምክንያት እንጂ፡፡ በኢየሱስ ስም እንመጣለን፤ አብም በኢየሱስ ስም ይቀበለናል፡፡

ይህንን እውነት አስረግጦ የሚደመድምላችሁ አንድ ሙከራ ይኸውላችሁ፡፡ በሚቀጥለው ጊዜ ስትጸልዩ በራሳችሁ ስም እንደ መጣችሁና በጽድቃችሁ ምክንያት መስማት ለማግኘት እንድምትጠይቁ ለእግዚአብሔር ንገሩት፡፡ ይህንን በዚያን ምሽት ሞክሬዋለሁ፡፡ እንዲህ ዐይነት ኀዘንና ብቸኝነት በፍጹም ተሰምቶኝ አያውቅም፡፡ ወደ ጌታ ኢየሱስ ስም አፈገፈግሁ፡፡



## ተጨማሪ ብርሃን

እግዚአብሔር በሚያስደንቅ መንገድ ተጨማሪ መረዳት ሰጠኝ፡፡ እኔና ቤተ ሰቤ ወንድሜንና ቤተ ሰቡን ለመጠየቅ ወደ አርካንሳስ ግዛት ሄደን ነበር፤ ወቅቱም የአካባቢው የንግድ ትዕይንት (ባዛር) የሚፋፋምበት ነበር፡፡ አንድ ምሽት ሁሉን ሰው በመኪና ጭነን ወደ ባዛሩ አቀናን፡፡ ልጆቻችን በባለ ሰማያዊ ሪባን አሳማም ሆነ በተሸላሚዋ ጊደር እንዳልተመሰጡ ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልፈጀብንም፡፡ መሄድ የፈለጉት ወደ መጋለቢያ ቦታ ነው፡፡ ስለዚህ ይበልጥ ባህላዊ ገጽታዎች ያሉበትን ቦታ ትተን ወደ ካርኒቫልና ጣፋጭ ምግቦች ወዳሉባቸው ቦታዎች አመራን፡፡

እያንዳንዱ ግልቢያ ዐሥር ሳንቲም ይጠይቃል፡፡ ትልቅ የባለ ዐሥር ሳንቲም ትኬቶች ጥቅል ገዛንና ዝግጅታችንን አመቻቸን፡፡ በዚያን ወቅት ወንድሜ ርብቃ የምትባል አንዲት ሴት ልጅ ስትኖረው፣ እኔ ደግሞ ዳግማዊ ሮኒ፣ እስጢፋኖስ እና ኪምበርሊ የሚባሉ ሦስት ልጆች ነበሩኝ፡፡ በመጋለቢያው መግቢያ አካባቢ ጥሩ ቦታ መርጬ፣ ተመቻችቼ ቆምኩና ልጆቹ እጃቸውን ዘርግተው ሲመጡ ከጥቅሉ ላይ ቀዩን ባለ ዐሥር ሳንቲም ትኬት እየቀደድኩ መስጠት ጀመርኩ፡፡

ዐልፎ ዐልፎ የዝቅዝቅ በሚሽከረከረው መጋለቢያ መግቢያ ላይ የትኬቱን ጥቅል ይዤ ቆሜያለሁ፡፡ መጀመሪያ ርብቃ እጇን ዘርግታ መጣችና ትኬት ሰጠኋት፡፡ ከዚያ ኪምበርሊ እጇን ዘርግታ ስትመጣ ትኬት ሰጠኋት፡፡ ቀጣዩ ሮኒ ነበር፤ ከዚያም እስጢፋኖስ - እያንዳንዳቸው ቀዩን ባለ ዐሥር ሳንቲም ትኬት ለመቀበል እጃቸውን ዘርግተው ነበር፡፡

ልክ ከእስጢፋኖስ በኋላ በሕይወቴ ሙሉ በፍጹም ዐይቼው የማላውቀው ልጅ መጣ - ቀዩን ባለ ዐሥር ሳንቲም ትኬት ለመቀበል እጁን ዘርግቷል፡፡ *ይህ ልጅ ማን ነው? ምን መውሰድ ነው የፈለገው? ይህ ትኬት ለእያንዳንዱ ቅጠል ዐሥር ሳንቲም ዋጋ አለው - እጁን ዘርግቶ ለመጣ ለእያንዳንዱ ልጅ ስታድሉት አትውሉም፡፡* ልጁ እዚያው ቆሞአል፤ እጆቹን ዘርግቶ፣ እየጠበቀ፡፡ ችላ አልኩት፡፡ እዚያው እንደ ቆመ ነው፤ ከእርሱ በኋላ ያለው ሰልፍ እየረዘመ ነው፡፡ ለመጋለብ ተራቸውን እየጠበቁ ያሉት ልጆቻችን የተፈጠረው ነገር ምን እንደ ሆነ ለማወቅ በመፈለግ ይቁነጠነጣሉ፡፡

በመጨረሻ እስጢፋኖስ ዘወር አለና ወደዚህ ሙጭጭ ያለ ትንሽ ለማኝ እያመለከተ፣ “አባቢ፤ ይህ ጓደኛዬ ነው። ትኬት እንደምትሰጠው ነግሬው ነው የመጣው” አለኝ።

*ጓደኛ!* ከመጣን ገና ሃያ ደቂቃ እንኳ አልሆነንም እኮ። ፊቴን መለስኩ። ልጁ አሁንም እዚያው ቆሞአል፤ እጆቹ እንደ ተዘረጉ ናቸው።

ምን እንዳደረግሁ ማወቅ ትፈልጋላችሁ? ቀዩን ባለ ዐሥር ሳንቲም ትኬት ቈረጥኩና ሰጠሁት - ስለ ፈለግሁ ወይም ስለ ተገባው አይደለም፤ ልጄ አባቱ ትኬት እንደሚሰጠው ለዚህ ልጅ በመናገሩ ምክንያት እንጂ። ልጄን ዕፍረት ውስጥ ልከትተውም ሆነ ውሸታም ላደርገው አልፈለግሁም።

ባያስተውለውም እንኳ ትንሹ ልጅ ትኬት ሲጠይቅ የነበረው “በእስጢፋኖስ ስም” ነበር። እኔም “በእስጢፋኖስ ስም” ትኬት ሰጠሁት። የልጄን ቃል አከበርኩ።

ከዚያ ገባኝ። ይኸው ነው! ወደ አብ እሄድና “ቀዩን ባለ ዐሥር ሳንቲም ትኬት ብጠይቅህ እንደምትሰጠኝ ልጅህ ነግሮኛል” እለዋለሁ። በኢየሱስ ስም እጠይቃለሁ፣ አብም በኢየሱስ ስም ይሰጠኛል።

አብ የልጁን ቃል ያከብራል።

ማስታወሻ

1. Curtis C. Mitchell, *Praying Jesus' Way* (Old Tappan, NJ: Fleming H. Revell Company, 1977) 11.
2. Ernest Kasemann, *Commentary of Romans* (Grand Rapids: Wm. B. Eerdmans Publishing Co., 1980) 292.



## ፬ - ታላቁ ምክንያተ ጸሎት

# እግዚአብሔር ጸሎትን ለምን እንደሚመልስ

እዚህ ጋ አንዳንድ እጅግ አስቸጋሪ ጥያቄዎችን ልናነሣ እንችላለን፤ እግዚአብሔር ሐሳቡን ይቀይራል? ጸሎት የእግዚአብሔርን ዕቅዶች ያስቀይራል? የእግዚአብሔር ፈቃድ ድንጋጌ ነው ወይስ ምኞት? ወይስ ሁለቱንም? ወይስ አንዱንም አይደለም? መልስ ፍለጋ እነዚህን ጥያቄዎች የማሳደድ ፍላጎት የለኝም፤ አሊያ ይህንን በማንሣትና ያንን በመጣል ተውጠን መቼም ወደ ጸሎት አንመጣም።

ለእነዚህም ሆነ ለሌሎች ጥያቄዎች የሚኖሩን መልሶች (1) የእግዚአብሔርን ሉዐላዊነት የማይነኩ፣ እና (2) በእርሱ ላይ መተማመናችንን የምንቀጥልበት ቦታ ሊኖራቸው ይገባል። እግዚአብሔር የሚናገረን በሚገባን ቋንቋ ሲሆን፣ የመጣልን የእግዚአብሔር ቃልም ይህ ነው - *እርሱ ጸሎታችንን ይመልሳል።* የተናገረው በዚህ መንገድ ሲሆን፣ እንድንቀበለው የፈለገውም ይህንኑ ነው።

ለመጸለይ ስለ ጸሎት ሁሉ ነገር እስኪገባን ድረስ የምንቈይ ከሆነ መቼም አንጸልይም። ቫንስ ሀቭነር፣ “ስለ ኤሌክትሪክ የማውቀው ነገር የለም፤ ነገር ግን ይህ እስኪሆን ድረስ በጨለማ አልቀመጥም” ይል ነበር። ለመጸለይ አስቀድመን ጸሎትን አበጥረን ማወቅ የለብንም።

### ጸሎት ምን ያህል ጠቃሚ ነው?

ጠቃሚው ነገር መጸለይ ነው። ምን ያህል ነው የሚጠቅመው? እግዚአብሔር ስንጠይቀው የሚያደርጋቸውና ካልጠየቅን የማያደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ። እኛ፣ “ይሁና፤ ምንም ቢከሰት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እግዚአብሔር ይህ እንዲኖረኝ ከፈለገ ይኖረኛል። እንዲሆን ከፈለገ ይሆናል” እያልን በግዴለሽነት እንናገራለን። ይህ በከፊል ብቻ እውነት ነው። “ብትለምኑ (ብትጠይቁ) አደርገዋለሁ” የሚለው የኢየሱስ ንግግር እኛ ካልጠየቅን እርሱም እንደማያደርገው ግልጽ አንድምታ ይዟል። ቅዱስ ያዕቆብ ይህንን ግልጽ አድርጎታል፤ “አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም” (ያዕ. 4፥2)።

## አሰደናቂ ግኝት

ለምሳሌ፣ በወንጌላቱ ስለተዘገቡት የፈውስ ተአምራዊ ምልክቶች አንድ አስደናቂ እውነታ አግኝቻለሁ:: በእነዚህ ተአምራዊ ምልክቶች ኢየሱስ ተነሣሽነቱን ሲወስድ የምናየው ከስንት አንዴ ነው:: ከሞላ ጎደል የምን መለከተው ሰዎች ካልጠየቁት በቀር የማይፈውሳቸው መሆኑ ነው:: አንዳንዴ ተከታትለውና አሳድደው ሊደርሱበት ይገባል:: በርጠሜዎስ ኢየሱስ እስኪሰማው ድረስ ደጋግሞና አብዝቶ በመጮኹ በአካባቢው የነበሩት ሰዎች ዝም እንዲል ዐይነ ስውሩን ለማኝ ተናግረውታል (ማር. 10፥46-52):: ኢየሱስ የሲሮፊኒቃዊቷን ሴት ልጅ ከመፈወሱ በፊት መጀመሪያ ችላ አላት፤ ከዚያ ደግሞ "ዘለፋት" (ማቴ. 15፥21-28):: ኢያኢሮስም ለሴት ልጁ ተነሣሽነቱን ወስዶ ወደ ኢየሱስ መምጣት ነበረበት:: ደም ይፈስሳት የነበረችዋ ሴት ኢየሱስ ትኩረት ሳይሰጣት በፊት ነካችው::

> እስቲ ምሳሌአችን ያደረግነውን ጥቅስ እንመልከት፤
>
> አብም ስለ ወልድ እንዲከበር፣ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ:: (ዮሐ. 14፥13)

ኢየሱስ የገባውን ቃል በሚቀጥለው ቍጥርም ይደግመዋል፤ "ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ *እኔ አደርገዋለሁ*" (ቍጥር 14፣ አጽንኦት የራሴ):: "እንድታደርጉት አግዛችኋለሁ" አለማለቱን ልብ በሉ:: "*እኔ* አደርገዋለሁ" ነው ያለው::

እስቲ፣ "በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን *ሥራ* ... ያደርጋል ... ከዚ ህም የሚበልጥ ያደርጋል" ወደሚለው ቍጥር 12 ለደቂቃ መለስ በሉ:: በአንዱ ቍጥር ላይ *እኛ* እንደምናደርግ ይናገርና ከዚያ በሚቀጥለው ቍጥር ደግሞ፣ "*እኔ* አደርገዋለሁ" ይላል:: እሺ፣ አድራጊው ማን ነው - ክርስቶስ ወይስ እኛ?

ሁለታችንም:: እኛ እና ኢየሱስ ነን *ሥራውን* የምንሠራው:: በዮሐንስ ምዕራፍ 14 ከቍጥር 8 እስከ 10 ውይይት ያካሄድንበትን ያለፈውን ምዕራፍ ታስታውሳላችሁ? ኢየሱስ አብን እንዲያሳያቸው ፊሊጶስ ጥያቄ ሲያቀርብ፣ ኢየሱስ እርሱን ካዩ አብን እንዳዩ ነገራቸዋል:: አብ በወልድ በኩል ነው የሚሠራው::

ስለ አብና ስለ ወልድ እውነት የነበረው ነገር ስለ እኛም እውነት ነው:: እኛ ትልልቅ ነገሮችን እንሠራለን፤ ግና *ሥራዎቹን* በእኛ በኩል የሚፈጽማቸው ራሱ ኢየሱስ ነው - በእምነት ለሆነ ጸሎታችን ምላሽ አድርጎ:: "ምድር እንቅስቃሴው ከሰማይ እንዲመጣ ትጠብቃለች" ማለት



እናዘወትራለን:: ሆኖም፣ "ሰማይ ጥያቄው ከምድር እንዲመጣ ትጠብቃለች" ማለትም እንችላለን::

እግዚአብሔር ለምን በዚህ መንገድ ማድረግ ፈለገ? ስለ ጸሎት ለመረዳት አስቸጋሪው ነገር እግዚአብሔር እንዲህ ዐይነቱን ኀይል በእኛ ዐይነቶቹ ሰዎች እጅ ውስጥ ለምን እንዳደረገ መረዳቱ ነው:: እግዚአብሔር ጸሎትን በመመለስ ለምን ይደሰታል? ኢየሱስ እኛ ጥያቄ ስናቀርብ ለማድረግ ለምን ቃል ገባ? "አብም ስለ ወልድ እንዲከበር" በማለት በግልጽ ነግሮናል (ቍጥር 13)::

## ታላቁ ምክንያት

አብም ስለ ወልድ እንዲከበር:: ታላቁ የጸሎት ሁሉ ምክንያት ይኸው:: ስለ ጸሎት ትልቁ ነገር እኛ የጠየቅነውን ማግኘታችን ሳይሆን፣ በእኛ ማግኘት ውስጥ የእግዚአብሔር መከበር ነው:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አሁንም አሁንም የምንመላለስበት ቱምቢ ይህ ነው::

በኢየሱስ ስም መጸለይ እስካሁን ካየናቸው እና ሦስቱ ግዙፋን ብዬ ከምጠራቸው ውስጥ ሁለተኛው ነው:: ሦስቱ ግዙፋን ስል ሦስት የጸሎት ማጣሪያዎችን ማለቴ ነው:: እያንዳንዱ ልመና በእነዚህ መግቢያዎች ዐውድ ውስጥ ነው የሚዋቀረው፤ (1) የእግዚአብሔር ፈቃድ፣ (2) የጌታ ኢየሱስ ስም፣ እና (3) የእግዚአብሔር ክብር:: በጌታ ኢየሱስ ስም የሚደረግ የትኛውም ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒም ሆነ ከእርሱ ክብር ጋር የማይጣጣም አይሆንም:: ስለዚህ የምጠይቀው ነገር እንደ ፈቃዱ ሲሆንና መልሱ ክብርን ለእግዚአብሔር የሚያመጣ ሲሆን ብቻ ነው በጌታ ኢየሱስ ስም መጸለይ የምችለው ማለት ትክክል ነው::

የምጠይቅበት ምክንያት እርሱ ከሚመልስበት ምክንያት ጋር ሲመሳሰል፣ በጸሎት ሜዳ ላይ ነው ያለሁት:: እርሱ የሚፈልገውን ነገር ስፈልግ - እኛ ሁለታችንም ተመሳሳይ ነገር ስንፈልግ ሥራ ጀምረናል::

እግዚአብሔር በጸሎት የሚደሰትበት ምክንያት እርሱ ለዚያ ጸሎት መልስ በመስጠት አንድ ነገር ሲያደርግ ያንን ማን እንዳደረገው ምንም ጥርጣሬ ስለማይኖር ነው:: ክርስቲያኖች፣ በተለይም እኛ አገልጋዮች፣ የነገሩን ምስጋና ለራሳችን ወስደን ለእግዚአብሔር ክብር የምንሰጥበት ዘዴ አለን:: የሆነ ታላቅ የሥራ ውጤት ሲኖር፣ ይህ አስደናቂ ነገር እንዲፈጸም በእንዴት ያለ ትጋት እንዳቀድነው፣ እንዳጠናነውና እንደ ቀየስነው፣ እንደገናም እንዴት ይበልጥ እንዳቀድነው፣ እንዴት ለረጅም ጊዜ በብርቱ እንደ ለፋንበት ያሸበረቀ ዝርዝር

ይዘን እናብራራለን፡፡ ከዚያም፣ “ክብሩ ለእግዚአብሔር ይሁን” በማለት ከግርጌ ለማከል ጠንቃቆች ነን፡፡ ለምግብ ቤት አስተናጋጅ ጉርሻ እንደምንሰጥ ዐይነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ስሙ በአክብሮት ይጠቀስለታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ እግዚአብሔር በግልጽ ለጸሎት መልስ በሆነ መንገድ ሲሠራ ምስጋናውንም ሆነ ክብሩን ይወስዳል፡፡

## ጉደኛ ቤተ ክርስቲያን! ጉደኛ ኬክ!

ለመጨረሻ ጊዜ በመጋቢነት ባገለገልኩበት ጊዜ ወጣት መዘምራኑ በአንድ ክረምት በሶልት ሌክ ከተማ በሚደረግ ከተማ አቀፍ የወንጌል ሥርጭት ላይ እንዲሳተፉ ተጋበዙ፡፡ ቀን ቀን በገበያ አዳራሾችና በመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች፣ ማታ ደግሞ በጆማ ስብከቱ ላይ ነው የሚያገለግሉት፡፡ ሁሉም በጉጉት ስሜታቸው ተቀሰቀሰ፡፡ ነገር ግን አራት ሺህ ችግሮች የነበሩብን ሲሆን፣ እያንዳንዱ ችግር ደግሞ ባለ መቶ ዶላር ነው፡፡ ጉዞው እኛ ያልነበረንን አራት ሺህ ዶላር ይፈልጋል፡፡

ገንዘቡን እንድናሰባስብ የሆነ ሰው ሐሳብ ሲያቀርብ ያለ ልቤ ሆኜ ወጣቶቹ የኬክ ቁርስ አዘጋጅተው የሚሸጡበትን መድረክ እንዲያመቻቹ ፈቃድ ሰጠሁ፡፡ እንዲህ ዐይነት ነገሮች በጣም ነው የሚያስጠሉኝ - ሰዎች ኬክ ሲገዙ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለተዘፈቀ እግዚአብሔር የርዳታ እጃቸውን የሚዘረጉ ነው የሚመስለኝ፡፡

ለሚሲዮናውያን እና ለሌሎች ክርስቲያናዊ ሠራተኞች ርዳታ ማሰባሰብ አስፈላጊ እንደ ሆነ ይገባኛል - እኔና ሚስቴ በርካታ እንዲህ ዐይነት ሰዎችን ለዓመታት ስንረዳ ቈይተናል፡፡ ይህኛው ግን የተለየ ነው፡፡

ለማንኛውም፣ አንድን ቅዳሜ መረጥንና አንድ መቶ ትኬቶችን አዘጋጅተን ኬክ ስንሸጥ ዋልን፡፡ ያንን ታሪከኛ ቅዳሜ መቼም አልረሳውም፤ ከተኛ በት ድንገት እንደሚባንን ሰው ነቃሁና ትዕይንቱ ቀልቤን ሳበው፡፡ ቤተ ክርስቲ ያናችን “ጉደኛ ሳንድዊች” ከተባለ ሳንድዊች መሸጫ አጠገብ ነው የምትገኘው፤ ሳንድዊች መሸጫው ትልልቅ ሳንድዊቾችን የሚሠራ ሲሆን፣ ሰዎች ሲያዩት “ጉደኛ ሳንድዊች!” ብለው ይጮኻሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ያዘጋጀችው ድንኳን “ጉደኛ ቤተ ክርስቲያን! ጉደኛ ኬክ!” ተብሎ በደማቁ ተጽፎበታል፡፡ ወጣቶቹ መኪኖች በበዙበት ዐውራ ጎዳና ላይ ቆመዋል፡፡ በጭንቅላታቸው ላይ “ጉደኛ ሳንድዊች” የሰጣቸውን አስቂኝ ባርኔጣ አድርገው፣ በዐንገታቸው ላይ ኬክ የያዘ ዝርግ ነገር አንጠልጥለዋል፡፡ በጋለ ስሜት ሥራቸውን እየሠሩ ነው፡፡ መኪኖች ፍጥነታቸውን እንዲቀንሱ ያደርጉና ቆመው ኬክ እንዲገዟቸው ይለምናሉ፡፡



መኪናዬን አቆምኩና ጭንቅላቴን አቀርቅሬ፣ ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ ሳልመለከት በቀጥታ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ገባሁ፡፡ “ጉደኛ ሳንድዊች” የሰጣቸውን አስቂኝ የአብሳይ ባርኔጣ አድርገው “እምነትና መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸው” ዲያቆናቼ መተላለፊያው ላይ ኬክ እየጋገሩ ቆመዋል፡፡ ጠረጴዛ ተዘጋጅቶ ለኬክ የተለየ ፍላጎት የሌላቸው፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን በዚህ ቀውስ ውስጥ ለማገዝ የፈለጉ ጥቂት ሰዎች ዙሪያውን ተቀምጠው ኬካቸውን በጥርሳቸው ይሸራርፋሉ፡፡ ቅመም አከፋፋዩ የሰጣቸውን ቅመማ ቅመም እያሸተትኩ ቆምኩ፤ ክሬም ሻጩ የሰጣቸው ስልስ ሽታ የእግዚአብሔርን መቅደስ ሞልቶታል፡፡

የዚያን ቀን 2,000 ዶላሩን አገኘን፡፡ ለዚያ ሞኝነት ንስሓ እስክገባ ድረስ እግዚአብሔር በቀጣዮቹ ሦስት ቀናት እናቴን ሲቀውረው ቈየ፡፡ ረቡዕ ምሽት በጥናት ክፍሌ ሆኜ ስለ ሁኔታው እየጸለይኩ ሳለ እግዚአብሔር፣ “ምን መሥራት እንደምችል እንዳሳያችሁ ፍቀዱ፡፡ ለቀጣዩ 2,000 ዶላር ተማመኑብኝና - ጠቅላላው 2,000 ዶላር በአንድ ሰው በኩል እንዲመጣ አደርጋለሁ” በማለት የተናገረኝ መሰለኝ፡፡

ያን ምሽት ቀሪው 2,000 ዶላር አሁንም እንደሚያስፈልገን፣ ነገር ግን ገንዘቡን ለማሰባሰብ ለኬክ ሽያጭ በፍጹም ወደ ጎዳና እንደማንወጣ - ቢያንስ በእኔ መጋቢነት ወቅት - ለቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ተናገርኩ፡፡ “እግዚአብሔር መዘምራኑ ወደ ሶልት ሌክ ከተማ እንዲሄዱ ከፈለገ” አልኳቸው፤ “ራሱን በሚያስከብርና ቤተ ክርስቲያኑን በማያዋርድ መንገድ ገንዘቡን ይሰጠናል፡፡”

እግዚአብሔር ካልደረሰልንና ገንዘቡን ካላገኘን ምን እንደምናደርግ ለማወቅ አንድ ሰው ጠየቀ፡፡

“አንሄድም” በማለት መለስኩ፡፡ “ያ ምናልባት እግዚአብሔር መዘም ራኑ ወደዚያ መሄዳቸውን እንዳልፈቀደ የሚናገርበት መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ ‘በእግዚአብሔር መንገድ የተሠራ የእግዚአብሔር ሥራ ከእግዚአብሔር ዘንድ አቅርቦትን በፍጹም አያጣም’ በማለት የተናገረው ዊልያም ኬሪ ይመስለኛል፡፡”

እግዚአብሔር እርሱን እንድታመን እንዴት በዚያን ቀን እንደ መራኝ ተረከሁላቸው፡፡ ሰዎቹም ተስማሙና እግዚአብሔር እንደ ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልገንን በክብር እንዲሞላብን ጸልየን ነገሩን ለእግዚአብሔር ተውነው፡፡

ከዚያ ገንዘቡን ማን ይሰጠን እንደ ሆነ በማሰብ መገረም ጀመርኩ፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ይህንን ማድረግ የሚችሉ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች

ነበሩ፤ ማንኛቸውም ወደ ፊት ወደ መድረኩ አልመጡም፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ከምሽቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ስልኬ ጮኸ፡፡ በቅርቡ ጋብቻ የፈጸመች አንዲት የቤተ ክርስቲያናችን ወጣት ነበረች፡፡ ኑሮአቸውን ለማሟላት እርሷም ሆነች ባሏ ሥራ መሥራት እንዳለባቸው ዐውቃለሁ፡፡

“መጋቢ፣ ከማግባቴ ጥቂት ወራት በፊት የመኪና አደጋ አጋጥሞኝ ከመድን ድርጅት 3,000 ዶላር ተቀብዬ ነበር፡፡ 2,000 ዶላሩ አሁንም በእጄ ይገኛል፡፡ ዛሬ ሙሉ ቀን ሥራ ላይ ሳለሁ ገንዘቡን ለመዘምራኑ እንድሰጥ ሲሰማኝ ነው የዋለው፤ ሆኖም ባሌን ሳላማክር አንድም ነገር ለማድረግ አልፈለግሁም፡፡ እርሱም ገና ከሥራ እንደ ገባ አንድም ቃል ከመናገሬ በፊት እግዚአብሔር 2,000 ዶላሩን ለወጣት መዘምራኑ እንድንሰጥ እንደሚፈልግ ማሰቡን ነገረኝ፡፡ ለዚህ ነው ለማድረግ የወሰንነው” በማለት ነገረችኝ፡፡

ኬክ ሸጠን 2,000 ዶላር አገኘን፤ 2,000 ዶላሩን ደግሞ በመጸለይ፡፡ ኬኩን ስንሸጥ የመዘምራኑ አባላት ጎዳና ላይ ለመቆማቸው ምስጋና አቀረብን፡፡ ዲያቆናቱ ቅዳሜአቸውን ኬክ ለመሸጥ በማዋላቸው ምስጋና አቀረብንላቸው፤ “ጉደኛ ሳንድዊች”ን ለአስቂኙ የአብሳይ ባርኔጣዎች አመሰገንን፡፡ ቅመም አከፋፋዩን ቅመማ ቅመሞቹን በቅናሽ ስለ ሸጠልን ስናመሰግን፣ ክሬም ሻጩንም አልረሳነውም - ከዚያ ደግሞ ሳናመሰግን ያለፍነው ሰው እንዳይኖር በማለት ስንጨነቅ ቈየን፡፡

2,000 ዶላሩን በጸሎት ስናገኝ ግን፣ እግዚአብሔርን ነው ያመሰገንነው፡፡ ክብሩንም ሆነ ምስጋናውን እርሱ ነው ጠቅልሎ የወሰደው፡፡ ለነገሩ፣ ጸሎት ማለት ይኸው ነው፡፡



# ክፍል ሁለት

## የምስጢራዊው መንግሥት ምስጢራዊ የጦር ዕቃ

## ፫ - እውነተኛው ፍልሚያ ያለበት ስፍራ

# የዓለማቱ ጦርነት

> መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። (ኤፌ. 6፥12)

ስለ አንድ ተሸንፎ የማያውቅና የማይሸነፍ የኤፌሶን ታጋይ የሚነገር ጥንታዊ ታሪክ አለ። ከግጥሚያ ወደ ግጥሚያ ተመልካቾችን እያስደነቀ፣ ተጋጣሚዎቹን በልጦ ያሸንፋል። በኦሎምፒያ ሲወዳደርም ተጋጣሚዎቹን ሁሉ እየዘረረ በተለመደው አይበገሬነቱ ቀጠለ - ባለሥልጣናቱ ቁርጭም ጭምጊቱ አካባቢ ኤፌሲያ ግራማታ ማሰሩን እስኪደርሱበት ድረስ። ኤፌሲያ ግራማታ (የኤፌሶን ደብዳቤዎች) የተጻፉ ምትሀታዊ መተቶች ሲሆኑ፣ አብዛኛውን ጊዜም በሆነ ከረጢት ነገር ውስጥ ተሰፍተው እንደ ክታብ ይደረጋሉ። እነዚህ መተቶች ከክርስቶስ ልደት በፊት ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የታወቁ ሲሆኑ፣ ክፉ መናፍስትንና አጋንንትን እንደሚያባርሩና ለአድራጊውም ልዩ ኀይልና ከለላ እንደሚሰጡት ይታመንባቸዋል። የኦሎምፒያ ባለሥልጣናት "ደብዳቤዎቹን" ከታጋዩ እግሮች ላይ ሲያነሡ ምትሀታዊ ኀይሉን ስላስወገዱበት በሦስት ተከታታይ ግጥሚያዎች በቀላሉ ተሸነፈ።[1]

ምናልባት ጳውሎስ ዘይቤውን ሲጠቀም፣ ሙሉውን ምዕራፍ በወታደራዊ ተምሳሌት ሲሞላ፣ አንድን ታጋይ ወስዶ "መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም" እያለ ሲናገር ይህን ታሪክ እያሰበ ሊሆን ይችላል።

ኤፌሶናውያን ለትግልም ሆነ ለምትሀት ቤተኛ ነበሩ። ትግል በምዕራባዊው የታናሹ እስያ ክፍል እጅግ ተወዳጅ ጨዋታ ሲሆን፣ ኤፌሶን ደግሞ በምትሀት ማዕከልነት ባለዝና ነበረች። የግሪኩ ዓለም ክፉ መናፍስትና ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኀይላት የተጨናወተው ዓለም ነበር። የግዛቱ ሦስተኛዋ ትልቅ ከተማ ኤፌሶን "ለሁሉም ዐይነት ምትሀታውያን፣ አስማተኞችና

አስመሳዮች መኖሪያነት ከሁሉ በብዙ የምትሻል እጅግ ምቹ ነበረች::"[2] ከተማዪቱ በተንባዮችና አስማተኞች ተወርራ ነበር::

ምናልባት ሐዋርያው ጳውሎስ ኤፌሲያ ግራማታን ለኀይል ምንጭነት ማጥለቃቸውን ትተው የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ "እንዲለብሱ" ለአንባቢዎቹ እየተናገረ እንደ ሆነ ማሰቡ ቀልብ የሚስብ ነገር ሊሆን ይችላል:: ከለመዱት የሥጋ-እና-ደም ትግል ጋር ሲነጻጸር የአማኞች እውነተኛ ተጋድሎ "መንፈሳዊ የጦር ዕቃን የሚጠይቅ የመንፈሳዊ ኀይል ግጭት ነው::"[3]

ከጨለማ ኀይላት ጋር የምናደርገው ተጋድሎ ተጋጣሚውን በቀላሉ መቋቋም የሚችል ታጋይ እንደሚያካሂደው ትግል የቀለለ አይደለም::

በሐዋርያው ጳውሎስ ውስጥ ያለው ሐሳብ ምንም ይሁን ምን አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ አንባቢዎቹ ላለባቸው ልዕለ ተፈጥሯዊ ውጊያ እንዲነቁ ፈልጓል::

## የኀይላት ግጭት:- የእግዚአብሔር ኀይል ከጨለማ ኀይላት ጋር ሲነጻጸር

የክርስትና ሕይወት የግጭት ሕይወት ነው:: ጦርነት ውስጥ ነው ያለነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ "የውጊያ ምዕራፍ" ውስጥ ከጠላት ጋር በተቃራኒ እንደምንቆም ስድስት ጊዜ ተናግሯል፤ ይህም ለጦርነቱ ግለትና ለውጊያው ግላዊ ባሕርይ አጽንዖት የሚሰጥ የጨበጣ ውጊያን የሚያመለክት ቃል ነው:: ዐወቅንም አላወቅንም በውጊያው ውስጥ በግላችንም እየተሳተፍን ጦርነቱ መካከል ነው ያለነው::

ክርስቲያን የሆነ ነገርን *ተቃውሞ የሚቆም* ነው፤ የሆነ ነገር ደግሞ ክርስቲያኑን *ተቃውሞ ይቆማል::* አማኝ እንደ መሆናችን ለማይታዩ ኀይላት የተቀናጀ ጥቃት ዒላማ ነን - እግዚአብሔርን ተቃውመው ያመፁ ስውር ኀይላት መዋቅር:: ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ክፉ ባላጋራዎች "አለቆች፣" "ሥልጣናት፣" "ገዦች፣" "የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት" በማለት ለያይቶ ያስቀምጣቸዋል::

ሐዋርያው ስለ አራት የተለያዩ የአጋንንት ክፍሎች እያስረዳ አይደ ለም:: እያንዳንዱ ቃል ከእግዚአብሔር እና ከሕዝቡ በተቃራኒ በተለያየ መን ገድ የተሰለፉትን ኀይላት ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋለ ነው:: "አለቆች" ደረጃቸ ውንና ሥልጣናቸውን ያሳያል:: "ሥልጣናት" ለሥልጣን ያላቸውን ዓላማ ያመ ለክታል:: "የጨለማ ዓለም ገዦች" ዓለም ፈጣሪውን ተቃውሞ በመነሣቱ ላይ ያላቸውን ቍጥጥር ይጠቁማል:: "በሰማያዊ ስፍራ ያሉ የክፋት መንፈሳውያን



ሠራዊት" የሚለውም የርኩሳን መናፍስቱን መኖሪያ፣ ወይም ቢያንስ ውጊያቸ ውን የት ድረስ እንደሚወስዱት - እስከ ሰማይ እንደሚያደርሱት ይገልጻል::[4]

ዋልተር ዊንክ እንደሚለው፣ "ይህ የቃላት ቁልል፣ ሰውርና ዓለምን እስከ መጠቅለል የሚደርሱ የሕይወት ጠር የሆኑ መንፈሳዊ ኀይላትን መረብ ለማስረዳት በተከታታይ የተቀመጠ ነው::"[5] እነዚህ ተምሳሌቶች ብቻ ወይም የንግግር ዘይቤዎች አይደሉም:: ውጊያው የምር ነው::

## ዋነኛው ዒላማ

በምልጃ ውስጥ ዋነኛው ዒላማ ሰውዬው ወይም ችግሩ አይደለም፤ ከጀርባ ያለው ኀይል ነው:: ከእነዚህ ጀርባ *ኀይላት* አሉ - ጥልቅ እና የጨለማ ኀይላት:: በዐይን የሚታየውን ዓለም ጠቅላላው ዓለም አድርጎ የመውሰድና ዐይናችን የሚያየውን ነገር የመጨረሻው እውነታ አድርጎ የማምታታትን ልማድ ጥሰን መውጣት አለብን:: "የዚህ ማምታታት ጦስ ... ከሚታዩት አላባውያን (*መሠረታዊ ነገሮች*) ጀርባ ላለ ስውር ኀይል ባርያ መሆን ነው::"[6]

*መንፈሳዊ ውጊያን* እየተጋፈጥን ነውና ዲያብሎስን በራሱ መሬት ልንጋጠመው ይገባል:: ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክቱ ምሽግን ለመስበር ብርቱ የሆነውን የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ እንጂ ሥጋዊ የጦር ዕቃን በዚህ ጦርነት እንደማንጠቀም ይናገራል (10፥3-4):: ውጊያችን አካላዊ ወይም ቁሳዊ አይደለምና የጦር ዕቃችን አካላዊም ሆነ ቁሳዊ ሊሆን አይችልም::

አል የሚባል ሰውን አስታውሳለሁ:: ላትወድዱት የምትችሉት ዐይነት ሰው አይደለም:: የጥሩ ሰብዕና ባለቤት ነው:: እጅግ የተሳካለት የሽያጭ ባለሞያ:: አልኮል የሚያዘወትር ክርስቲያን:: ሲሰክርም በሚስቱና በልጆቹ ላይ ጉዳት የሚያደርስ::

አልና እኔ ለበርካታ ጊዜአት ተነጋግረናል፤ ጸልየናልም - አንዳንዴ በመኖሪያ ቤቱ፣ አንዳንዴ ቢሮዬ ውስጥ:: መጽሐፍ ቅዱስን የእኔን ያህል ያውቃል:: በማማከረው ጊዜ እኔ አንድ ጥቅስ ስጀምር እርሱ ከነምዕራፍና ቍጥሩ ተናግሮ ይጨርሰዋል:: የሚረብሽ ነገር ነው:: አስቀድሞ የማያውቀውን አንድም ነገር ነግሬው አላውቅም:: እያለቀሰና ንስሓ እየገባ ጸልዮአል፤ ምንም ለውጥ ግን አልነበረም::

የተጨነቀች ሚስቱ አንድ ቀን ምሽቱ ከገፋ በኋላ ደወለች:: አል ሰክሮ ከሌላ ጊዜው በባሰ አኳኋን ጥቃት አድራሽ ሆኖአል:: ልጆቹን ይዛ ቤቱን ለቅቃ ሸሽታለች::

ወደ አል ቤት መኪናዬን እያሽከረከርኩ ሳለ የአል ችግር ችግሩ ሳይሆን ከችግሩ ጀርባ ያለው ኀይል መሆኑን እንዳስተውል ጌታ ረዳኝ፡፡ ሰይጣን በአል ሕይወት ውስጥ ምሽግ ስለ ገነባ አል ከጠጪነት ነጻ ከመውጣቱ በፊት ምሽጉ መፍረስ አለበት፡፡

ያን ምሽት እኔና አል በ2ኛ ቆሮንቶስ 10፥3-4 መሠረት ጸለይን፡፡ በሕይወቱ ያለውን የሰይጣን ምሽግ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ ምንነቱን በመግለጥ፣ የክርስቶስን ኀይል የበላይነት እያወጅንና እያረጋገጥን ተጋፈጥነው፡፡

በዚያን ምሽት በትክክል ምን እንደ ተፈጸመና እንዴት እንደ ተፈጸመ አላውቅም፤ ነገር ግን ከዚያን ጀምሮ እስካሁን ድረስ (ዐሥር ዓመት ዐልፎታል) አል አልኮል ጠጥቶ አለማወቁን *አስረግጬ* ዐውቃለሁ፡፡ መላው ሕይወቱም ተለውጧል፡፡

ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊ ውጊያን ስልት ለመረዳት ሁሌም ቀርፋፋ ሆና ቈይታለች፡፡ የሚያማምሩ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎችን፣ ሙዚቃዊ እንቅስቃሴ ለማሳየት የተቀናጀ የመዘምራን ቡድንንና ከፍተኛ ኀይል ያለውን የሕዝብ ድጋፍ ይዘን ነው ወደ ውጊያው እየወደቅንና እየተነሣን የምንጓዘው፡፡ እነዚህ ነገሮች መልካም ናቸው፤ ብቻቸውን ግን ለመንፈሳዊ ውጊያ ረብ የለሾች ናቸው፡፡

ጌታ ኢየሱስ የችግሩን ላይ ላይ ዐልፎ ከችግሩ ጀርባ ወዳለው ኀይል የሚደርስበት መንገድ ነበረው፡፡ ጴጥሮስ የጌታ ኢየሱስን ማንነት በተመለከተ አስደናቂ እወጃ ካደረገ በኋላ ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ስለ መሞት ሲናገር ሊገሥጸው ጀመረ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ምን ምላሽ ሰጠ? የጴጥሮስ የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት ላይ ጥያቄ አቀረበ ወይስ ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መሄድ አመክንዮአዊ ሙግት አቀረበ? አይደለም፤ ከችግሩ ባሻገር ሄዶ ከበስተ ጀርባ ወዳለው ኀይል ዐለፈና፣ "ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን!" አለ (ማቴ. 16፥23)፡፡

ጌታ ኢየሱስ ጠቡ ያለው ከስምዖን ጴጥሮስ ሥጋና ደም ጋር ሳይሆን፣ ከጨለማ መንፈሳዊ ኀይላት ጋር መሆኑን ዐውቋል፡፡

ጳውሎስና ሲላስ በፊሊጵስዩስ ሳሉ አንዲት ወጣት ምዋርተኛ ሴት፣ "የመዳንን መንገድ የሚነግሩአችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው" በማለት እየጮኸች ትከተላቸው ነበር (የሐዋ. 16፥17-18)፡፡ ሐዋርያው በምን ዐይነት መንገድ ችግሩን ተወጣው? የምዋርትን አደጋዎች ለልጃገረዲቱ በማስረዳት የተሳሳቱ መንገዶቿን እንድትቀይር ለማሳመን አፋጠጣት? እንዲያውም በተቃራኒው ወደ እርሷ ዘወር ብሎ፣ *"መንፈሱን* 'ከእርስዋ



እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ' አለው" በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ቍጥር 18 - አጽንኦት የተጨመረ)፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ችግሩን ዐልፎ ከችግሩ ጀርባ ወዳለው ኀይል ሄደ፡፡ ውጊያው መንፈሳዊ ነበረና መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎችን ተጠቀመ፡፡

በየትኛውም ውጊያ ውስጥ ጠላትን አሳንሶ መገመት እጅግ አደገኛ ነው፤ በመንፈሳዊ ውጊያም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ አጭበርባሪ ፖለቲከኞችን በታማኞች መተካት፣ የነቀዙ ተቋማትን አፍርሶ ኢፍትሐዊ ሕግጋትን መሻር፣ የወሲብ ምስሎችን የሚያስተላልፉ ሥዕሎችንና ጽሑፎችን መደምሰስና ውርጃን ማስወገድ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የውርጃ ተቃዋሚዎች የየግዛቶቹን ሕግ አውጪዎች አሳምነው ውርጃን ለማሳገድ ሙከራ ሲያካሂዱ በነበረበት "የዌብስተር ውሳኔ" ተብሎ በሚታወቀው ፍርድ ዋዜማ ቻርልስ ኮልሰን እንዲህ ብሎ ጻፈ፤

> ክርክሩ በሚካሄድባቸው ግዛቶች የምናሸንፍ ቢሆን እንኳ፣ ይህ የውርጃ ተቃዋሚዎች ትግል ፍጻሜ አይደለም፡፡ ይህ ሲሆን የሰው ሕግ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር እንዲስማማ ማድረጋችን ነው፤ ይህ ጥሩ ግብ ቢሆንም በቂ አይደለም፡፡ ሕጉ የግብረ ገብ (ሞራል) መምህር ቢሆንም ሕጉ ብቻውን የሰዎችን ግብረ ገባዊ ምርጫዎች መቀየር አይችልም፡፡ ሴቶች ሕገ ወጥ ውርጃዎችን መፈለጋቸው አይቀርም ... ሕግን ብቻ ሳይሆን ከዚያም ወደሚበልጥ መሠረታዊ ደረጃ ማለፍ አለብን፡፡[7]

የፊት ለፊት ፍልሚያዎችን እናሸንፍ ይሆናል፤ ነገር ግን ከእነዚህ ከፋቶች ጀርባ ካሉት አጋንንታዊ ኀይላት ጋር ያለውን ጉዳይ ካልተወጣን በምንቈርጠው ጭንቅላት ምትክ እንደ ሀይድራ ሌላ ጭንቅላት ብቅ ማለቱ (መብቀሉ) አይቀርም፡፡* እንደ ሄራክልስ ካሉት ዘጠኝ ራሶች መካከል ስምንቱን ብንቈርጥበት እንኳ ቀሪው ዘጠነኛ ራስ "የማይሞት" ሆኖ ጦር ዕቃዎቻችን ከሚደርሱበት ክልል ውጭ ሊሆን ይችላል፡፡ "ለውጥ ማምጣት ይቻላል፤ ግና የኀይሉ መንፈስም ሆነ መገለጫ ቅርጽ ከተነካ ብቻ ነው፡፡ ያ መንፈስ ደግሞ በመንፈሳዊ መንገድ ተለይቶ ሊታወቅ የሚችልና መንፈሳዊ ግፍጫ ብቻ የሚፈልግ ነው፡፡"[8]

---

* በግሪኮች ሐተታ አማልክት ውስጥ ዘጠኝ ራሶች ያሉት ጭራቅ ሲሆን፣ በጀግንነቱና በጥንካሬው በሚታወቀው ሄራክለስ ተገድሏል፡፡ ከሀይድራ ራሶች መካከል አንዱ ሲቈረጥ፣ በቦታው ሌላ ራስ በፍጥነት ያድጋል፡፡

ስውር ምሽጎችንና የማይታዩ ኀይላትን ድንገት በወረራ የምታጥለቀል ቁት እንዴት ነው? ምልጃ ብቅ የሚለው እዚህ ጋ ነው:: መቃወም በቂ አይደለም፤ መጸለይም አለብን:: የማርቆስ ወንጌል ዘጠነኛ ምዕራፍ አንድ በክፉ መንፈስ የተያዘን ልጅና የአባቱን ታሪክ ይዟል:: ጌታ ኢየሱስ ከጴጥሮስ፣ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር ተራራው ላይ ሳለ የቀሩት ደቀ መዛሙርት ጋኔኑን ከልጁ ለማስወጣት ያልተሳካ ሙከራ አካሂደዋል:: ጌታ ኢየሱስ ከመጣና ልጁን ነጻ ካወጣው በኋላ፣

> ደቀ መዛሙርቱ፣ "እኛ ልናስወጣው ያልቻልነው ለምንድን ነው?" ብለው ጠየቁት:: እርሱም "የዚህ ዐይነቱ ሊወጣ የሚችለው በጸሎትና በጾም ብቻ ነው አላቸው:: (ማር. 9፥28-29 - አ.መ.ት)::
>
> (በጾም ላይ ለተጨማሪ መረጃ ምዕራፍ 14ን ተመልከቱ::)

## ጦርነቱ የሚካሄደው የት ነው?

እስካሁን እንዳየነው ኤፌሶን 6 ስለ ጥያቄው ብዙ አብርሆት ይሰጣል:: ስኬታማ መንፈሳዊ ውጊያን ለማካሄድ መንፈሳዊ የጦር ዕቃና ጦር መሣሪያዎች ሊኖረን ይገባል:: ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያስፈልገንን ነገር በቍጥር 13-17 ውስጥ ይነግረናል፤

> *ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፣ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ:: እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፣ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፣ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫ ምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር፣ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው::*

አሁን እስቲ ሐዋርያው ጳውሎስን በቅርበት እንከተለው:: በመጀመ ሪያ በእርግጥም መንፈሳዊ ውጊያ፣ መንፈሳዊ መሣሪያዎችን የሚጠይቅ ጦርነት መኖሩን ይነግረናል:: ከዚያም ራሳችንን ለፍልሚያው እንድናዘጋጅ - የእግ ዚአብሔርን የጦር ዕቃ እንድናነሣ፣ በመንፈስ ቅዱስ ሰይፍ ራሳችንን እንድና ስታጥቅ ይነግረናል:: "እሺ ጳውሎስ፣ እነሆኝ፤ ለባብሼ ለጕዞ ተዘጋጅቻለሁ:: የድነትን ራስ ቁር አጥልቄአለሁ፤ ይህን መላውን አካል የሚሸፍን ትልቅ ጋሻ አንግቤአለሁ፤ የእውነት መታጠቂያውንም ወገቤን ለማጥበቅና ሌሎቹ ጦር



ዕቃዎች እንዳይወድቁ ሰብስቦ ለመያዝ ታጥቄዋለሁ:: እግሮቼም እግዚአብሔ ርን የመታዘዝ ዝግጁነትን ተጫምተዋል፤ ሰይፍም ይዣለሁ:: ታዲያ ውጊያው የት ነው? ለመፋለም ዝግጁ ነኝና የፍልሚያውን ስፍራ አመላክተኝ::"

አመላክቶናል፤ "በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ" (ቍጥር 18):: የምሩን ነው? ጥብቅ ዝግጅት አድርጌአለሁ:: አንድ ቶን የሚመዝን የብረት ልብስ ነው የለበስኩት፤ ይህን ግዙፍ ሰይፍ ሰድሬአለሁ፤ እና ጳውሎስ ምን እንዳደርግ ነው የሚነግረኝ? *እንድጸልይ::*

እስቲ ወደ ቍጥር 14 እንመለስ:: የጠቅላላው ምንባብ ቍልፍ ቃል በሆነው "ቁሙ" የሚል ትእዛዝ ነው የሚጀምረው:: "ቁሙ" ከሚለው ትእዛዝ በኋላ ቀሪዎቹ የቍጥር 14 ክፍሎችና ከቍጥር 15 እስከ 17 ያሉት ክፍሎች ለማብራራት የገቡ ናቸው:: ከዚያም፣ "በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ" ወደሚለው ቍጥር 18 ተመልሰን እንመጣለን:: እስቲ ቍጥር 14 ላይ ካለው "እንግዲህ" በሚለው ቃልና "ጸልዩ" በሚለው የቍጥር 18 ቃል መካከል ያሉትን ሁሉንም ነገሮች ብትተዉአቸው፣ "ቁሙ፤ እንግዲህ በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ" የሚል ዐረፍተ ነገር ይኖራችኋል:: *ውጊያው ጸሎት ነው:: ጸሎት መንፈሳዊው ጦርነት የሚፋፋምበት የውጊያ ስፍራ ነው::* ውጊያውን ድል መንሣትም ሆነ በውጊያው ድል መነሣት ያለው እዚህ ነው::

በስብከት ሆነ በማስተማር ወይም በምስክርነት የፍልሚያ ሜዳውን ከመርገጣችን በፊት ውጊያው በጸሎት ሜዳ ገና ድሮ ተወስኖ አልቋል:: ይህ በዘፀአት 17፥8-13 ውስጥ በደማቁ ተሥሏል:: እስራኤላውያን ከአማሌቅ ጋር በራፊዲም ሸለቆ ውስጥ ተገናኙ፤ አማሌቅም መንገድ ዘግቶ፣ "መሄድ የምትች ሉት እዚህ ድረስ ብቻ ነው:: ከንዴን ሳልንተራስ ከዚህ አታልፉም" አላቸው::

ሙሴም ኢያሱን፣ "ጕልማሶችን መርጠህ ውጣና አማሌቅን ተዋጋ፤ እኔ የእግዚአብሔርን በትር ይዤ በኮረብታው ራስ ላይ እቆማለሁ" አለው::

ኢያሱን ብሆን ኖሮ፣ "ሙሴ፣ እኔ የተሻለ ሐሳብ አለኝ፤ አንተ ለውጊ ያው ወደ ሸለቆው ውረድ፤ *እኔ* ወደ ተራራው ራስ ልውጣ" እለው ነበር::

ነገር ግን ኢያሱ የሙሴን ትእዛዝ ተቀብሎ አማሌቅን በሸለቆ ውስጥ ጦርነት ገጠመ::

በዚህ መካከል ሙሴ የእግዚአብሔርን በትር ይዞ በተራራው ላይ የነበረ ሲሆን፣ አንድ እንግዳ ነገር ተከሰተ:: ሙሴ እጁን ከፍ ሲያደርግ ኢያሱ ያሸንፋል፤ እጁን ዝቅ ሲያደርግ ግን አማሌቅ ያሸንፋል:: ልክ እንደ ሲምፎኒ

አርኬስትራ ጦርነቱ በእጁ የያዘውን በትር የሚከተል ሆነ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሙሴ ደከመና እጆቹ መክበድ ጀመሩ፡፡ በተራራው ላይ የእግዚአብሔር በትር ዝቅ አለና፣ በሸለቆው ውስጥ አማሌቅ ማሸነፍ ጀመረ፡፡

ከሙሴ ጋር በተራራው ላይ የነበሩት አሮንና ሖር ሙሴን ድንጋይ ፈልገው አስቀመጡት፤ ከዚያም አንዳቸው በግራ፣ ሌላኛው በቀኝ ጎኑ ቆመው የሙሴን እጆች "ፀሐይ እስክትገባ ድረስ" ሲደግፉ ዋሉና ኢያሱ ድል ነሣ፡፡ ቀጥሎ ያለውን፣ "ኢያሱ አማሌቅንና ሕዝቡን በሰይፍ ስለት አሸነፈ" የሚለውን አገላለጽ እወደዋለሁ (ዘፀ. 17፥13)፡፡

ጦርነቱ የተወሰነው የት ነው? ከኢያሱ ጋር በሸለቆው ውስጥ? አይደለም፤ ከሙሴ ጋር ተራራው ላይ እንጂ፡፡ በሸለቆ ውስጥ ድል የተገኘው በተራራው ላይ በተደረገው ምልጃ ነው፡፡ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በተራራው ላይ የእግዚአብሔርን በትር፣ የጌታ ኢየሱስን ስም ከፍ የሚያደርጉ ማላጆች ቢኖሯት ኖሮ ብዙ ድሎችን ባገኘች ነበር፡፡

የጠፉ ነፍሳትን (ሰዎችን) አሸንፎ ለማምጣት የሚካሄደውን ጦርነት በጸሎትና በምልጃ ነው ማሸነፍ የሚቻለው፡፡ ጦርነቱ *ጸሎት ነው፡፡* ወንጌል ሥርጭት ጦርነቱን ለማሸነፍ የሚደረግ ሙከራ አይደለም - ምርኮኞችን ጠራርጎ የማስወገድ ዘመቻ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ቁሳዊዎቹ ይዞታዎች፣ ሕንጻዎቹ፣ ድርጅታዊ መዋቅሮችና መርሐ ግብሮች በምልጃ ከተገኘው ድል ምርኮና ብዛበዛ ለመሰብሰብ ወደ ጦርነቱ ሜዳ የምንጓዝባቸው መጓጓዣዎች ናቸው፡፡

ምልጃ የምስጢራዊው መንግሥት ምስጢራዊ የጦር ዕቃ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ይህንን ያውቁ ስለ ነበር ለቄሳር መስገድን እምቢ ብለው ይጸልዩለት ነበር፡፡ ጳውሎስና ጴጥሮስ አንባቢዎቻቸውን በእነርሱ ላይ ደም አፍሳሽ ስደት ላወጀባቸው ለዚያው ሰው - ለንጉሡ እንዲጸልዩና እንዲገዙለት ማስጠንቀቃቸው ያስደንቃል (1ጢሞ. 2፥1-2፤ 1ጴጥ. 2፥17)፡፡

> አንበሶቹ በላያቸው እየሰፈሩባቸው ሳለ ክርስቲያኖቹ ኮላስየም ውስጥ ለጸሎት ሲንበረከኩ የተመልካቾቹን የበቀል ፍላጎት የሚያጎድፍ አንድ ነገር ነበር፡፡ ክርስቲያኖቹ በሞት ውስጥ ሆነው እንኳ የንጉሡን ጌትነት እና የመንግሥቱን "መንፈስ" መገዳደር ብቻ ሳይሆን፣ እየሞቱ እንኳ ፈቃዱን ለማስፈጸም እንደማይችል የንጉሡን ዐቅመ ቢስነት እያሳዩ ነው (ጌትነቱን እንዲቀበሉለት ነበር የሚፈልገው)፡፡ የመጨረሻ ዕጣው በሕዝብ ፊት ኀይል ማጣቱ ነው፡፡ አንበሶቹ የቅዱሳኑን ደም በሚልሱበት ጊዜ እንኳ ቄሳር የጦር ዕቃውን ተገፎ



> በክርስቶስ ድል የመንሣት ጉዞ ወደ ምርኮኝነት እያመራ ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ ሥልጣኑም ከሁሉ ከሚያንስ ሰው በአንድ እርከን ብቻ ከፍ ቢል ነው፡፡ ይህንን በማይቀበሉም ላይ የመረጡትን ቅጣት - ሞትን በመጠቀም በእውነትነት እንዲቀበሉት ለማስገደድ ተሞክሯል፡፡ ይኸውም ጠቅላላውን የሮማ ጨካኝ ስራዊት ከጸሎት የዘለለ ዐቅም በሌላቸው ትንሽ ቡድን ላይ ማሰማራት ነው፡፡ ይህ ትንሽ ወገን ጦርነቱን ያሸንፋል ብሎ ማን መገመት ይችል ነበር?[9]

<u>ማስታወሻ</u>


1. Clinton E. Arnold, *Ephesians: Power and Magic, The Concept of Power in Ephesians in Light of Its Historical Setting,* Society for New Testament Studies, Monograph Series 63 (Cambridge: Cambridge University Press, 1989), p. 15.
2. *Ibid.,* p. 14.
3. *Ibid.,* p. 116.
4. Curtis Baughan, *Ephesians* (Grand Rapids, MI: Zondervan Publishing House, 1977), p. 126.
5. Walter Wink, *Naming the Powers: The Language of Power in the New Testament,* The Powers, Vol. 1 (Philadelphia: Fortress Press, 1984), p. 85. See also Wesley Carr, *Angels and Principalities: The Background, Meaning and Development of the Pauline Phrase, Hai Archai Kai Hai Exousiai,* Society for New Testament Studies, Monograph Series 42 (Cambridge: Cambridge University Press, 1981), pp. 45-123.
6. *Ibid.,* p. 110.
7. Charles Colson, "How Prolife Protests Backfired," *Christianity Today,* Vol. 33, No. 18 (December 15, 1989), p. 826.
8. Wink, *Op. Cit.,* p, 129.
9. *Ibid.,* p. 111.

## ፮ - ከደፋር፣ ግትር ምልጃ የሚገኝ ትምህርት

# ሦስት ኀናዊ ጸሎት

በዓለም ላይ እጅግ አስፈሪው ድምፅ በእኩለ ሌሊት የሚሰማ የስልክ ጥሪ ነው።

በተከሰተ ቍጥር ቀጣዮቹን የመዝሙረኛው ቃሎች ሳያስታውሰኝ አያልፍም፤

> ከክፉ ነገር አይፈራም፤ በእግዚአብሔር ላይ ለመታመን ልቡ
> የጸና ነው። (መዝ. 112፥7)

ስልኬ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ላይ እየጠራ ነበር። በኒው ሜክሲኮ ሳደርግ ከነበረው ረጅም ጕዞ በኋላ ዐልጋ ላይ ከወደቅሁ ገና ሁለት ሰዓቴ ነው። ይህ የስልክ ጥሪ ደግሞ መጨረሻው ዕረፍት የሌለበት ሌላ የሰባት ወይም የስምንት ሰዓት ጕዞ ማለት እንደ ሆነ ዐውቃለሁ። ወንድሜ ነበር - እናታችን ለአምሳ ቀናት ሐኪም ቤት ከቈየች በኋላ በካንሰር እንደ ሞተች ነገረኝ።

ያገኘናቸውን ልብሶች በሁለት ሻንጣዎች ከታተትንና ልጆቹን ከአንቅልፋቸው በደንብ ሳይነቁ እየጎተትን መኪና ውስጥ አስገብተን ፀሓይን በአንድ ሰዓት ቀድመን ወደ ዋናው መንገድ ገባን። እንደ መታደል ሆኖ ጕዞአችን ላይ ችግር ሳይገጥመን በጥሩ ሁኔታ ያሰብንበት ደረስን።

ይህ የሆነው በነሐሴ ነበር። ከዚያም ያ ጊዜ ዐልፎ መስከረም ውስጥ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ቤቷ ውስጥ ተቀምጠን ስንጫወት የእናቴን ሞት አነሣሁ። ጓደኛዬ ድንገት ብድግ አለችና "ቀኑ ምን ነበር?" በማለት ጠየቀችኝ።

የሆነ ነገር ፍለጋ ወደ ሌላ ክፍል እየገባች ሳለ፣ ቀኑን ነገርኋት። ከአፍታ በኋላ የአንድ ማስታወሻ ደብተር ገጾችን እየገላለጠች ብቅ አለች።

"ይኸውልህ" አለችኝ ከገለጠችው ገጽ ላይ ቀኑንና መግቢያውን እያነበበች። ማስታወሻ ደብተሩ የጸሎት መጻፊያ ሲሆን፣ ነሐሴ ውስጥ



ለእሁድ አጥቢያ ፀሓይ ከመውጣቷ ከብዙ ጊዜ አስቀድሞ ለቤተ ሰቤና ለእኔ የመጸለይ ሸክም ከእንቅልፏ ቀሰቀሳት፤ ሸክሙም ከቀኑ አብዛኛውን ክፍል አብሮአት ቈየ።

ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት ምሽት በሰገነቱ ላይ ባለው ክፍል ውስጥ ለጴጥሮስ የነገረውን ከማስታወስ በቀር ምርጫ አልነበረኝም። ሰይጣን እንደ ስንዴ እንደሚያበጥረው ነገረውና፣ "እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና" አለው (ሉቃ. 22፥32)።

ጌታ ኢየሱስ ውጤቱ የማይታወቅ ይመስል "ከተመለስህ" ባለማለቱ ደስተኛ ነኝ። "በተመለስህ ጊዜ" በማለት ነው የተናገረው።

## ከምልጃ የሚገኝ ትምህርት

የክርስቶስ ምልጃ የጴጥሮስን እምነት መጥፋት በማስቀረት (ፍቅሩ ወድቋል፤ ልበ ሙሉነቱ ጠፍቷል፤ እምነቱ ግን አልጠፋም) የመመለሻን መንገድ ከፍቷል።

ለሌሎች ከምንጸልይበት ጊዜ ይልቅ ክርስቶስን ይበልጥ የምንመስል በት ጊዜ የለም። ምልጃ ሕይወታችንን ስለ ወዳጆችን አሳልፎ መስጠት ነው፤ አንዱ የሌላኛውን ሸክም መሸከሙ ነው፤ የክርስቶስን መከራ መካፈል ነው። የመቤዠት ሥራ፣ አስቀድሜም እንደ ተናገርሁት የምልጃ ሥራ ነው። ጌታ ኢየሱስ እየማለደ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ እየማለደ ነው፤ እናም እኛም መማለድ አለብን። ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መንፈሳዊ ውጊያ የጻፈውን ምንባብ (ኤፌ. 6፥10-17) ለምልጃ ጸሎት ልመና በማቅረብ ነው የሚደመድመው፤

> በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም
> ሐሳብ ዘወትር ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ
> ትጉ፤ ደግሞ የወንጌልን ምስጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን
> በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ። (ቍጥር 18-19
> - አጽንኦት የተጨመረ)

እግዚአብሔር አንዳችን ለሌላኛችን እንድንጸልይ ዕድልና ኀላፊነት በመስጠት እኛን የንጉሥ ካህናት ማድረጉ እንደ ደቀ መዛሙርቱ፣ "ጌታ ሆይ ... እንጸልይ ዘንድ አስተምረን" በማለት ወደ መጠየቅ ያመጣናል (ሉቃ. 11፥1)።

እነርሱን አስተማራቸው - እኛንም ያስተምረናል።

ጌታ ኢየሱስ መጀመሪያ ሉቃስ 11፥2-4 ላይ ያለውን "የምሳሌ ጸሎት"፣ ከዚያም በእኩለ ሌሊት የመጣውን ወዳጅ ምሳሌ ተጠቅሞ ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ ምላሽ ሰጠ። ምሳሌው ስለ ምልጃ ሦስት አካላትን የሚያካትት ኀይለኛ ምሳሌ ነው። ምልጃ ሦስት ጎናዊ ጸሎት ነው፤ የመጀመሪያው ሰው ለሌላኛው ሰው እንጀራ በመፈለግ ወደ ሦስተኛው ሰው የሚሄድበት።

> ከእናንተ አንዱ ወዳጅ ቢኖረውና በእኩለ ሌሊት ወደ እርሱ ሄዶ፣ "ወዳጄ ሆይ፤ ሦስት እንጀራ አበድረኝ፤ አንድ ባልንጀራዬ ከመንገድ መጥቶብኝ የማቀርብለት ምንም ነገር የለኝምና" ብሎ ለመነው እንበል። በቤት ውስጥ ያለውም፣ "አታስቸግረኝ፤ በሩ ተቈልፎአል፤ ልጆቼም አብረውኝ ተኝተዋል፤ ከእንግዲህ ተነሥቼ ልሰጥህ አልችልም" ይለዋልን? እላችኋለሁ፤ ወዳጁ በመሆኑ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፣ ስለ ንዝነዛው (ስለ ብዙ ልመናው) ብቻ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል። (ሉቃ. 11፥5-8 - አ.መ.ት)

## ምልጃ በድፍረት መጸለይ ነው

ደፋር፣ ጽኑ - የምልጃ ጸሎትን በትክክል የሚያስረዱ ቅጽሎች እነዚህ ብቻ ናቸው።

በታሪኩ ውስጥ ያለው ሁኔታ ድፍረትን የሚጠይቅ ነው። ጊዜው የማይመች ነበር፤ እኩለ ሌሊት ነበር። ሁኔታዎቹ የማይመቹ ነበሩ፤ "ልጆቼም አብረውኝ ተኝተዋል"።

በዚያ ወቅት መላው ቤተ ሰብ አንድ ላይ መተኛቱ የተለመደ ነበር - ሙቀትን ፍለጋ ሳይሆን፣ በቦታ እጥረት ምክንያት። ዐይነተኛው ባለ አንድ ክፍል መኖሪያ ቤት መላውን ቤተ ሰብ - ብዙውን ጊዜም ጥቂት እንስሳትን ጨምሮ የሚተኛበትን አንድ ትልቅ ምንጣፍ የያዘ ነው። "ልጆቼም አብረውኝ ተኝተዋል"። ልጆቻችሁ አልተኛ ብሎ የሚያስቸግርባቸውን የሚያቀውሱ ጊዜአት ታስታውሳላችሁ? ለአንድ ሰዓት ያህል ልታዜሙ፣ ልታንጎራጉሩና እሹሩሩ ልትሉ ትችላላችሁ። ከዚያም ልክ ልጁ ሲተኛላችሁ በሩ ይንኳኳል።

ሕፃኑ ገና ትንሽ ሸለብ ያደረገው መሆኑ ግን ሰውዬው በር መቀብቀቡን እንዲያቆም አያደርገውም። የጎረቤት መብራቶች እስኪበሩና ውሾች መጮኽ እስኪጀምሩ ድረስ በሩን በኀይል ማንኳኳቱን ይቀጥላል።

ደፋርና ግትር - መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ማላጆች በሙሉ እነዚህ ጠባያት ይታዩባቸዋል። ከእነዚህ መካከል ሁለቱን ማላጆች



በዚህ መጽሐፍ እናያለን - አብርሃምን እና ሙሴን። እስቲ አብርሃም ለአምላክ የለሿ ሰዶም ሲማልድ አድምጡ፤

> በውኑ ጻድቁን ከኀጢአተኛ ጋር ታጠፋለን? ... ይህ ከአንተ ይራቅ። ... የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን? (ዘፍ. 18፥23-25)

ይህን በማነብበት ጊዜ ሁሉ አብርሃም ከማን ጋር እየተነጋገረ እንደ ሆነ እንዳስታውሰው የሚጎተጉተኝ ነገር አለ። ይህ እጅግ ድፍረት የሚታይበት ጸሎት ነው።

ሙሴ ደግሞ ሌላኛው ደፋር ማላጅ ነው። በዘፀአት 32 አስደናቂ ታሪክ እየተፈጸመ ነው። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በተራራው ላይ ሳለ ሕዝቡ ልቅ ሆኑ። እግዚአብሔርን ረስተው ራሳቸው በገዛ እጃቸው የሠሩትን ጣዖት - የወርቅ ጥጃን ለማምለክ አጎነበሱ።

> ሕዝቡ ሊዘፍኑ ሲነሡ (ቍጥር 6)፣ እግዚአብሔርም ሊፈርድ ተነሣ፤
>
> እግዚአብሔር ሙሴን፣ "ከግብፅ ምድር ያወጣኻቸው ሕዝብህ ስተዋልና ውረድ" አለው። (ቍጥር 7 - አ.መ.ት)
>
> ትዕግሥቱ አለቀ፤ የእነርሱ ነገር በቃው። አበቃ። ታሪኩ ተፈጸመ።
>
> እኔ ይህን ሕዝብ አየሁት፤ እነሆ ዐንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው። አሁንም ቍጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ። (ቍጥር 10)

ሙሴ ግን ማለደላቸው፤ "ከመዓትህ ተመለስ፤ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ" (ቍጥር 12)። እግዚአብሔር የሙሴ ሕዝብ አድርጎ ሲጠራቸው፣ ሙሴ ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ በማለት እንደሚጠራቸው ልብ በሉ።

በዚህ ጸሎት ውስጥ ሙሴ ሁለት የድፍረት ነገሮችን ይናገራል። አንደኛ፣ እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ ቢያጠፋ ዝናውን እንደሚያበላሽ ይነግረዋል፤ እግዚአብሔር በተራራ መካከል ሊጨርሳቸው ነው ከግብፅ ያወጣቸው እያሉ ግብፃውያን ይሳለቃሉ (ቍጥር 12)።

ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርግ ከሆነ፣ የገባውን ተስፋ ማፍረስና የራሱን ቃል መጣስ ይሆንበታል፤ "በራስህ የማልህላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን እስራኤልንም አስብ" (ቍጥር 13)።

ውጤቱስ? “ከዚያም እግዚአብሔር ታገሠ፤ በሕዝቡም ላይ አመጣባቸዋለሁ ያለውን ጥፋት አላመጣባቸውም” (ቍጥር 14 - አ.መ.ት)፡፡ እስቲ አስቡት - የምልጃ ጦር ዕቃ የያዘ አንድ ሰው መላ አገሪቱን አዳነ፡፡

## ምልጃ ግትር ጸሎት ነው

በሉቃስ 11 የተተረከው ታሪክ ዋነኛ ክፍል ኢየሱስ ቀጣዩን ነገር የሚናገርበት ቍጥር 8 ነው፤

> እላችኋለሁ፤ ወዳጁ በመሆኑ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፣ ስለ ንዝነዛው ብቻ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል፡፡

“ወዳጅ” ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል ጠንካራ ቃል በመሆኑ ከድንገተኛ ወይም ከተራ ትውውቅ የዘለለ ጓደኝነት እንዳላቸው ያመለክታል፡፡ ቅርበትን የሚያሳይ ቃል ነው፤ “እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ”፡፡ እንደ ወንድማችሁ የምትወዱትን ሰው ከበር መመለስ የማይቻል ነገር ነው፡፡ ማንም ይህንን አያደርግም - በየትኛውም ሰዓት ቢሆን፡፡ ይህ ሰው ግን ያደርገዋል፡፡ እዚህ ጋ የምናገኘው ሁለት ግትር ሰዎችን ነው - አንደኛው ሰው እንጀራ ለማግኘት ቈርጦ ተነሥቷል፤ ሌላኛው ደግሞ ላለመስጠት ቈርጧል፡፡ ይህ ልቡን እንደ በሩ የከረቸመ ሰው ለወንድማዊ ፍቅር ካልተሸነፈ ለምን ሊሸነፍ ነው? ወዳጅነት በሩን እንዲከፍት ካላስቻለው ምን ሊያስከፍተው ይችላል?

ውትወታ፡፡ ይህ መንፈስ ጠንካራነትን የሚያሳይ ቃል ነው፡፡ *“ስለ ንዝነዛው (ስለ ብዙ ልመናው)* ብቻ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል፡፡” ለነገሩ ቃሉ ከመንፈስ ጠንካራነትም ይጠነክራል፡፡ ዕፍረት ማጣት፣ ዕፍረት የለሽነት ነው፡፡ አብዛኞቻችን እንዲህ ዐይነት ሁከት ብንፈጥርና የቅርብ ወዳጃችን ከዚያ እንድንሄድለት ቢነግረን ዕፍረቱ ይገድለናል፡፡ እኔ ብሆን ከዕፍረቱ የተነሣ ለተወሰኑ ወራት እዚያ አካባቢ አልደርስም፡፡ ይህ ሰው ግን እንዲህ አይደለም፡፡ የማፈር ዐቅም የለውም፡፡ የዕፍረት ነርቭ ኖሮት አይደለም የተወለደው፤ ዕፍረት አያውቅም፡፡ ስለዚህ፣ መንፈሱ ጠንከር ያለ ነው - ግትርና ዕፍረት የለሽ የሆነ መንፈስ ጠንካራነት፡፡ ሐሞት አለው፡፡

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ዕፍረት የለሽ ግትርነት በጸሎት ጊዜ ጠቃሚ አድርጎ እንደሚቈጥረው በመበለቲቱና በኢፍትሐዊው ዳኛ ታሪክ ውስጥም (ሉቃ. 18፥1-8) አጽንዖት የሰጠው መሆኑ ማስረጃ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔርን የማይፈራው፣ ለሰዎችም ከበሬታ የሌለው ዳኛ ፍትሕን ፍለጋ ወደ እርሱ የመጣችውን መበለት መርዳት እምቢ ብሏል፡፡ ይህ ለማመን የሚቸግር ሁናቴ



ነው፡፡ ማንስ ቢሆን እንዴት አንዲት መበለት መርዳትን እምቢ ሊል ይችላል? ነጥቡ እዚህ ላይ ነው፡፡

ዳኛው ዘንድ ኀዘኔታ ባይኖርም መበለቲቷ ዘንድ ግን ውትወታ (ችክታ) አለ፡፡ ዳኛው ለራሱ እንዲህ ሲል አሰበ፤

> ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ፣ ሰውንም ባላከብር ይህች መበለት ስለምትጨቀጭቀኝ እፈርድላታለሁ፤ አለበለዚያ ዘወትር እየተመላለሰች ታሰለቸኛለች፡፡ (ቍጥር 4-5 - አ.መ.ት)

ዳኛውን ያሳመነው የመበለቲቱ “ዘወትር መመላለስ” እንጂ በእርሱ በኩል የልብ ለውጥ ኖሮ አይደለም፡፡

በነገራችን ላይ “ማስልቸት” ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል (ቍጥር 5) አንድን ሰው ዐይን ዐይኑን መምታት፣ ዐይኑን ማበለዝ ማለት ነው፡፡ ብርቱ መበለት ናት - ዳኛው እንዳታበልዘው ፈርቷታል፡፡

ጌታ ኢየሱስ ታሪኩን እንዴት እንደሚያዛምደው አድምጡ፤

> ጌታም እንዲህ አለ፤ “ዐመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ፡፡ እግዚአብሔርስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? ከመጠን በላይስ ችላ ይላቸዋልን? እላችኋለሁ፤ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል” (ቍጥር 6-8 - አ.መ.ት)፡፡

አንድ ኢፍትሐዊ ዳኛ ለአንዲት መንፈሰ ጠንካራ መበለት ልመና እጅ ከሰጠ፣ እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ መንፈስ ጠንካራነት ምን ያህል ይበልጥ ያከብር ይሆን?

ያዕቆብ ከመልአክ ጋር ሲታገል የነበረበትን የብሉይ ኪዳን ታሪክ (ዘፍ. 32፥24-32) ታስታውሳላችሁ? እዚያ ታሪክ ውስጥ ሁልጊዜም የማይመቸኝ አንድ ነገር አለ፡፡ ያዕቆብን እየታገለው ያለው መልአክ ነው - መሄድ እየፈለገ ያዕቆብ አላስኬድ ብሎ የያዘው መልአክ፡፡ “ሊነጋ አቀላልቶአልና ልቀቀኝ” አለው መልአኩ፡፡

ያዕቆብ ደግሞ፣ “ካልባረክኸኝ አልለቅህም” በማለት መለሰለት (ቍጥር 26)፡፡

እዚህ ጋ ነው የማይመቸኝ - ተጠምጥሞ የያዘውን የሰው እጅ የእውነት ቢፈልግ ኖሮ ማስለቀቅ የማይችል መልአክ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ያዕቆብ እጅግ ጠንካራ ከመሆኑ የተነሣ መልአኩን ከምድር ጋር ሰፍቶ እንደ

*ያዘው ታምናላችሁ? ያ ትግል እንዲህ እንዲሆን ተብሎ ቀድሞ የተቀናበረ ነው::* መልአኩ፣ "ልቀቀኝና ልሂድ" በማለት ሲናገር፣ ድምፁን ዝቅ አድርጎ "እንደማታደርገው ግን ተስፋ አደርጋለሁ:: እንደ ያዝከ ትንሽ ከቈየህ በረከቱን ታገኛለህ" በማለት እያንሾካሾከ እንደሚሆን አምናለሁ::

በረከቱ ጋ ደርሰን ደርሰን ስንት ጊዜ ለትንሽ እንዳቆምን እገረማለሁ:: አብርሃም ዐሥር ሰዎች ጋ ባያቆም ኖሮ ሰዶም ትድን ነበርን? "ካልባረከኸኝ አልለቅህም" በማለት እንደ ያዕቆብ ብንጸልይ ቤተ ክርስቲያናችን፣ ከተማችን መንፈሳዊ መነቃቃት (ሪቫይቫል) ማግኘት አትችልም ነበርን?

## ምልጃ የመፍጨርጨር ጸሎት ነው

የሚፍጨረጨሩና የጕዳዩ አስቸኳይነት የሚገፋፋቸው (የሚያሳስባ ቸው) ወንዶችና ሴቶች ናቸው በእውነት የሚማልዱት:: "በጽዮን ያሉ ዓለመኞች" (አሞጽ 6፥1) የጠላትን ጦር ለመመለስ የምልጃ መታኮሻ ግምብ ውስጥ አይገኙም:: ግዴለሾቹ "ቀንና ሌሊት ዝም በማይሉት" ጕበኞች (ኢሳ. 62፥6) መካከል አይኖሩም:: ጦርነትን በግዴለሾች ማሸነፍ አይቻልም:: ከእነዚህ መካከል አንዳቸው ለመማለድ መሞከር ቢኖርባቸው እንኳ ወዲያውኑ "ተግባራዊ" ጥረት ወደማካሄድ ሲንሸራተቱ ይገኛሉ:: ለምንም ነገር ቢጸልዩ በግማሽ ልባቸው ምክንያት ዋጋ ቢስ መሆኑ እርግጥ ነው::

በጠቅላላው በዚህ ምሳሌ ውስጥ የመጨረሻ መፍጨርጨር ድምፀት አለ:: ግዴለሽ እንግዳ ተቀባይን የጎረቤቱን በር ሄዶ ለማንኳኳት ይበልጥ የተመቸ ሰዓት እስኪደርስ እንዲቈይ ማሳመን ቀላል ነው:: ነገሩ ብዙም ያላሳሰበው ሰው ሁሌም ሰበብ አያጣም፤ ያሳሰበው ግን ነገሩ የሚፈጸምበትን መንገድ አያጣም:: የሚፍጨረጨሩ ሰዎች ብቻ ናቸው የመፍጨርጨርን ድርጊት የሚፈጽሙትና የሚያሸንፉት::

## የማናመልጠው ኀላፊነታችን

ቫንስ ሀቨነር፣ "ሁኔታው አሳሳቢ ሲሆን፣ እኛ ግን የማንፍጨረጨር መሆናችን ላይ ነው ችግሩ ያለው" በማለት መናገር ያዘወትር ነበር::

"አንድ ባልንጀራዬ ከመንገድ መጥቶብኝ":: *መጥቶብኛል::* ወደ ጎረቤቴ፣ ወደ መጋቢዬ ሳይሆን ወደ እኔ ነው የመጣው:: ኀላፊነቱ የእኔ ነው:: አንድ ተጓዥ ምግብና ማደሪያ ፍለጋ ደጃችሁ ላይ ሲቆም አስፈልጎቱን እንድታሟሉለት ያልተጻፈ ሕግ አለ:: ይህን አለማድረግ ማኅበራዊ ግዴታን መዘንጋት ሲሆን፣ የተጓዡን ሕይወትም አደጋ ላይ ይጥላል::



ጕዞአቸው ወደ እኛ የሚያመጣቸው ሰዎች አሉ:: የሚኖሩት ከቤታችን ቀጥሎ ነው፤ ትምህርት ቤት አጠገባችን ነው የሚቀመጡት፤ አብረውን በአንድ የሥራ ገበታ ላይ ነው የተሰማሩት - በቅርብ ያለነው ክርስቲያኖች ደግሞ እኛ ብቻ ነን:: የማናመልጠው ኀላፊነታችን ናቸው::

አዲስ ኪዳን ስለ መጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ሲናገር ብዙ ጊዜ አንድን አስደናቂ ቃል ይጠቀማል:: ይህም *የተበተኑ* የሚል ነው:: ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ክርስቲያኖቹ ለሚደርስባቸው እንግልት የሚኖራ ቸውን አጸፋ ለማሳየት ይጠቀምበታል::

> ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ:: ... የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ:: (8፥1፣ 4)

በሐዋርያት ሥራ 11፥19 ላይም ቃሉ እንደገና ይከሰታል፤

> በእስጢፋኖስ ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት እስከ ፊንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንጾኪያም ድረስ ዞሩ::

ሐዋርያው ጴጥሮስም በ1ኛ ጴጥሮስ 1፥1 ላይ ተጠቅሞበታል፤

> የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ ... በጳንጦስና በገላትያ በቀጳዶቅያም በእስያም በቢታንያም ለተበተኑ መጻተኞች ...

ይህ የአይሁድ በየቦታው መበተን የተከሰተው አስገድዶ አገር በማስለቀቅና በተለያዩ መንገዶች ሲሆን፣ አንዳንዶቹ በፈቃደኝነት አገራቸውን ትተው፣ ሌሎቹ ደግሞ ያለ ፈቃዳቸው ወደ ባዕድ ምድር እንዲሰደዱ በማድ ረግ ነው:: ጴጥሮስ ቃሉን የተጠቀመው በዓለም ሁሉ ለተበተኑና አንድ ቀን ወደ ምድሪቱ እንደሚመለሱ ተስፋ ለሚያደርጉ አይሁዳውያን አማኞች ነው::

ያዕቆብም በመልዕክቱ ውስጥ ቃሉን ተጠቅሞታል፤

> የእግዚአብሔርና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ ለተበተኑ ለዐሥራ ሁለቱ ወገኖች ... (ያዕ. 1፥1)

ይህንን ቃል አስደናቂ የሚያደርገው ነገር በእርግጥም ትርጕሙ ነው፤ "ዘርን አዳርሶ መዝራት፣ ዘሪው ዘሩን መበተኑ":: ከስደቱ የተነሣ ክርስቲያኖች በየቦታው ተበተኑ:: ነገር ግን እግዚአብሔር ሲሠራ የነበረውን ነገር ተመ ልከቱ፤ ትልቅ የነፍሳት መከር ይኖር ዘንድ በዓለም ሁሉ ዘርን እየዘራ ነበር:: የተበተኑት እስራኤላውያን አማኞች በተለያዩ መሬቶች ላይ በእግዚአብሔር የተዘሩ ናቸው::

እዚያ አካባቢ፣ እዚያ ቤት መገኘታችሁ በዕድል እንደ ሆነ ነው የምታስቡት? እግዚአብሔር ከዚያ ምርኮ ስለ ፈለገ በዚያ የዘራው ዘር ልትሆኑ አትችሉምን?

*መሥሪያ ቤታችሁ እዚህ የመደባችሁና ወደዚህ ስፍራ የመጣችሁበት* ብቸኛ ምክንያትም ይኸው እንደ ሆነ ትናገሩ ይሆናል፡፡ ምናልባት ከዚህ ሊያልፍ ይችላል፡፡ ምናልባትም እግዚአብሔር በዚህ አካባቢ (ማኅበረ ሰብ) ዘር እየዘራ ሊሆንና የመጀመሪያዎቹን ክርስቲያኖች በአዳዲስ ስፍራዎች ለመዝራት ስደትን እንደ ተጠቀመ ሁሉ መሥሪያ ቤታችሁም የመዝራቱ መሣሪያ ሊሆን ይችላል፡፡

እግዚአብሔር አሁን ባላችሁበት ቦታ የተከላችሁ ምናልባት ጐዞው በእናንተ በኩል የሚያሳልፈው አንድ ጓደኛ እንደሚኖር በማወቁና ምናልባትም ይህ ሰው የሚያስፈልገውን ነገር ለይታችሁ እንድታውቁና በኢየሱስ ስም አስፈልጎቱን እንድታሟሉለት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሰው የማታመልጡት ኀላፊነታችሁ ነው፡፡

## በእጃችን በቂ ነገር ያለ መኖሩ

በእጃችን በቂ ነገር ያለ መኖሩ በተስፋ መቍረጥ ሊያፍጨረጭረን ይችላል፡፡ የእንግዳ ተቀባዩን በኀዘን የተሞሉ ቃላት አድምጡ፤ "የማቀርብለት ምንም ነገር የለኝምና" (ቍጥር 6)፡፡ ቃሎቹ እግዚአብሔር በእኛው ክልል ውስጥ ባስቀመጣቸው የሕይወት-እና-የሞት ኀላፊነቶች ፊት ያለንበትን ተስፋ አስቈራጭ ሁኔታ ያስተጋባሉ፡፡

"ጌታ ሆይ፤ ጎረቤቴ አልዳነም፤ በዚህም ላይ በካንሰር ተይዞ ወደ ሞት እያመራ ነው፤ የማቀርብለት ምንም ነገር የለኝም፡፡"

"ጌታ ሆይ፤ ለከባድ ፈተና የተዳረገች ወጣት ልጅ አለችኝ፤ የማቀርብላት ምንም ነገር የለኝም፡፡"

"ጌታ ሆይ፤ የሥራ ባልደረባዬ ... ቤቱ እየፈረሰ ነው፤ የማቀርብለት ምንም ነገር የለኝም፡፡"

ለእነዚህ ነገሮች በቂ ነገር ያለው ማን ነው? ማንም - ይህም "ምሕረትን እንድንቀበል፣ በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ" ወደ ጸጋው ዙፋን ሊያመጣን ይገባል (ዕብ. 4፥16)፡፡ ቤተ ክርስቲያን የአብን ደጆች በድፍረት ማንኳኳት ካልተማረች የሚያማምሩ ሕንጻዎቿ ባዶ ሌማቶች ይሆኑና የራባቸው መንገደኞች እንጀራ ሳያገኙባት እንደ ተራቡ እና ሆዳቸው



እንደ ጮኸ ከተቀናጀው የአምልኮ ሥርዐቷ ፊታቸውን መልሰው የሚሄዱባት ትሆናለች፡፡

አንድ ሰው እጅግ ከተራበ ከቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ ያገኘውን ምግብ ይበላል፤ ከቤተ ክርስቲያን ባዶ እጁን ከተመለሰ ዲያብሎስ በርካታ የቆሻሻ ቅርጫት ምግቦችን ይዞ እንደሚጠብቀው አትጠራጠሩ፡፡

አንድ ማለዳ በቤተ ክርስቲያናችን የተገኘውን ሱዳናዊ ወንጌላዊ በፍጹም አልረሳውም፡፡ የአምልኮው ሥርዐት ከመጀመሩ አስቀድመን በእኔ የጥናት ክፍል ተንበርክከን ሳለ፣ "አባት ሆይ፤ ዛሬ መጋቢውን ካልባረክኸው ሕዝቡ እንደ ተራበ መሄዱ ነው" በማለት ጸለየ፡፡ ጸሎቱ ውስጥ የነበረው የጕዳዩ አሳሳቢነት ድምፀት ዛሬ ድረስ ይሰማኛል፡፡

## አይቀሬው የእግዚአብሔር ሽልማት

ወደ ምሳሌው የመጨረሻ ነጥብ የሚወስደን አይቀሬው የእግዚአብ ሔር ሽልማት ነው፡፡ "የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል" (ሉቃ. 11፥8)፡፡ ሦስት እንጀራ ይሆን ያገኘው? አላውቅም፤ ነገር ግን የሚፈልገውን ሁሉ ነው ያገኘው፡፡ ማንም ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ ባዶ እጁን ከእግዚአብሔር አይሄድም፡፡ ክርስቶስ ቃል የገባው፤

> *ታዲያ እናንት ክፉዎች ሳላችሁ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣ የሰማዩ አባታችሁማ ለሚለምኑት መልካም ስጦታን እንዴት አብልጦ አይሰጣቸውም? (ማቴ. 7፥11 - አ.መ.ት)*

ወደ ምልጃ ስፍራ *ከትልቅ ጕድለታችን ጋር* እንቀርብና *ለትረፍርፎን* እንመለሳለን፡፡

እንጀራ ማግኛ አንድ ቦታ ብቻ አለ - እግዚአብሔር አብ፡፡ አንድ ማግኛ መንገድም አለ - መጠየቅ፡፡

## ፯ - የምልጃ ጸሎት ልብ

# ይዘታውን ማግኘት

ለአገልግሎት በሄድኩበት ሁሉ የሚያጋጥሙኝ ባሎቻቸው በጌታ ያልሆኑ ክርስቲያን፣ ብዙውን ጊዜ ደግሞ ታማኝ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑ ሚስቶች በርካቶች ሲሆኑ - ሚስቶቻቸው ያልዳኑ ክርስቲያን ባሎች ግን በአንድ እጅ ጣቶች የሚቈጠሩ መሆናቸው ይከነክነኛል:: ያልዳነ ባል ያላት ክርስቲያን ሴት ማግኘት የተለመደ ነው:: ያልዳነች ሚስት ያለችው ክርስቲያን ባል ግን ብርቅ ነው::

ይህም ምናልባት ፩ኛ ጴጥሮስ 3 ላይ ክርስቲያን ሚስቶች ያልዳኑ ባሎቻቸውን ለክርስቶስ ስለሚያሸንፉበት መንገድ ሐዋርያው ምክር ሲሰጥ ያልዳኑ ሚስቶች ላሏቸው ባሎች ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ የማይሰጥበት ምክንያት አካል ሊሆን ይችላል:: ለማንኛውም ባሎቻቸውን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ለሚፈልጉ ሚስቶች የሐዋርያው ጴጥሮስ ምክር ይህ ነው፤

> ሚስቶች ሆይ፤ እናንተም እንደዚሁ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ አንዳንድ ለቃሉ የማይታዘዙ ቢኖሩ፣ ያለ ቃል በሚስቶቻቸው አኗኗር ተማርከው ይመለሳሉ፤ ይህም የሚሆነው ንጹሕና ፍጹም አክብሮት የተሞላውን ኑሮአችሁን ሲመለከቱ ነው::
> (፩ጴጥ. 3፥1-2 - አ.መ.ት)

አንዲት ሚስት ስለ ክርስቶስ አንድም ቃል ሳትናገር ባሏን ወደ ክርስቶስ ማምጣት ትችላለች:: እውነቱን እንጋፈጠው፤ አንዳንድ ሰው በአንድ ሰው ብቻ እና በአንድ መንገድ ብቻ ነው ሊደረስ የሚችለው:: እዚህም ጋ በሚስቱ በኩል ሲሆን፣ ባሏም የሚድነው በሕይወቷ እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጎትቶ ስለ ተወሰደ፣ በመጋቢው ስለ ተነዘነዘ፣ ወይም በሚስቱ ስለ ተሰበከ አይደለም:: የሕይወቷን ንጽሕናና በአክብሮት መሞላት ያያል ("በአንክሮ ይከታተላል" ነው የግሪኩ ቃል ትርጒም)::

"ውበታችሁ" በማለት ጴጥሮስ ይቀጥላል፤



> በውጫዊ ነገር በመሸሞንሞን ይኸውም ሹሩባ በመሠራት፣ በወርቅ በማጌጥና በልብስ አይሁን፤ [ማስታወሻ:- ጴጥሮስ ሚስትየው ሹሩባ መሠራትና በወርቅና በልብስ ማጌጥ የለባትም እያለ አይደለም:: እነዚህ ነገሮች ምንም ችግር የላቸውም፤ ነገር ግን ባልየውን ለክርስቶስ አያሸንፉትም::] ነገር ግን ውበታችሁ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ፣ ገርና ጭምት መንፈስ ያለበት፣ ምንጊዜም የማይጠፋ የውስጥ ሰውነት ውበት ይሁን:: (ቍጥር 3-4 - አ.መ.ት)

### ይዘታዊ ጸሎት

ሚስትየው ባልዋን የምታሸንፈው በልመናዋ ሳይሆን *በይዘታዋ* - በመገዛት፣ በንጽሕናና በአክብሮት ይዘታ - እና በማይረግፈው የገርና የጭምት መንፈስ ውበት ነው:: ይህን ይዘታ ስታገኝ መላው ሕይወቷ የምልጃ ድርጊት ይሆናል:: የሚወደውን ምግብ ስታዘጋጅለት፣ ዓሣ ሲያጠምድ ስላመለጠው ዓሣ አሰልቺ ወሬ ሲያወራ ስታዳምጠው፣ የእግር ኳስ ግጥሚያዎችን አብራው በጽናት ተመልክታ ስትጨርስ እየማለደች ነው:: በግዴለሽነቱ የሚያደርስባትን ነገር ክርስቶስን በሚመስል መንፈስ ስትቀበል እየማለደች ነው:: እያንዳንዱ የልቧ ምት ምልጃ፣ በደም ሥሮቿ የሚያልፈው እያንዳንዱ የደም ጠብታ ልመና ነው:: በግዴለሽነቱ የተነሣ ከዐይኖቿ የምታፈስሰው እያንዳንዱ የእንባ ዘለላ ወደ እግዚአብሔር የሚደረግ ጸሎት ነው::

ይህም ለእውነተኛ ምልጃ እውነተኛ ቍልፍ አድርጌ ወደማምነው ነገር ያመጣናል:: ምልጃ ከጸሎት በላይ ነው:: ጸሎት የምልጃ ቅርጽና መግለጫ ነው እንጂ ብቻውን ምልጃ አይደለም:: ምልጃ ልመና አይደለም:: ምልጃ *ይዘታ* ነው:: የሆነ የምናደርገው ነገር አይደለም - የምንሆነው ነገር ነው:: በቀኑ የሆነ ሰዓት ላይ የምንያዝበት ልምምድ ሳይሆን - የምንኖረው ሕይወት ነው::

### ጥሩን ሰው ማግኘት አስቸጋሪ ነው

በሕዝቅኤሉ ምንባብ ውስጥ እግዚአብሔር ቅጥርን የሚሠራና "በፈረሰው በኩል በፊቱ የሚቆምለትን" ሰው ሲፈልግ ነበር:: እዚህ ጋ እግዚአብሔር አንድን የሚጸልይ ሰው የግድ እየፈለገ አይደለም፤ ይህ የሚጫወተው የራሱ ውስጥ ድርሻ ቢኖረውም:: ይዘታን የሚይዝና የሆነ ዐይነት ሕይወት የሚኖር ሰው እየፈለገ ነው::

ኤርምያስ ተመሳሳይ ፍለጋን ያስረዳል፤

> በኢየሩሳሌም መንገድ እየተመላለሳችሁ ሩጡ፣ ተመልከቱም፣ ዕወቁም፣ በአደባባይዋም ፈልጉ፤ ፍርድን የሚያደርገውን እውነትንም የሚሻውን ሰው ታገኙ እንደ ሆነ ይቅር እላታለሁ። (ኤር. 5፥1)

ምልጃ ይዞታን በእጅ ማስገባትና እዚያ ይዞታ ላይ ሆኖ መጸለይ ነው። "ይዞታዊ ጸሎት።"

በክርስቶስ ጉዳይ ኢሳይያስ ሲናገር፣ "ስለ ዐመፀኞች ማለደ" ይላል (53፥12)። ኢሳይያስ ክርስቶስ ስለ ዐመፀኞች ጸለየ ብቻ ማለቱ አይደለም - ለእነርሱ ኖረ፣ ለእነርሱ ሞተ። መላው ሕይወቱ፣ አገልግሎቱ፣ ውርደቱ፣ ሥቃዩ - ሁሉም ነገሩ ምልጃ ነበር። አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጡን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል - ምን ለማድረግ? ሊማልድልን። አሁን ይዞታውን እጁ አስገብቶ እዚያ ይዞታ ላይ ሆኖ እየጸለየ ነው።

ምልጃ የምንኖርበትና የምንጸልይበት ይዞታ ከሆነ፣ ታዲያ ይህንን ይዞታ እጃችን የምናስገባው እንዴት ነው?

## *ይዞታውን ማግኘት*

### *ደረጃ አንድ፦ ራስን አንድ ማድረግ*

እስቲ በሉቃስ 11 ላይ የተገለጸውን ሦስት ጎናዊ ጸሎት እንደገና እንመልከት። በታሪካችን ውስጥ ያለው ማላጅ ብዙ መሥዋዕትነት እንዲከፍል ነው የተጠራው። እንቅልፉንና ዕረፍቱን አጣ፤ አንድን እንግዳ ለመመገብ ጓደኝነቱን ለአደጋ አጋለጠ፤ መላው ጉዳይ ምቾት የሚነሣ ነበር የሆነበት። ሆኖም ቍልፉ መሥዋዕት ይህ ነበር - ራሱን ከመንገደኛውና ከመንገደኛው አስፈልጎት ጋር አንድ አደረገ።

ይህ ሰው አልተራበም፤ እንጀራም አያስፈልገውም። እንግዳው ነው የተራበው። አንዳንዶች፣ *የፈለገው ከልቡ ከሆነ የራሱን ልመና ራሱ ያካሂድ* በማለት ማሰብን ይመርጣሉ። ይህኛው እንግዳ ተቀባይ ግን የተራበው ራሱ እንደ ሆነ አድርጎ ነው ጉዳዩን ያየው፤ የእንግዳውን ቦታ ወሰደ። የምልጃ መሠረቱ ይህ ነው።

ለመማለድ ራሳችንን ከሌሎች ጉድለት ጋር አንድ እናደርጋለን። የተጎዱ ሰዎች የእነርሱን ዐይነት ጩኸት ያደምጣሉ - ብቻቸውን እንዳልሆኑ



ይነግራቸዋልና። ያ ጩኸት ጸሎታችን ነው። የእነርሱ ጩኸት ብዙ ያስ ከፍላቸዋል፤ የእኛ የማረጋገጫ ጩኸት ... የሆነ ነገር ያስከፍለናል።

እዚህ ጋ የጌታ ኢየሱስን ፈለግ መከተል እንችላለን። እግዚአብሔር የሰውን ዘር ለመዋጀት ሲወስን ሰው በመሆንና ሰው በሚመላለስበት ቦታ በመመላለስ ራሱን ከሰው ጋር አንድ አደረገ። እግዚአብሔር የማይታይ፣ የማይደረስበት፣ የማይገኝ፣ የማይታወቅ አምላክ ሆኖ አይደለም ወደ እኛ የመጣው። እንደ ሰው የሰው ስሜቶች፣ የሰው ፈተናዎችና የሰው ገደቦች ኖረውት ነው ወደ እኛ የመጣው። እጅግ ቀርቦ ከመምጣቱ የተነሣ ዮሐንስ፣ "እጆቻችንም የዳሰሱትን" በማለት ስለ ሕይወት ቃል ይናገራል (1ዮሐ. 1፥1)። *መዳሰስ* የሚለው ቃል የዐይነ ስውርን ሰው ዳበሳ ለማሳየትና የዳሰሳውን ትክክለኝነት አጽንኦት ለመስጠት ጥቅም ላይ የዋለ ቃል ነው።

የጌታ ኢየሱስ ጥምቀት ራሱን ከኀጢአተኞች ጋር አንድ የማድረግ ድርጊት ነው። የዮሐንስ ጥምቀት የንስሓና የኑዛዜ ጥምቀት ነው። ለዚህ ነው ከፈሪሳውያን አንዳቸውም ለመጠመቅ ተራ ያልያዙት - ያንን ማድረግ ኀጢአት እንዳለባቸው ማመን ይሆንባቸዋል። ጌታ ኢየሱስ እንዲያጠምቀው ዮሐንስን ሲጠይቀው፣ ዮሐንስ "እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል፤ አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን?" በማለት ተቃውሞ አቀረበ (ማቴ. 3፥14)። ኢየሱስን ለማጥመቅ አንዳችም ምክንያት የለም - ኀጢአት የለበትምና።

ሆኖም አንድ ምክንያት አለ - ኢየሱስ የመጣው ራሱን ከኀጢአተኞች ጋር አንድ ሊያደርግ እንደ ሆነ ገና ከአገልግሎቱ ጅማሬ አንሥቶ ግልጽ መደረግ አለበት፤ የዮሐንስ ጥምቀትም (እንደ ንስሓ ጥምቀትነቱ) የዚህ እወጃ አካል ነው።

ጌታ ኢየሱስ ስለ እያንዳንዱ የሰው ልጅ አስፈልጎት (ጉድለት) ነው የተሰየመው፤ ለተራቡት የሕይወት እንጀራ ነው። ለተጠሙት የሕይወት ውሃ ምንጭ ነው። ለታመሙት የገለዐድ መድኀኒት ነው። ለሚሞቱት ትንሣኤና ሕይወት ነው። ለብቸኞች ከወንድም ይልቅ የሚጠጋጋ ወዳጅ፣ ለተገለሉ የኀጢአተኞች ወዳጅ ነው። የጌታችን ከሰው ጋር አንድ ተደርጎ መቈጠር እየጨመረ ሄዶ መስቀሉ ላይ ከፍታው ላይ ደረሰ - በዚያ እርሱ "ከዐመፀኞች ጋር ተቈጥሮአልና" (ኢሳ. 53፥12)።

ሙሴም ዳግመኛ ያስተምረናል። ራስን አንድ ማድረግ እንዴት የምልጃ መግቢያ እንደ ሆነ ያሳየናል። በዘፀአት 32፥32 ላይ ያለውን የሙሴን ጸሎት አንዴ በድጋሚ ብንመልከተው፣ "ይህን ኀጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን ከጻፍከው መጽሐፍ እባክህ ደምስሰኝ" በማለት እግዚአብሔርን

ሲናገር እንሰማለን:: በሙሴ ጥያቄ ውስጥ ብዙ ያልገባን ነገር ቢኖርም እንኳ አንድ ነገር ግልጽ ነው - ሙሴ ከሕዝቡ ጋር ራሱን አንድ አድርጓል::

ወደ አዲስ ኪዳንም ስንመጣ ሐዋርያው ጳውሎስ ራስን አንድ አድርጎ ስለ መቍጠር ምስጢር በሮሜ 9፥1-3 ላይ የሆነ ውልብታ እንድናገኝ ያስችለናል፤

> ብዙ ኀዘንና የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሽምም፤ ኅሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል:: በሥጋ ዘመዶቼ ስለ ሆኑ *ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን* እጸልይ ነበርና (አጽንኦት የተጨመረ)::

የነገረ መለኮት ሰዎች በእነዚህ ቍጥሮች ላይ ለዓመታት መዘውራቸውን ሲዘውሩ ኖረዋል፤ ጳውሎስም እነዚህን ቃላት ሲጠቀም ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምንም ይሁን ምን አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ ለወንድሞቹ ያለው ሸክም እጅግ ስለ ገዘፈና ስለ በዛበት ከእነርሱ ጋር ለመቈጠር ፈቃደኛ ነበር:: ይህ ምልጃ ነው:: ስለዚህም ጳውሎስ ቀጣዩን ምዕራፍ ሲጀምር የሚያውጀው ነገር ሊያስደንቀን አይገባም፤

> ወንድሞች ሆይ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው:: (ሮሜ 10፥1)

ለምልጃ የሚጠየቀው ከሁሉ የላቀ ነገር ራስን ችግር ውስጥ ካለው ሰው ጋር አንድ የማድረግ ፈቃደኝነት፣ ሸክሙን የመውሰድ ዝግጁነት ነው:: ይኸውም በትክክል ሕይወትን ስለ ወንድም አሳልፎ መስጠት ነው::

## የመንፈሳዊ መከር ሕግ

ጌታ ኢየሱስ የመንፈሳዊ መከርን መንገድ በቀጣዩ ንግግር ውስጥ አመልክቷል፤

> የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች (ዮሐ. 12፥24)::

"ብቻዋን ትቀራለች" የሚለው ሐረግ ሁላችንንም ያመለክታል:: ይህ ለክርክር ብዙም ቦታ የለውም - ሕይወታችን ፍሬ ካላስገኘ መሞት ገና አልተማርንም ማለት ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን በ2ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ያጠናከረዋል:: ሕይወቱን ሲያስረዳ፣ ስለ ነበረበት ሁኔታ በዚህ መልኩ ይናገራል፤



> የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን::
>
> የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሥጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን ከኢየሱስ የተነሣ ዘወትር ለሞት አልፈን እንሰጣለንና::
>
> *ስለዚህ ሞቱ በእኛ ሕይወቱም በእናንተ ይሠራል* (2ቆሮ. 4፥10-12 - አጽንኦት የተጨመረ)::

እስቲ እነዚህ ቃላት ውስጣችን ይጥለቁ:: የመንፈሳዊ መከር ሕግ እነሆ፤

> *"ሞቱ በእኛ ሕይወቱም በእናንተ ይሠራል::"*

በኢየሱስ ዘንድ ድሉ የተገኘው "ፈቃድህ ይሁን" በማለት በጸለየበት የአትክልት ስፍራ ነው:: ጌቴሴማኒን ለቅቆ ሲሄድ የመስቀሉ ዋና ጕዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተደምድሞ ነበር:: እያንዳንዱ ማላጅም ጦርነቱን የሚያካሂድበት የየራሱ ጌቴሴማኒ አለው:: በምልጃ ውስጥ የጦርነቱ ድል የሚገኘው ወይም የሚታጣው ወደ ክርስቶስ ሥቃይ ለመግባትና እስከ መሥዋዕትነት ድረስ ራሳችንን ከሌሎች ጋር አንድ አድርጎ ለመቍጠር በሚኖረን ፈቃደኝነት ነው::

## ይዞታውን ማግኘት

### ደረጃ ሁለት፡- መሥዋዕትነት

ይህም ይዞታን ወደ ማግኘት ሁለተኛ ደረጃ ያመጣናል:: እንጀራ ለመበደር በእኩለ ሌሊት የወጣው ወዳጅ ልክ የተራበው እርሱ እንደ ሆነ ያህል ራሱን ከእንግዳው ጉድለት ጋር *አንድ ማድረግ* ብቻ ሳይሆን፣ ይህንኑ ጉድለት ለመሙላት *መሥዋዕትነት* ከፈለ:: እንጀራ ለመፈለግ አካላዊ ምቾቱንና ድሎቱን ትቶ ወጣ:: ምልጃ የመሥዋዕትነት አገልግሎት ነው::

ለዐመፀኞች ማላጅ እንደ መሆኑ፣ ክርስቶስ የራሱ ጸሎት መልስ ራሱ ነበር:: ሞቱን ለሚያስፈጽሙት ሰዎች፣ "አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" በማለት መስቀል ላይ ሆኖ ጸለየ (ሉቃ. 23፥34):: ነገር ግን አብ እነርሱን ይቅር ማለት የሚችልበት ብቸኛ መሠረት ይኸው የመስቀል ላይ ሥራ ነበር፤ ደም ሳይፈስ የኀጢአት ይቅርታ የለምና:: ከክርስቶስ ሥቃይ ጋር ከመተባበር ውጭ እውነተኛ ምልጃ ሊኖርም

አይችልም:: እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ እንዲፈጽመው ፈቃደኛ ካል ሆናችሁ በቀር እግዚአብሔር አንድ ነገር እንዲያደርግ አትጠይቁት::

## ይዞታውን ማግኘት

### ደረጃ ሦስት:- ሥልጣን

እንግዳ ተቀባዩ ራሱን ከሌላኛው ሰው ጋር አንድ ከማድረጉና ከመሥዋዕትነቱ ውስጥ የሚያስፈልገውን ሁሉ ከሚያመነታው ጓደኛው የማግኘት ሥልጣን ይወጣል:: "ተነሥቶ ... የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል" (ሉቃ. 11፥8)::

እስቲ እዚህ ጋ ቆም አንበልና ምን ያህል እንደ ተጓዝን እንመዝን:: የምልጃ ንድፍ እንዲህ ነው፤

ከሌሎች ጉድለት (አስፈልጎት) *ጋራ ራስን አንድ ማድረግ::*

እነዚህኑ ጉድለቶች ለማሟላት *መሥዋዕትነት መክፈል::*

የጎደለውን ነገር የማግኘት *ሥልጣን::*

ሙሴ ራሱን ከሕዝቡ ጋር *አንድ አደረገ::* "ያለዚያ ግን ከጻፍከው መጽሐፍ እባክህ ደምስሰኝ" (ዘፀ. 32፥32):: በተራራው ላይ ለአርባ ቀናት በመጾምና በመጸለይ ለእነርሱ *መሥዋዕትነት* ከፈለ:: በእርግጥም ደግሞ በጸሎት ከእግዚአብሔር ሥልጣንን አግኝቷል፤ እግዚአብሔር በመቅሠፍት ቢቀጣቸውም እንኳ አላጠፋቸውም፤ አልጣላቸውምም::

ኢየሱስ የባሪያን መልክ በመያዝ ራሱን *ከሰው ጋር አንድ አደረገ::* በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት ላይ ተሸክሞ ራሱን *መሥዋዕት* አደረገ:: በሰማይና በምድር ሁሉ ባለው *ሥልጣንም* ሰይጣንን ትጥቁን ገፎ፣ የሞትን መውጊያ ሰብሮና የክብር ደጅን ወለል አድርጎ ከፍቶ ሰውን ከኀጢአቱ ፈታው::

ኢየሱስ:: ሙሴ:: ጳውሎስ:: ፍለጋቸውን እንከተላለን:: ባሪያ ከጌታው አይበልጥም:: አትሳሳቱ፤ ድል የሚያስገኝ ምልጃ ዋጋ ያስከፍለናል - እንቅልፍ አልባ ሌሊቶች፣ ስውር እንባዎች፣ የራስን ፍላጎትና ምኞት መሥዋዕት ማድረግ፣ በክርስቶስ መከራ የጎደለውን የትኛውንም ነገር (ቈላ. 1፥24):: "ጽዮን እንዳማጠች ወዲያው ልጆቿን ወልዳለችና" (ኢሳ. 66፥8):: ምጥ ሳይኖር ሕይወት እንደማይኖር ተፈጥሮ ራሷ ታስተምረናለች::

ሞት በእኛ ውስጥ ሲሠራ ነው በምንጸልይላቸው ሰዎች ውስጥ ሕይወት የሚሠራው:: ይህ የመንፈሳዊ መከር ሕግ ነው:: በፈረሰው ቅጥር



ለመቆም ስንል በጥቅማችንና በምኞታችን ላይ፣ በዕቅዳችን ላይ፣ በምቾታችንና በድሎታችን ላይ ሞት የምናመጣ ከሆነና ከሆነ ብቻ ነው መከርን የመጠበቅ መብት የሚኖረን::

ይህን ይዞታ በእጃችን ለማስገባት ፈቃደኞች ነን?

## ፰ - የቅዱሳን ጸሎት ኀይል

# ለሌሎች መጸለይ

በእርጋታ ወዲህ ወዲያ የሚማታው የባሕር ማዕበል ለነፍሳችን ትንሽ እርጋታ እንዲያስገኝልን በማለት አንድ በጋ ላይ ወደ ቴክሳስ ደቡባዊ ጠረፍ ቤተ ሰቤን ይዤ ሄድኩ።

ዓመቱ ለእኛ ጥሩ ዓመት አልነበረም፤ በዚህም ላይ ገና መጋመሱ ነው። ከጉዞው ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ትንሹ ልጃችን እግሩን ተሰብሮ አዲስ ችግር ጨመረልን።

አሁን ከጭኑ እስከ እግሩ አውራ ጣት ድረስ በጀሶ ታስሯል። የተነሣው ራጅ ስብራቱን ብቻ ሳይሆን ዐጥንቱም ላይ ዕጢዎች መኖራቸውን ያሳያል። ምን እንደ ሆኑ ለማወቅ ገና ነው። ቢሆንም ግምቴን ተጠቀምኩ።

እናም እንደ ልባችን ፀሓይ እየሞቅን፣ እየዋኘንና የባሕሩን ውሃ እየተራጨን በዚያ ቈየን። በእያንዳንዱ ማለዳ ስነቃ ቀፋፊው ባልንጀራዬ - ድብታ (depression) አብሮኝ ይሆናል። ዐልጋው አጠገብ ይጠብቀኛል፤ ማዕበሉ ጠርጎ አልወሰደውም። ላራግፈው አልቻልኩም። እኔና ይህ ጥላዬ ሁሉም ቦታ አብረን ነው የምንሄደው።

እስከ ሐሙስ ምሽት። ስነቃ እዚያ አልነበረም። ተጠራጠርኩ። ቀኑን ሙሉ ከሆነ ጥሻ ውስጥ ብቅ ይላል በማለት ስጠባበቅ ቈየሁ፤ ግና ምልክቱም አልነበረም። በቅጡ ዘና ማለት ጀመርኩ። አንድም ነገር አልተለወጠም፤ ሆኖም ሁሉም ነገር ልዩ ነበር።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ቤት ስንመለስ ባልነበርኩባቸው ጊዜአት የተቆለሉትን ደብዳቤዎች ለማምጣት ወደ ቢሮዬ ሄድኩ። አንደኛው ደብዳቤ የተጻፈበት ወረቀት የያዘው ዓርማ ያልተለመደ ቢሆንብኝም እጅ ጽሑፉን ዐውቀዋለሁ። ስላለሁበት ሁኔታ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ጓደኛዬ ነው። ከቀኑ በታች ደብዳቤው የተጻፈበት ሰዓት አለ - ከሌሊቱ 9 ሰዓት።



*ውድ ሮን ... ፣*

*እግዚአብሔር አሁን እያለፍክበት ያለውን ጊዜ የእውነትን ምስጢር ለመረዳት የተከፈተ አዲስ በር እንዲያደርግልህ እጸልያለሁ፤ መጸለዬንም እቀጥላለሁ። እግዚአብሔር እጅግ ይወድሃልና በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ስታልፍ አብሮህ ነው ያለው ...*

*አሁን ሰብከት አያስፈልግም። አሁን አንተን በሚመለከት ለእኔ ትልቅ የሆነን ነገር ልነግርህ ነው። አሁን በምድር ላይ ከአንተ ጋር ያለኝን ጓደኝነት ያህል ዋጋ የምሰጠው ጓደኛ የለኝም። እግዚአብሔርንም የአንተን ሸክም ለማቅለል የተቻለውን ያህል ሸክም ወደ እኔ ልብ አስተላልፎ እንዲጭን ጠይቄዋለሁ። አብሬህ መሸከም እፈልጋለሁ። ይህም ንግግርን ወይም የደብዳቤ ልውውጥን አይጠይቅም። ነገር ግን እነዚህ መንፈሳዊ ልውውጦች በሚፈጸሙበት ክልል ውስጥ፣ እግዚአብሔርን የጠየቅሁት ሸክምህን ...*

ደብዳቤው ላይ የተጻፈው ቀን ያ ጭጋጋማ ባልንጀራዬ በሌለበት የነቃሁበት ሐሙስ መሆኑ አላስደነቀኝም።

ሐዋርያው ጳውሎስ አንዳችን የሌላኞችንን ሸክም እንድንሸከም የነገረን ይህንን አስቦ ይሆን? ማርቲን ሉተር ያልተለመደ ጥንካሬና ደስታ ሲሰማው፣ "እንደ ተጸለየልኝ ይሰማኛል" የሚለው ይህን ነበር ማለት ነው? ቲ ዴዊት ታልማጅ፣ "ለአንድ ሰው ልታደርጉለት የምትችሉት ከሁሉ የሚልቅ ኀይለኛ ነገር ቢኖር ለእርሱ መጸለይ ነው" በማለት ሲናገር በእርግጥም በአእምሮው የነበረው ይኸው ነው።

### እንደገና፣ ሦስት ጎናዊ ጸሎት

ጸሎት በእርግጥም የቀደመችዋ ቤተ ክርስቲያን ለጴጥሮስ ያደረገችለት ታላቅ ነገር ነው። ጳውሎስና በርናባስ ከአንጾኪያዋ ቤተ ክርስቲያን ለኢየሩሳሌም የሚሆን ርዳታ ይዘው በሚመጡበት ጊዜ ገደማ ሄሮድስ ለጋዋን ቤተ ክርስቲያን ማሸበር ጀመረ (የሐዋ. 12፥1)። መጀመሪያ የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብን ገደለው። ያም አይሁድን እጅግ ስላስደሰታቸው ቀጥሎ ጴጥሮስንም ለመግደል ተራ ያዘለት። ስለዚህ ይህንን ሐዋርያ በቍጥጥር ሥር አውሎ በዐሥራ ስድስት ጠባቂዎች እያስጠበቀ አሳደረው። ሲነጋ ጴጥሮስም ያዕቆብን በዚያ ዘግናኝ መንገድ በሰማዕትነት ይከተለዋል። ነገር ግን ...

> ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ *ነገር ግን* በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር። (የሐዋ. 12፥5 - አጽንኦት የተጨመረ)

ንጽጽሩን አስተውሉ - ጴጥሮስ በወኅኒ ይጠበቅ ነበር - **ነገር ግን** ቤተ ክርስቲያን በቋሚነት እየጸለየችለት ነበር። ጴጥሮስ በወኅኒ ታስሮ ሞቱን መጠበቁ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ቃል አይደለም፤ የመጨረሻ ቃል የነበረውና እንደ ሆነ መቀጠል የሚችለው "በቤተ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ጸሎት እየተደረገለት ነበር" የሚለው ነበር።

የያዕቆብን ሰማዕትነት ለመግለጽ በነባሩ መጽሐፍ ቅዱስ (ቀኀሥ ትርጉም) አምስት፣ በግሪኩ ደግሞ ሰባት ቃላት ብቻ የተሰጠው መሆኑ አላስገረማችሁም? ለትልቅና ተጽዕኖ ለሚፈጥር ሰው የሚሰጥ የዜና ሽፋን ነው ለማለት ይከብዳል። ሆኖም የጴጥሮስ ጉዳይ ዐሥራ ሰባት ቁጥሮችን ጠይቋል። ታሪኩ እየተካሄደ ለነበረው ግፍጫ (ፍጥጫ) ትኩረት ለመስጠት ሲባል ሆን ተብሎ ነው በዚህ መንገድ የቀረበው። ይኸውም በዓለምና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለና እስከ ዛሬ ድረስ የቀጠለ ግጭት ነው። ይህም ፖለቲካዊ ኀይል ከመንፈሳዊ ኀይል ጋር በተቃራኒ ሲጋጠም ነው።

ሉቃስ ታሪኩን እንደ ልቦለድ ጸሓፊ ሆኖ ነው የጻፈልን። ዝርዝር ትንታኔዎቹ ያምራሉ። ሄሮድስ ጴጥሮስን አራት አራት እየሆኑ ለሚጠብቁት ዐሥራ ስድስት ጠባቂዎች ነው የሰጠው፤ ጴጥሮስ የዳነው ሄሮድስ ሊገድለው ባሰበበት በዚያው ቀን ነው፤ በሁለት ሰንሰለት ታስሮ በሁለት ጠባቂዎች መካከል ነው የተኛው፤ የብረት መዝጊያ በሆነው በመግቢያ በሩ ላይ ጠባቂዎች ነበሩ፤ አንድ መልአክ መጥቶ ጴጥሮስ አጠገብ ቆመና ጎኑን መትቶ ቀሰቀሰው፤ ከዚያም እንዲነሣ፣ እንዲታጠቅ፣ ነጠላ ጫማውን እንዲያስር፣ ልብሱን እንዲለብስ እና እንዲከተለው ነገረው።

የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን የዘብ ጣቢያ ዐልፈው ሄዱ። ከዚያም "ዐውቆ" ወደ ተከፈተላቸው የከተማው የብረት መዝጊያ ደረሱ (ቁጥር 10)። ይኸውም፣ አጠገቡ እንደ ደረሱ "ወዲያውኑ" ራሱ መከፈቱን መግለጹ ነው። ሉቃስ እየተደሰተ ነው የጻፈው። የምትጸልየዋን ቤተ ክርስቲያን ድል ነሺነት እየገለጠ ነውና።

ስለ ምልጃ ሦስት ጎንዮሽነት ከዚህች ወጣት ቤተ ክርስቲያን ጸሎት የተሻለ ምስል የሚሰጠን ይኖራልን? ጥብቅ ጸሎት (1) ወደ እግዚአብሔር፣ (2) ለጴጥሮስ፣ (3) በቤተ ክርስቲያን።



የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን - ልክ እንደ መሥራቿ - ከዓለም ጋር ብርቱ ጠብ (ግጭት) መኖሩን ታውቃለች። ጠላትን መጋፈጫና በቀጥጥር ሥር ማዋያ ኀይሏ ያለው ጸሎት ውስጥ መሆኑንም ታውቃለች። የማታውቀው ነገር ቢኖር ምን ያህል ኀይል እንዳላት ነበር፤ ይህም ግን አሁን ሊገለጥ ነው።

ጴጥሮስ አንዴ በደኅና ከወኅኒው ከወጣ በኋላ መልአኩ ተለይቶት ሄደ። ጴጥሮስም ወደ ቀልቡ ሲመለስና በእርግጥም በጌታ መልአክ ከወኅኒ የወጣ እንጂ እያለመ አለመሆኑን ሲገነዘብ አማኝ ወገኖቹ እንደሚሰበሰቡበት ወደሚያውቀው ወደ ማርያም ቤት በቀጥታ አቀና።

> በሩንም ሲያንኳኳ ሮዳ የምትባል ሠራተኛ ልትከፍትለት ሄደች።
>
> የጴጥሮስ ድምፅ መሆኑንም ባወቀች ጊዜ ከደስታዋ የተነሣ ደጁን አልከፈተችም፤ ነገር ግን ወደ ውስጥ ሮጣ ጴጥሮስ በደጅ ፊት ቆሞ እንዳለ አወራች። (ቁጥር 14)

ይህ እጅግ አስደናቂ አይደለምን? እግዚአብሔር ጸሎታቸውን መልሷል - ጴጥሮስ በደጅ ቆሟል! እነርሱ የሰማይን ደጅ በጥያቄ ሲያንኳኩ፣ እግዚአብሔር በራቸውን በመልስ እያንኳኳ ነበር።

የሮዳን ዜና ስትሰማ ቤተ ክርስቲያን ምንድን ነው ያለችው? ዝግጁ ናችሁ? "አብደሻል እንዴ!" ነው ያሏት።

> ሰዎቹም "አብደሻል እንዴ!" አሏት፤ እርስዋ ግን ይህንኑ ደጋግማ በነገረቻቸው ጊዜ፣ "እንግዲያውስ የእርሱ መልአክ ነው" አሉ።
>
> ጴጥሮስ ግን በር ማንኳኳቱን ቀጠለ፤ እነርሱም በሩን ከፍተው ባዩት ጊዜ ተገረሙ። (ቁጥር 15-16)

እዚህ ጋ ለእኛ የሚሆን ማበረታቻ አለ። የመጀመሪያዎቹን ክርስቲያኖች እጅግ ከመውደዳችን የተነሣ ፍጹም እንደ ሆኑና እምነታቸው አንዳችም ጥርጥር እንደሌለበት እናስባለን። እነዚህ ቁጥሮች ይህ ትክክል እንዳልሆነ በግልጽ ያሳያሉ። ልክ እንደ ኤልያስ ሁሉ እነርሱም የእኛ ዐይነት ተፈጥሮ ነው የነበራቸው (ያዕ. 5፥17)፤ ነገር ግን ጸልየዋል። እግዚአብሔርም ደግሞ መልሶላቸዋል - ለማመን ምንም ያህል የዘገዩ ቢሆኑ እንኳ። አንዳንዴ እግዚአብሔር ጸሎታችንን የሚመልሰው፣ በእምነታችን ምክንያት ሳይሆን ከጸጋው የተነሣ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሌሎች በመጸለይ ያምናል:: መልእክቶቹ በጸሎት የተኸኀረኀሩ ናቸው፤ ለአንባቢዎቹ ስለ እግዚአብሔር ከመናገር፣ ለእግዚአብሔር ስለ አንባቢዎቹ ወደ መናገር በቀላሉ ነው የሚዞረው:: በምትኩ ደግሞ የአብያተ ክርስቲያናቱን ጸሎት ለማግኘት ይመኛል፤ መልእክት ለጻፈላቸው ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የጸሎት ጥያቄ አቅርቧል - ወደ ኋላ ከተመለሱት የገላትያ ሰዎች በቀር::

ምን ዐይነት ክስ ነው! ጸሎታችን የሌሎችን እገዛ ለመጠየቅ ብቁ እስከማይሆን ድረስ ምን ዐይነት ራስ ወዳድ ሥጋዊ አዘቅት ውስጥ ነው የጠለቅነው?

ምን ዐይነት ክብር ነው! ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ቈይታ ላይ ልበ ሙሉ ከመሆናቸው የተነሣ እርሱ ፊት ስማቸውን እንድናነሣላቸው ይጠይቁናል::

ምን ዐይነት ዕፍረት ነው! እንድንጸልይለት ሰው ሲለምነን በግዴለሽነት፣ "እሺ እጸልይልሃለሁ" በማለት እንመልሳለን፤ ነገር ግን በቀላሉ የተገባ ቃል በመሆኑ በቀላሉ እንረሳዋለን - ስላደረግነው ጸሎት ምስጋና የያዘች ትንሽዬ ማስታወሻ ስትደርሰን ነው ትዝ የሚለን::

ምን ዐይነት ኀላፊነት ነው! አንዷትን ቤተ ክርስቲያን ምረጡ - የትኛዋንም ቤተ ክርስቲያን - የአባላት መዝገቡን ከፈቱና ዝርዝሩን ተመልከቱ:: አቤት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሌሉ ሰዎች ስም ብዛት! አንድ ወቅት እዚያ ነበሩ፣ አሁን ግን የሉም፤ ለረጅም ጊዜ የሉም::

## የጨቅላዎች የቈይታ ምጣኔ

የምታውቁት እንዲህ ዐይነት ሰው ይኖር ይሆን? እንደሚኖር እርግጠኛ ነኝ:: ክርስትናና በተረፈረፉ ደቀ መዛሙርት ተትረፍርፏል፤ የአባላት ዝርዝሩ ለዚህች ዓለም ፍቅር ሲሉ ጌታን በተዉ ዴማሶች (2ጢሞ. 4፥10) ብዛት ተጨናንቋል:: ምን ነክቷቸው እንደ ሆነ በመገረም ራሳችንን እንነቀንቃለን:: "ምናልባት መጀመሪያም ከልባቸው አልነበረም:: ለነገሩማ፣ ጌዲዮ ከተነሣ አይቀር ለእሱኛው ግን የተለየ ስሜት ነው ያለኝ - ያውም በዚያ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ዐልፎ መጥቶ?" እንላለን::

ነገር ግን እስቲ አንድ ጥያቄ ላቅርብ:: ለዚያ በእምነቱ ሕፃን ለሆነው ሰው ጸልያችሁለታል? የመጀመሪያውን የዝገት (የድካም) ምልክት ስንመለከት፣ በአዲሱ ሕይወቱ ላይ ጠላት ቃፊር ማሰማራቱን ስንጠረጥር - ጸልየንለታል?



በጸሎት ሸክሙን በልባችን ይዘን፣ በጸጋው ዙፋን ፊት ተሸክመን በማቅረብ፣ የመከላከያ ቅጥር ዙሪያው ገንብተናል?

ልጅ የመውለድ ምጥ ሁለትዮሽ ነው:: አንድም፣ ጨቅላውን ወደዚህች ምድር የማምጣት ምጥ አለ፤ አንድም፣ ሕፃኑን በዚህ ዓለም ውስጥ የማሳደግ ጣርም አለ:: ኋለኛው ደግሞ ይብሳል:: ሕፃኑን ለመውለድ የሚደረገው አካላዊ ምጥ ከባድ ቢሆንም፣ በአመዛኙ ለጥቂት ሰዓታት ብቻ ይቈያል:: ያንኑ ሕፃን ማሳደግ ግን ለሕይወት ዘመን የሚቈይ ሲሆን፣ ፈጽሞ ጋብ የሚል አይደለም:: ሌዊስ ስሜደስ እንዳለው፣ "ልጅ ስትጸንሱ ለመሠቃየት ቃል ኪዳን ትፈጽማላችሁ::"¹

ሐዋርያው ጳውሎስ ልጅ የመውለድንም ሆነ ልጅ የማሳደግን ምጥ ያውቃል:: ለገላትያ ሰዎች (እንዲጸልዩለት ላልጠየቃቸው) ሲጽፍ እንዲህ ብሏቸዋል፤

> ልጆቼ ሆይ፤ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ *ዳግመኛ* ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል:: (ገላ. 4፥19 - አጽንኦት የተጨመረ)

ወላጃዊ ጭንቀቱ በጽሑፎቹ ሁሉ ውስጥ ይታያል - በተለይም ለኤፌሶን፣ ለፊልጵስዩስ፣ ለቈላስይስ ሰዎች በጻፋቸው:: ልጆቹን በምልጃ ክንዶች (ዕቅፍ) ውስጥ ነው የወለዳቸው::

## መልካም ሥራ ተጀመረ፤

## መልካም ሥራ ተጠናቀቀ

ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች የጻፈው ቃል ያስደስተኛል፤

> በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና:: (ፊልጵ. 1፥6)

እያንዳንዱ መጋቢ ስለ አባላቱ ለእግዚአብሔር ይህንን መናገር ቢችል ይወድዳል:: ነገር ግን ጳውሎስ ቍጥር 6 ላይ ካለው የማረጋገጫ ቃል በፊት በቍጥር 3 እና 4 ላይ ሌላ ነገር ተናግሯል፤

> ሁልጊዜ በጸሎቴ ሁሉ ስለ እናንተ ሁሉ በደስታ እየጸለይሁ፣ .. ባሰብኋችሁ ጊዜ ሁሉ አምላኬን አመሰግናለሁ::

የቍጥር 4 ምልጃ ከቍጥር 6 ዕወጃ ይቀድማል:: ምናልባት እኛም "ሁልጊዜ እጸልይልሃለሁ" ማለት ከቻልን፣ "እግዚአብሔር የጀመረውን እንደሚፈጽም እርግጠኛ ነኝ" ማለት እንችላለን::

ሐዋርያው ጳውሎስ ለእነዚህ አማንያን ለመንገር የሚገደድበት ሌላም ነገር ነበረው:: ለፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የጻፈው መልእክትም ትልቅ ተቀባይነት ስላገኘው ስጦታቸው (4፥10) ለማመስገንና ባለሥልጣናቱ ለኢፍትሐዊ እስራት ዳርገውት፣ ኢርትዐዊ የሆነ ነገር ከአንዳንድ ወንድሞች ቢደርስበትም በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑን ለመንገር የተጻፈ የምስጋና ደብዳቤ ነው:: እንዲያውም ስለ እርሱ ከመጨነቅ ይልቅ፣ የሆነው ሁሉ "በጸሎታችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት ለመዳኔ እንዲሆንልኝ ዐውቃለሁና" በማለት (1፥19) መደሰት እንዳለባቸው ይነግራቸዋል::

እነዚህ ጳውሎስን ለመጉዳትና በሥራው ላይ እንቅፋት ለመፍጠር የታቀዱት ነገሮች "ለመንፈሳዊ ደኅንነቱ" (እዚህ ጋ "መዳኔ" የተባለው ቃል ፍች) የሚጠቅሙ ሆኑ:: ሥራውን ከማጨናገፍ ይልቅ ሁኔታዎቹ ገፍቶ እንዲሄድ አደረጉት::

ጳውሎስ ወደ ሮም ለመሄድ ልቡ ተዘጋጅቷል:: በሐዋርያት ሥራ 19፥21፣ "ሮምን ... ማየት አለብኝ" ይላል (ኢ.መ.ት):: ደግሞም ሮምን ዐይቷል፤ ባሰበው መንገድ ግን አይደለም:: ወንጌሉን ያለ ዕፍረት በማወጅ በክርስቶስ አምባሳደርነቱ በታላቂቱ ከተማ እንደ ልቡ እንደሚራመድ ነበር የጠበቀው:: በምትኩ ግን በእስረኝነት ሰንሰለቱን እየጎተተ ነበር ወደ ሮም የተወሰደው::

ይህ አሁንም ቢሆን ተልዕኮውን ይበልጥ ስኬታማ እንዳደረገለት - በቄሳር ቤተ መንግሥት ውስጥ ስለ ጌታ መመስከሩን እና "እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንዲሆን በንጉሥ ዘበኞች ሁሉና በሌሎች ሁሉ ዘንድ ተገልጦአል" በማለት (ፊልጵ. 1፥13) ሐሳቡን ያጠናክራል::

የፊልጵስዩስ ሰዎች የተጨነቁባቸው መከራዎች ለወንጌሉ ትልቅ ዕድገት የሚያመጡ ሆነው ተለወጡ::

## ልመና እና አቅርቦት

ከዚያም ጳውሎስ ይህ እንዴት እንደሚፈጸም ይነግራቸዋል፤ እግዚአብሔር ሁለት መሣሪያዎችን ይጠቀማል - "ጸሎታችሁ"ን እና "የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት"ን (1፥19)::

እስቲ ቆም ብላችሁ አስቡት:: ወደ ውስጣችሁም ይዝለቅ:: የእግዚአብሔር መንፈስ "ድካማችንን ያግዛል" መባሉ (ሮሜ 8፥26) አዲስ ዜና



አይደለም:: የመንፈስ ቅዱስን መሰጠት እናውቃለን:: ታዲያ ይህ "ጸሎታችሁ" የተባለው ምንድን ነው? ጳውሎስ እየተናገረ ያለው የፊልጵስዩስ ሰዎች ጸሎት የመንፈስ ቅዱስን ረድኤት ያህል ለነጻ መውጣቱ አስፈላጊ መሆኑን ነው:: እናም *አስቀድም* የጠቀሰው የቅዱሳኑን ጸሎት መሆኑን መጠቆም እፈልጋለሁ:: ጸሎቶቻችሁ ያን ያህል ጠቃሚነት እንዳላቸው ታውቃላችሁ?

ይህንን ጥቅስ ሲያብራራ ካርል ባርዝ እንዲህ ይላል፤

> በግልጽ ለመናገር የፊልጵስዩስ ሰዎች ጸሎት አጠገቡ ማንም ቀጥሎ ሊቆም ከማይችለው ከመንፈስ ቅዱስ ቀጥሎ ለመቆም ጥቅም አልባ፣ ሰዋዊና ዐቅም የለሽ አይደለም::[2]

ጳውሎስ ሦስት ነገሮችን ያውቃል፤ (1) የፊልጵስዩስ ሰዎች እየጸለዩለት መሆኑን ያውቃል፤ (2) ደብዳቤው ሲደርሳቸው ደግሞ ይበልጥ እንደሚ ጸልዩለት ያውቃል፤ እና (3) ጸሎታቸውም የእግዚአብሔርን ባርኮቶች እንደሚያመጣለት ያውቃል::

ይህን የሚመስል ሐሳብ በ2ኛ ቆሮንቶስ ውስጥም ይገኛል:: ሐዋርያው ጳውሎስ የአገልግሎቱ ሸክም "የሞትን ድምፅ" በውስጣቸው ያሰማ እንደ ነበር ይናገራል (2ቆሮ. 1፥9)፤ ሆኖም ልበ ሙሉነቱን የጣለበት ጌታ ያደረገለትንም ይመሰክራል፤

> ይህን ከሚያህል ሞት አዳነን፤ ያድነናልም:: እናንተም ደግሞ *ስለ እኛ እየጸለያችሁ አብራችሁ ስትረዱን* ... ወደ ፊት ደግሞ እንዲያድን በእርሱ ተስፋ አድርገናል (ቍጥር 10-11 - አጽንኦት የተጨመረ)::

በመጋቢነት በማገለግልበት ወቅት በተለይ (ለግል ጉዳይ፣ ለልዩ ጥያቄ እና ለመሳሰሉ ነገሮች) የምጸልይላቸውን አባላት ስም ዝርዝር የምጽፍባት በኪስ የምትያዝ ትንሽዬ ጥቁር ደብተር ነበረችኝ:: አንድ ቀን በአንድ የእሁድ ማለዳ ስብከት ላይ ስለ ትንሿ ጥቁር ደብተሬ ሳላስበው ተናገርኩ:: ከዚያም ሁለት ጥያቄዎችን በሚያቀርቡ ሰዎች ተጥለቀለቅሁ፤ ስማቸው ደብተሬ ላይ እንደ ተጻፈ ማረጋገጥ በሚፈልጉና የሚጨነቁለትን ሰው ስም ደብተሬ ላይ እንዳክልላቸው በሚጠይቁ::

ጉጉታቸው አስደነቀኝ - ጸሎቴ ላይ ያላቸው ልበ ሙሉነትም አስፈራኝ:: በተደጋጋሚ የተጠየቅሁትን ማወቅ ትፈልጋላችሁ? የባሎቻቸውን ስም በደብተሬ ላይ እንዳሰፍር የሚጠይቁ ሚስቶች ይበዙ ነበር:: ጻፍኩላቸው:: አንድ ወቅት ክርስቲያን በነበሩት አሁን ግን በወደቁት በእነዚህ

ባሎች ስም አጠገብ የራሴን ጥያቄ ጻፍኩ፤ በዘዳግም 8፥3 ላይ ተመሥርቼ፣ "ጌታ ሆይ፤ እንዲርባቸው አድርግ" በማለት፤

> አስጨነቀህ፣ *አስራበህም፤* አንተም ያላወቅኸውን ... መና አበላህ:: (አጽንኦት የተጨመረ)

ጸሎቴ በራሳቸው አለመርካትንና ለሌላ ተጨማሪ ነገር ራብ እንዲኖራቸው ለማድረግ እግዚአብሔር በእነዚህ ባሎች ላይ ቅዱስ ጥማትን እንዲጨምርባቸው ነው:: ለማመን ቢከብድም አንዳቸውም ሳይቀሩ ከዚህ በፊት ፈጽመው በማያውቁት መንፈሳዊ ራብ እግዚአብሔር በሁሉም ሕይወት ላይ ተጽዕኖ አመጣ - ከዚያም በቤተ ክርስቲያንና በእነዚህ ሰዎች ቤት መንፈሳዊ መነቃቃት ተከስቶ አየን::

እግዚአብሔር በሕዝቡ በኩልና በጸሎታቸው መሥራትን መርጧል:: ጳውሎስም የቅዱሳኑ ጸሎት የመንፈስ ቅዱስን አቅርቦት ያህል አስፈላጊ መሆኑን አምኗል::

አሁን የቀረው የእኛም ማመን ነው::

<u>ማስታወሻ</u>

1. Lewis B. Smedes, *How Can It Be All Right When Everything Is All Wrong?* (San Francisco: Harper & Row Publishers, 1982) 63.
2. Karl Barth, quoted by Jacobus J. Miller, *The Epistle of Paul to the Philippians and Philemon,* The New International Commentary on the New Testament (Grand Rapids: Wm. B. Eerdmans Publishing Co., 1955) 57.



## ፱ - ጸሎት ላይ ላሉን አንዳንድ ጥያቄዎች የሚሆኑ መልሶች

# የእግዚአብሔር የጸሎት ዝርዝር

ጸሎት የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው::

ይህ ጠቃሚ መረጃ ነው:: ይህን የምለው ባለፉት ጊዜአት - እናም አሁንም - ከጸሎት ጋር አንዳንድ ትግሎች ስለ ነበሩኝ ነው:: ማለቴ፣ የጸሎት ሐሳብ አንዳንድ ፈታኝ ጥያቄዎችንና ተገቢ የሚመስሉ ተቃውሞዎችን ያስነሣል:: እናንተም ተመሳሳይ ጥያቄዎች እንደሚኖሯችሁ እወራረዳለሁ::

ጥያቄዎቹ እነዚህን ይመስላሉ:- የሰው ነጻ ፈቃድስ? መዳን የማይፈልግን ሰው እንዲያድን እግዚአብሔርን እንዴት ልጠይቅ እችላለሁ? ከሥጋዊነቱ መላቀቅ ለማይፈልግ ሥጋዊ ክርስቲያን እንዴት መጸለይ እችላለሁ? ይህን የሚመስሉ ጸሎቶች ከሰው ፈቃድ ጋር እንዴት ይታረቃሉ?

የእግዚአብሔር ሉዐላዊነትስ? በየትኛውም መንገድ ቢሆን እግዚአብ ሔር የፈለገውን አይደል የሚፈጽመው? በዚህ ላይ ደግሞ አስቀድሞ የወሰነው ነገር አለ! ማለቴ በእግዚአብሔር የተመረጡ በእግዚአብሔር የተመረጡ ናቸው፤ አይደል? ጸሎቴ አንድን ሰው ካልተመረጡት ክልል ወደ ተመረጡት ክልል ማምጣት ይችላልን?

የዚህ ውልውል መፍትሔ?

ጸሎት የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው:: ይህ ማለት ጸሎትን የከበቡ ጥያቄዎች፣ ተቃውሞዎችና ተቃርኖዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ጉዳዮች መሆናቸው ነው::

እኔን በሚመለከት በአእምሮዬ ሁለት ነገሮችን ነው ማኖር የምፈል ገው፤ (1) እግዚአብሔር እንድጸልይ አዞኛል:: ጸሎት የሚሠራው እንዴት እንደ ሆነ ባውቅም ባላውቅም፣ ያጋጠሙኝ ችግሮች ምንም ዐይነት ቢሆኑ እንድጸልይ ታዝዣለሁ:: መረዳት አለመቻሌ መጸለይ ላለመቻሌ ሰበብ አይሆንም:: ስለ ጸሎት የተረዳሁት ነገር ቢኖርም ባይኖርም ይህንን ዐውቃለሁ፤ ጸሎቴ ለውጥ እንደሚያመጣ እግዚአብሔር አረጋግጦልኛል::

(2) እግዚአብሔር የሚፈጽመው ነገር ሁሉ ከማንነቱ ጋር የሚጣጣም ነው:: ራሱን አይክድም፤ ከራሱም ጋር አይጣረስም:: በጸሎቱና በሰው ነጻ ፈቃድ መካከል ላለው ግልጽ ግጭት እንዴት መፍትሔ እንደሚያበጅለት አላውቅም፤ ነገር ግን ይህ እርሱን ካልረበሸው እኔንም እንዲረብሸኝ አልፈቅድም::

እግዚአብሔር እንድንጸልይ ማዘዝ ብቻ ሳይሆን (ለነገሩ "ጋብዞናል" የሚለውን እመርጣለሁ፤ ጸሎት የትእዛዝነቱን ያህል ልዩ መብትም ነውና) በምልጃችን ጊዜ የምንመራበት የጸሎት ዝርዝርም ሰጥቶናል::

የእግዚአብሔርን የጸሎት ዝርዝር በጳውሎስ የጢሞቴዎስ መልእክት ውስጥ እናገኘዋለን፤

> እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፣ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ:: (1ጢሞ. 2፥1-2)

ጳውሎስ ለወጣት ተከታዩ ስለ መጋቢነት አገልግሎት ትምህርት እየሰጠው ነው፤ እናም ሕዝቡ በአንድነት ሲሰባሰቡለት መጀመሪያ ማድረግ ያለባቸው ነገር መጸለይ እንደ ሆነ ይነግረዋል:: በአምልኮ አጀንዳ ላይ ቀዳሚው ይህ ነው - የቅደም ተከተል ቀዳሚነት ሳይሆን የጠቀሜታ ቀዳሚነት:: "ከሁሉ በፊት" ከሌሎች ልምምዶች ሁሉ በላይ "ጸሎት":: ጸሎት ከሁሉ የላቀ የአምልኮ መገለጫ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ከዚህ የሚበልጥ ነገር ልታደርግ አትችልም::

## ለዓለማዊ መሪዎች ጸልዩ

በዚህ የጸሎት ዝርዝር ውስጥ አንዳንድ ያልተጠበቁ ነገሮች አሉ:: በመጀመሪያ ጳውሎስ *ለዓለማዊ (ለአገር) መሪዎች* እንዲጸልዩ ይነግራቸዋል - "ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ":: ስለ ነገሥታት? ለንጉሡ መጸለይ አለብን? እንዴ ይህ እኮ ክርስቲያኖችን እያረደ ለአራዊት ሲወረውር የኖረ ነው:: እና ለእርሱ ልጸልይ ነው? እሺ፤ እጸልይለታለሁ - እግዚአብሔር በዚህ ኢአማኒ ላይ እሳትና ድኝ እንዲያዘንብበት እጸልይለታለሁ::

ጳውሎስ ያሰበው ግን እንዲህ አይደለም::

ይህ የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ዓለማዊ መንግሥት የተዋቀረው ለሰዎች ደኅንነት ስለ መሆኑ የጸና እምነት እንዳለው ያስምርበታል:: ይህንንም ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ አጽንኦት ይሰጠዋል (ክፍሉ በራሱ በስፋት የሚያወያይ ቢሆንም)፤



> ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለሥልጣኖች ይገዛ:: ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው:: (ሮሜ 13፥1)

ጴጥሮስም በስደት የተጨናነቁትን አማኞች እንዲህ ይላቸዋል፤

> ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዐት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን፣ ከሁሉ በላይ ነውና፤ ለመኳንንትም ቢሆን፣ ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት፣ በጎም የሚያደርጉትን ለማመስገን ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ:: በጎ እያደረጋችሁ የማያውቁትን ሞኞች ዝም ታሰኙ ዘንድ *የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና::* (1ጴጥ. 2፥13-15 - አጽንኦት የተጨመረ)

"ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ" የተባሉት ስመ ጥርና በከፍታ ስፍራ ያሉትን ሰዎች የሚመለከት ነው:: ሐረጉ በእኛ ላይ ሥልጣን ያላቸውን ሁሉ - አሠሪዎችን፣ አስተማሪዎችን፣ ወላጆችን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና የአገር መሪዎችን ያቅፋል::

እዚህ ጋ ልንነካቸው የሚያስፈልጉን ሁለት ጉልህ ሐሳቦች፣ አንደኛ ጳውሎስ "ነገሥታት" በማለት ብዙ ቍጥርን የመጠቀሙ ፋይዳ:: ጳውሎስ በወቅቱ የነበረውን ንጉሥ ወይም ገዥ ብቻ እንደማይመለከት ይጠቁማል - ይህም በቤተ ክርስቲያን ሁሌም ተፈጻሚነት እንዲኖረው ይጠብቃል::

ሁለተኛ፣ ጸሎቱ በዋናነት በነገሥታት ወደ ክርስቲያንነት መምጣት ላይ እንዲያነጣጥር አይደለም የጳውሎስ ሐሳብ:: ነገሥታት ትክክለኛና የተከበሩ መሪዎች እንዲሆኑ የግድ ክርስቲያኖች መሆን አያስፈልጋቸውም:: ጳውሎስ ጸሎት እንዲደረግላቸው ያሰበው፣ በመሪነት ሚናቸው ከባድ የኀላፊነት ሸክም ያለባቸውና በዜጎች ሕይወት ላይ ኀይለኛ ተጽዕኖ የሚያመጡ ሰዎች በመሆናቸው ላይ ነው:: የእግዚአብሔር መግቦት መድልዎ የለበትም፤ ዝናቡ በጻድቃንና ጻድቅ ባልሆኑት ላይ ይዘንባልና ጸሎታችንም እንዲህ መሆን አለበት - በአልኸኝነት ለሚጎዱንና ለሚያሳድዱን እንኳ መጸለይ አለብን (ማቴ. 5፥44):: ክርስቲያን ያልሆኑ አስተዳዳሪዎች እንኳ የጸሎታችን ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፤ መንግሥታቸው ምንም የከፋ ቢሆን፣ የመንግሥት አልባነትን ያህል አይከፋም::

ለእነርሱ በመጸለይ ባለሥልጣናት ኀይላቸውን በጥበብና በትክክል እንዲጠቀሙ ቤተ ክርስቲያን ታግዛቸዋለች:: ጳውሎስ፣ "እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር" ማለቱ (1ጢሞ.

2፥2) የእንደዚህ ዐይነት ጸሎትን ምክንያት ግልጽ አድርጎታል፡፡ መሪዎች በአግባቡ ሲያስተዳድሩ ዜጎቻቸው ጸጥ ያለ ሰላማዊ ኑሮ መኖር ይችላሉ፤ የዚህ ተቃራኒ ሲሆን ግን ሰላም ማጣትና ብጥብጥ ይሆናል - ይህም ዓለማችን አሁን ስላለችበት ሁኔታ ሥዕላዊ መግለጫ ይሰጠናል፡፡

ጥሩ መሪዎች ጥሩ መንግሥት ይፈጥራሉ፤ ይህም ጸጥተኛና ሰላማዊ ሕይወት እንዲኖር ያደርጋል፤ በመሆኑም ወንጌልን ለመስበክ የተመቸ ከባቢያዊ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፤ እንዲህ መሆኑ ደግሞ "ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኀኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ነው" (ቀ.ጢሞ 3-4)፡፡ ለሌሎች መጸለይ፣ የቃለ እግዚአብሔር ትእዛዝ ነው፤ የእግዚአብሔር ፈቃድም ነው፡፡

## ለመንፈሳዊ መሪዎች ጸልዩ

ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ ወንጌላዊ የቀጣይ ምሽት ስብከቱ "መጋቢያችሁን እንዴት እንደምትቀይሩ" የሚል ርዕስ እንዳለው አስታወቀ፡፡ ይህንንም ከአስጎምጂነቱ የተነሣ ሰዎች አይተዉት ብቻ ሊያልፉት ባለ መቻላቸው በቀጣዩ ምሽት አዳራሹ ከአፍ እስከ ገደፉ ጥቅጥቅ ብሎ ሞላ፡፡ ሰባኪው፣ "መጋቢያችሁን ለመቀየር ከፈለጋችሁ ጸልዩለት! መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድበትና እንዲያቀጣጥለው ጸልዩ!" በማለት ምስጢሩን ሲገልጽ አየሩ በጉባኤው በቅሬታ የማቃሰት ድምፅና በበርካታ አገልጋዮች የዕፎይታ ትንፋሽ ተሞላ፡፡

በእርግጥ የሞቅ ሞቅ ሰባኪ ብለው ስም ቢያወጡለትም ሐሳቡን አስተላልፎአል፡፡ አገልጋያችሁን ካልወደዳችሁት ቀይሩት - ጸልዩለት፡፡ ትልልቅ ሰባኪዎች ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናትን እንደሚፈጥሩ በአገልጋዮች አካባቢ አዘውትሮ ይነገራል፡፡ ይህ እውነት ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት ትልልቅ ሰባኪዎችን መፍጠራቸውም እውነት ነው፡፡ የምዕመናን የተሻለ መጸለይ የተሻለ ስብከት ከምስባኩ ያስገኛል፡፡

## በሕዝብ አገልግሎታቸው የእግዚአብሔር ባርኮት እንዲኖር

የጳውሎስ መልእክቶች ተለይተው ከሚታወቁባቸው መገለጫዎች አንዱ የምዕመናኑን ጸሎት ለማግኘት በቋሚነት የሚያቀርበው ጥያቄ ነው፡፡ በኤፌሶን 6፥18 ላይ እንዲህ ብሎ ጽፏል፤

> በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ ... ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ ... የወንጌልን ምስጢር በግልጥ



> እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ *ስለ እኔ ለምኑ፡፡* (አጽንኦት የተጨመረ)

እንደገና በቈላስይስ 4፥3-4 ላይም፣

> በዚያን ጊዜም ስለ እርሱ ደግሞ የታሰርሁበትን የክርስቶስን ምስጢር እንድንነግር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ፤ ልናገር እንደሚገባኝ ያሀል እገልጠው ዘንድ ጸልዩልኝ፡፡

ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የተከፈተ በርን በመስጠት ክርስቶስን በልበ ሙሉነትና በግልጽ መስበክ የሚችሉባቸውን መልካም አጋጣሚዎች እንዲያዘጋጅላቸው ለመጋቢያን፣ ለሚሲዮናውያንና ለወንጌላውያን በቋሚነት መጸለይ አለባቸው፡፡

## የሮሜው ጸሎት መልስ አገኘ

ጳውሎስ በሮሜ ላሉ አማኞች ሦስትዮሽ የጸሎት ጥያቄ አቅርቦ ነበር፤

> ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ የተጋድሎዬ አጋር እንድትሆኑ ... እለምናችኋለሁ፡፡ (1) በይሁዳ ካሉት ከማያምኑት እጅ እንድድንና (2) በኢየሩሳሌም ያለኝ አገልግሎትም በዚያ ባሉት ቅዱሳን ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጸልዩልኝ፤ (3) ይኸውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ እናንተ በደስታ እንድመጣና ከእናንተም ጋር እንድታደስ ነው፡፡ (ሮሜ 15፥30-32 - አ.መ.ት)

አዲስ ኪዳንን ካስተማሩኝ ፕሮፌሰሮች አንዱ ይህ ሦስትዮሽ ጸሎት እንዴት መልስ እንዳገኘ እንዲህ አስረድቷል፡፡[1]

አንደኛ፣ ጳውሎስ ለተቸገሩ አማኞች የሚሆን ርዳታ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ጠላቶቹ ተነሥተውበት ነበር (የሐዋ. 21፥27)፡፡ ታምናላችሁ? የሮም ወታደሮች ናቸው የታደጉት! የጳውሎስ ጠላቶች ግን ተስፋ አልቈረጡም፡፡ የግድያ አደጋ ሊያደርሱበት ሤራ ጎነጎኑ፡፡ ነገር ግን የጳውሎስ የወንድም ልጅ የሆነ ወጣት ሤራውን ሰምቶ ለጳውሎስ፣ ጳውሎስም በተራው ለመቶ አለቃው ነገረውና የመቶ አለቃው በብዙ መቶ የሚቈጠሩ ወታደሮችን ተጠቅሞ ጳውሎስን ከከተማ አስወጣው (የሐዋ. 23፥23ን ተመልከቱ)፡፡

ሁለተኛ፣ ጳውሎስ አገልግሎቱ በኢየሩሳሌም ባሉ ቅዱሳን ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ እንዲጸልዩለት፣ በሮም ለሚገኙ አማኞች ጥያቄ

አቅርቧል፡፡ እኛን ሊያስደንቀን ቢችልም ጳውሎስን ሁሉም ሰው አይደለም የሚወደው፡፡ በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን አወዛጋቢ ማንነት ነበረው፡፡ አብረውት የሚያመልኩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ትችት የሚያደርሱበት፣ ውሸት የሚናገሩበት እና የሚያደርገውን የማይገነዘቡለት ሰው ነበር፡፡ ስለዚህ የጸሎት ጥያቄው የምር ነበር፡፡ ሉቃስ የዚህን ጸሎት ምላሽ በተከታዮቹ ቃላት ገልጾታል፤

> ወደ ኢየሩሳሌም በደረስን ጊዜ ወንድሞች በደስታ ተቀበሉን፡፡ (የሐዋ. 21፥27)

የጳውሎስ ሦስተኛ ጥያቄ፣ "በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ እናንተ በደስታ እንድመጣና ከእናንተም ጋር እንድታደስ" የሚል ነበር፡፡ የጳውሎስ የሮሜ ጉዞ የራሱ አሸባሪና አስጨናቂ ገጠመኞች እንደ ነበሩት ሉቃስ ይነግረናል፡፡ መጀመሪያ፣ የመርከቡን ተሳፋሪዎች ሁሉ ሕይወት ሊቀጥፍ የሚችል ፈታኝ ማዕበል አጋጠማቸው፤ እግዚአብሔር ግን ለጳውሎስ የዋስትና ቃል ሰጠው፤

> ጳውሎስ ሆይ፣ አትፍራ፤ በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል፤ እነሆም፣ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር የሚሄዱትን ሁሉ ሰጥቶሃል፡፡ (የሐዋ. 27፥24)

ከዐሥራ አራት ቀናት በኋላ መርከቢቱ ከመሬት ጋር ተጋጭታ ተሰባበረች፤ ሆኖም ሁሉም ሰው በሰላም ወደ ጠረፍ ደረሰ፡፡

ከዚያም ከቅዝቃዜውና ከብርዱ ለመዳን ጳውሎስ ጭራሮ እየሰበሰበ እሳት ውስጥ ሲጨምር፣ ከጭራሮ መካከል እባብ ወጣችና ነደፈችው፡፡ ሌሎቹ ሰዎች ጳውሎስ በዚህ አደጋ ምክንያት ይሞታል በማለት ሲጠባበቁ ነበር፤ ይህ ለእነርሱ የጳውሎስ ነፍስ ገዳይነት ማረጋገጫ ነበር፡፡ ጳውሎስ ግን እባቢቱን ወደ እሳቱ አራገፋትና ሁሉም እስኪደነቁ ድረስ አንዳችም ጉዳት ሳያገኘው ቀረ፡፡

ጳውሎስ ሮሜ ደረሰ፤ እዚያ ያደረሰውም ከእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ጋር የተጣጣመው የሮሜ ክርስቲያኖች ጸሎት ነበር፡፡

## በግል ሕይወታቸው የእግዚአብሔር ጥበቃ እንዲኖር

ከጥቂት ሰዓታት በፊት ቴሌቭዥን እየተመለከትኩ እያለ አንድ ታዋቂ አገልጋይ ግብረ ገብ በጎደለው ጠባዩ ተከስሶ ከምስባኩ ሲወርድ የሚያሳይ አሳዛኝ ትዕይንት ሲተላለፍ አየሁ፡፡ ቊጥራቸው እየጨመረ ከመጣው የወደቁ



አገልጋዮች ጋር ተደመረ ማለት ነው፡፡ እነዚህ ጥቂት አገልጋዮች አብዛኞቹን የወንጌል አገልጋዮች ይወክላሉ የሚል እምነት የለኝም፤ ሆኖም ከሠላሳ ዓመታት በላይ በአገልግሎት እንደ መቆየቴ ሁሌም የግብረ ገባዊ ውድቀት ምሳሌዎች ቢኖሩም እንኳ ይህን ዐይነት ነገር ዐይቼ አላውቅም፡፡ ጠላት የወንጌሉን አገልጋዮች ዋጋ ለማሳጣት ከባድ የማጥቃት ዘመቻውን እንዳፋፋመ ጥርጥር የለኝም፡፡ እንደሚያገሳ አንበሳ የሚውጣቸውን መንፈሳዊ መሪዎች በመፈለግ እየዞረ ሲሆን፣ በርካቶችም መንጋጋው ውስጥ ገብተውለታል፡፡

የክርስቲያናዊ ሠራተኞችን ያህል ለሐሜትና ለአሽሙር የተጋለጡ ሌሎች ሰዎች ብዙ አይደሉም፡፡ ዓለም በሌሎች ላይ አይቶ እንዳላየ የሚያል ፈውን ነገር በአገልጋዮች ላይ ሲሆን መሳለቂያ ያደርገዋል፡፡ ጥቃቱ ሁላችንንም ይሰማናል፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ለእርሱና አብረውት ለሚያገለግሉ ሠራተኞች ከለላ እንዲሆኑላቸው የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችን የሚገፋፋቸው፤

> በቀረውስ ወንድሞች ሆይ ... እምነትም ለሁሉ ስለማይሆን ከዐመፀኞችና ከክፉዎች እንድንድን ስለ እኛ ጸልዩ (2ተሰ. 3፥1-2)፡፡

ግሱን በማየት እዚህ ጋ የጳውሎስ ጥያቄ የቀጣይነት ጊዜን የሚያሳይ ትእዛዝ እንደ ሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዕልፎ ዕልፎ "እግዚአብሔር ወደ አእምሮአቸው ሲያመጣው" እንዲያስታውሱት እየጠየቀ አይደለም፡፡ ሁል ጊዜም በንቃት ቋሚ የጸሎት ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ጥያቄ እያቀረበ ነው፡፡

ከአንዲት ቃል፣ ከትንሽ ጥርጣሬ እና ከዐይን ጥቅሻ ብዙም ያልዘለሉ ነገሮች የአንድን ሰው አገልግሎትና የቤተ ክርስቲያንን ምስክርነት ለማበላሸት በቂ ናቸው፡፡ ምልጃ በመንፈሳዊ መሪዎቻችን ዙሪያ የመከላከያ ቅጥር ሊገነባ ይችላል፡፡ "እንዲህ ዐይነቱ ጸሎት የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ማንሣት (ስድብ አምላክ)፣ ራስ ወዳድነት፣ ስስት፣ ታማኝነትን ማጉደል፣ ኢግብረ ገባዊነት፣ ጭከና እና ኢፍትሐዊነት የማያብቡበት፣ ሬይሞንድ ጆንሰን እንደ ሚለው፣ 'መከላከያ መድኀኒት የተረጨበት ከባቢ' ይፈጥራል፡፡"[2]

ፕሬዚዳንቱን በቴሌቭዥን ባየሁ ቊጥር ዙሪያውን በሚከብቡት ምስጢራዊ የጸጥታ ሠራተኞች ብዛት እገረማለሁ፡፡ ሮናልድ ሬጋን ላይ የግድያ ሙከራ ሲደረግ በጉልህ እንደታየው የፕሬዚዳንቱን ሕይወት ለማዳን የጸጥታ ሠራተኛው ጥይቱ በሚመጣበት አቅጣጫ ራሱን እስከ መወርወር ሊሄድ ይችላል፡፡

መንፈሳዊ መሪዎቻችን ከሚሰነዘርባቸው ጥቃት (ከስ) በጸሎት ጋሻ የሚከላከሏቸው እንዲህ ዐይነት የጸጥታ ሠራተኞች፣ መንፈሳዊ ዐጃቢዎች ናቸው የሚያስፈልጓቸው - እናንተ ከፈቀዳችሁ።

## ከጳውሎስ ጋር መጸለይ

አብዛኛው ጸሎታችን አማኞችን ወደ ማነጽ ማቅናት አለበት። አሁንም ሐዋርያው ጳውሎስ ምሳሌአችን ነው፤ በመልእክቶቹ ውስጥ ያሉት ጸሎቶች በእርሱ የጸሎት ሕይወት ውስጥ ይህ ዋነኛው ጉዳይ መሆኑን ያረጋግጣሉ። ለሌሎች ክርስቲያኖች መጸለይ ያለብኝ እንዴት ነው? ለሚለው ጥያቄም የመንፈስ ቅዱስ አብርሆት ያለበት ምላሽ ያቀርባሉ።

አማኞች በክርስቶስ ውስጥ ያላቸውን ወሰን አልባ ሀብት ማወቅ አለባቸው። እስቲ ጳውሎስ ሲጸልይ ስሙ፤

> የክብር አባት የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ይበልጥ እንድታውቁ፣ የጥበብና የመገለጥን መንፈስ እንዲ ሰጣችሁ ያለማቋረጥ እለምናለሁ። እንዲሁም የተጠራችሁለት ተስፋ፣ ይህም በቅዱሳኑ መካከል ያለውን ክቡር የሆነውን የርስቱን ባለጠግነት ምን እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ ... ለእኛ ለምናምነውም ከሁሉ በላይ የሆነውን ኀይሉን እንድታውቁ እጸልያለሁ። (ኤፌ. 1፥17-19 - አ.መ.ት)

በፈታኙ ለመበጠር እየወረደ ያለ አማኝ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው መንፈስ እርሱም ውስጥ መኖሩንና በዚሁ ጊዜም አጠገቡ እንደሚገኝለት ማወቁ ምን ማለት እንደ ሆነ እስቲ አስቡት። ልንጸልይ የሚገባው ለእነዚህ ዐይነት ሰዎች ነው።

ኤፌሶን 3፥14-19 የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልመናዎች መዝገብ ነው። ጳውሎስ በአብ ፊት ይንበረከክና በኤፌሶን ላሉ አማኞች ይጸልያል፤

- በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታቸው በኀይል እንዲጠነከሩ፣
- ክርስቶስም በውስጥ ሰውነታቸው በእምነት እንዲኖር፣
- የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ እንዲበረቱ፣
- እስከ እግዚአብሔር ሙላት ደርሰው እንዲሞሉ።

ሌላ ቱባ የጸሎት ዝርዝር በፊልጵስዩስ 1፥9-11 ይገኛል። ጳውሎስ በተለይ ለእነዚህ ክርስቲያኖች እንዲህ ይጸልያል፤



- ፍቅራቸው ከፊት ይልቅ እንዲያድግና እንዲበዛ፣
- የሚሻለውን ነገር ፈትነው እንዲያውቁ፣
- ቅኖችና ያለ ነውር እንዲሆኑ፣
- በጽድቅ ፍሬ እንዲሞሉ።

አንድ ተጨማሪ ምሳሌ፣ ቈላስይስ 1፥9-12። እዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቈላስይስ ክርስቲያኖች እንዲህ ይጸልያል፤

- የእግዚአብሔር የፈቃዱ ዕውቀት እንዲሞላባቸው፣
- በነገር ሁሉ ደስ ያሰኙት ዘንድ እንደሚገባ እንዲመላለሱ፣
- በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እንዲያፈሩ፣
- በእግዚአብሔር ዕውቀት እንዲያድጉ፣
- በኀይል ሁሉ እንዲበረቱ፣
- በማያቋርጥ አመስጋኝ ሕይወት እንዲኖሩ።

## አንዳንድ የልመና ጥቆማዎች

እስቲ ከእነዚህ የጳውሎስ ጸሎቶች ጥቂቶቹን ሰብስበን በአንድነት እንቀላቅላቸውና የቃለ እግዚአብሔራዊ ልመና ዝርዝር እናብጅ። ዝርዝሩን ስታነብቡ የሆኑ ወዳጆቻችሁ ወደ አእምሮአችሁ ይመጣሉ። ምናልባት መጀመሪያ መጸለይ የሚኖርባችሁ ለእነርሱ ነው። ለሌሎች ስትጸልዩ እንደዚህ ጸልዩ፤

- በክርስቶስ ውስጥ ላላቸው ወሰን አልባ ሀብት ዐይኖቻቸው እንዲከፈቱ፣
- በመንፈስ ቅዱስ እንዲበረቱ፣
- በእግዚአብሔር ሙላት እንዲሞሉ፣
- የክርስቶስን ፍቅር በሙላት እንዲያውቁና እንዲያደንቁ፣
- ለሌሎች ያላቸው ፍቅር ወደ መትረፍረፍ እንዲያድግ፣
- ትክክሉን ከስሕተት መለየት እንዲችሉና በነገር ሁሉ ትክክለኛውን ውሳኔ እንዲወስዱ፣

- ከማስመሰልና ከግብዝነት ርቀው ነቀፋ የሌለበት ሕይወት እንዲኖራቸው፣
- የጽድቅ ፍሬ እንዲሞላባቸው፣
- ለሕይወታቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁና ለዚያም ታማኝ እንዲሆኑ፣
- በሚያደርጉት ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያስደስቱ፣
- በእያንዳንዱ መልካም ሥራ ፍሬያማ እንዲሆኑ፡፡
- ስለ እግዚአብሔር ይበልጥ ለማወቅ እንዲራቡና እንዲጠሙ፣

ይህ የጸሎት ዝርዝር፣ የምትጸልዩላቸውን ሰዎች ስም በጠራችሁ ቍጥር መቍጠሪያ አሥርታችሁ እንድትደግሙበት አይደለም፡፡ እነዚህ ቃለ እግዚአብሔራዊ ጥቆማዎች ናቸውና በጸሎት ዝርዝራችሁ ላይ ያሉት ሰዎች ካለባቸው ጉድለት አኳያ በራሳችሁ አባባል እንደገና ልትጽፏቸው ትችላላችሁ፡፡

እግዚአብሔር የመንፈሱን አቅርቦት ጉድለት ወዳለባቸው አማኞች ለማምጣት የሚሠራው በጸሎታችን በኩል እንደ ሆነ አስታውሱ፡፡ ለሌሎች በመጸለይ የኢየሱስን ኀይል ወደ ሰዎች ሕይወት ማምጣት እንችላለን፡፡ ወደ ቈሰሉ ልቦች የእርሱን የፈውስ ኀይል መጋበዝ እንችላለን፡፡ በእነርሱ "መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲ ፈጽመው" መረዳታችንን ከጳውሎስ ጋር መናገር እንችላለን፡፡

እ.ኤ.አ በ1650 ጄረሚ ቴይለር *The Rules and Exercises of Holy Living (የቅዱስ አኗኗር መመሪያዎችና ልምምዶች)* የተሰኘ መጽሐፍ ጻፈ፡፡ በዚያም መጽሐፍ ስለ ጸሎት ይህንን ተናገረ፤

> እግዚአብሔር [የጸሎት ኀይልን] በሰዎች እጅ ውስጥ አደረገው፣ የሰዎች ጸሎትም ከተሞችና መንግሥታትን ከጥፋት አድኗል፤ ጸሎት ሙታንን ወደ ሕይወት አስነሥቷል፤ የእሳትን ኀይል አጥፍቷል፤ የአራዊትን አፍ ዘግቷል፤ የተፈጥሮን ሂደት ቀይሯል፣ በግብፅ እንዳይዘንብና በባሕሩ ላይ ድርቀት እንዲ መጣ አድርጓል፡፡ ጸሎት አማልክትን ሁሉ ይገዛል፤ ፀሓይን በመንገዷ አሥሮ በጨረቃ ሰረገላ መንኰራኲር ይቈያል፤ ደካማ አካላችንን ከሚደርስብን የጥቃትና የስደት ሰቆቃ ጋር ያስታርቀዋል፡፡ እግዚአብሔርን እያስደሰተ የሚያስፈልገንን ሁሉ ይሞላል፡፡



ማስታወሻ


1. Huber Drumwright, *Prayer Rediscovered* (Nashville: Broadman Press, 1978) 61-63.
2. John Stott, *Involvement: Being a Responsible Christian in a Non-Christian Society* (Old Tappan, NJ: Fleming H. Revell Company, 1984) 105.

## ፲ - ለኢአማንያን እየጸለያችሁ ነው?

# ለጠፉት መጸለይ

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንድ የታወቀ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስለ ጸሎት ተከታታይ ትምህርት እንድሰጥ ተጋበዝኩ፡፡ በጥያቄአቸው መሠረትም ላቀርብ ያሰብኳቸውን አምስቱንም መልእክቶች የያዘ የእጅ ጽሑፍ ማስታወሻ ላኩሁላቸው - ከእነዚህም አንዱ "ለጠፉት መጸለይ" የሚል ነበር፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ከኮሌጁ ጸሎት ቤት የትምህርት ኮሚቴ አባላት በአንዱ የተጻፈ፣ "ለጠፉት ስለ መጸለይ" የሚናገረውን መልእክት በሌላ እንድለውጥ የሚጠይቅ ደብዳቤ ደረሰኝ፤ እንደተባልኩትም አደረግሁ፡፡ ለጠፉት መጸለይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም የሚለው አቋም በትምህርት ቤቱ ፕሬዚዳንት የተያዘ የታወቀ አቋም ነው፡፡

እርሱና እኔ ርዕሰ ጉዳዩን የምንወያይበት ዕድል ባለማግኘታችን ሁልጊዜም እጸጸታለሁ፤ ምክንያቱም ልዩነቱን የፈጠረው በዋናነት የቃላት አተረጓጐም እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡ ተወያይተንበት ቢሆን ኖሮ የምናገርበት ርዕስ ይህንን ምዕራፍ ነበር የሚመስለው፡፡

### ለጠፉት መጸለይ እንችላለን?

የሐንስ 17 ላይ ያለው የኢየሱስ ጸሎት ለጠፉት መጸለይ እንደሌለብን ብዙ ጊዜ በማስረጃነት ይጠቀማል፡፡ በጸሎቱ ውስጥ ኢየሱስ፣ "እነርሱ የአንተ ስለ ሆኑ እጸልይላቸዋለሁ፤ ለሰጠኸኝና የአንተ ለሆኑት እንጂ ለዓለም አልጸልይም" ብሏል (ቍጥር 9 - አ.መ.ት)፡፡

ክርክሩ የተመሠረተው፣ ሰዎች ስለ ጉዳዩ አስቀድመው ከያዙት አመለካከት የተነሣ እንጂ ከፍሉ በሚለው ሐሳብ ላይ አይደለም፡፡ በዚያን ወቅት ኢየሱስ እየጸለየ ያለው ስለ ተከታዮቹ እንጂ ስለ ዓለም አልነበረም፡፡ ፈጽሞ ለዓለም መጸለይ ተገቢ እንዳልሆነ የሚጠቁም አንድም ነገር በዚህ ጸሎት ውስጥ አልቀረበም፡፡ በወቅቱ ኢየሱስ ለዓለም አልጸለየም፤ ነገር ግን ለዓለም መጸለይ እንደሌለብን አልተናገረም፡፡ እንዲያውም ከጥቂት ሰዓት



በኋላ፣ "አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" በማለት ከጠፋው ዓለም ስለ ተወሰነ ክፍል ጸሎት አቅርቧል፡፡

ላልዳኑት አይሁድ መጸለይ ለሐዋርያው ጳውሎስ ችግር አልነበረም፤ "ወንድሞች ሆይ፤ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው" (ሮሜ 10፥1)፡፡

በ፲ኛ ዮሐንስ 5፥14-15 ላይ ይህ ተስፋ ተሰጥቶናል፤

> በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል፡፡ የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመንነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን፡፡

እስቲ ይህን ተስፋ ከቀጣዮቹ ዐረፍተ ነገሮች ጋር አጣምሩት፡፡

> ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፤ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሓ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል፡፡ (2ጴጥ. 3፥9)

> እርሱ [እግዚአብሔር] ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ ይፈልጋል፡፡ (1ጢሞ. 2፥4 - አ.መ.ት)

የእግዚአብሔር ፈቃድ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የክርስቶስ የመስቀል ሞት እግዚአብሔር የማንንም መጥፋት ያለመውደዱን እውነታ አረጋግጧል፡፡ የጠፉት እንዲድኑ ስንጸልይ በተገለጠው የእግዚአብ ሔር ፈቃድ ውስጥ ነው፡፡ የጠፉት እንዲድኑ መጸለይ እንደሌለብን መናገር ግን እግዚአብሔር ትልቁን ሥራችንን እንድንሠራበት የሰጠንን ታላቅ ኀይል መካድ ነው፡፡

ሁልጊዜም እግዚአብሔር ፈቃዱን ለማከናወን ማላጆችን ይጠቀም ነበር፡፡ ምልጃ የእግዚአብሔር ቍጣ በግለ ሰቦች ወይም በሕዝብ ላይ ከመቃጠል እንዲዘገይ ከማድረግም በላይ እንዲቀር አድርጓል፡፡ በኢዮብ 42 ላይ እግዚአብሔር ኤልፋዝንና ሁለቱን ጓደኞቹን፣ "እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ" በማለት ወደ ኢዮብ ሄደው እንዲጸልይላቸው እንዲያደርጉ ይነግራቸዋል (ቍጥር 8)፡፡ የሙሴ ጸሎት ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ፍርድ ማዳኑን ቀደም ብለንም ዐይተናል፡፡ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ሲያጠፋ ሎጥን ያዳነው የአብርሃምን ምልጃ አስታውሶ ነው፡፡

አካል ጉዳተኛ ጓደኛቸውን ወደ ኢየሱስ ለማድረስ የሰገነቱን ጣራ የነደሉት ሰዎች "ማላጆች" ነበሩ፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፤

[ኢየሱስም] እምነታቸውን አይቶ "አንተ ሰው ኀጢአትህ ተሰረየችልህ" አለው:: (ሉቃ. 5፥20)

ኢየሱስ *እምነታቸውን* አየ:: ሰውዬው እምነት ያለው ስለ መሆኑ ምንም አልተነገረም:: ፈውሱን ያስገኘለት የጓደኞቹ እምነት ነበር::

ቀላል ሆኖ ጥልቁ እውነታ እግዚአብሔር ለጸሎት ምላሽ መስጠቱ ነው:: እግዚአብሔር ባንጸልይ ኖሮ የማያደርጋቸውን ነገሮች በመጸለያችን ምክንያት ያደርጋል (ምዕራፍ 2ን ተመልከቱ):: እግዚአብሔር እንዲህ ዐይነቱን ተወዳዳሪ የለሽ ልዩ መብትና እንዲህ ዐይነቱን ኀላፊነት በእጃችን ማኖሩ ከአእምሮ በላይ ቢሆንም - ይህንኑ ነው ያደረገው:: በምልጃ በኩል እኛም ከዚህ በፊት፣ ፊት ለፊት አግኝተን ለማናውቃቸው ሰዎች የድነት መሣሪያ ልንሆን እንችላለን:: በአንድ ቅጽበት እጅግ በራቁ የምድር ጥጋ ጥጎች ላይ ሚሲዮናዊ መሆን እንችላለን:: በምልጃ ከንዶች ዓለምን ይዘን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ልናነሣትም እንችላለን::

## መፈለግና ማዳን

ኢየሱስ፣ "የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና" በማለት ሲናገር (ሉቃ. 19፥10) ምን ማለቱ ነው? ይህም፣

> ያልዳነን ሰው ከማመልከት ያለፈ መሆን አለበት፤ በየስፍራው ሞልተዋልና:: ሐረጉ ... ያልዳኑትን ለድነት አስፈላጊ ከሆኑ ሁኔታዎች ጋር ወደ መቀራረብ ለማምጣት ስለሚደረግ መለኮታዊ ዝግጅት የሚያመላክት ነው::[1]

## ላልዳኑት መለኮታዊ ዝግጅት

ይህ በፊልጶስና በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ታሪክ ውስጥ ታይቷል (የሐዋ. 8፥26-40):: ኢትዮጵያዊው ለአምልኮ ከሄደበት ከኢየሩሳሌም እየተመለሰ የነበረ ሲሆን፣ በሰረገላው ተቀምጦ በኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ ስላለው መከራ የሚቀበል አገልጋይ እያነበበ ነበር:: ልክ በዚያው ቅጽበት (እርሱ ሲሮጥ ሳለ ያኛው እያነበበ ነበር) ፊልጶስ መንፈስ ቅዱስን ታዝዞ ሰውዬውን ተገናኘና የሚያነብበውን ያስተውለው እንደ ሆነ ጠየቀው:: አሁን ይህንን ነው ዝግጅት የምለው:: ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ከማየቱ በፊት፣ ሰውዬውን እንዲያገኘው መንፈስ ቅዱስ ሳይነግረው በፊት እንኳ ስለ ኢየሱስ እንዲሰማ እግዚአብሔር የሰውዬውን ልብ ሲያዘጋጀው ነበር:: ልክ ሰውዬው ዝግጁ ሲሆን ሥራውን እንዲያጠናቅቅ እግዚአብሔር ፊልጶስን ላከው::



የመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ታሪክም ተመሳሳይ ነው (የሐዋ. 10፥1 ጀምሮ):: ጴጥሮስ እንዲሄድ እግዚአብሔር ትእዛዝ ያስተላለፈው ቆርኔሌዎስ ወንጌሉን ለመስማት ዝግጁ ከሆነ በኋላ ብቻ ነው:: እንዴት እንደሚድን ጴጥሮስ ከመንገሩ በፊት ቆርኔሌዎስ ለመዳን ተዘጋጅቶ ነበር::

ለድነት ማዘጋጀት የድነት ሥራ አካል ነው:: ለተሰሎንቄ ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ይላቸዋል፤

> እኛ ግን በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፤ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፤ እግዚአ ብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና:: (2ተሰ. 2፥13)

የሐረጎቹን ቅደም ተከተል አስተውሉ፤ በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን ... መርጦአችኋልና:: በወንጌል ማመን በመንፈስ ቅዱስ ከመቀደስ መቅደም የለበትምን?

እዚህ ጋ መቀደስ ከድነት በፊት የመጣበት ምክንያት ጳውሎስ ስለ አማኞች መቀደስ ሳይሆን ስለ ኀጢአተኞች መቀደስ እያወራ በመሆኑ ነው:: ይህም የአንድን ያልዳነ ሰው ዙሪያ ገብ የሚያከብበት፣ ለይቶ የሚያወጣበትና በዚህም "አሁን የአንተ ጊዜ ነው" የሚልበት የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ነው::

በእግዚአብሔር መኖር የማያምን አንድ የኮሌጅ ተማሪ ድንገት ያጋጠሙት ጥቂት ክርስቲያን ተማሪዎች ስለ እምነታቸው በብርቱ ሲመ ሰክሩለት እንደ ነበር የሚያብራራ ደብዳቤ ለሲ ኤስ ሊዊስ ጻፈለት:: እነዚህ ተማሪዎች ሲናገሯቸው የነበሩት አንዳንድ ነገሮች ረብሸውታል፤ ስለዚህ በከባድ ትግል ውስጥ እያለፈ ነው:: ዶ/ር ሊዊስ ስለዚህ ጉዳይ ያለውን አመለካከት ማወቅ ፈልጓል:: ሊዊስም እንዲህ ብሎ ጻፈለት፤ "አብቅቶልሃል፤ እኔ እንደማስበው መረቡ ውስጥ ገብተህ ተጠላልፈሃል እኮ - መንፈስ ቅዱስ እየተከታተለህ ነው:: ታመልጣለህ የሚል ጥርጥር የለኝም::"

ድነት እንዲሁ ራሱን አይከስትም:: "የእሳት ሰረገላው ዝቅ ብሎ እያንዳንዱን በየተራ ብድግ እያደረገ ወደ ክብር አይወስድም::"[2]

ተመሳሳይ ሐሳብ በ1ኛ ጴጥሮስ 1፥2 ላይ እናገኛለን:: ጴጥሮስ የተበተኑትን መጻተኞች፣ "እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት" በማለት ይገልጻቸዋል::

እዚህም እንደገና የሐረጎቹ ቅደም ተከተል ወሳኝ ነው:: "በመንፈስም እንደሚቀደሱ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመ ረጡት":: መታዘዝና ደም መረጨት ከመቀደስ እንደሚቀድሙ እናስባለን:: ግን አሁንም ድነትን ከሚከተለው የአማኙ ቅድስና ይልቅ ድነትን ስለ ሚያመጣው ቅድስና ነው ጴጥሮስ እየተናገረ ያለው:: ምልጃ በዚህ መለኮታዊ ተውኔት ላይ ዐቢይ ሚና ይጫወታል::

ለጠፉት በምንጸልይበት ጊዜ የሚያግዙን አንዳንድ ነገሮች ከዚህ ቀጥለው ቀርበውልናል:: እነርሱም የምንማልድባቸው ዐውዶች ናቸው::

## ኀጢአተኛው ያለበት ሁኔታ

**1. የጠፋው ሰው በዚህ ዓለም አምላክ የታሰረ ነው::** የወንጌል *ሥርጭታችን* በስብከትም ይሁን በጸሎት ይህንን እውነታ ታሳቢ ማድረግ አለብን:: እስቲ አግባብነት ያላቸውን አንዳንድ ጥቅሶች እንይ::

> እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን እንደሚሰጣቸው ተስፋ በማድረግ የሚቃወሙትን በየዋሕነት የሚያቃና መሆን ይኖርበታል:: ይኸውም ወደ አእምሮአቸው ይመለሳሉ፤ *ፈቃዱን ሊያስፈጽማቸው ምርኮኛ አድርጎ ከያዛቸው ከዲያብሎስ ወጥመድም ያመልጣሉ* በማለት ነው:: (2ጢሞ. 2፥25-26 - አ.መ.ት - አጽንኦት የተጨመረ)

ሰዎች በሰይጣን "ከነነፍሳቸው ታግተዋል" (የግሪኩ ቃል ትርጉም)፤ በእርሱ ምርኮኛነታቸውም የፈቃዱ እስረኞች ናቸው:: ብቸኛ ተስፋቸው ንስሓን እግዚአብሔር የሚፈቅድላቸው ከሆነ ነው::

> ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፤
>
> *በማይታዘዙት ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፣* በፊት ተመላለሳችሁባቸው:: (ኤፌ. 2፥2 - አጽንኦት የተጨ መረ)

እዚህ ጋ "ለሚሠራው" የሚለው የግሪክ ቃል በቁሙ ሲተረጐም "ኀይል መስጠት" ማለት ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ የሚያደርገ ውን እንቅስቃሴ በሚገልጥ መልኩ በሌሎች ስፍራዎችም ጥቅም ላይ ውሏል:: ያላመነው ሰው በዲያብሎስ መንፈስ ኀይል የሚሰጠው ነው:: በእርግጥ፣ ያላመነ ሰው ይህንን አያውቅም፤ ቢያውቅ ኖሮ አይፈልገውም ነበር:: ነጻ እንደ



ሆነ ያስባል (ይህም የመጥፋቱ አንድ መገለጫ ነው)፤ በእውነቱ ግን እርምጃዎቹ በአየሩ አለቃ ኀይል ተገድዶ የሚፈጽማቸው ናቸው::

በ1ኛ ዮሐንስም፣ "ከእግዚአብሔርም እንደ ሆንን ዓለምም በሞላው በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን" ይላል (5፥19)::

መዝገበ ቃላት የሆንኩ ከመሰልኩ ይቅርታ አድርጉልኝ፤ ነገር ግን "እንደ ተያዘ" ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል ልጇ ወደ እንቅልፍ ይሄድ ዘንድ በክንዶቿ እቅፉ የምታወዛውዝ እናት ምስል ነው ያለው:: የጠፉት ነፍሳት ጉልህ ምስል ይህ ነው - በጸጥታ ወደ እንቅልፍ እንዲሄዱ በረዳት የለሽነትና በተስፋ ቢስነት በሰይጣን ክንዶች ታቅፈዋል::

> ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤
>
> ብርቱ ሰው በሚገባ ታጥቆ ቤቱን ከጠበቀ፣ *ንብረቱ በሰላም ይቀመጣል::* ነገር ግን ይበልጥ ብርቱ የሆነ ሰው መጥቶ ካጠቃውና ካሸነፈው ታምኖበት የነበረውን ትጥቁን ያስፈታዋል፤ ምርኮውንም ወስዶ ለሌሎች ያካፍላል (ሉቃ. 11፥21-22 - አ.መ.ት - አጽንኦት የተጨመረ)::

በዚህ ምንባብ ኢየሱስ በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል አጋንንትን ያስወጣል በሚል ለቀረበበት ክስ ምላሽ እየሰጠ ነበር (ከሉቃስ 11፥14 ጀምሮ):: በኢየሱስ ምላሽ ውስጥ ሁለት ነገሮች በተለይ ትኩረት ይሻሉ::

> አንደኛ፣ ሰዎች የተገለጹት፣ ሰይጣን እንዳያመልጡት በንቃት የሚጠብቃቸው ንብረቶቹ ተደርገው ነው፤
>
> ሁለተኛ፣ ኢየሱስ እነዚህን ምርኮኞች ነጻ ከማውጣቱ በፊት ማራኪያቸውን ሰይጣንን ትጥቅ ማስፈታት አለበት:: ይህን በአእምሮአችን ብናኖረው ይጠቅመናል::

ለጠፋ ሰው ስንጸልይ የሰውዬውን ፈቃድ እያስገደድን አይደለም፤ ፈቃዱን ከሰይጣን እስር *እያስለቀቅን እንጂ::*

**2. የጠፋው ሰው ለወንጌል በዚህ ዓለም አምላክ የታወረ ነው::** እስቲ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚለውን እናድምጥ፤

> ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው:: ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው *የዚህ ዓለም አምላክ*

> *የማያምኑትን ሐሳብ አሳወረ፡፡* (2ቆሮ. 4፥3-4 - አጽንኦት የተጨመረ)

ያልዳነ ሰው ራሱን እንደ ጠፋ ኀጢአተኛ የመመልከት ወይም የወንጌሉን መልእክት የመረዳት ዐቅም የለውም፡፡ ሰይጣን መንፈሳዊ መታወር አድርሶበታል፡፡ ጳውሎስ ይህንን ይነግረናል፤

> ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም፡፡ (1ቆሮ. 2፥14)

ያልዳነ ሰው አእምሮ ላይ የተጋገረውን ጨለማ ምንም ዐይነት ሰዋዊ ኃይል፣ አመክንዮም ሆነ ሙግት ጥሶት ሊገባ አይችልም፡፡ ያምን ዘንድ የድነትን መንገድ በቀላሉ ልናስረዳው አንችልም፡፡ ዲያብሎስ አንድን ሰው ከድነት ለማስቀረት ሰካራም፣ ወይም ነፍሰ ገዳይ ማድረግ አይኖርበትም፡፡ ለክርስቶስ ወንጌል የታወረ አድርጎ ማስቀረት ብቻ ነው የሚያስፈልገው፡፡

**3. የትኛውም ሰው ለመዳን ከሙብቃቱ በፊት፣ ይህ የዲያብሎስ (1) እስር እና (2) መታወር መሸነፍ አለበት፡፡** ነጻ መውጣትና አብርሆት መኖር አለበት፡፡ አስቀድመንም እንዳየነው፣ ኢየሱስ ምርኮኞቹን ከማስለቀቁ በፊት ከዲያብሎስ ጋር ያለውን ጉዳይ መወጣት (መጨረስ) ይኖርበታል፡፡

ይህም ለጠፉት በመጸለይ ውስጥ ልናስተውለው ወደሚገባን ቀጣይ እውነት ይወስደናል፤

## የሰይጣን ድል መነሣት

ዲያብሎስ የተሸነፈ ጠላት ነው፡፡ ሽንፈቱም ሁለት ገጽታ እንዳለው አዲስ ኪዳን በግልጽ ያስተምራል፡፡ *መጀመሪያ*፣ ፍጹማዊ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ኀይለኛውን ሰው (ዲያብሎስን) እንዳሰረው አስቀድመን በሉቃስ 11 አይተናል፡፡ ሌላ የሚያግዘን ምንባብም በዕብራውያን 2፥14-15 ውስጥ እናገኛለን፤

> እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞቱ እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስን ነው፤ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሀት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ፡፡

> ሌላ ምንባብ እንዲህ ይላል፤



> ኀጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፤ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኀጢአትን ያደርጋልና፡፡ ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ፡፡ (1ዮሐ. 3፥8)

> በቈላስይስ ውስጥ ደግሞ ስለ ክርስቶስ እንዲህ እናነብባለን፤

> በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፤ አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፣ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው፡፡ (2፥14-15)

የዚህ ምንባብ ቋንቋ ጦርነትን አሸንፈው የሚመጡ የሮማ ጄኔራሎች ከሚያደርጉት ወታደራዊ ሰልፍ የተወሰደ ነው፡፡ ጠላትን ካሸነፈ በኋላ አሸናፊው የጦር መሪ የተሸናፊውን ጦር መኮንኖች ከሰረገላው ጋር በሰንሰለት አስሮ እየጎተተ ወደ ሮም ያመጣቸዋል፡፡ ድል ማግኘታቸውን ለከተማዪቱ ያበስር ዘንድም አንድን ሯጭ አስቀድሞ ይልካል፤ እናም ሕዝቡ ከመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰልፎ ትዕይንቱን ለማየት ይጠብቃል፡፡

በነገራችን ላይ፣ ሯጩ ምን እየሠራ እንደ ሆነ ታውቃላችሁ? እየሰበከ ነው፡፡ "የምስራች አብሳሪ"ን፣ እና ዐዋጅ ነጋሪን ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውለው ቃል ነው ስብከትንም ለማሳየት የዋለው፡፡ የምስራቹ ድል ማግኘቱ አይደለም፤ ከተገኘ የቈየውን ድል መመስከር ነው፡፡

በመጨረሻ መለከት እየተነፋ፣ ዜጎች ሆታ እያሰሙ፣ የአበባ ጉንጉን እየታደለ፣ ድል አድራጊው ጀግናም በነጫጭ ፈረሶች በሚሳብ ሰረገላ ተቀምጦ ድል ነሺው ሠራዊት እየተጓዘ ይደርሳል፡፡ ከበስተኋላም ከእነርሱ ሩጫ ጥቂት ፈጠን ከሚለው ሰረገላ ጋር የታሰሩት የተሸናፊው ጦር መሪዎች - እየወደቁ፣ እየተነሡ፣ መሬት ላይ እየተጎተቱ ይደርሳሉ፡፡ አሸናፊው ጠላቶቹን በማድቀቅ ብቻ ሳይሆን በግልጥ እያዞረ ለሕዝብ በማሳየት ያዋርዳቸዋል፡፡

ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ሲሞት ሰይጣንን ከነመላ ዐማፅያኑ አሸንፎታል፤ ሞትን ድል አድርጎ ሲነሣም በግልጥ (በአደባባይ) እያዞረ አሳይቷቸዋል፡፡ የሰይጣን ሽንፈት ፍጹማዊ ነው፡፡

"እሺ እንዲህማ ከሆነ ከእርሱ ጋር እንዲህ ዐይነት ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ የገባሁት እንዴት ነው? ዲያብሎስ የታሰረ ከሆነ፣ የታሰረበት ሰንሰለት እጅግ በጣም ረጅም መሆን አለበት፤ ወይም•የታሰረው ከእኔ ጋር ይሆናል፡፡ ለመሆኑ ለሰይጣን ሽንፈቱ እንዲነገረው ተደርጓል? ሽንፈቱን ያወቀ እኮ አይመስልም" ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል፡፡ ጥሩ ጥያቄ ነው፣ ጥሩ መልስም አለው፡፡

የሰይጣን ሽንፈት ፍጹማዊ ቢሆንም፣ ለጊዜው - እግዚአብሔር በታሪክ ላይ ያለውን መጋረጃ እስኪገልጥ ድረስ - ከሽንፈቱ ጋር የተያያዘውን ሁለተኛ ነገር መፈጸም ይገባል፡፡ ይኸውም ሽንፈቱን በቅጡ ተረድተን በተገቢ መልኩ ልንገልጽ የተገባን መሆኑ ነው፡፡ ይህ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ላደረገልን ለእያንዳንዱ ነገር እውነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን በአግባቡ መውሰድ አለብን፡፡[3]

ማቴዎስ 18፥18ን ተመልከቱ፤

> እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡፡

ምልከታችንን ከሰማይ መውሰድ ነው ያለብን፡፡ በሰማይ የታሰረውን የትኛውንም ነገር በምድርም እናስረዋለን፡፡ በሰማይ የተፈታውን ደግሞ በምድር እንፈታዋለን፡፡ ነገሮችን ከሰማይ የዕይታ አቅጣጫ ማየት አለብን፡፡ እናም አሁን ከሰማይ የዕይታ አቅጣጫ ሲታይ ሰይጣን ታስሮአል? አዎን፡፡ ከሰማይ የዕይታ አቅጣጫ ሲታይ የሰይጣን ባሮች ተፈትተዋልን? አዎን፡፡ በፍጹማዊነት፡፡

ያዕቆብ ስለዚህ ጉዳይ ትክክለኛ ምስል ይሰጠናል፤ "እንግዲህ ለእግዚ አብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ፤ ከእናንተም ይሸሻል" (4፥7)፡፡

አሁን፣ እስቲ እናጠቃልለው፡፡ ያልዳኑቱ በባርነት እንደ ታሰሩና ለወንጌል እንደ ታወሩ፣ ይህንንም ያደረገው ዲያብሎስ መሆኑን እስካሁን ተነጋግረናል፡፡ ስለሆነም የትኛውም ሰው ከመዳኑ በፊት ነጻ መውጣትና አብርሆት ማግኘት አለበት፡፡ አሁን ይህ የሚቻል ነገር ነው፤ ምክንያቱም ያንን ሰው ያሰረውና ያሳወረው ዲያብሎስ በክርስቶስ ተሸንፎ ኃይል አልባ ተደርጓልና፡፡ ይህም ወደ ቀጣዩ ሐሳብ ያመጣናል፡፡

## የክርስቶስ መስቀል

በክርስቶስ የተገኘው ስርየት ምልጃ የሚያርፍበት ዋነኛ አዕማድ ነው፡፡ 1ኛ ዮሐንስ 2፥1-2 እንዲህ ይላል፤

> ልጆቼ ሆይ፤ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ፡፡ ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰርያ ነው፤ ለኃጢአታችን ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ፡፡



ማስተሰርያ ማለት "የስርየት መሥዋዕት" ወይም "መሸፈኛ" ማለት ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ በመስቀሉ ላይ ኃጢአታችንን በደሙ ሸፍኖአል፤ ነገር ግን የእኛን ብቻ ሳይሆን በዓለም ያሉትን ሰዎች ኃጢአት ሁሉ ነው፡፡ እርሱ "የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" ነው (ዮሐ. 1፥29)፡፡ እዚህ ጋ አንድ ሰው፣ "በእግዚአብሔር የተመረጡ ሰዎች ብቻ ኃጢአታቸው ይሰረይላቸዋል በሚለው የውስን ስርየት አስተምህሮ ነው የማምነው" በማለት ይናገር ይሆናል፡፡ ሆኖም መርሑ ተመሳሳይ ነው፤ የተመረጡት የሚድኑበት መሠረት የክርስቶስ የስርየት ሥራ ነው፡፡ ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት ወደ ሲኦል አይወርዱም፤ ሲኦል የሚወርዱት በክርስቶስ የተደረገውን ስርየት ሳይቀበሉ በመቅረታቸው ነው፤

> ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፣ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና፡፡ በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል፡፡ (ዮሐ. 3፥17-18 - አጽንኦት የተጨመረ)

የጠፋው ሰው ለምን ይኰነናል? ስለሚሰርቅ፣ ስለሚሳደብ ወይም ስለሚሰክር ነው? አይደለም፡፡ የሚኰነነው ባደረገው ነገር አይደለም፤ *ባላደረገው እንጂ፡፡ አላመነም፡፡* ያላመኑ ሙታን የመጨረሻ ፍርድ ምን እንደሚመስል ምስሉን በራእይ መጽሐፍ እናገኛለን፤

> *ሙታንን ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፤ መጻሕፍትም ተከፈቱ፡፡ ሌላም መጽሐፍ፣ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ተከፈተ፡፡ ሙታንም በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው መሠረት እንደ ሥራቸው መጠን ተፈረደባቸው፡፡ ባሕርም በውስጡ የነበሩትን ሙታን ሰጠ፤ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ውስጥ የነበሩትን ሙታን ሰጡ፤ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተፈረደበት፡፡ … ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ተጣለ፡፡* (ራእይ 20፥12-15 - አ.መ.ት - አጽንኦት የተጨመረ)

ያልዳኑት ሙታን እንደየሥራቸው ሲፈረድባቸው፣ ወደ እሳት ባሕር በሥራቸው ምክንያት እንዳልተጣሉ አጢኑ፡፡ የሰዎች ሥራ የተመዘገበባቸው መጻሕፍት የተከፈቱት የሰዎቹን የድነት አስፈልጎት ለማረጋገጥ ነው፡፡ ወደ እሳት ባሕር የተጣሉት በሕይወት መጽሐፍ ላይ ስማቸው ስላልተጻፈ ነው፡፡ ምንም ዐይነት መጥፎ ነገር ቢመዘገብባቸው ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ላይ ከተጻፈ ከዘላለማዊ ቅጣት ያመልጣሉ፡፡

ለጠፉት የመጸለይ መብታችን ክርስቶስ የኀጢአታቸውን ዋጋ በደሙ በመክፈሉ እውነታ ላይ የተመሠረተ ነው:: በመብት ደረጃ የእርሱ በሆነው ነገር ላይ ነው የይገባኛል ጥያቄ እያቀረብን ያለነው::

በቴክሳስ ግዛት ባለው ፎርት ዎርዝ ከተማ የሚገኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪ ሳለሁ በታሕሳስ ወር ፍሎሪዳ ውስጥ ለአንድ ሳምንት በተካሄደ ኮንፈረንስ ላይ በስብከት አገለገልኩ:: ሚስቴና የሁለት ዓመት ወንድ ልጄ ወላጆቿን ሊጠይቁ አርካንሳስ ሄደዋል:: አገልግሎቴን ስጨርስ ደግሞ ያሉበት ድረስ ሄጄ አገኘኋቸውና ተመልሰን በዚያ የታሕሳስ ብርድ ወደ ፎርት ዎርዝ ደረስን:: ወደ ቤት ስንገባም ውስጡም የውጭውን ያህል ይበርዳል:: የቤት ማሞቂያው ጋዝ አቅርቦት እንደ ተቋረጠ ለመረዳት ብዙ ጊዜ አ ልወሰደብኝም:: ሚስቴና ልጄ በብርድ እየተንዘፈዘፉ ስልኩን አንሥቼ ወደ ጋዝ አቅራቢው ኩባንያ ደወልኩና ምን እየተካሄደ እንደ ሆነ ጥያቄ አቀረብኩ ላቸው:: በስመ አብ! ብርዱ ሊገድለን ደርሶ ነበር::

አንድ እንደ አየሩ የቀዘቀዘ ድምፅ መለሰልኝ፤ "ይኸውሎት አቶ ደን፤ ያለፈውን ወር ክፍያ አልከፈሉም:: ልናገኝዎትም አልቻልንም፤ ለዚህ ነው የጋዙን መስመር የቈረጥነው::"

"ግን እኮ ከፍያለሁ" አልኩኝ::

"አዝናለሁ፤ ስለ መክፈልዎ የሚናገር አንድም ነገር የለም" በማለት በረዷማው ድምፅ መለሰ:: "ስለዚህ የጋዙን መስመር መልሰን ከመክፈታችን በፊት ነገ ቢሮአችን ድረስ መጥተው መክፈል አለብዎት::"

"አንዴ ቆየኝ" አልኩኝ:: ስልኩን አስቀመጥኩና ጠረጴዛዬን እያራ ገፍኩ መፈለግ ጀመርኩ:: ምን እንደምፈልግ ታውቃላችሁ? ተከፍሏል የሚል ማሕተም ያለበትን የኩባንያውን የከፍያ ደረሰኝ:: ደግሞም አገኘሁት:: የክፍያ ማረጋገጫዬን ይዤ፣ የስልኩን እጀታ ዘልዬ አነሣሁና ጋዙ እንዲቀጠልልኝ፣ ይህም አሁኑኑ እንዲፈጸም ለባለ በረዶ ድምፁ ተናገርኩ:: ብዙም ሳይቈይ ተቀጠለ::

ክርስቶስ ደሙን ሲያፈስ ለጠፉ ነፍሳት ቤዛ ከፈለ:: እግዚአብሔርም በሦስተኛው ቀን ከሙታን ሲያስነሣው ደረሰኙ ላይ ሙሉ በሙሉ ተከፍሏል ብሎ አተመበት::

እግዚአብሔር በልባችሁ ላኖረው ሰው በምትጸልዩበት ጊዜ፣ "ልትጸልዩለት መብት የላችሁም:: ንብረቴ ነው:: እርሱ የእኔ ነው" የሚል በረዷማ ድምፅ አንዳንዴ የምትሰሙበት ጊዜ ይኖር ይሆናል::



ያኔ ወደ ክፍያ ማስረጃው፣ ወደ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እያመለከታችሁ ያንን በረዷማ ድምፅ (ዲያብሎስን) እግዚአብሔር ንብረቱን እንዳሳሻገበትና ሙሉ በሙሉ እንደ ገዛው ልትነግሩት ትችላላችሁ::

ለጠፉት በኢየሱስ ስም ስንጸልይ ቀድሞውኑ ጌታ ኢየሱስ በደሙ የከፈለበት ደረሰኝ ላይ ነው የይገባኛል ጥያቄ የምናቀርበው:: "ያለ ምንም ጥርጥር በእንዲህ ዐይነት ጸሎት በልባችን ያሉትን ሰዎች መዳን እርግጠኛ እንሆናለን:: በኢየሱስ ስም መጸለይም ጠላት በሰው ፈቃድ ላይ ውጊያ ከሚያካሂድበት ሜዳ ጥሎ እንዲሄድና ያም ሰው በትክክል ለመምረጥ ነጻ እንዲሆን ያደርገዋል::"[4]


<u>ማስታወሻ</u>

1. Lewis Sperry Chafer, *The Evangelism* (Findley, Ohio: The Dunham Publishers Company, 1919) 3, 4.
2. John Eadie, *Thessalonians: A Commentary on the Greek Text* (Grand Rapids: Baker Book House, n.d.) 203.
3. For a discussion of this see, *The Faith Crisis* by Ronald Dunn (Wheaton, IL: Tyndale House Publishers, 1984), pp. 63-67. ተሻሽሎ በሌላ ርእስ የታተመው የዚህ መጽሐፍ ቅጂ *የእምነት ኃይል* በሚል ወደ አማርኛ ተመልሷል::
4. S. D. Gordon, *Quiet Talks on Prayer* (Old Tappan, NJ: Fleming H. Revell Company, 1967 reprint) 132.

# ክፍል ሦስት

# የሚጸለይ ሕይወት

በኩል ጭከና የመሰለው ነገር በእውነቱ ርኅራኄ መሆኑን በጭራሽ መገመት ያስቸግራል።

አንዳንድ ጊዜ የወይኑን አትክልተኛ በስሕተት እንገምተዋለን። ምናልባት በተመደበልን ቦታ ተቀምጠን፣ በወይኑ ተክል ላይ እየኖርን፣ መልካም ፍሬ እያፈራን ይሆናል፤ ድንገት ወደ ወይኑ ዕርሻ የሚገባ ከበድ ያለ ኮቴ እንሰማለን። ከዚያም፣ "የወይኑ አትክልተኛ መጥቷል፤ በእጁም መግረዣ መቀስ ይዟል" የሚለው ወሬ ወዲያውኑ በወይን ዕርሻው መኻል ይሰራጫል። ከዚያም አትክልተኛው ከፊት ለፊታችሁ ቆሞ፣ ያለ አንዳች ማብራሪያ፣ አንዳንድ ምርጥ አካላችሁን እየቈረጠ ማስወገድ ይጀምራል። በቅርባችሁ ያሉ ሌሎች የወይን ዛፎች ሊያበረታቷችሁ ይሞክራሉ፤ "ሁሉም ነገር ይስተካከላል" ይሏችኋል፤ "ለመልካም ይሆንላችኋል" ይሏችኋል፤ "ትለምዱታላችሁ" ይሏችኋል። እንደማትለምዱት ግን ታውቃላችሁ። የዓመቱ ምርጥ ፍሬያማ ቅርንጫፍ ተብላችሁ ከተሸለማችሁ በኋላ የወይኑ አትክልተኛ እንዲህ ዐይነቱን ጭካኔ የሚፈጽምበትን ምክንያት መረዳት ያቅታችኋል።

ሆኖም፣ ቅርንጫፍ ከሆናችሁ ግርዛት ከግዛት ጋር የተያያዘ ነው፤ ከሥራ ጋር የተያያዘ አደጋ ነው። ቅርንጫፎች መጠቀሚያ መሣሪያዎች እንጂ ጌጦች አይደሉም። እዚህ ጋ ግርዘት "ማጥራት" በሚል ቃል የተተረጐመ ሲሆን፣ ይህም ወይኑን በተመለከተ ሲወሰድ፣ "ለጊዜው የማያስፈልጉ ዕንጨቶችን በማስወገድ መግረዝ" ማለት ነው።

ግርዘቱን የሚያካሂደው አብ ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ቃል የመግረዣ መሣሪያው ነው (ዮሐ. 15፥3)። የቅርንጫፉን ዋነኛ ኀይል ፍሬ ከማስገኘት አቅጣጫ የሚያስቀይር በቅርንጫፉ ላይ ያለ የትኛውም ነገር ተቈርጦ ይወገዳል። አትክልተኛው መጥፎዎቹን ነገሮች ሁሉና ከጥሩዎቹም በርካቶቹን ይገርዛቸዋል። የመጥፎዎቹን መቈረጥ አስፈላጊነት ለጋዎቹ ቅርንጫፎች እንኳ ሊገነዘቡት ይችላሉ፤ በርካታ ጥሩዎች መቈረጣቸውና መወገዳቸው ግን ጭከናና አባካኝነት ይመስላል፤ አትክልተኛውም ግርዘቱን በማካሄድ የሚደሰት፣ በሥቃያችን የሚረካ ይመስላል። ያን ውብ ዕንጨት፣ እነዚያን ተወዳጅ ቅጠሎች ማስወገድ - ከምላ ጐደል ወንጀል ነው።

የወይኑ ጌታ ግን ጥቅም አልባ ዕንጨቶችን ብቻ ነው የሚያስወግደው። ዕንጨቱ ያማረ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ቦታ ከመያዙም በላይ፣ ሌላኛው ቅርንጫፍ ጣፋጭ ደወይን ፍሬዎችን እንዲያስገኝ የሚያስችለውን ውድ ማዕድንም ይሻማል።

2. መጽሐፍ ቅዱስን *በንቃት* አንብቡ:: አእምሮአችሁ ንቁና አዲስ የሚሆንበትን ጊዜ ምረጡ:: ለእግዚአብሔር ጥድፊያ ከበዛበት ቀናችሁ ላይ አንቅልፍ የተጫጫነውን ትራፊ አትስጡ::
3. መጽሐፍ ቅዱስን *በሥርዐት* አንብቡ:: ዘሌዋውያን 11፥3ን አንብባችሁ፣ ከዚያ ራእይ 5፥7ን ብታነብቡና ቀጥላችሁም መዝሙር 15፥4ን አንብባችሁ ግራ ብትጋቡ በመጽሐፍ ቅዱስ አታሳብቡ:: አንድ መጽሐፍ ምረጡና (ለምሳሌ፣ ፊልጵስዩስን) ከምዕራፍ አንድ፣ ቊጥር አንድ፣ ቃል አንድ ጀምሩና መላው መጽሐፍ እስኪያልቅ አንብቡ:: መጽሐፍ ቅዱስ በወጉ ሲነበብ በሚሰጠው ስሜትና ትርጒም ትደነቃላችሁ::
4. መጽሐፍ ቅዱስን *በተለያዩ አማራጮች* አንብቡ:: የተለያዩ ትርጒሞችን ተጠቀሙ:: ለአማርኛ አንባቢዎች የቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ትርጒም (1954)፣ የ1997 አዲስ ትርጒም፣ አዲሱ መደበኛ ትርጒም፣ ሕያው ቃል ትርጒምን እጠቁማለሁ::
5. መጽሐፍ ቅዱስን *በጸሎት* አንብቡ:: ዛሬ የምትኖሩበትን ነገር እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት:: ቊጥሮቹን (ጥቅሶቹን) ወደ ጸሎትና ምስጋና ቀይሩአቸው::
6. መጽሐፍ ቅዱስን *በሚጠባበቅ ልብ* አንብቡ:: የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁን እግዚአብሔር በቃሉ እንደሚገናኛችሁና እንደ ሚናገራችሁ በመጠባበቅ አድርጉት::
7. መጽሐፍ ቅዱስን *በታዛዥነት* አንብቡ:: የማንታዘዘው ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱሱ መጨረሻ ተከድኖ መደርደሪያ ላይ መቀመጥ ይሆናል:: መገለጥ ምላሽን ይሻል:: ታዛዥነት የየዕለቱ ጥሞና ከንቱ ሥርዐት እንዳይሆን ይጠብቃል::

የሚጸልይ ሕይወት "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት" የሚኖርበት ሕይወት ነው (ቈላ. 3፥16)::



## 10 - ለመጸለይና ጌታን ለመፈለግ ዐይነተኛው ሁኔታ

# ጾም:- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥናት

የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለሁ ቤተ ሰባችን ወደ አዲስ ቤት ተዛወረ:: ማድቤቱ ግድግዳ ላይ ከምድጃው በላይ በቀይ ቀለም የተጻፈ መፈክር ነበር፤ "የሰው ልቡ በሆዱ በኩል ነው" የሚል:: ዛሬ ዛሬ ምናልባት አንዳንዶች ጾታዊ መድልዎ የሚንጸባረቅበት አባባል ነው በማለት ቢያጣጥሉት እንኳ የያዘው እውነት ሚሊዮን ጊዜ ተደጋግሞ ተረጋግጧል:: ለነገሩማ፣ ዲያብሎስም ለሺዎች ዓመታት በዚህ መመሪያ ሲጠቀም ቈይቷል:: የሰው ልቡ በአካላዊ ፍላጎቱ በኩል መሆኑን ድሮ ነው የደረሰበት::

ሰው የተሰናከለበት የመጀመሪያው ፈተና ከአካላዊ ፍላጎቱ ጋር የተገናኘ ነበር::

> ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣ ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደ ሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ ሰጠችው፤ እርሱም በላ:: (ዘፍ. 3፥6 - አ.መ.ት)

ከዚያ ከመጀመሪያው የኀጢት ተሞክሮ በኋላ በምግብ ፍላጎት ላይ ያነጣጠሩ የማያቋርጡ ፈተናዎች ሲግተለተሉ ኖረዋል:: ኖኅ ከእግዚአብሔር ቊጣ ታላቅ መዳን ከሆነለት በኋላ አካላዊ ፍላጎቱን ያላግባብ ተጠቀመበትና ሰከረ:: ይስሐቅ ዔሳውን ከያዕቆብ ይልቅ ይወድ የነበረው ዔሳው ጥሩ አዳኝ ስለ ነበርና በበርካታ ጥሩ ጥሩ ምግቦች አባቱን ስለሚያንበሸብሸው ነበር:: እንዳለመታደል ሆኖ ዔሳውም ሆዱ አመዛዛኝነቱን እንዲጫነው ፈቀደና ብኩርናውን ለአንድ ሰሀን ምስር ወጥ ሸጠ::

ሐዋርያው ጳውሎስ እስራኤል ከግብፅ ካመለጠች በኋላ የፈጸመ ችውን ምንዝርና በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፥7 ላይ እንዴት እንዳብራራው ልብ በሉ:: ከስተቱን እንድዘግብ እኔ ብመረጥ ኖሮ የወርቁን ጥጃና በዚያን ቀን የተደረ

ጉትን መጥፎና አዋኪ ነገሮች እንደምጠቅስ አስባለሁ፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ግን እንዲህ አልነበረም፡፡ "ሕዝቡ ሊበሉና ሊጠጡ ተቀመጡ፤ ሊዘፍኑም ተነሡ" በማለት በቀላሉ ገልጾታል፡፡ እውነተኛው ምክንያት የወርቁ ጥጃ ሳይሆን የሰዎቹ ሥጋዊ ፍላጎት መሆኑን ያውቅ ነበር፡፡

በኢየሱስ የምድረ በዳ ፈተና ወቅት ዲያብሎስ የመጀመሪያውን ጥይት የተኮሰው በሰው ልጅ አካላዊ ፍላጎት ላይ ነው፤ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል" አለው (ማቴ. 4፥3)፡፡ በኋላ ደግሞ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች "ሆዳቸው አምላካቸው" ከሆኑ ሰዎች ራሳቸውን እንዲያጠኑ ያስጠነቅቃቸዋል (ፊልጵ. 3፥19)፡፡

## በብሉይ ኪዳን የጾም ጉልህ ድርሻ

በእነዚህና በሌሎች ምንባቦች ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በሰው መንፈሳዊ ሕይወትና በአካላዊ ፍላጎቱ መካከል ያለውን ግልጽ ግንኙነት ይገልጣል፡፡ እዚህ ጋ የሚታይ ሥርዐት ማጣት በሌሎች የሕይወት ዘርፎች ሥርዐት የማጣት ምልክት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጾም ብዙ የሚናገረው ለዚህ ይሆናል፡፡

በርካታ ክርስቲያኖች ጾም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ዐይነት ጉልህ ድርሻ እንዳለው ሲገነዘቡ ይደነቃሉ፡፡ ምናልባት ብዙዎቻችን የክርስቲያን ሕይወት አካል መሆኑን ፈጽሞ በቁም ነገር አላጤንነው ይሆናል፡፡ ከልክ ካለፈ ሕግ አጥባቂ ሃይማኖተኛነት ጋር ስለምናያይዘውም ለሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አግባብነት የሌለው አድርገን በተግባራችን ገሸሽ አድርገነዋል፡፡ ነገር ግን በምልጃ (ጸሎት) ጥልቅ እውነቶች ላይ በቁም ነገር የሚደረግ የትኛውም ጥናት ጾምን ችላ ማለትም ሆነ እንደ ጥቅም አልባ ማየት አይችልም፡፡ ስለዚህ አጠር ያለ ጥናት እናስከትላለን፡፡

ኤልያስ ከኤልዛቤል ጋር ካካሄደው ፍጥጫ በኋላ ለሕይወቱ መነቃቃትን ፍለጋ ለአርባ ቀናት የጾመበትን የኮሬብ ተራራ ጉዞ አደረገ (1ነገ. 19፥8)፡፡

የአስቴር ጾም ለሕዝቧ ባስገኘችው ነጻ መውጣት ላይ ጠቃሚ ሚና ተጫውቷል (አስ. 4፥16)፡፡

ዳዊትም ልጁን በሽታ ሲቀሥፈው ጾሟል (2ሳሙ. 12፥16)፡፡ ዳንኤልም የእግዚአብሔር ሰማያዊ መልእክተኛ የጠላትን መቋቋም ጥሶ በመምጣት ከእግዚአብሔር ዙፋን የተላከለትን መልስ እስኪሰጠው ድረስ እየጾመ ጸልዮአል (ዳን. 10፥3)፡፡ ዕዝራና ነህምያ በአገራዊ (ብሔራዊ) ቀውስ ወቅት ጾምን ዐውጀዋል (ዕዝራ 8፥21፤ ነህ. 1፥4)፡፡



## ጾም በአዲስ ኪዳን

ጾም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ በሉቃስ 2፥37 ላይ፣ "በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር" ተብሎ ስለ ነቢዩቱ ሐና ተዘግቧል፡፡ የዮሐንስ መጥምቁም እየጾመ ደቀ መዛሙርቱም እንደዚሁ እንዲያደርጉ አስተምሯል፡፡

ጌታ ኢየሱስም ጾሟል፤ ከተከታዮቹም ይህንኑ እንደሚጠብቅባቸው ግልጽ አድርጓል፡፡ ለምሳሌ፣ የማቴዎስን ስድስተኛ ምዕራፍ ውሰዱ፡፡ በዚህ ምዕራፍ፣ ትክክለኛውን ነገር በተሳሳተ መነሻ ሐሳብ ስለ ማድረግ ደቀ መዛሙርቱን አስጠንቅቋቸዋል፡፡ "የክርስትና ሕይወት ተሰባሪ ነውና ተጠንቀቃችሁ ያዙት፡፡ የልባችሁ ሐሳብ ንጹሕ መሆኑን አረጋግጡ" በማለት መክሮአቸዋል፡፡ ሳነሣው ሐሳብ ምሳሌ ለመስጠትም ሦስት ሃይማኖታዊ ተግባራትን በመውሰድ ከእግዚአብሔር ምስጋና ይልቅ የሰዎችን ምስጋና ለማግኘት እንዴት ሊፈጸሙ እንደሚችሉ አሳይቷል፡፡

የመረጣቸው ሦስት ተግባራት ምጽዋት መስጠት፣ ጸሎትና ጾም ናቸው፡፡ ቍጥር 16ን ልብ በሉ፤ "ስትጦሙ ..."፤ ከዚያም ቍጥር 17ን፣ "አንተ ግን ስትጦም ..."፡፡ *ስትጦሙ ... ስትጦም፡፡* ኢየሱስ፣ "ከጦማችሁ ... ከጦምህ" አላለም፡፡ ደቀ መዛሙርቱ እንዲጾሙ የተጠበቀ ነበር፡፡ በመሠረቱ፣ ኢየሱስ ጾምን እንደ ምጽዋት መስጠትና ጸሎት መደበኛ ሃይማኖታዊ ተግባር ያደርገዋል፡፡ የትኛውም የዘመኑ ክርስቲያን ምጽዋት መስጠት (በጎ ምግባር) እና ጸሎት ጊዜ ዐልፎባቸዋል አይልም፡፡ ጾምም እንዲሁ ነው፡፡ ኢየሱስ ከጸሎትና ከበጎ ምግባር ጋር አንድ መስመር ላይ አኑሮታል፡፡

በማቴዎስ 9፥14-15 ላይ ይህን እናገኛለን፤

> በዚያን ጊዜ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ቀርበው "እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ የምንጦመው፣ ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጦሙት ለምንድን ነው?" አሉት፡፡ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፤ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ፡፡"

ኢየሱስ በአካል በደቀ መዛሙርቱ መካከል ሳለ መጾም አያስፈል ጋቸውም ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስ ከዓለም ሲወሰድ የጾም ጊዜ ይመጣል፡፡ ዛሬ፣ ሙሽራውን እየጠበቅን ሳለ ጾም የሚያስፈልግባቸው ጊዜአት አሉ፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ የኢየሱስን ጌትነት ከተቀበለ በኋላ ወዲያውኑ ለሦስት ቀናት ጾመ (የሐዋ. 9፥9)። ጾም የሕይወቱና የአገልግሎቱ ቋሚ አካል ነበር። ለቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ግል አገልግሎቱ ሲጽፍላቸው እንዲህ ይላቸዋል፤

> ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን፤ በብዙ መጽናት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በወኅኒ፣ በሁከት፣ በድካም፣ እንቅልፍ በማጣት፣ *በመጦም* (2ቆሮ. 6፥4-5 - አጽንኦት የተጨመረ)

ከዚያም እንደገና በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፥27፣ "በድካምና በጥረት፣ ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፣ በራብና በጥም፣ ብዙ ጊዜም በመጦም ... ነበርሁ" በማለት ተናግሯል።

የሐዋርያት *ሥራ* መጽሐፍ ጾም የሊጋዋ ቤተ ክርስቲያን ወሳኝ አካል እንደ ነበረ ያሳያል።

> እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፣ "በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው *ሥራ* ለዩልኝ" አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ፣ ከጸለዩም፣ እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው። (የሐዋ. 13፥2-3)

የሐዋርያት *ሥራ* 14፥23 የጳውሎስንና የበርናባስን አዲስ የተመሠረቱትን ማኅበረ ምዕመናን የማጠናከር ሚሲዮናዊ ተልእኮ ያብራራል፤

> በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ ጦመውም ከጸለዩ በኋላ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው።

## የጾም ብያኔ

የዕብራይስጡ ቃል "አፍን መሸፈን" የሚል ትርጉም ሲኖረው፣ የግሪኩ ቃል ደግሞ "አለመብላት" ማለት ነው፤ ጾም ግን ከመራብ እጅግ ያልፋል። በመሠረቱ፣ ጾም ከምግብና ውሃ ጋር ብቻ የተቆራኘ አይደለም፤ እነዚህ ዋና መገለጫዎቹ ቢሆኑም። ባልና ሚስት ራሳቸውን ለጸሎት በሙላት ለመስጠት በጋራ ስምምነት ከግብረ *ሥጋ* "መጾም" ይፈልጉ ይሆናል (1ቆሮ. 7፥5)።

ይህን ፍች እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ፤ *ጾም በመንፈሳዊ ምክንያቶች ከተወሰኑ አካላዊ ፍላጎቶች በፈቃደኝነት ራስን ማቀብ ነው።* አብዛኛውን ጊዜ ጾም ከምግብና ከመጠጥ መታቀብ ሲሆን፣ ሌሎች ነገሮችንም ሊያካትት ይችላል።



## የተለያዩ ዐይነት አጽዋማት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ተለያዩ ዐይነት አጽዋማት (ጾሞች) ይናገራል። አንዳንድ አጽዋማት *የአደባባይ (በይፋ የሚደረጉ)* ናቸው። የነነዌ ንጉሥ የነቢዩ ዮናስን ትንቢታዊ መልእክት ከሰማ በኋላ ከተማ አቀፍ ጾም ዐወጀ፤ እንስሳቱን እንኳ ከምግብና ከመጠጥ ከለከለ (ዮናስ 3፥5-10)። ነቢዩ ኢዩኤል የጌታን ምሕረትና መንፈሳዊ መነቃቃት ፍለጋ ለአገር አቀፍ ጾም ጥሪ አደረገ (ኢዩ. 1፥14)።

በርካታ ጾሞቻችን ግን *የግል (የብቻ)* መሆን አለባቸው። በማቴዎስ 6፥16-18 ላይ ኢየሱስ እየጾምን እንደ ሆነ ለሰዎች የሚያሳውቅ አለባበስም ሆነ አኳኋን እንዳይኖረን አስጠንቅቆናል። ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ "መጋቢው የአርባ ቀን ጾሙን አጠናቀቀ" የሚል ርእስ የያዘ የዜና ቤተ ክርስቲያን ሕትመት ደርሶኝ ነበር። በጾሙ ያገኛቸው መንፈሳዊ ነገሮች ቢኖሩ እንኳ ለሕዝብ በማስ ተዋወቅ ድርጊቱ እንዳጣቸው በዚያን ወቅት አስቤ ነበር። አላውቅም። አርባ ቀን መጾምና ስለ ጉዳዩ ለሆነ ሰው አለመናገር እጅግ ከባድ ይሆን ይሆናል።

## ጾም ምን ያህል ርዝመት ይኖረዋል?

መጽሐፍ ቅዱስ የአንድ ቀን፣ የሰባት ቀናት፣ የሃያ አንድ እና የአርባ ቀናት ርዝመት ስላላቸው አጽዋማት ዘግቧል። የጊዜ ገደብ የለውም። ኢየሱስ ለአርባ ቀናት እንዲጾም "መንፈስ [ቅዱስ] ወሰደው" (ማቴ. 4፥1-2)፤ እኛም ስለ ጊዜው ርዝመት መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን መፍቀድ አለብን። ለነገሩ ጾም ለመጀመር መንፈስ ቅዱስን ለመስማት ንቁ የሆነ ክርስቲያን መቼ መቆም እንዳለበት ለማወቅም ንቁ ይሆናል።

## የጾም ደረጃዎች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ ከሚያስደንቁት የጾም ገጽታዎች አንዱ የጾም ደረጃዎች ናቸው። አንዳንዶች ያለ ምግብና ውሃ፣ ሌሎች ደግሞ ያለ ምግብ ሲጾሙ፣ ከወይንና ከአስደሳች ምግብ በመታቀብ የጾሙም አሉ። እነዚህን የተለያዩ ደረጃዎች በየፈርጃቸው መመልከቱ እንደሚረዳ አስባለሁ።

ምንም ምግብና መጠጥ የማይወሰድበት *ጽኑ* ጾም አለ። በሐዋርያት *ሥራ* 9፥9 የሚገኘው የጳውሎስ ጾም ጽኑ ጾም ነበር። ሙሴ ሕጉን ከእግዚአብሔር ሲቀበል ሲጾም የነበረው ጾም በዚሁ ክፍል ይካተታል። ለአርባ ቀናት ያለ ምግብና መጠጥ ቆየ፤ ጽኑና አስቸጋሪ ጾም።

*በመደበኛ* ጾም ውስጥ ሰው አይመገብም፤ ውሃ ግን ይጠጣል፡፡ ይህ የተለመደ የጾም መንገድ ነው፡፡ የኤልያስ ጾም ምናልባት መደበኛ ጾም ሳይሆን አይቀርም፤ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ያለ ምግብ መጓዙን ብቻ ነውና (1ነገ. 19፥8)፡፡ ጌታ ኢየሱስም በአርባ ቀናት ጾሙ ውሃ ይጠጣ እንደ ነበር ይታሰባል፤ ወንጌላቱ ስለ ረሃቡ እንጂ ስለ ጥማቱ አንዳች አይነግሩንምና፡፡

ከዚያ ደግሞ *ከፊል* ጾም አለ፡፡ ይህ በዳንኤል 10፥3 ላይ ተገልጿል፤ “ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ምርጥ ምግብ አልበላሁም፤ *ሥጋም* ሆነ የወይን ጠጅ ወደ አፌ አልገባም፤ ቅባትም አልተቀባሁም” (አ.መ.ት)፡፡

## ጾም ለምን?

ይህን ጠቃሚ ነጥብ አጽንኦት እንድሰጠው ፍቀዱልኝ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጾም ዓላማ ሁልጊዜም *መንፈሳዊ* ነው፤ የሆነ መንፈሳዊ ግብ ለመምታት፡፡ ጾም አካልን በማጥራትና ክብደትን በመቀነስ ለጤና አስተዋጽኦ ቢያደርግም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አተያይ ይህ ጾም አይደለም፡፡ ለእኔ፣ እግዚአብሔር ለሆነ ምክንያት እንድጾም ሲመራኝ መፈጸም አይከብደኝም፡፡ ረሃቡ ብዙም አያስቸግረኝም፡፡ ክብደት ለመቀነስ ስጾም ግን በየአቅጣጫው ጦርነት ይፈጠራል፡፡

## *ለመንፈሳዊ መገራት መጾም*

ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደምናየው እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲጾሙ ያዘዘበት ቀዳሚ ሐሳብ ራስን ማዋረድና ራስን ዝቅ ማድረግ ነው፡፡ በመዝሙር 35፥13 ዳዊት እንዲህ ይላል፤ “እኔስ እነርሱ በታመሙ ጊዜ ማቅ ለበስሁ፤ ነፍሴንም በጾም አደከምኋት”፡፡

እንደገናም በመዝሙር 69፥10 ላይ፣ “ነፍሴን በጾም አስመረርሁአት፤ ለስድብም ሆነብኝ” ይላል፡፡ ይህ ውብ ሐሳብ ነው፤ *ጾም የነፍስ ለቅሶ ነው፡፡*

ከዚያም በመዝሙር 109፥24፣ “ጒልበቶቼ በጾም ደከሙ፤ *ሥጋዬም* ቅቤ በማጣት ከሳ” ይላል፡፡

በዕዝራ 8፥21፣ “በአምላካችን ፊት ራሳችንን እናዋርድ ዘንድ ... በዚያ በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጾም ዐወጅሁ” የሚል እናነብባለን፡፡

እግዚአብሔር ከሕዝቡ አብዝቶ ከሚፈልጋቸው ነገሮች አንዱ ትሑታን እንዲሆኑ ነው፡፡ አንዳንዴ “ጌታ ሆይ፤ ትሑት አድርገኝ” ብለን እንጸልያለን፡፡ ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጸሎት ነው ብዬ አላስብም፡፡



እግዚአብሔር እኛን ትሑት ማድረግ እንዳለበት የሚናገር አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አግኝቼ አላውቅም፡፡ እርሱ ዝቅ ያደርገን ይሆናል፤ ነገር ግን እኛ ራሳችን ትሑት መሆን አለብን፡፡ ይህ የእኛ ኀላፊነት ነው፡፡ እደግመዋለሁ፤ ትሕትና (ራስን ማዋረድ) የእግዚአብሔርን ልብ ስለሚያስደስት እንዲባርከን ያስችለዋል፡፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ ያውጃል፤

> ጎበዞች ሆይ፤ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፤ *እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፡፡* እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኀይለኛው ከእግዚ አብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፡፡ (1ጴጥ. 5፥5-6 - አጽንኦት የተጨመረ)

ኢየሱስ ለደቀ መዝሙርነት ያደረገልን ጥሪ ሁለተንናችንን በእርሱ ውስጥ እናገኝ ዘንድ ራሳችንን እንድንክድ የሚጋብዝ ነው፡፡ እውነተኛ (ከልብ የመነጨ) ኀዘን ከምግብ ፍላጎት ይበልጣልና ጾም የመለኮታዊ ኀዘን እና ንስሓ ትክክለኛ መግለጫ ነው፡፡ ስለዚህም ጾም የውስጣዊ ንስሓችን ውጫዊ መገለጫ ይሆናል፡፡

በአካላዊ ፍላጎትና በመንፈሳዊ መገራት መካከል ያለውን ግንኙነት አስታውሱ፡፡ የሰዶም ኀጢአት “እንጀራን ከመጥገብ” ጋር የተያያዘ ነው (ሕዝ. 16፥49)፡፡ ስለ እስራኤልም ሲናገር እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “ካጠገብ ኋቸውም በኋላ አመነዘሩ” (ኤር. 5፥7)፡፡ የምግብና የመጠጥ ፍላጎት አላግባብ ለጥቅም ሲውል፣ በሌሎች አቅጣጫዎች ሕይወት ለጥቃት ይጋለጣል፡፡ ተቃራኒውም እውነት ነው፤ አካላዊ ፍላጎቶች በቍጥጥር ሥር ሲውሉ፣ መንፈሳዊ ሕይወት ይጠነክራል፤ ይበረታልም፡፡ ይህ ትልቅ አጽንኦት የሚያስፈልገው እውነት ነው፡፡ *ጾም ሥጋን (አካልን) ለማስገዛትና የፍላጎት ገዢ ለመሆን የሚያግዝ መንፈሳዊ ሥርዐት (መገራት) ነው፡፡*

## ጾም እንደ መንፈሳዊ ባልንጀራ

ጾም ለብቻው የሚተገበረው ከስንትና ስንት አንዴ ነው፡፡ ሁልጊዜም ከሌላ መንፈሳዊ ተግባር ጋር ይያያዛል፡፡ ጾምን ለብቻው እንድንፈጽም የትም አልታዘዝንም፤ እንድንጾም *እና* እንድንጸልይ፤ ማቅ እንድንለብስ፣ ዐመድ እንድንነሰንስ (የመለኮታዊ ኀዘን እና ንስሓ ምልክቶች ናቸው) *እና* እንድንጾም፣ ጌታን *በጾም* እንድንፈልግ፣ ወይም ጌታን *በጾም* እንድናመልክ እንጂ፡፡

ጾም እነዚህ ሌሎች መንፈሳዊ ልምምዶች ይበልጥ በውጤታማነት የሚተገበሩበትን ድባብ ይፈጥራል፤ መንፈሳዊ ልምምዶቹ በጾም መንፈስ ውስጥ ይበለጽጋሉ፡፡ ለጸሎትና ጌታን ለመፈለግ ተስማሚ ድባብ ነው፡፡ በጾም ራሳችንን ከምድር እናላቅቅና በጸሎት ራሳችንን ከሰማይ ጋር እናያይዛለን፡፡ በጥልቅ መንፈሳዊ ጥሞና ወቅት ይበልጥ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እንድንተው ያስችለናል፡፡ በጾም ወቅቶች ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ በጸሎት ውስጥ ይበልጥ ነጻነት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ይበልጥ አብርሆት፣ ለእግዚአብሔር ሀልዎትም ይበልጥ ጥልቅ ስሜት እንደሚኖረኝ አስተውያለሁ፡፡

በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጾም የመንፈሳዊ መረዳታችንን ከፍታ ይጨምረዋል፤ ለእግዚአብሔር ነገሮችም ይበልጥ ንቁ ያደርገናል፡፡ የኢየሱስ የአርባ ቀናት የምድረ በዳ ጾም፣ መጋፈጥ ለነበረበት ኀይለኛ የሰይጣን ጥቃት አዘጋጅቶታል፡፡ ዳንኤልም ከእግዚአብሔር ዘንድ መገለጥ የተቀበለው በጸሎትና በጾም ነበር፡፡ በአንጾኪያ በነበረችው ቤተ ክርስቲያንም ጌታን ሲያመልኩና ሲጾሙ መንፈስ ቅዱስ ለጳውሎስና ለበርናባስ ያለውን ዕቅድ ገለጠላቸው፡፡ ጳውሎስና በርናባስ ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን የሾሙትና ለጌታ አደራ የሰጧቸው በጸሎትና በጾም ድባብ ውስጥ ነበር፡፡ ሙሴ ሕጉን ሲቀበል በጾምና በጥበቃ መንፈስ እንደ ነበር በዘዳግም 9፥9-10 ይናገራል፡፡

## ለመለኮታዊ ጥበቃ መጾም

የነጻ መውጣትና የጥበቃ ጾም ምሳሌ በዕዝራ 8፥21-23 ይገኛል፤

> ራሳችንን በአምላካችን ፊት ዝቅ እንድናደርግ፣ *ጕዞውም ለእኛና ለልጆቻችን፣ ለንብረታችንም ሁሉ የተቃና እንዲሆንልን፣* እዚያው በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጾም ዐወጅሁ፡፡ "መልካሚቱ የአምላካችን እጅ በሚፈልጉት ሁሉ ላይ ናት፤ እርሱን በሚተዉ ሁሉ ላይ ግን ቍጣው ትወርድባቸዋለች" ብለን ለንጉሡ ነግረነው ስለ ነበር፣ በመንገድ ላይ ከጠላት የሚጠብቁን ወታደሮችንና ፈረሰኞችን እንዲሰጠን ንጉሡን ለመጠየቅ ዐፍሬ ነበር፡፡ ስለዚህ ጾምን፤ ወደ አምላካችንም ስለዚህ ነገር ልመና አቀረብን፤ እርሱም ጸሎታችንን ሰማ፡፡ (ኢ.መ.ት - አጽንኦት የተጨመረ)

ይህ ውብ ታሪክ ነው፡፡ ሕዝቡ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም የአራት ወራት ጕዞ ሊጀምሩ ነው፤ ጕዞውም ሽፍቶች በተሰገሰጉበት ድንጋያማ ምድረ



በዳ ውስጥ የሚደረግ ነው፡፡ ንጉሡ ዕዝራንና ሕዝቡን እንዲያጅቡ ወታደሮቹን ለመላክ ጠይቆ ነበር፤ ዕዝራ ግን የሚያስፈልጋቸው ጥበቃ አምላካቸው ብቻ መሆኑ ላይ ተመክቶ (ተኩራርቶ) እምቢ አለ፡፡

በባቢሎን ቅጥር ውስጥ በሰላም እየኖሩ እግዚአብሔርን ስለ መታመን ማውራት ቀላል ነው፡፡ የሚያግዛችሁ የሥጋ ለባሽ ከንድ በሌለበት በአደጋ መካከል ራሳችሁን ስታገኙ ግን ሌላ ታሪክ ነው፡፡ እዚህ ጋ ነው በርካታ ክርስቲያኖች ለዓለም መሣለቂያ ምክንያት የሚሆኑት፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን፤ ቍርጠኛው ጊዜ ሲመጣ ዕዝራ ርዳታ ፍለጋ ወደ ዓለም አልሮጠም፡፡ ይህን ማድረግ አሳፋሪ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ምንም እንኳ ዕዝራ ሥጋ ለባሽ ቢሆንም፣ በሥጋ መሣሪያዎች አልተዋጋም፤ ጾም ዐውጆ እግዚአብሔርን ፈለገ እንጂ፡፡ ጌታም ታደጋቸው፡፡

ሁለተኛ ዜና ምዕራፍ 20 እስከ ዛሬ ከተካሄዱት ጦርነቶች ሁሉ ልዩ ስለ ሆነ እንግዳ ጦርነት ይተርካል (ምዕራፍ 4ን ተመልከቱ)፡፡ ንጉሡ ኢዮሳፍጥ ግዙፍ የሶሪያ ጦር ጥቃት ሊሰነዘርበት እየመጣ ነበር፡፡ ጕዳዩን የተገነዘበው ኢዮሳፍጥ እጅግ ስለ ፈራ፣ "እግዚአብሔርንም ሊፈልግ ፊቱን አቀና፤ በይሁዳም ሁሉ ጾም ዐወጀ" (2ዜና 20፥3)፡፡ ከዚያም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤

> አምላካችን ሆይ፤ አንተ አትፈርድባቸውምን? ይህን የመጣ ብንን ታላቅ ወገን እንቃወም ዘንድ አንችልም፤ የምናደርገውን አናውቅም፤ ነገር ግን ዐይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው፡፡ (ቍጥር 12)

እየጾሙና እየጸለዩ ሳለም እግዚአብሔር የጦርነት ዕቅድ ሰጣቸው፡፡ ይኸውም ንጉሡ ከተዋጊ ሠራዊቱ በፊት የሙዚቃ ባለሞያዎችን እንዲልክ የሚጠይቅ ልዩ ዕቅድ ነበር፡፡ ለእግዚአብሔር እንዲዘምሩና እንዲያመሰግኑ የተመደቡት እነዚህ መዘምራን ከሠራዊቱ ፊት ወጥተው፣ "ዝማሬውንና ምስጋናውን በጀመሩ ጊዜ ይሁዳን ሊወጉ በመጡት በአሞንና በሞዓብ ልጆች፣ በሴይርም ተራራ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ድብቅ ጦርን አመጣባቸው፤ እነርሱም ተመቱ" (ቍጥር 22)፡፡ በነገራችን ላይ፤ ይህ ታላቅ የጾም መግለጫ ነው - "ነገር ግን ዐይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው፡፡"

በእኛም ዘመን እግዚአብሔር ከጠላቶቻችን የሚያድነንን (የሚታደገንን) የውጊያ ዕቅድ ለመግለጥ እየጠበቀ ሊሆን ይችላልን? እግዚአብሔርን የሚፈልግና በምድሪቱ ጾምን የሚያውጅ ሌላ ኢዮሳፍጥንስ እየጠበቀ ይሆን?

## የእግዚአብሔርን ቍጣ ለማስቀረት መጾም

እግዚአብሔር ተናግሯል፡፡ ነነዌ በአርባ ቀናት ውስጥ ትጠፋለች፡፡ ጕዳዩ እርግጠኛ የነበረ ከመሆኑ የተነሣ ፍርዱ ሲቀር፣ እየመጣ የነበረውን መዓት ያወጀው ነቢዩ ዮናስ እጅግ ተቈጥቶ ለመሞት እግዚአብሔርን ለመነ፡፡ ነገር ግን የዚያች ኀጢአተኛ ከተማ ንጉሥ ማቅ ለብሶና ዐመድ ነስንሶ ንስሓ ገባና ከተማ አቀፍ ጾም ዐወጀ፡፡ እናም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤

> እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደ ተመለሱ ሥራቸውን አየ፡፡ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም፡፡ (ዮናስ 3፥10)

## በምልጃና በጾም ነጻ መውጣት

እስከ አሁን ያየናቸው ምሳሌዎች በአብዛኛው የራስ ነጻ መውጣት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር *ሌሎችንም* ነጻ ለማውጣት ምልጃንና ጾምን ይጠቀማል፡፡ ሦስት ጕዳዮችን እንድጠቅስ ፍቀዱልኝ፡፡

በዕዝራ 10፥6 እንዲህ እናነብባለን፤

> ዕዝራም ከእግዚአብሔር ቤት ፊት ተነሥቶ ወደ ኤልያሴብ ልጅ ወደ ዮሐናን ጓዳ ገባ፤ ስለ ምርኮኞቹም ኀጢአት ያለቅስ ነበርና ገብቶ እንጀራ አልበላም፤ ውሃም አልጠጣም፡፡

ሕዝቡ በምርኮ ሳሉ እስራኤላዊ ያልሆኑ ሰዎችን በማግባት የእግዚ አብሔርን ትእዛዝ አፈረሱ፤ ዕዝራ ስለ ኀጢአታቸው የነበረው ኀዘንም በጾም ተገለጸ፡፡ ውጤቱም ሕዝቡ ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ ጣዖት አምላኪዎችን (እስራኤላዊ ያልሆኑ ሰዎችን) ማግባታቸውን መተዋቸው ነበር፡፡

የምልጃና የጾም ሌላ ምሳሌ በነህምያ የመጀመሪያ ምዕራፍም ይገኛል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ሰው ወደ ኋላቸው ስለ ተመለሱ ሕዝቦች ይጸልያል፤

> ይህን ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፣ አያሌ ቀንም አዝን ነበር፤ በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር፤ እንዲህም አልሁ፣ "አቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ፣ ለሚወድዱህና ትእዛዝህን ለሚያደርጉ ቃል ኪዳንንና ምሕረትን የምትጠብቅ፣ ታላቅና የተፈራህ አምላክ ሆይ፣ እኔ ባሪያህ ዛሬ በፊትህ ስለ ባሪያዎችህ ስለ እስራኤል ልጆች ሌሊትና ቀን የምጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ ጆሮህ ያድምጥ፤ ዐይኖችህም



> ይከፈቱ፤ በአንተ ላይም ያደረግነውን የእስራኤልን ልጆች ኀጢአት እናዘዝልሃለሁ፤ እኔና የአባቴ ቤት በድለናል፡፡ (ነህ. 1፥4-6)

ከሙሴ የሚበልጥ በጸሎትና በጾም ሌሎችን ነጻ የማውጣት ምሳሌ አይገኝም፡፡ ሙሴ ምናልባት በቅዱሱ እግዚአብሔርና በኀጢአተኛ ሕዝብ መካከል ባለው ክፍተት መካከል መቆምን ከማንም በላይ (ከኢየሱስ በቀር) ያውቃል፡፡ ከመሞቱም አስቀድሞ የሥልጣን ወንበሩን በሙተው ስለ እነርሱ ያደረገውን ምልጃ ያስታውሳቸዋል፤

> ስለ ሠራችሁት ኀጢአት ሁሉ፣ እርሱንም ለማስቈጣት በእግዚ አብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር ስላደረጋችሁ፣ እግዚአብሔር ሊያጠፋችሁ ከተቈጣባችሁ ከቍጣውና ከመዓቱ የተነሣ ስለ ፈራሁ፣ እንደ ፊተኛው በእግዚአብሔር ፊት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ወደቅሁ፤ እንጀራ አልበላሁም፣ ውሃም አልጠጣሁም፡፡ *እግዚአብሔርም በዚያን ጊዜ ደግሞ ሰማኝ፡፡* እግዚአብሔርም አሮንን ሊያጠፋው እጅግ ተቈጣው፤ *ስለ አሮንም ደግሞ በዚያን ጊዜ ጸለይሁ፡፡* (ዘዳ. 9፥18-20 - አጽንኦት የተጨመረ)

አስቡት እስቲ፤ *አንድ ሰው* በጾምና በምልጃ ዋጋ ከፍሎ፣ መላ አገሪቱ ከፍርድ ነጻ ወጣች፡፡ ክርስቲያኖች በጸሎትና በጾም እንዲህ ዐይነቱን ኀይል ለመጠቀም መብታቸውና ኀላፊነታቸው ቢነቁ በቤቶቻችን፣ በአብያተ ክርስቲያናችን፣ *በዓለማችን* ምን ሊከሰት እንደሚችል ለመገመት እንኳ እንደፍራለንን? ለመሆኑ፣ ነጻ የወጡ ሕይወቶች የማያቋርጥ ሰልፍ ከጨለማ ወደ ብርሃን መንግሥት ሲጎርፍ በዐይነ ኅሊናችሁ ማየት ትችላላችሁ? አስቸጋሪ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው ወደ ኢየሱስ የመጡላቸው አባቶችና እናቶች የደስታ ጩኸት ሰማያትን ሲያጥለቀልቅ መስማት ትችላላችሁ? በመቶዎች የሚቈጠሩ ማላጆች ምሽጉን ጥሰው የኀጢአት ምርኮኞችን ነጻ ሲያወጡ ሰይጣን በሽንፈት ሲወሽቅ ማየት ትችላላችሁ?

## የጾም ሽልማት

ኢየሱስ እንዲህ አለ፤

> አንተ ግን በምትጾምበት ጊዜ ፊትህን ታጠብ፤ ራስህንም ተቀባ፤ በዚህም መጾምህ በስውር ያለው አባትህ ብቻ የሚያውቀው፣ ከሰዎች ግን የተሰወረ ይሆናል፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል፡፡ (ማቴ. 6፥17-18 - አ.መ.ት)

ኢየሱስ የሽልማትን አነሣሽነት አሳንሶ አልተመለከተውምና ከበጎ አድራጎትና ከጸሎት ጋር በጤናማ (በተገቢ) መንፈስ የጾሙ ብድራት እንደሚቀበሉ ቃል ገብቷል። በሃይማኖተኝነታቸው በሌሎች ፊት ሞገስ ለማግኘት የሚጾሙ የሚያገኙትን ብድራት ደግሞ በቍጥር ዐሥራ ስድስት ይጠቅሰዋል፤ "ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል።"

ጌታ ኢየሱስ ዋጋን ለመናገር በቍጥር 16 ላይ የተጠቀመበት ቃል በቍጥር 18 ከተጠቀመበት የተለየ ነው። የግብዞችን ዋጋ ለመናገር ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ዋጋው *አሁኑኑ እንደሚከፈል* እና *በሙሉ እንደሚከፈል* የሚናገር አንድምታ አለው። በሌላ አገላለጽ "የሚያዩትን ነው የሚያገኙት"። በትክክለኛው መንፈስ ለሚጾሙ በምላሽነት የሚሰጠውን ዋጋ ለማስረዳት የተጠቀመበት ቃል ሐሳብ ግን በጊዜ ሂደት የሚገኝን መታደስ የያዘ ነው። የጾም ዋጋ የትርፍ ድርሻው በየጊዜው እያደገ እንደሚሄድ የንግድ ተቋም ነው። እግዚአብሔር የጾምን ዋጋ ከቀን ወደ ቀን ለእናንተና ለሌሎች መግለጡን ይቀጥላል።



በኩል ጭከና የመሰለው ነገር በእውነቱ ርኅራኄ መሆኑን በጭራሽ መገመት ያስቸግራል።

አንዳንድ ጊዜ የወይኑን አትክልተኛ በስሕተት እንገምተዋለን። ምናልባት በተመደበልን ቦታ ተቀምጠን፣ በወይኑ ተክል ላይ እየኖርን፣ መልካም ፍሬ እያፈራን ይሆናል፤ ድንገት ወደ ወይኑ ዕርሻ የሚገባ ከበድ ያለ ኮቴ እንሰማለን። ከዚያም፣ "የወይኑ አትክልተኛ መጥቷል፤ በእጁም መግረዣ መቀስ ይዟል" የሚለው ወሬ ወዲያውኑ በወይን ዕርሻው መኻል ይሰራጫል። ከዚያም አትክልተኛው ከፊት ለፊታችሁ ቆሞ፣ ያለ አንዳች ማብራሪያ፣ አንዳንድ ምርጥ አካላችሁን እየቈረጠ ማስወገድ ይጀምራል። በቅርባችሁ ያሉ ሌሎች የወይን ዛፎች ሊያበረታቷችሁ ይሞክራሉ፤ "ሁሉም ነገር ይስተካከላል" ይሏችኋል፤ "ለመልካም ይሆንላችኋል" ይሏችኋል፤ "ትለምዱታላችሁ" ይሏችኋል። እንደማትለምዱት ግን ታውቃላችሁ። የዓመቱ ምርጥ ፍሬያማ ቅርንጫፍ ተብላችሁ ከተሸለማችሁ በኋላ የወይኑ አትክልተኛ እንዲህ ዐይነቱን ጭካኔ የሚፈጽምበትን ምክንያት መረዳት ያቅታችኋል።

ሆኖም፣ ቅርንጫፍ ከሆናችሁ ግርዛት ከግዛት ጋር የተያያዘ ነው፤ ከሥራ ጋር የተያያዘ አደጋ ነው። ቅርንጫፎች መጠቀሚያ መሣሪያዎች እንጂ ጌጦች አይደሉም። እዚህ ጋ ግርዘት "ማጥራት" በሚል ቃል የተተረጐመ ሲሆን፣ ይህም ወይኑን በተመለከተ ሲወሰድ፣ "ለጊዜው የማያስፈልጉ ዕንጨቶችን በማስወገድ መግረዝ" ማለት ነው።

ግርዘቱን የሚያካሂደው አብ ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ቃል የመግረዣ መሣሪያው ነው (ዮሐ. 15፥3)። የቅርንጫፉን ዋነኛ ኀይል ፍሬ ከማስገኘት አቅጣጫ የሚያስቀይር በቅርንጫፉ ላይ ያለ የትኛውም ነገር ተቈርጦ ይወገዳል። አትክልተኛው መጥፎዎቹን ነገሮች ሁሉና ከጥሩዎቹም በርካቶቹን ይገርዛቸዋል። የመጥፎዎቹን መቈረጥ አስፈላጊነት ለጋዎቹ ቅርንጫፎች እንኳ ሊገነዘቡት ይችላሉ፤ በርካታ ጥሩዎች መቈረጣቸውና መወገዳቸው ግን ጭከናና አባካኝነት ይመስላል፤ አትክልተኛውም ግርዘቱን በማካሄድ የሚደሰት፣ በሥቃያችን የሚረካ ይመስላል። ያን ውብ ዕንጨት፣ እነዚያን ተወዳጅ ቅጠሎች ማስወገድ - ከሞላ ጐደል ወንጀል ነው።

የወይኑ ጌታ ግን ጥቅም አልባ ዕንጨቶችን ብቻ ነው የሚያስወግደው። ዕንጨቱ ያማረ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ቦታ ከመያዙም በላይ፣ ሌላኛው ቅርንጫፍ ጣፋጭ የወይን ፍሬዎችን እንዲያስገኝ የሚያስችለውን ውድ ማዕድንም ይሻማል።

ፍሬ የለሽ ለመሆን ወደ ዓለም መመለስ አይኖርብንም፤ አንዳንዴ በቀላሉ በበርካታ “መልካም” እንቅስቃሴዎች (*ሥራዎች*) እንያዛለን፡፡ የምርጡ ነገር ግዙፍ ጠላት መጥፎው አይደለም፤ ጥሩው እንጂ - ለማደግ ስፍራ እስኪታጣ ድረስ ሕይወታችንን ቅጥ ያሳጡ ጥሩ ነገሮች፣ ፍሬ ለማፍራት ዐቅም እስኪጠፋ ድረስ ኀይላችንን የሚያሟጥጡ ነገሮች ናቸው፡፡ *ለመሆን* ጊዜ እስኪጠፋ ድረስ *በመሥራት* ባተሌ ሆነናል፡፡ ብዙ ዕንጨቶች አሉን፡፡

## የሚያስፈልገው አንድ ነገር

ይህ በማርያምና በማርታ ሕይወት በተከሰተ ነገር በሥዕላዊ መንገድ ተብራርቷል፡፡ በትክክልም ማርታን ባያችኋት ቊጥር ኩሽና ነው የምታገኙአት፤ ልጅት ማብሰል ትወዳለች፡፡ እኅቷ ማርያም እንድታግዛት ማድረግ ግን አቅቷታል፡፡ ማርያም ደግሞ ትኩረቷን የሰጠቻቸው ሌሎች ነገሮች ነበሯት፡፡ ታሪኩ በሉቃስ 10፥38-42 ውስጥ ተነግሯል፡፡

> *ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ መንገድ ሲሄዱ፣ ኢየሱስ ወደ አንድ መንደር ገባ፤ ማርታ የተባለች አንዲት ሴትም በቤቷ ተቀበለችው፡፡ እርሷም ማርያም የምትባል እኅት ነበረቻት፤ ማርያምም ቃሉን እየሰማች በጌታ እግር ሥር ተቀምጣ ነበር፡፡ ማርታ ግን በሥራ ብዛት ትባክን ነበርና ወደ እርሱ ቀርባ፣ “ጌታ ሆይ፣ እኅቴ ሥራውን ለእኔ ብቻ ጥላ ስትቀመጥ ዝም ትላለህን? እንድታግዘኝ ንገራት እንጂ” አለችው፡፡* (ኢ.መ.ት)

እስቲ ለደቂቃ ቆም እንበል፡፡ እዚህ ሐሳብ ላይ የማን ደጋፊ ናችሁ? እኔን በሚመለከት፣ በማርታ ወገን ነኝ፡፡ ሁሉንም ነገር ብቻዋን *መሥራት* አይኖርባትም፡፡ ማርያም ሰነፍ ናት፡፡

> እሁን ደግሞ ጌታ ኢየሱስ የሚለውን እንስማ፤

> *ጌታ ግን እንዲህ ሲል መለሰላት፤ “ማርታ፣ ማርታ፤ ስለ ብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ፤ ትዋከቢአለሽም፤ የሚያስፈልገው ግን አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ማርያምም እኮ የሚሻለውን ድርሻ መርጣለች፤ ይህም ከእርሷ አይወሰድም፡፡”*

ይህ ያልተጠበቀ ነገር ነው፡፡ የሚያስፈልገው ነገር *አንድ ብቻ* ነው? ለዚህ ዝግጁ ነን? ከምናደርጋቸው በርካታ ነገሮች፣ መልካም ነገሮች፣ ጠቃሚ ነገሮች ውስጥ አንድ *ነገር* ብቻ ነው የሚያስፈልገው? አዎን ትክክል ነው፤ አንድ ነገር ብቻ፡፡ ማርታ ሥራ ብዙነቷ ቀልቧን ስለ ወሰደው አልተገነዘበ ችውም፡፡ ኢየሱስ የማርታን “ብዙ ነገር” ከማርያም “አንድ ነገር” ጋር



አነጻጽሮታል፡፡ ማርታ ጌታን በማገልገል ሥራ ከመወጠሯ የተነሣ እዚያ በመገኘቱ መደሰት አልቻለችም፡፡

ማርታ ለክርስቶስ የምትፈጽመው አገልግሎት ደስታንና ሰላምን ወደ ልቧ ማምጣት ሲኖርበት፣ ይልቁኑ ጭንቀትን፣ ውጥረትንና ቊጣን ነው ያመጣባት፡፡ ለመልካም የታሰበ ድካሟ በእርሷና በእኅቷ መካከል ያለውን ስምረት መስበርን አስከተለ፤ ጠቅላላውን ጉዳይም ጭጋጋማ አደረገው፡፡ ተመሳሳይ ነገር ተከስቶባችሁ ያውቅ ይሆን?

ጌታ ኢየሱስ ማርታ ባትመግበውም መኖሩ ስለማይቀር የሚያስ ፈልገው አንድ ነገር ነው፡፡ ካስፈለገ፣ እያንዳንዱን ድንጋይ ዳቦ ማድረግ ይችል ነበር፡፡

> ብራብም ለአንተ አልነግርህም፤ ዓለምና ሞላው የእኔ ነውና፡፡
> (መዝ. 50፥12)

አዎን፤ ኢየሱስ ማርታ ባትመግበውም ይተርፋል፤ *ማርታ ግን ኢየሱስ ባይመግባት አትተርፍም፡፡* በርካታ ስኬታማ ክርስቲያኖች ክርስቶስን በማገልገል ከመወጠራቸው የተነሣ ከእርሱ ገበታ ለመቀመጥና በቃሉ ግብዣ ለመደሰት ጊዜ በማጣት “በወይኑ ተክል ላይ ሞተው” አይቻለሁ፡፡

ማርያም “የሚሻለውን ድርሻ መርጣለች፡፡” ይህም ከምግብ ጋር የተገናኘና ኩሽና ውስጥ የተለመደ ሐረግ ነው፡፡ ግብዣ ላይ ለክብር እንግዳው ተለይቶ የሚቀመጥ ብልት፣ የተሻለው ድርሻ ነበር፡፡ ማርታ ለኢየሱስ የተሻለውን ድርሻ እያዘጋጀችለት እንደ ሆነ ስታስብ፣ እርሱ ለማርያም ሰጣት፡፡

## እንብቡና እጨዱ

በኢየሱስ እግር ተቀምጣችሁ፣ በህልዎቱ እየተደሰታችሁ፣ የቃሉን ግብዣ እየተመገባችሁ ጊዜ ታሳልፋላችሁ? በታማኝነትና በትጋት መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናትን ሌላ ምንም ነገር ሊተካው አይችልም፤ ጸሎትም እንኳ፡፡ እንድታነቧቸውና የተሻለውን ድርሻ እንድታጭዱ የሚያግዙ ጥቂት ጥቆማዎች ይኸዉላችሁ፤

1. መጽሐፍ ቅዱስን *በመደበኛነት (በቋሚነት)* እንብቡ፡፡ የተከፈተ ቃሉን ይዛችሁ ለብቻ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ሳታሳልፉ ፀሓይ አትጥለቅ፡፡ ያልቋሰ፣ ያላደረ መና በየቀኑ መሰብሰብ አስፈላጊ ነው፡፡

2. መጽሐፍ ቅዱስን *በንቃት* አንብቡ:: አእምሮአችሁ ንቁና አዲስ የሚሆንበትን ጊዜ ምረጡ:: ለእግዚአብሔር ጥድፊያ ከበዛበት ቀናችሁ ላይ እንቅልፍ የተጫጫነውን ትራፊ አትስጡ::
3. መጽሐፍ ቅዱስን *በሥርዐት* አንብቡ:: ዘሌዋውያን 11፥3ን አንብባችሁ፣ ከዚያ ራእይ 5፥7ን ብታነብቡና ቀጥላችሁም መዝሙር 15፥4ን አንብባችሁ ግራ ብትጋቡ በመጽሐፍ ቅዱስ አታሳብቡ:: አንድ መጽሐፍ ምረጡና (ለምሳሌ፣ ፊልጵስዩስን) ከምዕራፍ አንድ፣ ቍጥር አንድ፣ ቃል አንድ ጀምሩና መላው መጽሐፍ እስኪያልቅ አንብቡ:: መጽሐፍ ቅዱስ በወጉ ሲነበብ በሚሰጠው ስሜትና ትርጉም ትደነቃላችሁ::
4. መጽሐፍ ቅዱስን *በተለያዩ አማራጮች* አንብቡ:: የተለያዩ ትርጉሞችን ተጠቀሙ:: ለአማርኛ አንባቢዎች የቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ትርጉም (1954)፣ የ1997 አዲስ ትርጉም፣ አዲሱ መደበኛ ትርጉም፣ ሕያው ቃል ትርጉምን እጠቁማለሁ::
5. መጽሐፍ ቅዱስን *በጸሎት* አንብቡ:: ዛሬ የምትኖሩበትን ነገር እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት:: ቍጥሮቹን (ጥቅሶቹን) ወደ ጸሎትና ምስጋና ቀይሩአቸው::
6. መጽሐፍ ቅዱስን *በሚጠባበቅ ልብ* አንብቡ:: የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁን እግዚአብሔር በቃሉ እንደሚገናኛችሁና እንደ ሚናገራችሁ በመጠባበቅ አድርጉት::
7. መጽሐፍ ቅዱስን *በታዛዥነት* አንብቡ:: የማንታዘዘው ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱሱ መጨረሻ ተከድኖ መደርደሪያ ላይ መቀመጥ ይሆናል:: መገለጥ ምላሽን ይሻል:: ታዛዥነት የየዕለቱ ጥሞና ከንቱ ሥርዐት እንዳይሆን ይጠብቃል::

የሚጸልይ ሕይወት "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት" የሚኖርበት ሕይወት ነው (ቈላ. 3፥16)::



## 10 - ለመጸለይና ጌታን ለመፈለግ ዐይነተኛው ሁኔታ

# ጾም:- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥናት

የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለሁ ቤተ ሰባችን ወደ አዲስ ቤት ተዛወረ:: ማድቤቱ ግድግዳ ላይ ከምድጃው በላይ በቀይ ቀለም የተጻፈ መፈክር ነበር፤ "የሰው ልቡ በሆዱ በኩል ነው" የሚል:: ዛሬ ዛሬ ምናልባት አንዳንዶች ጾታዊ መድልዎ የሚንጸባረቅበት አባባል ነው በማለት ቢያጣጥሉት እንኳ የያዘው እውነት ሚሊዮን ጊዜ ተደጋግሞ ተረጋግጧል:: ለነገሩማ፣ ዲያብሎስም ለሺዎች ዓመታት በዚህ መመሪያ ሲጠቀም ቈይቷል:: የሰው ልቡ በአካላዊ ፍላጎቱ በኩል መሆኑን ድሮ ነው የደረሰበት::

ሰው የተሰናከለበት የመጀመሪያው ፈተና ከአካላዊ ፍላጎቱ ጋር የተገናኘ ነበር::

> ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣ ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደ ሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ ሰጠችው፤ እርሱም በላ:: (ዘፍ. 3፥6 - አ.መ.ት)

ከዚያ ከመጀመሪያው የገነት ተሞክሮ በኋላ በምግብ ፍላጎት ላይ ያነጣጠሩ የማያቋርጡ ፈተናዎች ሲግተለተሉ ኖረዋል:: ኖኅ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ታላቅ መዳን ከሆነለት በኋላ አካላዊ ፍላጎቱን ያላግባብ ተጠቀመበትና ሰከረ:: ይስሐቅ ዔሳውን ከያዕቆብ ይልቅ ይወድ የነበረው ዔሳው ጥሩ አዳኝ ስለ ነበርና በበርካታ ጥሩ ጥሩ ምግቦች አባቱን ስለሚያንበሸብሸው ነበር:: እንዳለመታደል ሆኖ ዔሳውም ሆዱ አመዛዛኝነቱን እንዲጫነው ፈቀደና ብኩርናውን ለአንድ ስሀን ምስር ወጥ ሸጠ::

ሐዋርያው ጳውሎስ እስራኤል ከግብፅ ካመለጠች በኋላ የፈጸመ ችውን ምንዝርና በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፥7 ላይ እንዴት እንዳብራራው ልብ በሉ:: ክስተቱን እንድዘግብ እኔ ብመረጥ ኖሮ የወርቁን ጥጃና በዚያን ቀን የተደረ

ጉትን መጥፎና አዋኪ ነገሮች እንደምጠቅስ አስባለሁ። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን እንዲህ አልነበረም። "ሕዝቡ ሊበሉና ሊጠጡ ተቀመጡ፤ ሊዘፍኑም ተነሡ" በማለት በቀላሉ ገልጾታል። እውነተኛው ምክንያት የወርቁ ጥጃ ሳይሆን የሰዎቹ ሥጋዊ ፍላጎት መሆኑን ያውቅ ነበር።

በኢየሱስ የምድረ በዳ ፈተና ወቅት ዲያብሎስ የመጀመሪያውን ጥይት የተኮሰው በሰው ልጅ አካላዊ ፍላጎት ላይ ነው፤ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል" አለው (ማቴ. 4፥3)። በኋላ ደግሞ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች "ሆዳቸው አምላካቸው" ከሆኑ ሰዎች ራሳቸውን እንዲያጠሩ ያስጠነቅቃቸዋል (ፊልጵ. 3፥19)።

## በብሉይ ኪዳን የጾም ጉልህ ድርሻ

በእነዚህና በሌሎች ምንባቦች ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በሰው መንፈሳዊ ሕይወትና በአካላዊ ፍላጎቱ መካከል ያለውን ግልጽ ግንኙነት ይገልጣል። እዚህ ጋ የሚታይ ሥርዐት ማጣት በሌሎች የሕይወት ዘርፎች ሥርዐት የማጣት ምልክት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጾም ብዙ የሚናገረው ለዚህ ይሆናል።

በርካታ ክርስቲያኖች ጾም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ዐይነት ጉልህ ድርሻ እንዳለው ሲገነዘቡ ይደነቃሉ። ምናልባት ብዙዎቻችን የክርስቲያን ሕይወት አካል መሆኑን ፈጽሞ በቁም ነገር አላጤንነው ይሆናል። ከልክ ካለፈ ሕግ አጥባቂ ሃይማኖተኛነት ጋር ስለምናያይዘውም ለሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አግባብነት የሌለው አድርገን በተግባራችን ገሸሽ አድርገነዋል። ነገር ግን በምልጃ (ጸሎት) ጥልቅ እውነቶች ላይ በቁም ነገር የሚደረግ የትኛውም ጥናት ጾምን ችላ ማለትም ሆነ እንደ ጥቅም አልባ ማየት አይችልም። ስለዚህ አጠር ያለ ጥናት እናስከትላለን።

ኤልያስ ከኤልዛቤል ጋር ካካሄደው ፍጥጫ በኋላ ለሕይወቱ መነቃቃትን ፍለጋ ለአርባ ቀናት የጾመበትን የኮሬብ ተራራ ጉዞ አደረገ (1ነገ. 19፥8)።

የአስቴር ጾም ለሕዝቧ ባስገኘችው ነጻ መውጣት ላይ ጠቃሚ ሚና ተጫውቷል (አስ. 4፥16)።

ዳዊትም ልጁን በሽታ ሲቀሥፈው ጾሟል (2ሳሙ. 12፥16)። ዳንኤልም የእግዚአብሔር ሰማያዊ መልእክተኛ የጠላትን መቋቋም ጥሶ በመምጣት ከእግዚአብሔር ዙፋን የተላከለትን መልስ እስኪሰጠው ድረስ እየጾመ ጸልዮአል (ዳን. 10፥3)። ዕዝራና ነህምያ በአገራዊ (ብሔራዊ) ቀውስ ወቅት ጾምን ዐውጀዋል (ዕዝራ 8፥21፤ ነህ. 1፥4)።



## ጾም በአዲስ ኪዳን

ጾም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብቻ የተገደበ አይደለም። በሉቃስ 2፥37 ላይ፣ "በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር" ተብሎ ስለ ነቢዩቱ ሐና ተዘግቧል። ዮሐንስ መጥምቁም እየጾመ ደቀ መዛሙርቱም እንደዚሁ እንዲያደርጉ አስተምሯል።

ጌታ ኢየሱስም ጾሟል፤ ከተከታዮቹም ይህንኑ እንደሚጠብቅባቸው ግልጽ አድርጓል። ለምሳሌ፣ የማቴዎስን ስድስተኛ ምዕራፍ ውሰዱ። በዚህ ምዕራፍ፣ ትክክለኛውን ነገር በተሳሳተ መነሻ ሐሳብ ስለ ማድረግ ደቀ መዛሙርቱን አስጠንቅቋቸዋል። "የክርስትና ሕይወት ተሰባሪ ነውና ተጠን ቅቃችሁ ያዙት። የልባችሁ ሐሳብ ንጹሕ መሆኑን አረጋግጡ" በማለት መክሮአቸዋል። ላነሣው ሐሳብ ምሳሌ ለመስጠትም ሦስት ሃይማኖታዊ ተግባራትን በመውሰድ ከእግዚአብሔር ምስጋና ይልቅ የሰዎችን ምስጋና ለማግኘት እንዴት ሊፈጸሙ እንደሚችሉ አሳይቷል።

የመረጣቸው ሦስት ተግባራት ምጽዋት መስጠት፣ ጸሎትና ጾም ናቸው። ቍጥር 16ን ልብ በሉ፤ "ስትጦሙ …"፤ ከዚያም ቍጥር 17ን፣ "አንተ ግን ስትጦም …"። *ስትጦሙ … ስትጦም።* ኢየሱስ፣ "ከጦማችሁ … ከጦምህ" አላለም። ደቀ መዛሙርቱ እንዲጾሙ የተጠበቀ ነበር። በመሠረቱ፣ ኢየሱስ ጾምን እንደ ምጽዋት መስጠትና ጸሎት መደበኛ ሃይማኖታዊ ተግባር ያደርገዋል። የትኛውም የዘመኑ ክርስቲያን ምጽዋት መስጠት (በጎ ምግባር) እና ጸሎት ጊዜ ዐልፎባቸዋል አይልም። ጾምም እንዲሁ ነው። ኢየሱስ ከጸሎትና ከበጎ ምግባር ጋር አንድ መስመር ላይ አኑሮታል።

በማቴዎስ 9፥14-15 ላይ ይህን እናገኛለን፤

> በዚያን ጊዜ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ቀርበው "እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ የምንጦመው፣ ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጦሙት ለምንድን ነው?" አሉት። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፤ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ።"

ኢየሱስ በአካል በደቀ መዛሙርቱ መካከል ሳለ መጾም አያስፈልጋቸውም ነበር። ጌታ ኢየሱስ ከዓለም ሲወሰድ የጾም ጊዜ ይመጣል። ዛሬ፣ ሙሽራውን እየጠበቅን ሳለ ጾም የሚያስፈልጋባቸው ጊዜአት አሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ የኢየሱስን ጌትነት ከተቀበለ በኋላ ወዲያውኑ ለሦስት ቀናት ጾመ (የሐዋ. 9፥9)። ጾም የሕይወቱና የአገልግሎቱ ቋሚ አካል ነበር። ለቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ግል አገልግሎቱ ሲጽፍላቸው እንዲህ ይላቸዋል፤

> ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን፤ በብዙ መጽናት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በወኅኒ፣ በሁከት፣ በድካም፣ እንቅልፍ በማጣት፣ *በመጦም* (2ቆሮ. 6፥4-5 - አጽንኦት የተጨመረ)

ከዚያም እንደገና በ2ኛ ቆሮንቶስ 11፥27፣ "በድካምና በጥረት፣ ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፣ በራብና በጥም፣ ብዙ ጊዜም በመጦም ... ነበርሁ" በማለት ተናግሯል።

የሐዋርያት *ሥራ* መጽሐፍ ጾም የለጋዋ ቤተ ክርስቲያን ወሳኝ አካል እንደ ነበረ ያሳያል።

> እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፣ "በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው *ሥራ* ለዩልኝ" አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ፣ ከጸለዩም፣ እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው። (የሐዋ. 13፥2-3)

የሐዋርያት *ሥራ* 14፥23 የጳውሎስንና የበርናባስን አዲስ የተመሠረቱትን ማኅበረ ምዕመናን የማጠናከር ሚሲዮናዊ ተልእኮ ያብራራል፤

> በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ ጦመውም ከጸለዩ በኋላ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው።

## የጾም ብያኔ

የዕብራይስጡ ቃል "አፍን መሸፈን" የሚል ትርጕም ሲኖረው፣ የግሪኩ ቃል ደግሞ "አለመብላት" ማለት ነው፤ ጾም ግን ከመራብ እጅግ ያልፋል። በመሠረቱ፣ ጾም ከምግብና ውሃ ጋር ብቻ የተቆራኘ አይደለም፤ እነዚህ ዋና መገለጫዎቹ ቢሆኑም። ባልና ሚስት ራሳቸውን ለጸሎት በሙላት ለመስጠት በጋራ ስምምነት ከግብረ *ሥጋ* "መጾም" ይፈልጉ ይሆናል (1ቆሮ. 7፥5)።

ይህን ፍች እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ፤ *ጾም በመንፈሳዊ ምክንያቶች ከተወሰኑ ሥጋዊ ፍላጎቶች በፈቃደኝነት ራስን ማቀብ ነው።* አብዛኛውን ጊዜ ጾም ከምግብና ከመጠጥ መታቀብ ሲሆን፣ ሌሎች ነገሮችንም ሊያካትት ይችላል።



## የተለያዩ ዐይነት አጽዋማት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ተለያዩ ዐይነት አጽዋማት (ጾሞች) ይናገራል። አንዳንድ አጽዋማት *የአደባባይ (በይፋ የሚደረጉ)* ናቸው። የነነዌ ንጉሥ የነቢዩ ዮናስን ትንቢታዊ መልእክት ከሰማ በኋላ ከተማ አቀፍ ጾም ዐወጀ፤ እንስሳቱን እንኳ ከምግብና ከመጠጥ ከለከለ (ዮናስ 3፥5-10)። ነቢዩ ኢዩኤል የጌታን ምሕረትና መንፈሳዊ መነቃቃት ፍለጋ ለአገር አቀፍ ጾም ጥሪ አደረገ (ኢዩ. 1፥14)።

በርካታ ጾሞቻችን ግን *የግል (የብቻ)* መሆን አለባቸው። በማቴዎስ 6፥16-18 ላይ ኢየሱስ እየጾምን እንደ ሆነ ለሰዎች የሚያሳውቅ አለባበስም ሆነ አኳኋን እንዳይኖረን አስጠንቅቆናል። ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ "መጋቢው የአርባ ቀን ጾሙን አጠናቀቀ" የሚል ርእስ የያዘ የዜና ቤተ ክርስቲያን ሕትመት ደርሶኝ ነበር። በጾሙ ያገኛቸው መንፈሳዊ ነገሮች ቢኖሩ እንኳ ለሕዝብ በማስ ተዋወቅ ድርጊቱ እንዳጣቸው በዚያን ወቅት አስቤ ነበር። አላውቅም። አርባ ቀን መጾምና ስለ ጕዳዩ ለሆነ ሰው አለመናገር እጅግ ከባድ ይሆን ይሆናል።

## ጾም ምን ያህል ርዝመት ይኖረዋል?

መጽሐፍ ቅዱስ የአንድ ቀን፣ የሰባት ቀናት፣ የሃያ አንድ እና የአርባ ቀናት ርዝመት ስላላቸው አጽዋማት ዘግቧል። የጊዜ ገደብ የለውም። ኢየሱስ ለአርባ ቀናት እንዲጾም "መንፈስ [ቅዱስ] ወሰደው" (ማቴ. 4፥1-2)፤ እኛም ስለ ጊዜው ርዝመት መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን መፍቀድ አለብን። ለነገሩ ጾም ለመጀመር መንፈስ ቅዱስን ለመስማት ንቁ የሆነ ክርስቲያን መቼ መቆም እንዳለበት ለማወቅም ንቁ ይሆናል።

## የጾም ደረጃዎች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ ከሚያስደንቁት የጾም ገጽታዎች አንዱ የጾም ደረጃዎች ናቸው። አንዳንዶች ያለ ምግብና ውሃ፣ ሌሎች ደግሞ ያለ ምግብ ሲጾሙ፣ ከወይንና ከአስደሳች ምግብ በመታቀብ የጾሙም አሉ። እነዚህን የተለያዩ ደረጃዎች በየፈርጃቸው መመልከቱ እንደሚረዳ አስባለሁ።

ምንም ምግብና መጠጥ የማይወሰድበት ጽኑ ጾም አለ። በሐዋርያት *ሥራ* 9፥9 የሚገኘው የጳውሎስ ጾም ጽኑ ጾም ነበር። ሙሴ ሕጉን ከእግዚአብሔር ሲቀበል ሲጾም የነበረው ጾም በዚሁ ክፍል ይካተታል። ለአርባ ቀናት ያለ ምግብና መጠጥ ቈየ፤ ጽኑና አስቸጋሪ ጾም።

በመደበኛ ጾም ውስጥ ሰው አይመገብም፤ ውሃ ግን ይጠጣል:: ይህ የተለመደ የጾም መንገድ ነው:: የኤልያስ ጾም ምናልባት መደበኛ ጾም ሳይሆን አይቀርም፤ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ያለ ምግብ መጓዙን ብቻ ነውና (1ነገ. 19፥8):: ጌታ ኢየሱስም በአርባ ቀናት ጾሙ ውሃ ይጠጣ እንደ ነበር ይታሰባል፤ ወንጌላቱ ስለ ረሃቡ እንጂ ስለ ጥማቱ አንዳች አይነግሩንምና::

ከዚያ ደግሞ *ከፊል* ጾም አለ:: ይህ በዳንኤል 10፥3 ላይ ተገልጿል፤ "ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ምርጥ ምግብ አልበላሁም፤ *ሥጋም* ሆነ የወይን ጠጅ ወደ አፌ አልገባም፤ ቅባትም አልተቀባሁም" (አ.መ.ት)::

## ጾም ለምን?

ይህን ጠቃሚ ነጥብ አጽንኦት እንድሰጠው ፍቀዱልኝ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጾም ዓላማ ሁልጊዜም *መንፈሳዊ* ነው፤ የሆነ መንፈሳዊ ግብ ለመምታት:: ጾም አካልን በማጥራትና ክብደትን በመቀነስ ለጤና አስተዋጽኦ ቢያደርግም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አተያይ ይህ ጾም አይደለም:: ለእኔ፣ እግዚአብሔር ለሆነ ምክንያት እንድጾም ሲመራኝ መፈጸም አይከብደኝም:: ረሃቡ ብዙም አያስቸግረኝም:: ክብደት ለመቀነስ ስጾም ግን በየአቅጣጫው ጦርነት ይፈጠራል::

## ለመንፈሳዊ መገራት መጾም

ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደምናየው እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲጾሙ ያዘዘበት ቀዳሚ ሐሳብ ራስን ማዋረድና ራስን ዝቅ ማድረግ ነው:: በመዝሙር 35፥13 ዳዊት እንዲህ ይላል፤ "እኔስ እነርሱ በታመሙ ጊዜ ማቅ ለበስሁ፤ ነፍሴንም በጾም አደከምኋት"::

እንደገናም በመዝሙር 69፥10 ላይ፣ "ነፍሴን በጾም አስመረርሁአት፤ ለስድብም ሆነብኝ" ይላል:: ይህ ውብ ሐሳብ ነው፤ *ጾም የነፍስ ለቅሶ ነው::*

ከዚያም በመዝሙር 109፥24፣ "ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ፤ *ሥጋዬም* ቅቤ በማጣት ከሳ" ይላል::

በዕዝራ 8፥21፣ "በአምላካችን ፊት ራሳችንን እናዋርድ ዘንድ ... በዚያ በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጾም ዐወጅሁ" የሚል እናነብባለን::

እግዚአብሔር ከሕዝቡ አብዝቶ ከሚፈልጋቸው ነገሮች አንዱ ትሑታን እንዲሆኑ ነው:: አንዳንዴ "ጌታ ሆይ፤ ትሑት አድርገኝ" ብለን እንጸልያለን:: ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጸሎት ነው ብዬ አላስብም::



እግዚአብሔር እኛን ትሑት ማድረግ እንዳለበት የሚናገር አንድም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አግኝቼ አላውቅም:: እርሱ ዝቅ ያደርገን ይሆናል፤ ነገር ግን እኛ ራሳችን ትሑት መሆን አለብን:: ይህ የእኛ ኀላፊነት ነው:: እደግመዋለሁ፤ ትሕትና (ራስን ማዋረድ) የእግዚአብሔርን ልብ ስለሚያስደስት እንዲባርከን ያስችለዋል:: ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ ያውጃል፤

> ጎበዞች ሆይ፤ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፤ *እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል::* እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኀይለኛው ከእግዚ አብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ:: (1ጴጥ. 5፥5-6 - አጽንኦት የተጨመረ)

ኢየሱስ ለደቀ መዝሙርነት ያደረገልን ጥሪ ሁለተንናችንን በእርሱ ውስጥ እናገኝ ዘንድ ራሳችንን እንድንክድ የሚጋብዝ ነው:: እውነተኛ (ከልብ የመነጨ) ኀዘን ከምግብ ፍላጎት ይበልጣልና ጾም የመለኮታዊ ኀዘን እና ንስሓ ትክክለኛ መግለጫ ነው:: ስለዚህም ጾም የውስጣዊ ንስሓችን ውጫዊ መግለጫ ይሆናል::

በአካላዊ ፍላጎትና በመንፈሳዊ መገራት መካከል ያለውን ግንኙነት አስታውሱ:: የሰዶም ኀጢአት "እንጀራን ከመጥገብ" ጋር የተያያዘ ነው (ሕዝ. 16፥49):: ስለ እስራኤልም ሲናገር እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "ካጠገብ ኋቸውም በኋላ አመነዘሩ" (ኤር. 5፥7):: የምግብና የመጠጥ ፍላጎት አላግባብ ለጥቅም ሲውል፣ በሌሎች አቅጣጫዎች ሕይወት ለጥቃት ይጋለጣል:: ተቃራኒውም እውነት ነው፤ አካላዊ ፍላጎቶች በቍጥጥር ሥር ሲውሉ፣ መንፈሳዊ ሕይወት ይጠነክራል፤ ይበረታልም:: ይህ ትልቅ አጽንኦት የሚያስፈልገው እውነት ነው:: *ጾም ሥጋን (አካልን) ለማስገዛትና የፍላጎት ገገር ለመሆን የሚያግዝ መንፈሳዊ ሥርዐት (መገራት) ነው::*

## ጾም እንደ መንፈሳዊ ባልንጀራ

ጾም ለብቻው የሚተገበረው ከስንትና ስንት አንዴ ነው:: ሁልጊዜም ከሌላ መንፈሳዊ ተግባር ጋር ይያያዛል:: ጾምን ለብቻው እንድንፈጽም የትም አልታዘዝንም፤ እንድንጾም *እና* እንድንጸልይ፤ ማቅ እንድንለብስ፣ ዐመድ እንድንነሰንስ (የመለኮታዊ ኀዘን እና ንስሓ ምልክቶች ናቸው) *እና* እንድንጾም፣ ጌታን *በጾም* እንድንፈልግ፣ ወይም ጌታን *በጾም* እንድናመልክ እንጂ::

ጾም እነዚህ ሌሎች መንፈሳዊ ልምምዶች ይበልጥ በውጤታማነት የሚተገበሩበትን ድባብ ይፈጥራል፤ መንፈሳዊ ልምምዶቹ በጾም መንፈስ ውስጥ ይበለጽጋሉ:: ለጸሎትና ጌታን ለመፈለግ ተስማሚ ድባብ ነው:: በጾም ራሳችንን ከምድር እናላቅቅና በጸሎት ራሳችንን ከሰማይ ጋር እናያይዛለን:: በጥልቅ መንፈሳዊ ጥሞና ወቅት ይበልጥ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እንድንተው ያስችለናል:: በጾም ወቅቶች ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ በጸሎት ውስጥ ይበልጥ ነጻነት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ይበልጥ አብርሆት፣ ለእግዚአብሔር ህልዎትም ይበልጥ ጥልቅ ስሜት እንደሚኖረኝ አስተውያለሁ::

በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጾም የመንፈሳዊ መረዳታችንን ከፍታ ይጨምረዋል፤ ለእግዚአብሔር ነገሮችም ይበልጥ ንቁ ያደርገናል:: የኢየሱስ የአርባ ቀናት የምድረ በዳ ጾም፣ መጋፈጥ ለነበረበት ኀይለኛ የሰይጣን ጥቃት አዘጋጅቶታል:: ዳንኤልም ከእግዚአብሔር ዘንድ መገለጥ የተቀበለው በጸሎትና በጾም ነበር:: በአንጾኪያ በነበረችው ቤተ ክርስቲያንም ጌታን ሲያመልኩና ሲጾሙ መንፈስ ቅዱስ ለጳውሎስና ለበርናባስ ያለውን ዕቅድ ገለጠላቸው:: ጳውሎስና በርናባስ ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን የሾሙትና ለጌታ አደራ የሰጧቸው በጸሎትና በጾም ድባብ ውስጥ ነበር:: ሙሴ ሕጉን ሲቀበል በጾምና በጥበቃ መንፈስ እንደ ነበር በዘዳግም 9፥9-10 ይናገራል::

## ለመለኮታዊ ጥበቃ መጾም

የነጻ መውጣትና የጥበቃ ጾም ምሳሌ በዕዝራ 8፥21-23 ይገኛል፤

*ራሳችንን በአምላካችን ፊት ዝቅ እንድናደርግ፣ ጉዞውም ለእኛና ለልጆቻችን፣ ለንብረታችንም ሁሉ የተቃና እንዲ ሆንልን፣* እዚያው በአኅዋ ወንዝ አጠገብ ጾም ዐወጅሁ:: "መልካሚቱ የአምላካችን እጅ በሚፈልጉት ሁሉ ላይ ናት፤ እርሱን በሚተዉ ሁሉ ላይ ግን ቍጣው ትወርድባቸዋለች" ብለን ለንጉሡ ነግረነው ስለ ነበር፣ በመንገድ ላይ ከጠላት የሚጠብቁን ወታደሮችንና ፈረሰኞችን እንዲሰጠን ንጉሡን ለመጠየቅ ዐፍሬ ነበር:: ስለዚህ ጾምን፤ ወደ አምላካችንም ስለዚህ ነገር ልመና አቀረብን፤ እርሱም ጸሎታችንን ሰማ:: (ኢ.መ.ት - አጽንኦት የተጨመረ)

ይህ ውብ ታሪክ ነው:: ሕዝቡ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም የአራት ወራት ጉዞ ሊጀምሩ ነው፤ ጉዞውም ሽፍቶች በተሰገሰጉበት ድንጋያማ ምድረ



በዳ ውስጥ የሚደረግ ነው:: ንጉሡ ዕዝራንና ሕዝቡን እንዲያጅቡ ወታደሮቹን ለመላክ ጠይቆ ነበር፤ ዕዝራ ግን የሚያስፈልጋቸው ጥበቃ አምላካቸው ብቻ መሆኑ ላይ ተመክቶ (ተኩራርቶ) እምቢ አለ::

በባቢሎን ቅጥር ውስጥ በሰላም እየኖሩ እግዚአብሔርን ስለ መታመን ማውራት ቀላል ነው:: የሚያግዛችሁ የሥጋ ለባሽ ክንድ በሌለበት በአደጋ መካከል ራሳችሁን ስታገኙ ግን ሌላ ታሪክ ነው:: እዚህ ጋ ነው በርካታ ክርስቲያኖች ለዓለም መሣለቂያ ምክንያት የሚሆኑት:: እግዚአብሔር ይመስገን፤ ቍርጠኛው ጊዜ ሲመጣ ዕዝራ ርዳታ ፍለጋ ወደ ዓለም አልሮጠም:: ይህን ማድረግ አሳፋሪ ሆኖ አግኝቶታል:: ምንም እንኳ ዕዝራ ሥጋ ለባሽ ቢሆንም፣ በሥጋ መሣሪያዎች አልተዋጋም፤ ጾም ዐውጆ እግዚአብሔርን ፈለገ እንጂ:: ጌታም ታደጋቸው::

ሁለተኛ ዜና ምዕራፍ 20 እስከ ዛሬ ከተካሄዱት ጦርነቶች ሁሉ ልዩ ስለ ሆነ እንግዳ ጦርነት ይተርካል (ምዕራፍ 4ን ተመልከቱ):: ንጉሡ ኢዮሳፍጥ ግዙፍ የሶሪያ ጦር ጥቃት ሊሰነዝርበት እየመጣ ነበር:: ጉዳዩን የተገነዘበው ኢዮሳፍጥ እጅግ ስለ ፈራ፣ "እግዚአብሔርንም ሊፈልግ ፊቱን አቀና፤ በይሁዳም ሁሉ ጾም ዐወጀ" (2ዜና 20፥3):: ከዚያም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤

> አምላካችን ሆይ፤ አንተ አትፈርድባቸውምን? ይህን የመጣ ብንን ታላቅ ወገን እንቃወም ዘንድ አንችልም፤ የምናደርገውን አናውቅም፤ ነገር ግን ዐይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው:: (ቍጥር 12)

እየጾሙና እየጸለዩ ሳለም እግዚአብሔር የጦርነት ዕቅድ ሰጣቸው:: ይኸውም ንጉሡ ከተዋጊ ሠራዊቱ በፊት የሙዚቃ ባለሞያዎችን እንዲልክ የሚጠይቅ ልዩ ዕቅድ ነበር:: ለእግዚአብሔር እንዲዘምሩና እንዲያመሰግኑ የተመደቡት እነዚህ መዘምራን ከሠራዊቱ ፊት ወጥተው፣ "ዝማሬውንና ምስጋናውን በጀመሩ ጊዜ ይሁዳን ሊወጉ በመጡት በአሞንና በሞዓብ ልጆች፣ በሴይርም ተራራ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ድብቅ ጦርን አመጣባቸው፤ እነርሱም ተመቱ" (ቍጥር 22):: በነገራችን ላይ፤ ይህ ታላቅ የጾም መግለጫ ነው - "ነገር ግን ዐይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው::"

በእኛም ዘመን እግዚአብሔር ከጠላቶቻችን የሚያድነንን (የሚታደገንን) የውጊያ ዕቅድ ለመግለጥ እየጠበቀ ሊሆን ይችላልን? እግዚአብሔርን የሚፈልግና በምድሪቱ ጾምን የሚያውጅ ሌላ ኢዮሳፍጥንስ እየጠበቀ ይሆን?

## የእግዚአብሔርን ቍጣ ለማስቀረት መጾም

እግዚአብሔር ተናግሯል፡፡ ነነዌ በአርባ ቀናት ውስጥ ትጠፋለች፡፡ ጉዳዩ እርግጠኛ የነበረ ከመሆኑ የተነሣ ፍርዱ ሲቀር፣ እየመጣ የነበረውን መዓት ያወጀው ነቢዩ ዮናስ እጅግ ተቈጥቶ ለመሞት እግዚአብሔርን ለመነ፡፡ ነገር ግን የዚያች ኀጢአተኛ ከተማ ንጉሥ ማቅ ለብሶና ዐመድ ነስንሶ ንስሓ ገባና ከተማ አቀፍ ጾም ዐወጀ፡፡ እናም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤

> እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደ ተመለሱ ሥራቸውን አየ፡፡ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም፡፡ (ዮናስ 3፥10)

## በምልጃና በጾም ነጻ መውጣት

እስከ አሁን ያየናቸው ምሳሌዎች በአብዛኛው የራስ ነጻ መውጣት ምሳሌዎች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር *ሌሎችንም* ነጻ ለማውጣት ምልጃንና ጾምን ይጠቀማል፡፡ ሦስት ጉዳዮችን እንድጠቅስ ፍቀዱልኝ፡፡

> በዕዝራ 10፥6 እንዲህ እናነብባለን፤
>
> ዕዝራም ከእግዚአብሔር ቤት ፊት ተነሥቶ ወደ ኤልያሴብ ልጅ ወደ ዮሐናን ጓዳ ገባ፤ ስለ ምርኮኞቹም ኀጢአት ያለቅስ ነበርና ገብቶ እንጀራ አልበላም፤ ውሃም አልጠጣም፡፡

ሕዝቡ በምርኮ ሳሉ እስራኤላዊ ያልሆኑ ሰዎችን በማግባት የእግዚ አብሔርን ትእዛዝ አፈረሱ፤ ዕዝራ ስለ ኀጢአታቸው የነበረው ኀዘንም በጾም ተገለጸ፡፡ ውጤቱም ሕዝቡ ኀጢአታቸውን እየተናዘዙ ጣዖት አምላኪዎችን (እስራኤላዊ ያልሆኑ ሰዎችን) ማግባታቸውን መተዋቸው ነበር፡፡

የምልጃና የጾም ሌላ ምሳሌ በነህምያ የመጀመሪያ ምዕራፍም ይገኛል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ሰው ወደ ኋላቸው ስለ ተመለሱ ሕዝቦች ይጸልያል፤

> ይህን ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፣ አያሌ ቀንም አዝን ነበር፤ በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር፤ እንዲህም አልሁ፣ "አቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ፣ ለሚወድ ዱህና ትእዛዝህን ለሚያደርጉ ቃል ኪዳንንና ምሕረትን የምትጠብቅ፣ ታላቅና የተፈራህ አምላክ ሆይ፣ እኔ ባሪያህ ዛሬ በፊትህ ስለ ባሪያዎችህ ስለ እስራኤል ልጆች ሌሊትና ቀን የምጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ ጆሮህ ያድምጥ፤ ዐይኖችህም ይከፈቱ፤ በአንተ ላይም ያደረግነውን የእስራኤልን ልጆች ኀጢአት እናዘዝልሃለሁ፤ እኔና የአባቴ ቤት በድለናል፡፡ (ነህ. 1፥4-6)



ከሙሴ የሚበልጥ በጸሎትና በጾም ሌሎችን ነጻ የማውጣት ምሳሌ አይገኝም፡፡ ሙሴ ምናልባት በቅዱሱ እግዚአብሔርና በኀጢአተኛ ሕዝብ መካከል ባለው ክፍተት መካከል መቆምን ከማንም በላይ (ከኢየሱስ በቀር) ያውቃል፡፡ ከመሞቱም አስቀድሞ የሥልጣን ወንበሩን በመተው ስለ እነርሱ ያደረገውን ምልጃ ያስታውሳቸዋል፤

> ስለ ሠራችሁት ኀጢአት ሁሉ፣ እርሱንም ለማስቈጣት በእግዚ አብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር ስላደረጋችሁ፣ እግዚአብሔር ሊያጠፋችሁ ከተቈጣባችሁ ከቍጣውና ከመዓቱ የተነሣ ስለ ፈራሁ፣ እንደ ፊተኛው በእግዚአብሔር ፊት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ወደቅሁ፤ እንጀራ አልበላሁም፣ ውሃም አልጠጣሁም፡፡ *እግዚአብሔርም በዚያን ጊዜ ደግሞ ሰማኝ፡፡* እግዚአብሔርም አሮንን ሊያጠፋው እጅግ ተቈጣው፤ *ስለ አሮንም ደግሞ በዚያን ጊዜ ጸለይሁ፡፡* (ዘዳ. 9፥18-20 - አጽንኦት የተጨመረ)

እስቡት እስቲ፤ *አንድ* ሰው በጾምና በምልጃ ዋጋ ከፍሎ፣ መላ አገሪቱ ከፍርድ ነጻ ወጣች፡፡ ክርስቲያኖች በጸሎትና በጾም እንዲህ ዐይነቱን ኀይል ለመጠቀም መብታቸውና ኀላፊነታቸው ቢነቁ በቤቶቻችን፣ በአብያተ ክርስቲያናችን፣ *በዓለማችን* ምን ሊከሰት እንደሚችል ለመገመት እንኳ እንደፍራለንን? ለመሆኑ፣ ነጻ የወጡ ሕይወቶች የማያቋርጥ ሰልፍ ከጨለማ ወደ ብርሃን መንግሥት ሲጎርፍ በዐይነ ኀሊናችሁ ማየት ትችላላችሁ? እስቸጋሪ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው ወደ ኢየሱስ የመጡላቸው አባቶችና እናቶች የደስታ ጩኸት ሰማያትን ሲያጥለቀልቅ መስማት ትችላላችሁ? በመቶዎች የሚቈጠሩ ማላጆች ምሽጉን ጥሰው የኀጢአት ምርኮኞችን ነጻ ሲያወጡ ሰይጣን በሽንፈት ሲወሸቅ ማየት ትችላላችሁ?

## የጾም ሽልማት

> ኢየሱስ እንዲህ አለ፤
>
> አንተ ግን በምትጾምበት ጊዜ ፊትህን ታጠብ፤ ራስህንም ተቀባ፤ በዚህም መጾምህ በስውር ያለው አባትህ ብቻ የሚያውቀው፣ ከሰዎች ግን የተሰወረ ይሆናል፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል፡፡ (ማቴ. 6፥17-18 - አ.መ.ት)

ኢየሱስ የሽልማትን አነሣሽነት አሳንሶ አልተመለከተውምና ከበጎ አድራጎትና ከጸሎት ጋር በጤናማ (በተገቢ) መንፈስ የጾሙ ብድራት እንደሚቀበሉ ቃል ገብቷል:: በሃይማኖተኝነታቸው በሌሎች ፊት ሞገስ ለማግኘት የሚጾሙ የሚያገኙትን ብድራት ደግሞ በቍጥር ዐሥራ ስድስት ይጠቅሰዋል፤ "ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል::"

ጌታ ኢየሱስ ዋጋን ለመናገር በቍጥር 16 ላይ የተጠቀመበት ቃል በቍጥር 18 ከተጠቀመበት የተለየ ነው:: የግብዞችን ዋጋ ለመናገር ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ዋጋው *አሁኑኑ እንደሚከፈል* እና *በሙሉ እንደሚከፈል* የሚናገር አንድምታ አለው:: በሌላ አገላለጽ "የሚያዩትን ነው የሚያገኙት":: በትክክለኛው መንፈስ ለሚጾሙ በምላሽነት የሚሰጠውን ዋጋ ለማስረዳት የተጠቀመበት ቃል ሐሳብ ግን በጊዜ ሂደት የሚገኝን መታደስ የያዘ ነው:: የጾም ዋጋ የትርፍ ድርሻው በየጊዜው እያደገ እንደሚሄድ የንግድ ተቋም ነው:: እግዚአብሔር የጾምን ዋጋ ከቀን ወደ ቀን ለእናንተና ለሌሎች መግለጡን ይቀጥላል::



# ክፍል አራት

# *የሚያደምጥ አምላክ*

## ፲፫ - አንዳንድ የጸሎት ለምኖች እና እንዴቶች

# እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚመልሰው ጸሎት

አንድ ሚሲዮናዊ በውጭ አገር ለሚያገለግሉ ሚሲዮናውያን ደብዳቤ በሚልክ የሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ካለች አንዲት ብላቴና ደብዳቤ እንደ ደረሰው ከጥቂት ጊዜአት በፊት አጫወተኝ:: አስተማሪያቸው እውነተኛና ታታሪ ሚሲዮናውያን እጅግ ሥራ ስለሚበዛባቸው ለደብዳቤዎቻቸው መልስ ላይሰጡ እንደሚችሉ ነግራቸው ነበርና የደረሰው ደብዳቤ በአጭሩ እንዲህ የሚል ነበር፤

*ውድ ቄሰ ሰሚዝ፣*

*እየጸለይንልህ ነው:: መልስ እየጠበቅን አይደለም::*

ትንሿ ልጅ ሳታውቅ የብዙ ክርስቲያኖችን የጸሎት ሕይወት ጠቅልላ (ጨምቃ) አቅርባዋለች፤ *እየጸለይንልህ ነው:: መልስ እየጠበቅን አይደለም::* እውነቱን ለመናገር ብዙዎቻችን ጸሎታችን ምላሽ ሳያገኝ ሲቀር አንደነቅም፤ ምላሽ ሲያገኝ እንጂ:: መሆን የነበረበት ግን ተቃራኒው ነው::

ቤቱ ያለውን ማብሪያና ማጥፊያ ስሜን መብራቱ በመብራቱ አልደነቅም:: የመኪናዬን ቍልፍ ሳዞር (ምሳሌው አጠራጣሪ እንደ ሆነ ዐውቃለሁ)፣ ሞተሩ በመነሣቱ አልደነቅም:: እናም እግዚአብሔር ጸሎቴን ሲመልስ ልደነቅ አይገባኝም ነበር:: የእግዚአብሔር ሐሳብ ጸሎታችን እንዲመለስ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ያልተመለሱ ጸሎቶች የመኖራቸውን እውነታ ቢቀበልም፣ ጸሎቶች እንደማይመለሱ ግን በፍጹም ግምት አይወስድም:: መልስ ያገኙ ጸሎቶች የዘወትር ሁነቶች እንጂ የተለዩ አጋጣሚዎች መሆን የለባቸውም::

ሆኖም ጸሎት ከክርስትና ሕይወት ግዙፍ ምስጢራት አንዱ ነው:: አንዳንድ ጊዜ፣ ጸሎቶቻችን በተከታታይ አዎንታዊ መልስ ሲያገኙ እንዴት መጸለይ እንዳለብን በመጨረሻ እንደ ተረዳን እናስባለን:: ከዚያ ደግሞ ጸሎቶቻችን በጥጥ ወደ ተወተፈ ጀሮ የሚደርሱ የሚመስልበትና መስመሮች ሁሉ እንደ ተያዙ የሚገልጥ ምላሽ የምናገኝበት ረጅም ወቅት ይገጥመናል::

ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን፣ “ጌታ ሆይ፤ ጸሎት አስተምረን” ማለታቸው አይገርምም:: ይህን ልብ በሉ፤ ጸሎት በተፈጥሮ ወይም ያለ አንዳች ጥረት አይመጣም - ልንማረው ይገባል:: ከሁሉ የላቀ መምህር እንዳለንና ለማስተማር ያለው ፍላጎትም እኛ ለመማር ካለን ፍላጎት እጅግ እንደሚልቅ ማወቅ መልካም ነው::

## የጸሎት አርአያ (ሞዴል)

መጸለይን በመማር ሂደት ውስጥ ሁለት ጥያቄዎች መፍትሔ ማግኘት አለባቸው፤ *እንዴት* እንደሚጸለይና ስለ *ምን* እንደሚጸለይ:: በጸሎት ውስጥ የምንጋፈጠው እያንዳንዱ ችግር በእነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን፣ ኢየሱስ ሁለቱንም በማቴዎስ 6፥1-13 መልሷቸዋል::

ይህ ምንባብ በእርግጥ የተራራው ስብከት አካል ነው:: እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚመልሰውን ጸሎት መንፈሳዊ ቅድመ ሁኔታዎችና የጸሎቱን ተለይቶ የሚታወቅ ይዘት ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሯቸዋል::

የክርስቶስ ዕቅድ በሃይማኖታዊ ሥርዐትነት የምንደጋግመው የጸሎት ቅርጽ መስጠት አይደለም፤ “በከንቱ መድገም” በማለት ከገለጸው ሐሳብ ጋር ይጋጫልና:: የጌታ ሐሳብ ስንጸልይ የምንከተለው ምሳሌ መስጠት ነው:: ይህ አርአያ (ሞዴል) ነው፤ ንድፍ ነው:: በመርሕ ደረጃ ሁሉንም ነገር ይሸፍናል፤ እግዚአብሔርን ልንጠይቀው የምንችለውንም ነገር ሁሉ አካትቷል:: መቼም ሊያጋጥመን የሚችለው እያንዳንዱ አስፈልጎት በዚህ ሞዴል ጸሎት ተሸፍኗል:: ስንጸልይ፣ ጸሎታችን ምንም ዐይነት ርዝመት ቢኖረው፣ እዚህ የሚገኙትን መርሖች መተንተናችን ነው፤ ዐፅሞቹን ሥጋ ማልበሳችን ነው:: ለመጸለይ መንገዱ ይህ እንደ ሆነ ኢየሱስ ተናግሯል:: በእነዚህ ዝርዝር ሁኔታዎች መሠረት የተጸለየ እያንዳንዱ ጸሎት ምላሽ ያገኛል::

ምላሽ ስለሚያገኝ ጸሎት አራት ክፍሎችን ከእነዚህ ጥቅሶች ማግኘት ይቻላል:: ነገር ግን እነዚህን አራት አስፈላጊ ነገሮች ከመመርመራችን አስ ቀድመን፣ የምንባቡን መዋቅር መመልከቱና ጠቅለል አድርጎ ማየቱ ይረዳናል:: የላቀው መምህር እያስተማረ ነው:: መጀመሪያ እንዴት **እንደማይጸለይ** ያስተምረናል፤ ከዚያም እንደዚያ የማይጸለይበትን ምክንያት ያቀርብልናል፤ በመጨረሻም፣ እንዴት **እንደሚጸለይ** ይነግረናል::

## እንዴት እንደማይጸለይ

ኢየሱስ ይህንን የተራራውን ስብከት ክፍል በማስጠንቀቂያ ነው የሚጀምረው፤



ሰዎች እንዲያዩላችሁ፣ መልካም ሥራችሁን በፊታቸው ከማድረግ ተጠንቀቁ፤ እንዲህ ካደረጋችሁ ከሰማዩ አባታችሁ ዋጋ አታገኙም:: ግብዞች በሰዎች ዘንድ ለመከበር ብለው በየጎዳናውና በየምኩራቡ እንደሚያደርጉት፣ አንተም ለድኾች ምጽዋት በምትሰጥበት ጊዜ ይታይልኝ ብለህ ጥሩምባ አታ ስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፤ እንዲህ የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል:: እናንተ ግን ለድኾች ስትሰጡ ቀኝ እጃችሁ የሚያደርገውን ግራ እጃችሁ አይወቅ፤ ምጽዋታችሁ በስውር ይሁን፤ በስውር የተደረገውን የሚያይ አባታችሁም ዋጋችሁን ይከፍላችኋል:: (ማቴ. 6፥1-4 - አ.መ.ት)

ኢየሱስ በጸሎት ውስጥ ስላሉ ሁለት የተለመዱ አደጋዎች - እንደ ግብዞች መጸለይና እንደ አሕዛብ መጸለይ - ያስጠነቅቀናል::

- ግብዞች በተሳሳተ መነሻ (ሰበበ ድርጊት) ይጸልያሉ::
- አሕዛብ በተሳሳተ መንገድ ይጸልያሉ::
- ግብዞች የጸሎትን ዓላማ ያበላሻሉ::
- አሕዛብ የጸሎትን ባሕርይ በተሳሳተ መንገድ ይገነዘባሉ::
- ግብዞች ሰውን ለማስደነቅ ይጸልያሉ::
- አሕዛብ እግዚአብሔርን ለማስደነቅ ይጸልያሉ::
- የግብዞች ስሕተት ሆን ተብሎ የተደረገ ነው::
- የአሕዛብ ስሕተት ባላዋቂነት የተደረገ ነው::

## እንደ ግብዞች አትጸልዩ (ቍጥር 5፣ 6)

አንዳንድ የግብዞችና የአሕዛብ መገለጫዎች በሁላችንም ውስጥ ተደ ብቀው ይገኛሉ:: ጸሎትን ሌሎችን ለማስደነቅና ትኩረት ለመሳብ የመጠቀም ፈተናው አለ፤ ይህ በውስጣችን ያለው ግብዝነት ነው:: እንደዚሁም፣ እግዚአብሔርን በረጅምና ድምፁ ጎልቶ በሚወጣ ጸሎት ማሳመን እንደሚቻል በማሰብ ያለ ማሰላሰልና ያለ ዝግጅት ወደ ጸሎት መጣደፍ አለ፤ ይህ ደግሞ በውስጣችን ያለው አሕዛብነት ነው:: እነዚህ ሁለት ሕጸጾች በእውነተኛ ጸሎት ውስጥ ያለውን ሕይወት አንቀው ስለሚይዙ መወገድ አለባቸው:: ይህ እንዴት እንደሚደረግ ኢየሱስ በቀጣዮቹ ቍጥሮች ይነግረናል::

**አሉታዊው አስተምህሮ፣**

ስትጸልዩ እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ እነርሱ ለሰዎች ለመታየት ሲሉ በየምኩራቡና በየመንገዱ ማእዘን ላይ ቆመው መጸለይን ይወዳሉና። (ኢ.መ.ት - ቍጥር 5ሀ)

**ምክንያቱ**

እውነት እላችኋለሁ፤ ሙሉ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። (ቍጥር 5ለ)

**አዎንታዊው አስተምህሮ፣**

አንተ ግን ስትጸልይ ወደ ክፍልህ ግባ፤ በሩንም ዘግተህ በስውር ወዳለው አባትህ ጸልይ፤ **በስውር** የተደረገውን የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል። (ቍጥር 6 - ኢ.መ.ት)

## እንደ አሕዛብ አትጸልዩ (ቍጥር 7-13)

**አሉታዊው አስተምህሮ፣**

አሕዛብ በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ። (ቍጥር 7)

**ምክንያቱ**

ስለዚህ አትምሰሉአቸው፤ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና። (ቍጥር 8)

**አዎንታዊው አስተምህሮ፣**

እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡

"በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤
ስምህ ይቀደስ፤
መንግሥትህ ትምጣ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች
እንዲሁ በምድር ትሁን፤
የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።
እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣
በደላችንን ይቅር በለን።
ከክፉም አድነን እንጂ
ወደ ፈተና አታግባን፤



መንግሥት ያንተ ናትና፤
ኀይልም፣ ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን"። (ቍጥር 9-13)

## እንዴት እንደሚጸለይ

እሁን እግዚአብሔር ሁልጊዜም ወደሚሰማው ጸሎት አራት ቅመሞች ትኩረታችንን እናዙር።

### 1. ከልባችን በቅንነት መጸለይ አለብን (ቍጥር 5)

በቍጥር 5 እንደምናየው ጸሎት በመጀመሪያ የልብ ቅንነትን ይጠይቃል። ኢየሱስ በሕዝብ ፊት የሚደረግን ጸሎት አላወገዘም፤ "ለሰዎች ለመታየት" ሲባል የሚደረግን ጸሎት እንጂ።

የሰከነው እውነት እነሆ። የሰው ከሁሉ ከፍ ያለውና እጅግ ቅዱስ የሆነው ተግባር ጸሎት ነው፤ በእርግጥም በጸሎት እልፍኝ ውስጥኛ መቅደስ ውስጥ ስንሆን ከኀጢአት አደጋ ነጻ ነን። ሆኖም ስርስር ከሚመጣና ነገርን ከሚያበላሽ የኀጢአት ኀይል እዚያ ውስጥ እንኳ ማምለጥ አንችልም። እጅግ የተቀደሱ አፍታዎቻችን የታላቅ ኀጢአቶች ወቅት ሊሆኑ ይችላሉ። የረከሱ ሐሳቦች፣ ተገቢ ያልሆኑ መነሣሻዎች እጅግ የተቀደሰውን ስፍራ ጥሰው በመ ግባት ጭቃማ እግራቸውን በዙፋን ከፍሉ ወለል ላይ በአብሪት ይጠርጋሉ።

በጣም የላቁ ተግባሮቻችን አንዳንድ ጊዜ እጅግ ዝቅ ባሉ ጎትጓች ምክንያቶች የተቀሰቀሱ ናቸው። "ከንቱነት" አለ ናፖሌዮን፣ "የአብዮት መንሥኤ ነው። ነጻነት ሰበብ ብቻ ነው።" በመጸለይ ጥረት ውስጥ ስለ ራሳችን እውነቱን እንደርስበት ይሆናል፤ ምናልባት በስውሩ የጸሎት መሠዊያ ውስጥ "የውስጣዊ" ንጽሕናችንን የመጨረሻ ፈተና እንገናኛለን።

ጸሎታችንን የመንፈሳዊ ደረጃ አርማ ስናደርገው ግብዝነት ይሆናል። ጸሎትን ሌሎችን ለማስደነቅ ስንጠቀምበት ግብዞችን እንሆናለን። በተለይ በሕዝብ ፊት የሚደረግ ጸሎት ለዚህ ፈተና የተጋለጠ ነው።

ከቅርብ ጊዜ በፊት እንዳገለግል የተጋበዝኩበት ኮንፈረንስ ሊቀ መንበር በሕዝብ ፊት በሚያደርጋቸው መሳጭ ጸሎቶች ተለይቶ ይታወቃል። ብዙዎች ሁሌም የጸሎቶቹን ውበት በማድነቅ በፊቱ ይናገራሉ። የትኛውም ሥጋ ለባሽ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ነበር። ለመጸለይ ሲቆም (ይህን ደግሞ አዘውትሮ ያደርጋል)፣ ተፈጥሯዊ ያልሆነ ወፈር ያለ የጉልፒት ድምፅ ማሰማትና ልታይ ልታይ የሚሉ ሐረጎችን እንደ ተራራ መቆለል እየተጠ

ናወተው መጣ:: ሼክስፒር እንኳ የሚመሰጥበት ዐይነት ነበር:: ለዚህ ሰው ጸሎት ትርኢት ለሕዝብ የሚቀርብ ዐውደ ርእይ ሆኖበታል:: ጸሎትን የሰዎችን ትኩረት ወደ ራሳችን ለመሳብ ስንጠቀምበት የምንጸልየው ወደ እግዚአብሔር ሳይሆን ወደ ሰዎች፣ የምንፈልገውም የእርሱን በረከት ሳይሆን የእነርሱን አድናቆት ይሆናል::

የጸሎት ብልሽት ረቂቅ ሊሆን ይችላል:: ለስብሰባ ከቤቴ በሺዎች የሚቈጠር ኪሎ ሚትር ርቄ በሄድኩበት ስፍራ አንድ ምግብ ቤት ውስጥ ቁርሴን እየበላሁ ነበር:: አስተናጋጇ ምግቤን ስታቀርብልኝ ራሴን ዝቅ አድርጌ እግዚአብሔርን አመሰገንኩ:: ግማሽ እንቁላል እንዳገባደድኩ የሆኑ ጥንዶች ወደ ጠረጴዛዬ ተጠጉና ሮናልድ ደን ስለ መሆን አለመሆኔ ጠየቁኝ:: መሆኔን ተናዘዝኩ::

"ወደ ምግብ ቤቱ ስትገባ" አለ ወንድዬው፣ "አንተ መሆንህን ለሚስቴ ነግሬአት ነበር፤ እርግጠኞች ግን አልነበርንም::"

ከዚያ ሚስትየው ቀጠለች፤ "ለማዕዱ ካመሰገንክ አንተ መሆንክን እንደምናውቅ ለባሌ ነገርኩት:: ጠበቅንህ፤ ራስህንም ዝቅ ስታደርግ አንተ እንደ ሆንክ ዐወቅን::"

እናም አሁን ምግብ ቤት ብቻዬን ስመገብ ስለ ምግቡ የምጸልየው በእውነትም አመስጋኝ ሆኜ እንደሆን ወይም የሆነ ሰው እየተመለከተኝ ሊሆን ስለሚችል እንደ ሆነ አላውቅም:: መንፈሳዊ ዝናችሁ አደጋ ላይ ሲወድቅ ምንም መነሻ ምክንያት ከምታጡ ትንሽ እንኳ ቢኖራችሁ ይሻላል::

የግል ጸሎታችን እንኳ በዚህ በሽታ ሊለከፍ ይችላል:: ከሁሉም መንፈሳዊ ተግባሮቻችን መካከል የዚህኛውን ያህል ለከንቱ ትዕይንት የተጋለጠ የለም:: አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የጸሎት ሕይወታቸውን በተመለከተ የበታችነት ስሜት ያለባቸው ይመስለኛል፤ እናም የመጸለይን "ምስጢር የተረዱ" ሲገጥ ሟቸው በአድናቆታዊ ፍርሀት ያዩአቸዋል:: ያም በጸሎት ወደምናሳልፈው ረጅም ሰዓት የሰዎችን ትኩረት በመሳብ ከበሬታን የመፈለግ ፈተና ውስጥ ይከትተናል:: በሌላ አነጋገር፣ ሙሉውን ሌሊት በጸሎት ማሳለፍና ይህንንም ለማንም አለመንገር እጅግ ከባድ ይሆናል::

በጸሎት እግዚአብሔርን በምንቀርብበት ጊዜ ከሙቼውም ይልቅ ሙሉ በሙሉ ቅንና በነገር ሁሉ እውነተኛ መሆን አለብን:: በግልጽነትና በእውነተኛ ነት፣ ለማስመሰልም ሆነ ለይምሰል ሳይሆን - ማለትም በንጹሕ መነሻ ስሜት ወደ ጸሎት ስንሄድ እግዚአብሔር በጸጋው ዙፋን ይቀበለናል::



አሃ፤ ችግሩ አለ ለካ:: ንጹሕ ያልሆነን መነሻ ስሜት እንደ ማስገዛት የሚያስቸግር ነገር የለም:: የገዛ ራሳችን የከፋ ጠላት ራሳችን ነን:: የክርስቶስ ትእዛዝ እጅግ የማይቻል ከመምሰሉ የተነሣ ተስፋ ቈርጠን ጭራሹኑ ላለ መጸለይ እናስብ ይሆናል:: በጸሎት ውስጥ ወዳለው ወደዚህ ልባዊ ቅንነት እንዴት ነው የምንደርሰው?

መልሱ በሚቀጥለው የጸሎት ቅመም ውስጥ ይገኛል::

## 2. **በምስጢር መጸለይ አለብን** (ቍጥር 6)

የሃይማኖት ምስጢሩ ምስጢራዊ ሃይማኖት ነው ሲባል አንድ ጊዜ ሰምቼ ነበር:: በሰዎች ለመታየት ከመጸለይ መዳኛው፣ እግዚአብሔር ብቻ ማየት በሚችልበት ቦታ - በምስጢር - መጸለይ መሆኑን ኢየሱስ ይነግረናል:: ይህን ሲናገር በጭራሽ በሰዎች ፊት መጸለይ እንደሌለብን መናገሩ አይደለም:: የቦታ ምስጢራዊነት ጠቃሚና ጌታችንም ሲተገብረው የነበረ ቢሆንም እንኳ እርሱ የሚናገርለት ምስጢራዊነት ከአካላዊነት ይልቃል::

በመሠረቱ የአደባባይ ጸሎታችን በግል ጸሎታችን ሊደገፍ ይገባዋል:: በመድረክ ብቻ የምንጸልይ ከሆነ ግብዞች ነን:: ታማኝነት የሞላበት ግላዊ የጸሎት ሕይወት ከሌለን የመድረክ ጸሎታችን ለታይታ የሚደረግ እንጂ ሌላ አይሆንም::

ኢየሱስ የሚናገርለት ምስጢራዊ ጸሎት በአደባባይም ሊደረግ ይችላል:: በዋናነት ምስጢራዊነቱ አእምሮአዊና መንፈሳዊ ነው:: ቍልፉ ሐረግ፣ "በስውር ወዳለው አባትህ ጸልይ" የሚለው ነው:: በአደባባይ ጸሎት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ከመጸለይ ይልቅ ወደ አድማጮቹ እንጸልይ ይሆናል:: እያንዳንዱ ሰው በየተራ ጮክ ብሎ በሚጸልይበት የጸሎት ጉባዔ ተካፍዬ ዐውቃለሁ፤ እያንዳንዱ ጸሎትም በልባዊ "አሜኖች" ይታጀብ ነበር - የእኔ ተራ እስኪደርስ ድረስ:: ለመጸለይ የእናንተ ተራ ሲሆን ሁሉ ነገር እንዴት ጸጥ እንደሚል አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? ስለዚህም አብረዋችሁ የሚጸልዩ ወገኖችን ጠምዝዞ "አሜኖች" የሚያወጣ ጸሎትን ፍለጋ የጸሎት ከረጢታችሁን ስታተራምሱ ራሳችሁን አግኝታችሁ አታውቁም?

ወይም የቤተ ሰብ የጸሎት ጊዜን ወደ ሰማዩ አባታችሁ በመጸለይ ፈንታ ቤተ ሰባችሁን ለመስበክ ተጠቅማችሁበት አታውቁም? ያው እንደ ምታውቁት፣ "ጌታ ሆይ ዮሐንስ ነገ አንበሳ •ግቢ ልወስደው እንደማልችል እንዲገባው አድርግ:: ሰላም ‑የቆሸሹ ልብሶቿን እንድትሰበስብና ክፍሏን

እንድታጸዳ እርዳት፤ በሳምንቱ መጨረሻም እንግዶች ይመጣሉና በላይ ግቢውን እንዲያጸዳ እርዳው" ዐይነቶቹን ማለቴ ነው::

በምስጢር መጸለይ "ወደ አባታችሁ መጸለይ" ነው:: ይህም *በሀልዎቱ ላይ ማተኰር* ማለት ነው:: ትኩረታችን በእርሱ ላይ፣ በፈቃዱ ላይ፣ በክብሩ ላይ ያነጣጥራል ማለት ነው:: በስፍራው ካሉት ከሌሎች ይልቅ የእርሱን *መገኘት* (ሀልዎት) ይበልጥ እናውቃለን ማለት ነው:: ዓለምን በውጭ አስቀርተን በሩን ስንዘጋ፣ በውስጥ ከእርሱ ጋር ቀርተን በሩን ዘጋነው ማለት ነው:: በሰዎች በተጨናነቀ ክፍል ውስጥ እንኳ እየጸለዩ በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ከእግዚአብሔርና ከእነርሱ በቀር አንድም ሰው የሌለ ያህል ሆነው ስለሚጸልዩ ጥቂት ሰዎች ሰምቻለሁ::

ሌላው በምስጢር የመጸለይ ትርጒም *ከእርሱ የምናገኘው ምስጋና ይበቃናል* ማለት ነው:: ኢየሱስ ስለ ግብዞች ጸሎት ሲናገር፣ "ዋጋቸውን ተቀብለዋል" ይላል (ቍጥር 2):: ስለ ጾም እንደሚናገረው ምንባብ ሁሉ እዚህም፣ "ሙሉ በሙሉ የሚፈጸም፣ ወዲያውኑ የሚደረግ፣ በኋላ የሚመጣ ቀሪ የሌለው" ክፍያን የሚያሳይ ቃል ነው የተጠቀመው:: በእርግጥም፣ ግብዞች የሚፈልጉት ይህንን ነው - እዚያው ዋጋ መቀበልን:: የሰዎችን ምስጋና ከፈለጉ፣ ሊያገኙት ይችላሉ:: ይህ ለየትኛውም ሰው እውነት እንደ ሆነ አስባለሁ፤ አንድ ሰው የዘመኑን ሰዎች ምስጋናና ጭብጨባ ማግኘት ላይ ልቡን ካዋለ፣ ምኞቱና የሕይወቱ አንቀሳቃሽ ኀይል ይህ ከሆነ፣ የፈለገውን ያንኑ ነገር ምናልባት ያገኝ ይሆናል:: ይህንን አጥብቆ የሚፈልግ ሰው የሚያገኘው ነገር የተገባው ነው - የሚያገኘው ግን ያንኑ ብቻ ነው:: "ዋጋቸውን ተቀብለዋል" - በሙላትና በመጨረሻ ክፍያነት::

ኢየሱስ ከአብ ስለሚገኘው ዋጋ (ክፍያ) ሲያወራ፣ በጾም ርእስ ጒዳይ እንዳደረገው ሁሉ እዚህም የሚጠቀመው የተለየ ቃል ነው፤ ሊከፈል የተዘጋጀን ካሳ፣ በንግድ ላይ እየተገኘ ያለን ትርፍ የሚጠቁም ቃልን:: አሁን በጸሎት መልሶች፣ ከእርሱ ጋር በሚኖር ተግባቦት በሚገኝ የእግዚአብሔር ሰላም፣ እግዚአብሔር በእኛ ጥያቄ መሠረት ሲሠራ በማየት፣ ከእርሱ ጋር ላለን ኅብረት ጥልቀት በማግኘትና በሌሎች በርካታ ተጨማሪ መንገዶች ዋጋችንን እንቀበላለን:: በፊቱ በምንቆምበት ቀን የምስጋናውን ስጦታዎች ስንቀበል ደግሞ ተጨማሪና ትልልቅ ክፍያዎች ይመጡልናል:: ግብዙን ሰው ከሰዎች ምስጋና በቀር ምንም አያረካውም፤ "የምስጢር ጸላዩንም" ከእግዚአብሔር ምስጋና በቀር ምንም አያረካውም::



በቲአትር መድረክ ላይ የምትተውኑ ተዋንያን ናችሁ እንበል:: የመድረኩ ተዋናይ እናንተ ናችሁ፤ ታዳሚዎቹ ፊታችሁ ተቀምጠዋል:: ቲአትሩ ሲያልቅ፣ የታዳሚዎቹን ጭብጨባ ትሰማላችሁ:: ለተመልካቾቹ ትተውናላችሁ፤ እነርሱም በተራቸው ያጨበጭቡላችኋል፤ ዋጋችሁን ተቀብላችኋል::

በጉባዔ ስትጸልዩ ግን ጉባዔው ተመልካቻችሁ (ታዳሚያችሁ) እንዳልሆነ ማስታወስ አለባችሁ:: ለእነርሱ አይደለም "የምትተውኑት":: *ታዳሚያችሁ እግዚአብሔር ነው፤* ጭብጨባውን፣ ምስጋናውን፣ አድናቆቱን ፍለጋ ለእርሱ ነው "የምትተውኑት"::

እንዲህ ዐይነቱ ሰው በአደባባይም ሆነ በጓዳ ከልቡ በቅንነት ለመጸለይ ችግር አይኖርበትም::

## 3. ቀለል አድርገን መጸለይ አለብን (ቍጥር 7-8)

ኢየሱስ እዚህ ጋ የኰነነው *ከንቱ* ድግግሞሽን እንጂ ድግግሞሽን አይደለም:: የግሪኩ ቃል ወደ አማርኛ ለመተርጐም የሚያስቸግር ቢመስልም የማነብነብ ወይም በቃላት ጎርፍ ውስጥ የመቀባጠር ሐሳብን ያዘለ ነው:: "እንደ አሕዛብ ስትጸልዩ አታነብንቡ" በማለት የሕያው ቃል ትርጒም ይገልጸዋል::

አሕዛብ አማልክቶቻቸው በጸሎቱ ርዝመትና በተነገሩት ቃላት ብዛት እንደሚመሰጡ ያምናሉ:: በዋናነት ለእነርሱ ጸሎት ማለት ለሚፈልጉት በረከት ብቁ እንደ ሆኑ አማልክቶቻቸውን የማሳመን ጒዳይ ነው:: አማልክቱ ዝለው የተጠየቁትን እስኪሰጡ ድረስ የማዳከም ጸሎት ነው::

በጸሎት ምን ያህል አሕዛብ መሆን እንደምንችል ያስደንቃል:: በሚቀጥለው ጊዜ ስትጸልዩ ራሳችሁን አድምጡ፤ አብዛኛው ጸሎታችሁ እግዚአብሔር ነገሮችን በእናንተ መንገድ እንዲያይ የማሳመን ሙከራ ሆኖ ታገኙት ይሆናል:: አንዳንድ ጊዜ የጸሎቴ አብዛኛው ክፍል፣ ጥብቁን የእግዚአብሔር እጅ ፈልቅቆ የምከፍት ይመስል፣ እግዚአብሔር እንዲያምንብኝ ወይም ራሴ ባበጀሁት መንገድ ከእኔ ጋር እንዲተባበር ከመሞከር ያልዘለለ እንደ ነበረ አልከድም::

ኢየሱስ እንደዚያ እንዳንጸልይ ይነግረናል:: ለምን? "ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና" (ቍጥር 8):: አሕዛብ ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ በመሆኑ የተሳሳተ ጸሎት ይጸልያሉ::

እንዴት እንደምንጸልይ የሚወስነው የእግዚአብሔር ጠባይ ነው፤ ስለዚህም ለጸሎት ዋናው ነገር የምንጸልየው ወደ ምን ዐይነት አምላክ እንደ

ሆነ ማወቁ ነው፡፡ ቅዱስ አውግስጢኖስ፣ “ጌታ ሆይ፤ የትኛው እንደሚቀድም እንዳውቅ ፍቀድልኝ፤ አንተን መጥራት ነው ወይስ አንተን ማወደስ? በተጨማሪም፣ አንተን ማወቅ ነው ወይስ አንተን መጣራት? *ሳያውቅህ ሊጠራህ የሚቻለው አለን? የሚያውቅህም፣ ከሆንከው በላይ አይጠራህምና”* በማለት ጸልዮአል (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡

ኢየሱስ እግዚአብሔርን የገለጸው “አባታችሁ” በማለት ሲሆን፣ ስንጸልይም “አባታችን ሆይ” እንድንል ነግሮናል (ቍጥር 9)፡፡ እነኚህ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔርን ለመጥራት ጥቅም ላይ የዋሉበት የመ ጀመሪያ ጊዜ ይህ ነው፡፡ ግንዛቤው በአዲስ ኪዳን ልዩት (unique) ቢሆንም በሚያሳዝን ሁኔታ ሐሳቡ ከአብዛኛው የዘመናችን ክርስትና የጠፋ ይመስላል፡፡ ኢየሱስ ሲጸልይ “አባት ሆይ” በማለት ነው፡፡ (እንዲህ ያልጸለየበት አንድ ቦታ ብቻ ሲሆን፣ ይኸውም “አምላኬ አምላኬ፣ ስለ ምን ተውኸኝ?” በማለት በመስቀል ላይ የጮኸበት ነው፡፡) ሐዋርያው ጳውሎስ በጸሎቱ እግዚአብሔርን የሚጠራው፣ “የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እና አባት” በማለት ነው፡፡ ልጅ አባቱን በሚያነጋግርበት ቅለትና አስፈልጎቱን አባቱ አስቀድሞ የሚያውቅ ለት ልጅ በሚኖረው እርግጠኝነት እንድንጸልይ ታዘናል፡፡

አንዳንዶች እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን አስቀድሞ እንደሚያውቅ የሚናገረው ዐረፍተ ነገር ጥያቄ ማቅረብ እንደማያስፈልገን እንደሚጠቁም ያምናሉ፡፡ “እግዚአብሔር አስቀድሞ ካወቀ፣ ምን መቸገር ያስፈልጋል? እንደ ሚያስፈልገን ካወቀና እንዲኖረን ከፈለገ እናገኛለን” በማለት ያስባሉ፡፡ አንድ ዝነኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ወደ ጸሎት ጓዳ የመግባትና ስለ ነገሮች ለእግዚአብሔር ልመና የማቅረብ ጉዳይ “ከጸሎት ጅምናስቲክነት” የዘለለ ነገር እንዳልሆነ ተናግሯል፡፡ የዚህ አመለካከት ብቸኛው ስሕተት፣ ሐሳቡ ሙሉ በሙሉ ስሕተት መሆኑ ነው፡፡

ኢየሱስ እግዚአብሔርን በዚያ መንገድ እንድንተረጕመው እንዳላሰበ ግልጽ ነው፡፡ በቀጣዮቹ ቍጥሮች የሐዋርያት ጸሎትን ሲያስከትል፣ የተወሰኑ ነገሮችን ለይተን በመጥቀስ እንድንጸልይ ይነግረናል፤ ከእነዚህ ልመናዎችም አንዱ የዕለት እንጀራ ነው፡፡ በእርግጥም አባታችን ይህ እንደሚያስፈልገን ከመጠየቃችን አስቀድሞ ያውቃል፡፡

ቃላቱ ለመጸለይ *እንድንበረታታ* እንጂ ከመጸለይ እንድንታቀብ የታቀዱ አይደሉም፡፡ ለአስፈልጎታችን እግዚአብሔርን ማሳመን እንደ ማይኖርብን ከመረዳት በሚመነጭ ልበ ሙሉነት ነው መጸለይ ያለብን፤ እኛ አስፈልጎታችንን ከማወቃችን በፊት እንኳ እንደሚያስፈልገን እርሱ ዐውቋል፡፡



ልጄ የኮሌጅ ተማሪ ሳለ በአብዛኞቹ የሳምንት መጨረሻ ቀናት ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል ተጕዞ ወደ ቤት ይመጣል፡፡ የሚመጣው እኔ የሰጠሁትን ግዙፍ፣ ጥቁር፣ የጃጀ ተንደርበርድ መኪና እየነዳ ሲሆን፣ መኪናውን በመስታዎት የተሠራ ዕቃ መጫኛና የሚያስገመግም ክላክስ አስገጥሞለት ስሙን መርፊ ብሎ ሰይሞታል (“የሚበላሽ ነገር ካለ መበላሸቱ አይቀርም” ከተባለው “የመርፊ ሕግ” ነው የወሰደው)፡፡ ቤት ሲመጣ አንዳንድ ጥገናዎች ካስፈለጉት በማለት መኪናውን አዘውትሬ እፈታትሻለሁ፡፡

አንድ ቅዳሜ ማለዳ ጥናት ክፍሌ ውስጥ በግዴለሽነት እየተንጎራደደ፣ በሐሳብ ተውጦ እዚህና እዚያ ሲመለከት ቈየና ቀስ ብሎ ስለ መኪናው ማውራት ጀመረ፡፡ በዝግታና በእርጋታ ጀመረና ወደ ኋለ የጥድፊያ ንግግር በፍጥነት ተሸጋገረ፡፡ መኪናው አዳዲስ ጎማዎች እንደሚያስፈልጉት ሊያሳምነኝ ነበር ሙከራው፤ ገንዘብ እንደሌለው፣ ጉድለቱ አስቸኳይ እንደ ሆነ፣ ብድር ልሰጠው እችል እንደ ሆነ፣ ምናምን ... በከንቱ መደጋገም ማውራቱን ቀጠለ፡፡ ትንፋሽ ለመውሰድ ንግግሩን ገታ ሲያደርግ ዘልዬ ገብቼ፣ “እስጢፍ፤ ዛሬ ጥዋት መኪናህን አይቼዋለሁ፤ አዳዲስ ጎማዎች እንደሚያስፈልጉህ ዐውቃለሁ” አልኩት፡፡

“በእውነት?”

“አዎን፡፡”

ስለ አስፈልጎቱ እኔን ማሳመን እንደማያስፈልገው ሲረዳ ጠቅላላው አቀራረቡ ተቀየረ፡፡ “ጸሎት” ይላል ሪቻርድ ትሬንች፣ “የእግዚአብሔርን ማመንታት ማሳመኛ አይደለም፤ በእግዚአብሔር ፈቃደኝነት ላይ ራስን መጣል ነው፡፡”

ጸሎትን ደጋግሞ ማቅረብ ሁልጊዜም ከንቱ አይደለም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ስለ ጸሎት ያቀረባቸው ሁለት ምሳሌዎች (ሉቃ. 11፥4-9 እና 18፥1-8) አጽንኦት ያልተቋረጠ ድግግም ነው፡፡ ኢየሱስ ራሱም በጌቴሴማኒ ሲጸልይ ሦስት ጊዜ ደጋግሟል፡፡ ደጋግሞ መጸለይ በሸክም የዛለ ልብ ማቃሰት ሊሆን ይችላል፤ ወደ እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ከመጮኽ በቀር አንዳች ልናደርግ የማንችለው ብርቱ ሸክም፡፡

## 4. **ለይተን በማሳወቅ መጸለይ አለብን** (ቍጥር 9)

ቀለል አድርገን የምንጸልየው እንዴት ነው? ጌታ ኢየሱስ በቀጣዩ ቍጥር ይነግረናል፤ “እንግዲህእናንተስ እንዲህ ጸልዩ (ቍጥር 9)፡፡ በተሳሳተ መንገድ ስለ መጸለይ ሲነግረን ቈየና አሁን ደግሞ ትክክለኛውን መንገድ

ያሳየናል፡፡ በቀላሉ መጸለይ በግልጽ ለይቶ መጸለይ ነው፡፡ በግልጽ ተለይተው የታወቁ ጸሎቶች "በሐዋርያት ጸሎት" ውስጥ አሉ፡፡

ቀደም ብዬ እንደ ጠቀስኩት፣ ጌታ ኢየሱስ ይህ ጸሎት ከመደበኛ ቡራኬነት ያለፈ እንዲሆን ነው ሐሳቡ፡፡ በግልም ሆነ በጋራ አምልኮአችን ላይ ብንጠቀመው ጥሩና ትክክልም ነው፤ በዋናነት የታቀደው ግን ለዚህ አይደለም፡፡ ከሁሉ በፊትና በቀዳሚነት ወደ ጸሎታችን የሚመራን ምሳሌ ነው፡፡

እዚህ ጋ ሁለት እውነታዎች ትኩረት ይሻሉ፤ አንድ፣ ጸሎት *ተግባር* ነው፡፡ ስንኖር የጸሎት ዝንባሌ እንዲኖረን ቢያስፈልግም፣ ጸሎት ከዝንባሌ ነትም ያልፋል፡፡ አንድ ሰው እንዳስቀመጠው፣ ሁሉ ነገር በክርስቶስ የእኛ መሆኑን መገንዘብ ብቻ አይደለም፡፡ ለክርስቶስ፣ ጸሎት ጅማሬና ፍጻሜ ያለው ተግባር ነበር፤ "ኢየሱስ ... ጸሎቱንም እንደ *ጨረሰ*" (ሉቃ. 11፥1 - ኢ.መ.ት)፣ *"ስትጸልዩ እንዲህ በሉ"* (ሉቃ 11፥2 - አጽንኦት የተጨመረ)፡፡

ሁለት፣ ጸሎት *ጥየቃ* ነው፡፡ ጸሎት ልመና ነው፤ ምስጋና አይደለም፡፡ በእርግጥ ግላዊ አምልኮአችን ምስጋናን ማካተት አለበት፤ በጸሎት ጊዜአችንም እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን፤ ነገር ግን ጸሎትና ምስጋና አንድ አይደሉም፡፡ ጸሎትን ለማመልከት ጥቅም ላይ ከዋሉ የተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት አብዛኛው እጅ፣ ከሞላ ጎደል አንድም ሳይቀር፣ ያለ አንዳች እፍረት፣ የልመና ቃላት ናቸው፡፡

ይህን ለማስረዳት የምደክምበት ምክንያት ቤተ ክርስቲያን የምስጋናን ምንነት እንደገና የተረዳች ስለሚመስል ነው - ስለዚህም ምስጋና በአስተምህሮም ሆነ በዝማሬ ከፍተኛ አጽንኦት እየተሰጠው ነው፡፡ ሆኖም የዚህ አጽንኦት እየጨመረ መሄድ አንዳንዶች የሚዛናዊነትን ድንበር እንዲጥሱ አድርጓቸዋል፡፡

በቅርቡ አንድ የኮንፈረንስ ተናጋሪ ስለ ምስጋና ሲያስተላልፍ በነበረው መልእክት በክርስቶስ እያደግን (እየበሰልን) ስንመጣ ምስጋና ልመናን እንደሚተካ - ጥየቃ እያነሰ፣ ምስጋና እንደሚጨምር አትቷል፡፡ ከዚያም፣ እስካሁን የጸሎት "የልመና እርከን" ላይ ከሆንን *ሥጋውያን* መሆናችንን እስከ መናገር ደርሷል፡፡ ዘልዬ በመነሣት፣ "እንዲህማ ከሆነ፣ ኢየሱስም *ሥጋዊ* ነበር" በማለት እንድናገር የተፈጠረብኝን ውስጣዊ ጉትጎታ መቋቋም አልቻልኩም ነበር፤ ምክንያቱም ከሞላ ጎደል ሁሉም የኢየሱስ ጸሎቶች የልመና ጸሎቶች ነበሩ፤ ስለ ራሱ ያደረጋቸው ልመናዎች፡፡ የጳውሎስም ጸሎቶች ልመናዊ ነበሩ፡፡ ክርስቶስም ሆነ ጳውሎስ እንድንጠይቅና መጠየቃችንን እንድንቀጥል አስጠንቅቀውናል፡፡



ጌታ ያስተማረን ጸሎት ("የሐዋርያት ጸሎት") መቶ በመቶ የልመና ነው፡፡ "ስምህ ይቀደስ" የሚለው ሐረግ እንኳ ልመና ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ፣ "ስትጸልዩ አስቀድማችሁ ማድረግ ያለባችሁ ነገር የአብን ስም መቀደስ ነው" በማለት አይደለም የተናገረው፡፡ "ስትጸልዩ፣ 'ስምህ ይቀደስ' በሉ" ነው ያለው፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ስም ይቀደስና ይከበር ዘንድ የሚጠይቅ ልመና ነው፡፡

የሐዋርያት ጸሎት በትእዛዝ መልክ ከቀረቡ ስድስት ልመናዎች የተገነባ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ልመና ወቅትም እግዚአብሔርን አንድን በግልጽ የተጠቀሰ ጉዳይ እንዲፈጽም እየጠየቅነው ነው፡፡ ጸሎቱ እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ልመናዎችን የያዙ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ ጸሎቱ ላይ መደበኛ ማብራሪያ ማዘጋጀት የራሱን አንድ መጽሐፍ ይጠይቃል፤ እዚህ ማቅረብ የምንችለው ዋና ዋና ሐሳቦቹን ብቻ ነው፡፡

የጸሎቱ የመጀመሪያ ክፍል *የአብን ክብር* ይመለከታል (ቍጥር 9፣ 10)፡፡

እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚመልሰው ጸሎት የእርሱን ጥቅም ከእኛ በማስቀደም ለአብ ክብር ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ይህም ራስን ባዶ የማድረግና በእግዚአብሔር ነገሮች የመጠመድ አንድምታ አለው፡፡ ስለ ራሳችን ማሰብ የምንችለው በዚህ ሁኔታ ራሳችንን ከረሳን በኋላ ብቻ ነው፡፡

1. የእግዚአብሔር ስም ይከበር ዘንድ መጸለይ አለብን፤ "ስምህ ይቀደስ፡፡"
2. የእግዚአብሔር አመራር ይመሠረት ዘንድ መጸለይ አለብን፤ "*መንግሥትህ ትምጣ፡፡*"
3. የእግዚአብሔር ፈቃድ ይፈጸም ዘንድ መጸለይ አለብን፤ "ፈቃድህ ... ትሁን፡፡"

የጸሎቱ ሁለተኛ ክፍል *የቤተ ሰብን አካላዊና መንፈሳዊ ደኅንነት ይመለከታል*፡፡

1. ለዕለታዊ መግቦት መጸለይ አለብን፤ "የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፡፡"
2. ለዕለታዊ ይቅርታ (ምሕረት) መጸለይ አለብን፤ "በደላችንን ይቅር በለን፡፡"

3. ለዕለታዊ ጥበቃ (ከለላ) መጸለይ አለብን፤ "ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን::"

በምሳሌ ጸሎቱ መግቢያ ላይ በጠቅላላው ጸሎት ላይ ጥላውን የሚያጠላ ሐረግ አለ፤ ይኸውም መድረኩን ለልመናዎች በማዘጋጀት ለእውነተኛ ጸሎቶች ሁሉ መሠረት የሚያበጅ ነው፤ "አባታችን ሆይ::" እነዚህ ሁለት ቃላት መላውን ጸሎት ያጠቃልላሉ::

*የእኛ::* ቃሉ ብዙ ጊዜ ትኩረታችንን እንደማያገኝ ግልጽ ነው:: *የእኛ* አባት:: የዕለት እንጀራችንን *(የእኛን እንጀራ):: በደላችንን (የእኛን በደል):: (እኛን) አታግባን:: (እኛን)* አድነን:: ይህ ቤተ ሰባዊ ጸሎት ነው:: የትኛውም የእግዚአብሔር ልጅ ብቻውን አይጸልይም:: አንዱ ልጅ ሲጸልይ መላው ቤተ ሰብ እንደሚጸልይ ይታሰባል:: ይህም ጌታ ኢየሱስ፣ "አባት ሆይ፤ አንተ በእኔ እንዳለህ፣ እኔም በአንተ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ" (ዮሐ. 17፥21) በማለት ኋላ ላይ ለተከታዮቹ ሲጸልይ ምን ማለቱ እንደ ሆነ ጥቆማ ይሰጣል::

*የእኛ::* ይህ ምልጃ ነው - ራስ ወዳድነት የሌለበት ምልጃ:: የቤተ ሰቡ አባል ስለ ራሱ ብቻ አይደለም የሚጸልየው፤ ለእያንዳንዱ የቤተ ሰቡ አባል እንጂ:: ለራሱ የሚፈልገውን ለመላው ቤተ ሰብም ይፈልጋል:: እንደ አንድ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባል፣ አንድነቱ እንደ ተዋቀረበት አካል፣ እያንዳንዱ አባል እንዲኖረው የማልፈልገውን ነገር ለራሴ የመጠየቅ መብት የለኝም:: በመጨረሻ ጸሎቱ ምንም ዐይነት ቢሆን፣ ከሌሎች ቀድሜ እንድ ደራጅ፣ ከሌሎች የሚበልጥ ይዞታ እንዲኖረኝ፣ በአብ ፊት ከሌሎች የተሻለ ቅርበት እንድይዝ፣ ቤተ ክርስቲያኔ እዚያ ማዶ ካለችው ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ እንድታድግና እንድትበለጽግ ማድረጊያ መንገድ አይደለም::

*አባት* ሌላኛው ቃል ነው:: ሁሉም ጸሎት ይህን እንዲያሟላ ይጠበቅበታል:: ጸሎት የቤተ ሰብ ጉዳይ ነውና "አባታችን ሆይ" ማለት የሚችሉ ብቻ በእውነት (በትክክል) መጸለይ ይችላሉ::

ይህ የመጸለይ መብታችን ነው:: በጀርባ በር ተኮልኩለን ምጽዋት (እርጥባን) ለማግኘት የምንለማመጥ ለማኞች አይደለንም:: በአብ ገበታ የተቀመጥን ልጆች ነን:: ጄ ዲ ጆንስ ከአንድ ጦር ሜዳ በድል አድራጊነት ወደ ሮም እየተመለሰ ስለ ነበረ ንጉሥ አንድ ታሪክ ይነግረናል:: አስደናቂው ባለ ግርማ ሰልፍ ወደ መንገዱ ሲቃረብ አንድ ትንሽ ልጅ መንገዱ ዳርና ዳር በመሰመር በመቆም አጥር በሆኑት ወታደሮች ሥር ሾለከና ንጉሡን ወደ ያዘው



ውድ ሰረገላ አቀና:: አንዱ ወታደር ጨምድዶ ያዘውና "ያ እኮ ንጉሡ ነው" በማለት ጮኸበት::

ልጁም ራሱን አስለቅቆ አመለጠና ወደ ሰረገላው እየሮጠ፣ "*የአንተ ንጉሥ፣ የእኔ* አባት" በማለት ጮኾ መለሰ::

እግዚአብሔር እኛን መሳዮችን በዙፋን ክፍሉ በመቀበልና አሳዛኝ ጥያቄዎቻችንን በመስማት እንዲቸገርልን ምን መብት አለን?

ስንጸልይ፣ *"አባታችን ሆይ"*.ማለት አለብን::

## ፲፮ - የእግዚአብሔር ሉዐላዊነት ምስጢር

# ዝምታ በሰማይ

እግዚአብሔር የሕይወቴን ሁለት ግዙፍ ጸሎቶች አልመለሰም። ሁለቱንም የምፈልጋቸው መልስ ካገኙ ሌሎች ጸሎቶቼ ሁሉ ይልቅ ነበር፤ ለእነዚህ ለሁለቱ ጸሎቶቼ ስል በደስታ ሁሉንም ማጣት እፈቅድ ነበር። ደንግጫለሁ፤ ግራ ገብቶኛል፤ ተጎድቻለሁ።

የደነገጥኩበት ምክንያት እግዚአብሔር ሊመልሳቸው እንደሚወድ ዐውቅ ስለ ነበር ነው። ለእኔና ለካዬ ቃል ገብቶልን ነበር፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ "ቃል" ነበረን፤ የሚጠበቅብንንም በሙሉ አድርገን ነበር፤ አምነናል፤ በእምነት ጸልየናል፤ ዐውጀናል፤ እንደ ተፈጸመ አድርገን ወስደነዋል፤ ደሙን ረጭተናል፤ ዲያብሎስን ገሥጸናል፤ ስለ መልሶቹ እግዚአብሔርን በቅድሚያ አመስግነናል - ጾመናልም። እግዚአብሔር ከአሁን በፊት በርካታ እንደዚህ ዐይነት ጸሎቶችን መልሷል።

ግራ የተጋባሁበት ምክንያት በጸሎት ላይ መጽሐፍ እየጻፍኩ ስለ ነበር ነው። በአገሪቱ እየዞርኩ ሰዎች እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው እየተናገርኩና አብያተ ክርስቲያናት የጸሎት አገልግሎቶችን እንዲያቋቁሙ እያገዝኩ ነበር። በጥሩ ሁኔታ እያደገና እያፈራ የነበረው የቤተ ክርስቲያኔ የጸሎት አገልግሎት ከሩቅ ስፍራዎች እንኳ ትኩረት እየሳበ ነበር። እንዴት እንደሚጸለይ ዐውቃለሁ። ጸሎት ልዩ ስጦታዬ ነበር።

የተጎዳሁበት (የተቈጣሁበት?) ምክንያት እግዚአብሔር ስለ ከዳኝ ነበር። እኔም እንደ ኤርምያስ፣ "አቤቱ፤ አታለልኸኝ፤ እኔም ተታለልሁ" ማለት አሰኘኝ (ኤር. 20፥7)። አሞኝቶኛል፤ ለትንንሽ ጸሎቶች ትልልቅ መልሶችን በመስጠት አስጎምጅቶኛል፤ ትልቁ ጸሎት ሲመጣ ግን፣ ምንም። መልስ የለም፤ ማብራሪያ የለም፤ ምንም ነገር የለም። ሰማይ ዝም ብሏል።

የጸሎት ሕይወቴ ጠወለገ። ለመጸለይ ስሞክር፣ "ምን እያደረግህ ነው? ሰንደገና እየጸለይክ ነው እንዴ? ባለፈው ጊዜ መች ጠቀመህና! ዝም ብለህ ነው ጊዜህን የምታባክነው" በማለት እነዚያ ያልተመለሱ ሁለት ጸሎቶች እንደሚያሽካኩ ሁለት ግልፍጥ ጋኔኖች በላዬ ያንጓብባሉ።



ጸሎቶቼ ጕሮሮዬ ውስጥ ይሞታሉ።

ሲ. ኤስ ሌዊስ ቀጣዩን ሲጽፍ ተሰምቶት ሊሆን የሚችለው ስሜት እንደ ተሰማኝ አስባለሁ።

> በዚህ መካከል እግዚአብሔር የት ነው? ይህ እጅግ ዕረፍት ከሚነሡ (የበሽታ) ምልክቶች አንደኛው ነው። ደስተኛ ስትሆኑ፣ ማለትም እርሱ እንደሚያስፈልጋችሁ እስኪ ጠፉችሁ ድረስ እጅግ ስትደሰቱ፣ በምስጋና ፊቱ ከቀረባችሁ እጆቹን ዘርግቶ ይቀበላችኋል። ነገር ግን እስቲ ጭንቅ ውስጥ ገብታችሁ፣ ሌላው ሁሉ ርዳታ ከንቱ ሆኖባችሁ ወደ እርሱ ሂዱ፣ ምንድን ነው የምታገኙት? በሩ ፊታችሁ ላይ ተወርውሮ ሲዘጋ፣ ከውስጥ በኩል ሲቀረቀርና ተደጋግሞ ሲቈለፍ ነው የምትሰሙት። ከዚያ በኋላ - ጸጥታ። ፊታችሁን አዙራችሁ ትሄዱም ይሆናል።[1]

እግዚአብሔር ግን በዚያ መልኩ ሕይወቴ እንዲጠናቀቅ አል ፈቀደም። በጭራሽ ነገሩን ማስተዋል እንደማይችል እስኪያስተውል ድረስ እየወደደውና እያስተማረው ወንበዴውን ተከታተለው። ስሜቶቼ የአላዋቂነቴ እንጂ የግዴለሽነቱ ውጤቶች እንዳልሆኑ ተማርኩ። እግዚአብሔር ከነገረ መለኮታችን በላይ ነው፤ ስለ ጸሎት ያለን ሐሳብ እርሱን አያስረውም። እግዚአብሔር ሉዐላዊነቱን የሚያስናክል ምንም ዐይነት የስምምነት ሐሳብ አይፈጽምም፤ ቃልም አይገባም። የእግዚአብሔርን ሉዐላዊነት በጥንቃቄ የማያስቀምጥ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜም ሆነ ተዛምዷዊ ፍታቴ የተሳሳተ ትርጓሜ ነው። ጒጒቴና ናፍቆቴ እግዚአብሔርን አያስረውም። የእኔ ምኞት እርሱን አያዘውም።

### መሠረታዊዎቹ ሕግጋት

በዐሥራዎቹ ዕድሜ የነበረውን ልጃቸውን ከሁለት ወራት በፊት ከቀበሩ እናትና አባት ጋር ባለፈው ምሽት አብሬ ነበርኩ። በልጅነቱ አካል ጉዳተኛ በሚያደርግ በሽታ ተጠቅቶ ነበር። ሞቱ አይቀሬ ነበር። ቤተ ሰቦች የሚወዱትን ሰው ከቀበሩ በኋላ የሚያወሯቸውን የተለመዱ ነገሮች ስንነጋገር ቈየን። በተለያዩ ሐረጋትና ቃላት እየቀያየርን ያቀረብናቸው ጥያቄዎቻችን የትኛውንም ቅርጽ ቢይዙ ሄደው ሄደው አንድ ጥያቄ ጋ ነው የሚደርሱት፤

"ለምን?" የጎረቤት ልጆች ሲሯሯጡ፣ ሲጯጯኹና ሲሥቁ መስኮት ጋ ቆመው እየተመለከቱ ይህን ጥያቄ አለመጠየቅ ከባድ ነው:: በዚህ ጊዜ ከጌታ የምትገኝ ትንሽ ብርሃን ረጅም ርቀት ታስጉዛለች:: ከልክ ያለፈ ነገር መጠየቅ አይደለም አይደል?

ለሁለት ሰዓታት ስናወጣና ስናወርድ ከቈየን በኋላም አልበቃንም:: ማለት እችል የነበረውን ብቸኛ ነገር አልኳቸው:: ሁሉ ከተነገረና ከተደረገ በኋላ ወደዚህ ነው የሚደረሰው፤ "እግዚአብሔር በሰማይ፣ አንተም በምድር ነህ" (መክ. 5፥2)::

ይህን በአእምሮ ማኖሩ መልካም ነው:: መሠረታዊ ሕግጋቱ እነዚህ ናቸው::

> በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሰው ጥሶ ሊያልፍ የማይችለው ክፍት ቦታ አለ:: ይህን ማድረግ ቢቻለው ኖሮ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረው ግንኙነት ላይ ኀይል ይኖረው ነበር፤ ስለዚህም በራሱ በእግዚአብሔር ላይ ኀይል ይኖረው ነበር:: ነገር ግን የትኛውም ፍጥረት እንዲህ ዐይነት ኀይል የለውም:: ፍጥረት እንዲህ ዐይነቱ ኀይል እንዳለው ማመን (ማሰብ) ጣዖት አምልኮ ነው::[2]

እኛ ግን ይህንን "ክፍት ቦታ" አንቀበልም:: ዐቅመ ቢስነታችንን ያስታውሱናልና ለምስጢራት ቦታ የለንም:: ያዕቆብ ሲታገለው የነበረው "ሰው" መለኮታዊ ኀይል ያለው መልአክ መሆኑን ከተረዳ በኋላ፣ "እባክህ ስምህን ንገረኝ" በማለት የጠየቀው ለዚህ ነው (ዘፍ. 32፥29 - አ.መ.ት)::

የጥንቱ ሰው የሕይወት ዕጣውን በሚወስኑ መለኮታዊ ኀይላት እንደ ተከበበ ያምን ነበር:: ከእነዚህ ኀይላት መካከል አንዱ በሚታይና በሚዳሰስ መልኩ ከተገለጠ መለኮታዊ ኀይሉን ለግል ዕቅዱ መሳካት መጠቀም እንዲችል አጥብቆ መያዝ፣ አለመልቀቅና ከራሱ ጋር ማሰር እንዳለበት ያስባል:: እምነቱም፣ የዚህን ኀይል ስም ካወቃችሁ እንዲመጣ ልታዝዙት፣ ልታስገድዱት፣ እንደ ፈቃዳችሁ ልትጠመዝዙት እንኳ እንደምትችሉ እስከ ማሰብ ይደርሳል::

> ስለዚህ፣ ከሰው ልጅ ጥያቄዎች ሁሉ እጅግ አስቸኳይ በሆነው በዚህ ስምን ለማወቅ በሚሰነዝር ጥያቄ ውስጥ የሰው አስፈልጎት ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ፊት ያለው ድፍረት ሁሉ ... ተጠቅልሎ ይገኛል:: ይህንን እግዚአብሔርን የማግኘትና ከራሱ ጋር የማሰር የሰው ልጅ ጥንታዊ ጥማት ማዳፈን የሚችል ምንም ፍላጎት የለም::[3]



ማኑሄ ስለ ሳምሶን ውልደት የምስራች ይዞ ለሚሰቱ የተገለጠላትን የእግዚአብሔር መልአክ ሲገናኝ ተመሳሳይ ታሪክ በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ይገኛል:: ማኑሄ ያዕቆብ የጠየቀውን ተመሳሳይ ጥያቄ ይጠይቃል፤ "ነገርህ በደረሰ ጊዜ እንድናከብርህ ስምህ ማነው?" (መሳ. 13፥17):: ስሙ ግን ድብቅ (ቍጥር 18)፣ እጅግ አስፈሪና ቅዱስ በመሆኑ ሊነገር የማይቻል ነበርና እንደ ያዕቆብ ምስጢራዊ ተጋጣሚ ሁሉ መልአኩም ለጥያቄው መልስ አልሰጠም:: ምስጢሩና ነጻነቱ እንዲነካበት አልፈቀደም::

## የእግዚአብሔር ምስጢራዊ ነጻነት

እግዚአብሔር እንደ መረጠው ለመሥራት ነጻ ሆኖ ይኖራል:: ለምሳሌ የዚህ መጽሐፍ መነሻ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከሕዝቅኤል 22፥30 ውሰዱ፤ "ቅጥርን የሚጠግንን፣ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፤ ነገር ግን አላገኘሁም::" ውጤቱስ? "ስለዚህ ቍጣዬን አፈሰስሁባቸው" (ቍጥር 31):: የሚማልድ ባለመኖሩ ምክንያት እግዚአብሔር ቍጣውን አፈሰሰ::

ከዚያም በኢሳይያስ 59፥16 ላይ፣ "ሰውም እንደሌለ አየ፤ ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ" የሚል እናነብባለን:: አሁንም እግዚአብሔር በቅጥሩ ክፍተት በኩል የሚቆም፣ ማላጅ ፈለገ፤ ነገር ግን አላገኘም:: ውጤቱ? "የገዛ ክንዱ መድኀኒት አመጣለት፤ ጽድቁም አገዘው::" የሚማልድ ባለመኖሩ ምክንያት እግዚአብሔር ድነቱን አደረገ::

በሕዝቅኤል፣ እግዚአብሔር ሰው አለማግኘቱ ኀይሉን በፍርድ ለማሳየት ጥሩ አጋጣሚ ሰጠው:: በኢሳይያስ፣ እግዚአብሔር ሰው አለማግኘቱ ኀይሉን በማዳን ለማሳየት ጥሩ አጋጣሚ ሰጠው::

ጽጌረዳዎች ሁሉ ቀይ መሆናቸውን ካመንን፣ አንድ ሰው ቢጫ ጽጌረዳ ቢያመጣልን በማስመሰል የተሠራ እንደ ሆነ እንናገራለን - ሁሉም ጽጌረዳዎች ቀዮች ናቸውና:: ችግር ውስጥ የምንገባው እዚህ ጋ ነው፤ እግዚአብሔር ጸሎታችንን የሚመልስበትን ጊዜ፣ ስፍራና ዘዴ ያካተተ የአእምሮ ምስል አበጅተን እግዚአብሔርን የመጠባበቅ ክፉ ልማድ አለን::

እኛ ልናየው እንችላለን፤ ጸሎታችን ሊመለስ የሚችልበት፣ ችግሩ መፍትሔ የሚያገኝበት አንድ መንገድ ብቻ መኖሩ ግልጽ ነው:: ማንም ሊያየው ይችላል::

እግዚአብሔር ልክ እኔ በጠበቅሁት መንገድ ስለ መሥራቱ ብዙ ጊዜ ማስታወስ አልችልም፡፡ ግልጹን ነገር ወስዶ በተቃራኒው የሚፈጽምበት መንገድ አለው፡፡ ምላሹ ያስቀመጥነውን ምስል እጅግ ካለመምሰሉ የተነሣ እግዚአብሔር ጭራሹኑ መልስ እንዳልሰጠ የምናስብባቸው አንዳንድ ወቅቶችም አሉ፡፡ አይሁዳውያን በኢየሱስ ጉዳይ እንደዚሁ ነው ያደረጉት፡፡ ኢየሱስ መሲሑ መምሰል አለበት ብለው የሚያስቡት ምስል የለውም፤ ስለዚህ መሲሕ እንዳልነበር ደመደሙ፡፡

እግዚአብሔር ጸሎትን የሚመልስባቸው መንገዶች እስከዚህ ሰዓት ድረስ ምስጢር ሆነውብኝ ቀርተዋል፡፡ መሆን ያለበትም እንዲሁ ነው - ማን ዐውቆ የጨረሰውን አምላክ ማምለክ ይፈልጋል?

## ለማመን ዝግተኛ

ምርጥ ጓደኞችን ለራሴ አግኝቻለሁ፡፡ አንዳንድ ትልልቅ መልካም ሰዎች መለኮታዊ መገረሞችን በልባቸው ተሸክመዋል፤ በምላሽ መገረም እና በምላሽ አልባነት መገረም፡፡ ከእነዚህ መካከል እጅግ ያገዙኝ ሁለት ሰዎች የመጥምቁ ዮሐንስ ወላጆች ዘካርያስ እና ኤልሳቤጥ ናቸው፡፡

ሉቃስ በወንጌሉ የመጀመሪያ ምዕራፍ፣ "ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ፤ ሚስቱም ... ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ" በማለት ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ የሚሄዱ ጻድቃን እንደ ነበሩ በመናገር ጥንዶቹን ያስተዋውቀናል፡፡ "ኤልሳቤጥም መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜያቸው አርጅተው ነበር" (ሉቃ. 1፥5-7)፡፡

አንድ ቀን ዘካርያስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ዕጣን እያጠነ ሳለ የጌታ መልአክ በዕጣን መሠዊያው በስተቀኝ በኩል ተከሰተና፣ "ዘካርያስ ሆይ፣ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ" አለው (ቍጥር 11-13)፡፡

ከዚያም ዘካርያስ ክስተት አምጪ ጥያቄውን አቀረበ፤ "ይህን በምን ዐውቃለሁ? እኔ ሽማግሌ ነኝ፤ ሚስቴም በዕድሜ ገፍታለች" (ቍጥር 18 - አ.መ.ት)፡፡ ክስተት አምጪ ብዬ የሰየምኩበት ምክንያት እኔ ድንገት መልአክ ፊቴ ተገልጦ ጸሎቴ እንደ ተሰማልኝ ቢነግረኝ ወደ ማመን ስለማዘነብል ነው፡፡ ይህኛው መልአክ ደግሞ ተራ መልአክ አልነበረም፤ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ገብርኤል እንጂ (ቍጥር 19)፡፡ ሆኖም ልዩ መልእክት ይዞ መልእክተኛ መገለጡ እንኳ ዘካርያስን አላሳመነውም፡፡ ስለዚህም የመልአኩን



ቃል አላመነምና እግዚአብሔር በድዳነት መታው፡፡ እግዚአብሔር ዛሬም አለማመንን በዚህ መንገድ የሚገናኝ ቢሆን ኖሮ አብዛኞቻችን በቀረው ሕይወታችን ሁሉ መናገር አቅቶን በቀረን ነበር፡፡

ዘካርያስ ጥያቄውን ለማቅረብ ጥሩ ምክንያት ነበረው፤ ባልተመለሱ ጸሎቶች ዓመታትን ማሳለፉ ለማመን ዝግተኛ አድርጎታል፡፡ ገብርኤል የጠቀሰው፣ ልጅ ለማግኘት ያቀረቡት ጸሎት ታሪክ ለመሆን የተቃረበ ሳይሆን አይቀርም፤ ሁለቱም ልጅ መውለጃ ዕድሜን ካለፉ ብዙ ቈይተዋልና፡፡ በነገራችን ላይ ዘካርያስ ይህንን ውብ አድርጎ ነው የገለጸው፤ "ይህን በምን ዐውቃለሁ? እኔ ሽማግሌ ነኝ፤ *ሚስቴም በዕድሜ ገፍታለች"* በማለት፡፡ "እኔ ሽማግሌ ነኝ፤ ሚስቴም አሮጊት ናት" ወይም "እኔ አርጅቻለሁ፤ ሚስቴም አርጅታለች" አላለም፡፡ ዘካርያስ ጠንቃቃ ዲፕሎማት ነበር፡፡

የመልአኩን ቃል በመጠራጠሩ ብዙ ልንፈርድበት አይገባም፡፡ አባት የመሆን ሕልሞቹ ለእውነታው እጅ ከሰጡ ቈይተዋል፡፡ እናም ግን ...

... እዚህ ደግሞ በቀጥታ ከእግዚአብሔር የመጣ መልአክ ፊቱ ቆሞ ነገሩ እንደሚከሰት ያረጋግጥለታል፡፡ ዘካርያስ እግዚአብሔር ጸሎትን እንዴት እንደሚመልስ አንዳንድ ነገሮችን መማር ጀመረ፡፡ በቀጣዩ ምዕራፍ ታሪኩን ስንከተል፣ ምናልባት እኛም እንማር ይሆናል፡፡

*ማስታወሻ፡- ዛሬ ላይ ሆነን ከሚታየን ይልቅ ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት ብዙ ይታየናል፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ስለ እነዚያ ያልተመለሱ ሁለት ጸሎቶቼ ሳስብ ስለ ጸሎትና ስለ እግዚአብሔር የተማርኩባቸው፣ መልስ ያገኙ ሌሎች ጸሎቶቼ ተጣምረው ከተማርኩት ይበልጣል፡፡ ማን ያውቃል፤ ወደ ጌታ በምሄድበት ጊዜ እግዚአብሔር ትክክለኛውን ነገር እንዳደረገ አስብም ይሆናል፡፡*

## ማስታወሻ

1. C. S. Lewis, *A Grief Observed* (New York: Seabury Press, 1963) 4, 5.
2. Paul Tillich, quoted by Mark Kline Tylor, *Paul Tillich, Theologian of the Boundaries* (San Francisco, Collins Liturgical Publications, 1987) 106.
3. Gerhard Von Rad, *Genesis* (Philadelphia: The Westminster Press, 1972) 322.

## ፲፯ - አንዳንድ መንገዶቹ ላይ ምልከታ

# እግዚአብሔር ጸሎትን እንዴት እንደሚመልስ

*ዘካርያስ እግዚአብሔር ጸሎቱን ሲመልስለት ደንግጦ ነበር::*

*እግዚአብሔር ጸሎቴን ስላልመለሰልኝ ደንግጬ ነበር::*

የዘካርያስን ድንጋጤ ከእኔ ይልቅ ወድጄዋለሁ:: በጸሎቱ ከእኛ የተሻለ ስኬት ስላለው እግዚአብሔር ጸሎትን እንዴት እንደሚመልስ እንዲያሳየን ብንፈቅድለት ይሻለናል::

## እግዚአብሔር ቈይቶ ይመልሳል

*መቼ ነው እግዚአብሔር ጸሎትን የሚመልሰው?*

*ብዙውን ጊዜ ወዲያውኑ ሲመልስ፣ አንዳንድ ጊዜ ግን ቈይቶ ነው::*

ብልጥ ለመሆን እየሞከርኩ አይደለም:: "የሚመለስ" ጸሎት ስንጸልይ፣ ማለትም እንደ ፈቃዱ የሆነ ጸሎት ሲሆን (1ዮሐ. 5፥14፣ 15)፣ ወዲያውኑ ሰምቶ ይመልሳል:: እግዚአብሔር እውነታዎቹን ለመመርመር፣ ለመማከርና ለመስማማት ኮሚቴ አይሰበስብም:: የቀረበለትን ጥያቄ ለማጤንም ጊዜ አያስፈልገውም:: "እንዲህም ይሆናል፤ ሳይጠሩ እመልስ ላቸዋለሁ፤ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ" (ኢሳ. 65፥24)::

ጸሎቱ *የሚፈቀደው* ወዲያውኑ ነው፤ በእጃችን *የሚገባው* ግን ምናልባት ዘግይቶ ይሆናል::

መልአኩ ይህንን ነበር ለዘካርያስ ለመንገር ሲሞክር የነበረው፤ "ጸሎትህ ተሰምቶልሃል" (ሉቃ. 1፥13):: የቃሎቹ አቀማመጥ ዘካርያስ በዚያን ቀን ቤተ መቅደስ ውስጥ እያገለገለ እንኳ ልጅ ለማግኘት ሲጸልይ የነበረ ያስመስላል:: እውነታው ግን፣ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ በወቅቱ ጸሎቱን እያካሄዱ ያልነበረ መሆኑ ነው:: ዘካርያስ ለመልአኩ ያቀረበው ጥያቄ ጸሎቱን ካቆሙ



ረጅም ጊዜ እንደ ሆናቸው ያሳያል:: ልጅ ለማግኘት የነበራቸው ምኞት የከሰመ ተስፋ ነበር:: አሁን የዘካርያስን ጥያቄ በተሻለ መረዳት እንችላለን::*

ቀደም ብሎ ለተተወው የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ጸሎት ስለ ተሰጠው ምላሽ ሌላ ፍንጭ አለ:: "ጸሎትህ ተሰምቶልሃል" የሚለው ዐረፍተ ነገር ጠቃሚ ነው:: "ተሰምቷል" ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል "ተሰምቶ ነበር" ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፤ ዐውዱ ግንዛቤ ውስጥ ከገባም እንዲህ ተብሎ መተርጐም አለበት:: ይህ በቀድሞ ጊዜ ውስጥ ቀርቦ የነበረ ጸሎት - እና በቀድሞ ጊዜ የተመለሰ ጸሎት ነበር::

በግሪኩ ንባብ ውስጥ "ተሰምቷል" የሚለው ቃል አብሮት የተያያዘ ቅድመ ቅጥያ (ምዕላድ) አለው፤ ይህም ቃሉን በአዲስ ኪዳን ውስጥ አምስት ጊዜ ብቻ የሚገኝ ብዙም ያልተለመደ ቃል አድርጎታል:: ቅድመ ቅጥያው ዓላማን፣ ተግባርን፣ ዝንባሌን፣ ውጤትን ይገልጻል:: ቅድመ ቅጥያውና ግሱን ያካተተ የቃል በቃል ትርጉም ይህን ይመስላል፤ "ጸሎትህ *ለመደረግ ተሰምቶ ነበር*":: እግዚአብሔር ጸሎትን ሲሰማ፣ *ያደርገዋል::* እግዚአብሔር ምናልባት ጥያቄአቸውን ከዓመታት በፊት ነው የፈቀደው፤ አሁን ደግሞ *ሊሰጣቸው* ነበር::

የዚህን ተመሳሳይ ሐሳብ በዳንኤል ዐሥረኛ ምዕራፍ ውስጥም እናያለን:: ነቢዩ ምንም ዐይነት ምላሽ ሳያገኝ ለሦስት ሳምንታት እየጸለየና እየጾመ ቈይቷል:: ከዚያም ተከታዩን መልእክት ይዞ መልአክ ተገለጠለት፤

> ዳንኤል ሆይ፣ አትፍራ፤ ልብህ ያስተውል ዘንድ፣ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት *ከመጀመሪያው ቀን* ጀምሮ ቃልህ ተሰምቷል፤ እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ:: የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ እነሆም፣ ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፤ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውኩት:: (ዳን. 10፥12-13 - አጽንኦት የተጨመረ)

---

* የጸሓፊው ማስታወሻ:- አንዳንድ ተርጓሚዎች የዘካርያስ ጸሎት መሠዊያው ዘንድ ከነበረው ቈይታ ጋር መጣጣም እንደ ነበረበት ይናገራሉ:: ለግላዊ ባርኮት መጸለይ በእርሱ ደረጃ ላለ ሰው የማይታሰብ ስለ ነበረ፣ ወንድ ልጅ ለማግኘት ያቀረበው ጸሎት በመሠረቱ ስለ ሕዝቡ ነጻ መውጣት (መዳን) ወይም ቃል ስለ ተገባው መሲሕ እንደ ሆነ ያስባሉ:: ሆኖም ይህ የተጠመዘዘ ትርጓሜ ዐውዱንና ተውላጠ ስሙን ከግምት አይከትም፤ ለምሳሌ፣ "ሚስትህ [የአንተ ሚስት] ወንድ ልጅ [ለአንተ] ትወልድልሃለች" የሚለውን::

ይህ ከእነዚህ ቃላት ላይ የሸረሪት ድር ማጥሪያ ቦታ አይደለም:: ለእኛ ዓላማ ፋይዳ ያለው ዳንኤል ለሦስት ሳምንታት ሲጸልይና ሲጾም የነበረና በዚያ ጊዜ ማለቂያ ላይ መልአክ መልስና ማብራሪያ ይዞ የመምጣቱ እውነታ ነው:: የዳንኤል ጸሎቶች በጸለያቸው በመጀመሪያ ቀን ተሰምተው ነበር፤ በዚያው በመጀመሪያ ቀን መልአኩ መልሱን እንዲያደርስ ተልኮ ነበር፤ ነገር ግን የመንገድ መጨናነቅ ለሃያ አንድ ቀናት አዘግይቶታል::

"ከመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቷል::" *የተፈቀደው ወዲያውኑ ነው፤ የተሰጠው ግን ዘግይቶ ነው::*

ሁላችንም ለዚህ የጸሎት የተስፋ ቃል ቤተኞች ነን፤ "የጸለያችሁትን፣ የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁ እመኑ፤ ይሆንላችሁማል" (ማር. 11፥24):: የ1997 ትርጉም፣ "ስለዚህ በጸሎት ማናቸውንም ነገር ብትለምኑ፣ እንደ *ተፈጸመላችሁ* አድርጋችሁ እመኑ፤ የምትለምኑትም ሁሉ *ይሰጣችኋል"* ይላል (አጽንኦት የተጨመረ)::

አዲሱ መደበኛ ትርጉም ደግሞ፣ "በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደ ተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል" በማለት ያስቀምጠዋል::

አንድን በእጃችሁ የገባ ነገር እንደ ተቀበላችሁት ለማመን ብዙም እምነት አይጠይቅም:: ገና እጃችሁ ያልገባን ነገር እንደ ተቀበላችሁት ማመን ግን - ይሄ ነው እምነት::

## እግዚአብሔር በተሻለ ይመልሳል

ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ቈይቶ የሚመልሰው በተሻለ ለመመለስ መሆኑን ዘካርያስ ተምሯል::

የጽሕፈት ጠረጴዛዬ ላይ ባለው የእርሳስ መያዣ ላይ፣ "እግዚአብሔር ምርጫውን ለእርሱ ለሚተዉለት ምርጡን ነገር ይሰጣቸዋል" የሚል ጽሑፍ አለ:: እውነት አይደለምን?

አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምኑት ምን እንደሚል ስለማያውቁ እንደ ሆነ አስባለሁ:: ለምሳሌ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙር 34፥10 ላይ፣ "እግዚአብሔርን የሚፈልጉት ግን ከመልካም ነገር ሁሉ አይጎድሉም" ይላል:: በመዝሙር 84፥11 ደግሞ ይህንን ተስፋ ይገባል፤ "እግዚአብሔር፣ በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያጎድላቸውም::" ይህንን በእውነት እናምናለንን?



ታዲያ እግዚአብሔር አንድ ነገር ሲያስቀርብን ለምን እናጉረ መርማለን? ነገሩ የሚጠቅመን ቢሆን ኖሮ ይሰጠን ነበር:: የቢሊ ግራሃም ሚስት ሩት ግራሃም ሲናገሩ፣ "እግዚአብሔር እያንዳንዱን ጸሎቴን መልሶልኝ ቢሆን ኖሮ፣ የተሳሳተ ባል ሰባት ጊዜ አገባ ነበር" ብለዋል:: ስለ አንዳንድ ያልተመለሱ ጸሎቶች እግዚአብሔር ይመስገን::

እግዚአብሔር ቈይቶ ብቻ አይመልስም፤ ነገር ግን የተሻለ ይመልሳል:: ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ለማግኘት መጀመሪያ እንደ ጸለዩ፣ በወጣትነታቸው ሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮ ብለን እናስብ:: እጅግ ይደሰቱና ልጁን በሙሉ ልባቸው ይወዱት እንደ ነበር እርግጠኛ መሆን እንችላለን:: በመጨረሻው ግምገማ ግን ልጁ ተወልዶ፣ ኑሮውን ኖሮ እንደ ሚሞት እንደ ማንኛውም ሌላ ልጅ የማይታወስ እፍኝ ዐፈር ሆኖ ነበር የሚቀረው:: ዛሬ ማንም አያስታውሰውም ነበር፤ ስለ እርሱ የሚካሄድ ምንም ስብከት አይኖርም ነበር፤ ስሙም ሆነ የወላጆቹ ስም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሕያው አይሆንም ነበር::

እግዚአብሔር ሌላ የተሻለ ነገር ሰጣቸው:: መጥምቁ ዮሐንስን፣ የመጨረሻውን የብሉይ ኪዳን ነቢይ፣ ትንቢቱ ሲፈጸም ያየውን ብቸኛ የብሉይ ኪዳን ነቢይ ሰጣቸው:: ልጃቸው የኢየሱስ የአክስት ልጅ፣ ለመሲሑ መንገድን የሚጠርግ መልእክተኛ፣ "ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም" በማለት ኢየሱስ የተናገረለት ሰው ነበር (ማቴ. 11፥11)::

እግዚአብሔር ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥ በስተርጅና ወንድ ልጅ የማግኘትን ያልተጠበቀ ደስታ፣ በእነርሱ ዕድሜ ያሉ ጥንዶች የማያገኙትን ልዩ ደስታ፣ ለብዙ ዓመታት በተደረገ ጥበቃ የተገዛ ደስታን ሰጣቸው:: ዕድሜአቸው እየቀነሰ ሲሄድ ደስታቸው ከፍ እያለ ሄደ:: እግዚአብሔር ምርጡን ስጦታ እስከ መጨረሻው አቈየው::

በእርግጥ በወቅቱ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ላይስማሙ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል:: ምናልባት፣ እስኪያረጁ ድረስ መጠበቁ መልካም እንዳልሆነ ያስቡ ይሆናል:: *እኛ ግን የተሻለ እናውቃለን::*

## እግዚአብሔር ሁኔታው በሰው ዘንድ የማይቻል ሲሆን ይመልሳል

እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ሁኔታው በሰው ዘንድ የማይቻል እስኪሆን እንደሚቈይ ዘካርያስ ተረድቷል::

ቤተ ክርስቲያናችን የምልጃ ጸሎት አገልግሎቷን እንደ ጀመረች እንግዳ ነገር ተከሰተ:: ፊቷ ላይ ድንጋጤ የሚነበብባት አንዲት ወጣት አንድ

እሁድ ማለዳ የአምልኮ አገልግሎቱ መገባደጃ ላይ ወደ ጎን ጎተት አደረገችኝና በጆሮዬ ማንሾካሾክ ጀመረች:: ስላልዳኑ ባሎቻቸው ትልቅ ተስፋ ይዘው በአዲሱ የጸሎት አገልግሎታችን ከተመዘገቡ በርካታ ሴቶች አንዷ ናት:: ይህ ከሆነ ሦስት ወር ሆኗል::

"አንድ ችግር ተፈጥሯል" አለች በሹክሹክታ::

"ምን?"

"ባሌ" አለች:: "ለሦስት ወራት ስጸልይለት የነበረው እና ..."

"እና?"

እንባ በዐይኖቿ ግጥም አለና ላለማልቀስ ትታገል ጀመር:: "ብሶበታል" ፈንቅሏት ወጣ:: "በእግዚአብሔር ላይ፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ፣ በእኔ ላይ ጥላቻው ጨምሯል:: ነገሩ እየተሻሻለ አይደለም - እየባሰ እንጂ::"

ተመሳሳይ መልእክቶችን ከሌሎችም ተቀብያለሁ:: አንድ ሰው ከበርካታ ወራት በፊት ወደ ጥናት ክፍሌ መጣና ሥራው ላይ ስለ ተከሰተው አሳሳቢ የገንዘብ ችግር ለመጸለይ ቃል ኪዳን ገባን:: በኋላ፣ ነገሮች እንዴት እየሄዱ እንደ ሆነ ስጠይቀው፣ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ "አስፈሪ ነው" በማለት መለሰ:: ከዚያም እጁን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጎ፣ "ታውቃለህ መጋቢ፣ አንዳንዴ፣ ወደዚህ ጸሎት ጉዳይ በጭራሽ ባልከተትከኝ ኖሮ እያልኩ እመኛለሁ" አለኝ እየቀለደ (እኔ እንደማስበው)::

ይህ ከእግዚአብሔር መንገዶች አንዱ ነው፤ ብዙውን ጊዜ ጣልቃ ከመግባቱ በፊት ሁኔታው እንዲባባስ ይፈቅዳል:: በዘካርያስና ኤልሳቤጥ ጉዳይም ሁለቱም ልጅ መውለጃ ዕድሜን እስኪያልፉ ጠብቋል:: አካላዊ ሁኔታው የማይቻል ሲሆን፣ እግዚአብሔር ልጅ ሰጣቸው::

አንዳንዴ ነገሮች ከመሻሻላቸው በፊት ይባባሳሉ:: ይህ ከተከሰተ እንዳይደናገጡ ጀማሪ ማላጆችን አስጠነቅቃለሁ:: ስጸልይላቸው የነበሩ ሰዎች ቀስ በቀስ ስሜታቸው ከግዴለሽነት ወደ ጠላትነት ሲሸጋገር ተመልክቻለሁ:: ይህ የመንፈስ ቅዱስ የመውቀስ ሥራ ምልክት ሊሆን እንደሚችል አምናለሁ:: እግዚአብሔር በአንድ ግለ ሰብ ላይ እያጠበበበት ሲመጣ ያ ሰው ግዴለሽ ሆኖ መቅረት አይችልም - ጠላትም የተወሰደበትን ግዛት እንደገና ለመያዝ መልሶ ማጥቃቱን እንደሚጨምር መገመት ይቻላል::

በሌላ አገላለጽ፣ የምጸልይበት የትኛውም ጉዳይ ወደ መሻሻል ሲሄድ መባባስን ጎብኝቶ እንደሚያልፍ ተረድቻለሁ::



እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከሣራ ጋርም እንዲሁ ነው የሠራው:: እግዚአብሔር አብርሃም የብዙ ሕዝብ አባት እንደሚሆን፣ የምድር ሕዝቦች ሁሉ በዘሩ እንደሚባረኩ፣ ዘሩ እጅግ ከመብዛቱ የተነሣ እርሱን ከመቍጠር የሰማይ ከዋክብትን መቍጠር እንደሚቀልል ቃል ገብቶለት ነበር:: "አብራምም በእግዚአብሔር አመነ" (ዘፍ. 15፥6)::

የዕድሜ መግፋት እየወረሳችሁ ሲመጣና ምንም ሳይከሰት ሲቀር እምነታችሁ መቆየት ከባድ ነው:: ማመን በእርግጥም ከመክበዱ የተነሣ አብርሃም ወደ እስማኤል እንደ ሮጠው እናንተም ለምትክ ትሮጣላችሁ:: እግዚአብሔር ቀድሞ *የፈቀደውን* ነገር *ለመስጠት* አብርሃም 100 ዓመትና ሣራም 90 ዓመት እስኪሞላቸው ጠበቀ::

እግዚአብሔር ተስፋውን ቢያድስም እንኳ (ዘፍጥረት 17)፣ አብርሃም ለማመን ተቸገረ::

> ሣቀም፤ በልቡም አለ፤ የመቶ ዓመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሣራ ትወልዳለችን? (ዘፍ. 17፥17)

አብርሃም ሣቀ:: ምን ያድርግ *ታዲያ*? ሐሳቡ አስቂኝ ነበራ! የሣቀው ስላላመነ ነበር::

ሣራም እንዳላመነች እናውቃለን፤ እርሷም *ሥቃለችና*:: አንዲት የ90 ዓመት አሮጊት ማርገዟን ካወቀች የምታደርጋቸው ብዙ ነገሮች ይኖሯት ይሆናል፤ መሣቅ ግን አንዱ አይደለም::

እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ለምን ይሠራል?

## እግዚአብሔር ለክብሩ ይመለሳል

*እግዚአብሔር ሁልጊዜም ይበልጥ ክብር የሚያመጣለትን መንገድ ይጠቀማል::* ይህንን፣ "የማይለወጥ የሰማይ ሕግ" በሚለው ማህደር ውስጥ ልንከትተው እንደምንችል አምናለሁ:: በምዕራፍ 4 እንዳየነው፣ እኛ ጥያቄ ከማቅረባችንና እርሱ ምላሽ ከመስጠቱ ጀርባ ያለው መነሻ ሐሳብ፣ "አብም ስለ ወልድ እንዲከበር" ነው (ዮሐ. 14፥13):: እነዚህን ነገሮች ወደ ኋላ ሄደን ባየናቸው ቍጥር ሁሉም ነገር ወደዚህ ፍጻሜ እንደሚያመራ ይበልጥ እናስተውላለን፤ ወደ እግዚአብሔር ክብር:: አብርሃም፣ "ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠ ... በእምነት በረታ" (ሮሜ 4፥20):: ከዚህ በኋላ ልጅ መውለድ

የማይቻል ሲሆን፣ አብርሃምም በእስማኤል ጉዳይ እንዳደረገው ለነገሮች በራሱ እጅ መፍትሔ ማበጀት ሳይችል ሲቀር እግዚአብሔር ተንቀሳቀሰ፡፡ እናም በመጨረሻ ልጁ ሲወለድ፣ እግዚአብሔር እንዳደረገው አንድም ጥርጣሬ አልነበረም - ምስጋናውንና ክብሩን እርሱ ወሰደ፡፡

ይህንን ስለማናስተውል እኛ ከማዕበሉ በታች ስንሰምጥ አንዳንዴ እግዚአብሔር ዝም ብሎ እንደሚቆም ስናስብ እንገኛለን፡፡ በደንታ ቢስነቱ ተጎድተንና እጅግ ተቈጥተን፣ "ጌታ ሆይ፤ ስንጠፋ አይገድህምን?" በማለት እንጮኻለን፡፡ ይህ ግን የእኛ ሐሳብ ነው፡፡ እየጠፋን አይደለም፤ እርሱም የማይገደው አይደለም፡፡

ማንሊ ቢስሊ ሲናገር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁበትን ጊዜ አስታውሳለሁ፡፡ አገልጋዮችና ሚስቶቻቸው የሚበዙበት ወደ ስድሳ ገደማ ሰዎች የተገኙበት ኢ-መደበኛ ጉባዔ ነበር፡፡ ማንሊ ወንጌላዊና የሪቫይቫል አገልጋይ ሲሆን፣ ለሁለት ረጅም ዓመታት ሲያሠቃዩት ከነበሩት አምስት በሽታዎች ማገገሙ ነበር፤ ከእነዚህም ሁለቱ ለሞት የሚያበቁ ነበሩ (ቢያንስ፣ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸው ነበር)፡፡ ከሐኪም ቤት ከወጣ ገና ጥቂት ቀናት ስለ ነበር መቆም አቅቶት ረጅም ወንበር ላይ ተቀምጦ፣ ሕመም እየተነበበበት ዝግ ባለ ድምፅ ተናገረ፡፡ የጀመረባቸው ቃላት፣ "ወገኖች፤ እግዚአብሔር አይጎዳንም" የሚሉ ነበሩ፡፡

በዚያን ጊዜ ደግሞ፣ እግዚአብሔር እኔን እየገደለኝ ነበር፡፡

ያ የእኔ ምልከታ ነበር፡፡ እግዚአብሔር እየገደለኝ አልነበረም፤ እያዳነኝ እንጂ (ሕይወትን ለማዳን ስለ ማጥፋት የሆነ ነገር ማንበቤን አስታውሳለሁ)፡፡ እንደ ሙሴ፣ እግዚአብሔርን ማየት ፈልጌ ነበር፤ ከፊት ለፊት እርሱን ማየት ነበር የፈለግሁት፤ የመመሪያውን መጽሐፍ መልከት ማድረግ ፈለግሁ፡፡ እርሱን ከመከተሌ በፊት የሚሄደው ወዴት እንደ ሆነ ማወቅ ፈለግሁ፡፡

ሆኖም፣ እንደ ሙሴ የማላውቀውን ትእዛዝ ይገፔ ነው የተጓዝኩት፡፡ እግዚአብሔርን የማየው መለስ ብዬ ስመለከት ብቻ ነው፡፡ የመጣሁበትን መንገድ ቆም ብዬ የኋሊት ስመለከት በእያንዳንዱ ኩርባ የእግዚአብሔርን እጅ አይና በመንገዱ ላይ እያንዳንዱን እርምጃ አዳኙ ጌታ እንደ መራኝ ዐውቃለሁ፡፡

የጸሎት መልስ በሚዘገይባቸው ፈታኝ ጊዜአት ይህ እውነታ፣ ምናልባትም ከሌሎቹ በተሻለ ድጋፍ ሆኖኛል፡፡ በሞት ሽረት ኑሮ በማለፍ ውስጥ ከስለታማ ጠርዞች የሚጠብቅ የግጭት መከላከያ ሆኖኛል፡፡



አስታውሱ፤ *እግዚአብሔር ሁልጊዜም ይበልጥ ክብር የሚያመጣለትን መንገድ ይጠቀማል፡፡*

እናም፤ *ወደ መሻሻል ሲሄድ በመባባስ በኩል ለጉብኝት ብቅ ይል ይሆናል፡፡*

## እግዚአብሔር ከመለኮታዊ ዕቅድ አኳያ ይመልሳል

ዘካርያስ እግዚአብሔር መለኮታዊ ዕቅድን ከማሟላት ጋር ሲያያዝ ጸሎትን እንደሚመልስ ተምሯል፡፡

እግዚአብሔር ምንም "አስፈልጎት" እና ምንም "ችግር" እንደሌለው ዐውቃለሁ፤ ሆኖም ይህንን ነጥብ ለማስረዳት እነዚህን ቃላት ልጠቀማቸው እፈልጋለሁ፡፡ እግዚአብሔር የዘካርያስን ጸሎት ለመመለስ ለምን ያንን የተለየ ጊዜ መረጠ? ለምን ዐሥር ዓመት ቀደም አላለም? ለምን ከዐሥር ዓመት በኋላ አላደረገውም? እግዚአብሔር ጸሎቱን የመለሰበት ምክንያት ያኔ መልስ መስጠት "ስላስፈለገው" ነው፡፡ የዘመኑ ፍጻሜ ደርሷል፤ እናም መጥምቁ ዮሐንስ "ያስፈልገው" ነበር፡፡ እግዚአብሔር የመሲሑን መንገድ የሚጠርግ መልእክተኛ "አስፈለገው"፤ ስለዚህም የዘካርያስን አስፈልጎት በማሟላት ውስጥ የራሱንም አሟላ፡፡ ለዘካርያስ ችግር መፍትሔ ሲያበጅ ለራሱም አበጀ፡፡

ከዚያ ደግሞ ሐና አለች፡፡ ታሪኳ 1ኛ ሳሙኤል የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ ይገኛል፡፡ ከመካንነት ጋር ከተያያዘው ዕፍረት ጋር ባደረገችው ትግል ልጅ የሌላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች የተሸከሙትን ዕፍረትና መገለል ትወክላለች፡፡ ሐና ሞገስ ማጣቷን እንዲያስወግድላትና ልጅ እንዲሰጣት ከዓመት ዓመት ወደ እግዚአብሔር ትጮኽ ነበር፡፡ ሸክሟ እጅግ ከመክበዱ የተነሣ በቃላት ልትገልጸው አልቻለችም፤ ከንፈሯን ብታንቀሳቅስም አንድም ድምፅ ሳታሰማ ልመናዋን እያሰማች ወደ እግዚአብሔር ቃተተች፡፡ ካህኑ ዔሊም በእንደዚህ ዐይነት ስሜት ስትጸልይ ሲመለከት በሰካራምነት ከሰሳት፡፡

እግዚአብሔር ጸሎቷን መለሰ - በመጨረሻ፡፡ መልሳ ለእግዚአብሔር የሰጠችውንና በእስራኤል ዘንድ ታላቅ ዳኛና ነቢይ የሆነውን ሳሙኤልን ሰጣት፡፡

እግዚአብሔር ጸሎቷን መቼ ነው የመለሰው? "ሲያስፈልገው"፡፡ እስራኤል ዳኛና ነቢይ "ሲያስፈልጋት" እግዚአብሔር የራሱ ሳሙኤል "የሚያስፈልገው" ጊዜ ደረሰ፤ እናም የሐናን "ችግር" ሲፈታ የራሱንም ፈታ፡፡

እግዚአብሔር ሁሌም በቤዝዎታዊ ዕቅድ ነው የሚመላለሰው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ብዙ ተአምራት ፈጽሟል፤ አንዱም ግን ለታይታ አልነበረም፡፡ ልጅ ሳለሁ በቴምፐል ቲአትር ቤት መድረክ ጫፍ ተቀምጬ በጊዜው የነበረውን *የነገሥታት ንጉሥ* የተሰኘ ባለ ጥቍርና ነጭ ቀለም (እና ድምፅ አልባ) ፊልም ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቴ ትዝ ይለኛል፡፡ ወታደሮቹ ኢየሱስን በሄሮድስ ፊት ሲጎትቱት ተመለከትኩ፡፡ ኢየሱስ ተአምር እንዲሠራ ሄሮድስ ሲገፋፋው ኢየሱስን ለመገፋፋት ከመቀመጫዬ ወደ ፊት ጠጋ አልኩኝ፤ ሄሮድስ ተአምር ካየ ኢየሱስን ይለቅቀዋል፡፡ ታሪኩ እንዴት እንደሚያልቅ ዐውቃለሁ፤ ሆኖም በድራማው ተመስጬ ነበር፡፡ ኢየሱስ እዚያ ቆሞ ሄሮድስን እንኳ አለማናገሩን ማመን አልቻልኩም፤ ማድረግ የነበረበት አንዲት ትንሽ ተአምር ብቻ ነበር፤ ያኔ ነጻ ሆኖ ይሄድ ነበር፡፡

ለምን አላደረገም? ይችል ነበር - አንድ ተአምር ለማድረግ እጅግ በጣም አንገብጋቢ ጊዜ ሆኖ ነበር የታየኝ፡፡ ለነገሩስ ተአምራቱ ለመሲሕነቱ በምልክትነት የታቀዱ አልነበሩምን? ሽማግሌውን ሄሮድስን በአንድ ተአምር ለምን አላስደነቀውም?

ያ ዐይነቱ ተአምር ከሁሉ በፊት በእግዚአብሔር ቤዝዎታዊ ዓላማ ተወስዷል፡፡ ኢየሱስ ተአምራቱን በዚያ ክልል ውስጥ ወስኗቸዋል፡፡ በሄሮድስ ፊት በዝምታ ሲቆም ኢየሱስ ሰዓቱ መድረሱን (በዮሐንስ 12፥27 ላይ የተናገረውን) ተረድቷል፡፡ ከሄሮድስም ሆነ ከጭፍሮቹ፣ ወይም ከጲላጦስ ወይም ከአይሁድ መሪዎችና ከሕዝብ መንጋቸው ማምለጥ አልፈለገም፤ ለመሞት መጥቷልና፡፡

## እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ ይመልሳል

ጸሎቶቻችን ከመለኮታዊ አስፈልጎት ጋር መተሳሰር አለባቸው፤ በእግዚአብሔር ቤዝዎታዊ ጅረት ውስጥ መፍሰስ አለባቸው - ከእግዚአብሔር ፈቃድ አኳያ፡፡

"እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ" በክርስትና መዝገበ ቃላት ውስጥ ሌላኛው አስፈሪ ሐረግ ነው፡፡ ይህም፣ ክርስቲያኖች በልበ ሙሉነት እንዳይጸልዩ ምናልባትም ከሌላ ከማንኛውም ነገር በላይ ተስፋ የሚያስቈርጥ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እናጣውና ቀሪ ዘመናችንን ሁሉ ዋጋ ስንከፍል እናሳልፋለን በማለት ማሰቡ ያስጨንቃል፡፡

ስለ ሕይወታችን ዝርዝር ጒዳዮች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አንችልም፤ እናም ስለምንጸልይበት ስለ ሁሉም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ



ማወቅ አያስፈልገንም፡፡ ይህ *ቅርቡ* የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ ነገር ግን *ሩቁን* የእግዚአብሔር ፈቃድ ማወቅ ይቻለናል፡፡ ለምሳሌ፣ *ሥራ* በማጣቴ ቤተ ሰቤን ማስተዳደር አቅቶኛል ልበል፡፡ አስፈልጎቴ እንዲሞላ በእርግጠኝነት መጸለይ እችላለሁ፤ እንደሚያሟላቸው እግዚአብሔር ቃል ገብቷልና (ፊልጵ. 4፥19)፡፡ ሩቁ የእግዚአብሔር ፈቃድ በማለት የምጠራው ይህንን ነው፡፡ ቅርቡ የእግዚአብሔር ፈቃድ እግዚአብሔር ያንን አስፈልጎት *እንዴት* ነው የሚያሟላው ከሚለው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እግዚአብሔር ጒድለቴን እንዲ ሞላልኝ ስጠይቀው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እየጸለይኩ መሆኔን ዐውቃለሁ፡፡ እግዚአብሔር ባለዝሆኑን ሎተሪ እንዳሸንፍ በመፍቀድ ጒድለቴን እንዲሞላልኝ ከጠየቅሁት ግን ተመሳሳይ ልበ ሙሉነት አይኖረኝ ይሆናል፡፡ ሚሊዮን ብር ማሸነፍ *ከቅርቡ* የእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ይያያዛል፡፡ እግዚአብሔር የሚያስፈልገኝን እንደሚሰጠኝ ዐውቃለሁ፤ ግና እኔን ሚሊየነር በማድረግ ላይሆን ይችላል፡፡ ለነገሩማ፣ አይደለም፡፡ ጠይቄ ዐውቃለሁ፡፡

## ማለት ያለባችሁን ሳታውቁ ስትቀሩ

## ምን እንደምትሉ

የምንጸልየው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆን አለመሆኑን የምና ውቅበት መንገድ አለ፡፡ ኢየሱስ ወደ መስቀሉ ሲቃረብ ባደረገው የመጨረሻ ሰፊ ይፋዊ ንግግሩ ውስጥ የሚያስጨንቀውን ነገር በግልጽ አስቀምጧል፤

> አሁንስ ነፍሴ ተጨነቀች፤ ምን ልበል? አባት ሆይ፤ ከዚህ ሰዓት ታድነኝ? የለም፤ ይሁን የመጣሁት ለዚህች ሰዓት ነውና፡፡ *አባት ሆይ፤ ስምህን አክብረው፡፡* (ዮሐ. 12፥27-28 - አ.መ.ት. - አጽንኦት የተጨመረ)

ኢየሱስ ውስጡ ድረስ "ተጨንቆ" ከራሱ ጋር ይሟገት ነበር፤ "ምን ልበል?" ከመስቀሉ እንዲያድነው ወደ አባቱ መጸለይ ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን "ሰዓቲቱ" ወደ ዓለም የመጣባት ምክንያት ናት፡፡ ይህ የኢየሱስን ሰው-ነት በጨረፍታ እንድንመለከት ምስጢረ አምላክ-ሰው ገለል ያለበት አስደናቂ ክስተት ነው፡፡ "ምን ልበል?" የእግዚአብሔር ልጅ ውስጡ እጅግ በመከፋፈሉ ቃላት አጥቶ፣ "ምን ልበል?" ብሎ እንደሚጮኽ አልመን እንኳ እናውቃለን?

"አባት ሆይ፤ ስምህን አክብረው" በሚሉት ቃላት ግጭቱን አበረደው፡፡ ምን ማለት እንዳለባችሁ ሳታውቁ ስትቀሩ ማለት ያለባችሁ ይህንን ነው፡፡ ምን እንደምትጸልዩ ሳታውቁ ስትቀሩ እንደዚህ ነው መጸለይ ያለባችሁ፡፡ "አባት ሆይ፤ ስምህን አክብረው" ማለት ሁሌም ትክክል ነው፡፡

ልመናዎቻችንን ሁሉ ይህን መሸፈኛ ስናለብሳቸውና ይህም በእውነት ከልባችን ከሆነ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እየጸለይን ነው።

ለእኔ፣ ይህ የእግዚአብሔር ክብር፣ የስሙ ከበሬታ፣ ከልመናዎች ሁሉ ይበልጣል ማለት ነው፤ ከእግዚአብሔር ስም መከበርና ከልመናዬ ምላሽ ማግኘት መምረጥ ካለብኝ (የመምረጥ መብት እንዳለኝ ይታሰብና) የእግዚአብሔርን ክብር እመርጣለሁ ማለት ነው።

የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪ ሳለሁ አንድ ዓርብ ዕለት እኔና አንድ ጓደኛዬ በሳምንቱ ማለቂያ ላይ ወደ ቤት ለመሄድ ወሰንን። በአሮጌ ፎርድ መኪናዬ ውስጥ ታጨቅንና ጉዞአችን የሰላም እንዲሆንልን እንዲጸልይ ጓደኛዬን ጠየቅሁት። ራሴን ዝቅ አድርጌ ዐይኖቼን ስጨፍን፣ "ጌታ ሆይ፤ እንድትጠብቀንና የጉዞ ምሕረት እንድታደርግልን እንጸልያለን - በሆስፒታል አልጋ ላይ ይበልጥ ልናከብርህ የምንችል እስካልሆነ ድረስ" በማለት ሲጸልይ ሰማሁት።

ከዚያ ቀን በኋላ ጓደኛዬን ስለ ምንም ነገር እንዲጸልይ ጠይቄው አላውቅም። ሆኖም፣ በሆነ ባልተለመደ መንገድም ቢሆን ጓደኛዬ ትክክል ነበር። ስለ ምንም ነገር ብንጸልይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቅድሚያውን ይወስዳል። አንዳንዴ እግዚአብሔር የሚበልጠውን ለመስጠት የሚያንሰውን ያስቀራል፤ የራሱን ዕቅድ ሳያመቻምች የጠየቅሁትን ለመስጠት አይችል ይሆናል። ስለዚህ ኢየሱስ እንደ ጸለየው መጸለይ አለብን፤ "አባት ሆይ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን፤ የአንተ እንጂ" (ሉቃ. 22፥42)።



## ፲፰ - ጸሎትን መቼ ማቆም እንዳለብን መወሰኛ ሦስት መንገዶች

# እስከ መቼ?

"ስለ አንድ ጉዳይ ለምን ያህል ጊዜ ነው መጸለይ ያለብን?" የሚል ጥያቄ ብዙ ጊዜ ይቀርብልኛል። እግዚአብሔር በዘካርያስ እንዳደረገው መልሱን ካዘገየ፣ መዘግየት ይሁን ክልከላ በምን ማወቅ ይቻለናል? እግዚ አብሔር በከለከለው ነገር ላይ ጥየቃችንን መቀጠል አንፈልግም። በሌላ መልኩ ደግሞ፣ እንድንቈይ እየነገረን ከሆነም ተስፋ መቍረጥ አንፈልግም።

ከእነዚህ ሦስት ነገሮች አንዱ እስኪከሰት እንድንጸልይና መጸለያችንን እንድንቀጥል ሐሳብ አቀርባለሁ፤

፩. **መልሱን እስከንቀበል።** አንዳንዶች ለአንድ ነገር ከአንድ ጊዜ በላይ መጸለይ የእምነት መጉደል፣ ጸሎታችንን ባዶ የሚያደርግ የእምነት ማጣት ድርጊት እንደ ሆነ ይናገራሉ። ለዚህም ሙግታቸውን በተከታዩ ዐይነት ምሳሌ ያቀርባሉ፤ አንድ ልጅ በሚቀጥለው ቀን ወደ ኳስ ሜዳ እንዲወስደው አራት ሰዓት ላይ አባቱን ይጠይቃል፤ አባትየውም እንደሚወስደው እሺታውን ይገልጻል። አምስት ሰዓት ላይ ልጁ እንደ ገና ይጠይቃል፤ አባትየውም እንደ ገና እሺታውን ይገልጻል። ስድስት ሰዓት ላይ ልጁ እንደገና ይጠይቃል፤ ሰባት ሰዓት ላይም ይጠይቃል፤ ስምንት ሰዓትም ላይ ይጠይቃል። ልጁ ደጋግሞ የሚጠይቀው ለምንድን ነው? አባቱን ባለማመኑ እንደ ሆነ ግልጽ ነው። ይህ በእርግጥም አባትየውን ያሳዝነዋል። ስለዚህ በእውነትም እምነት ካለን፣ አንዴ መጠየቅ ነው የሚያስፈልገን።

ይህ ምክንያታዊ እንደሚመስል (የሆነ ፋይዳም እያጣ ይሆናል) እቀበላለሁ፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ብዬ ግን አላስብም። ኢየሱስ ባልተቋረጠ ጥየቃ ያምናል። ስለ ጸሎት የሰጠን ሁለት ምሳሌዎችን ብቻ ሲሆን፣ የሁለቱም ምሳሌዎች አጽንኦት ያልተቋረጠ ጥየቃ ነው (በምሽት የመጣው ጓደኛ፣ ሉቃስ ፲፩፣ እና መበለቲቱና ዳኛው፣ ሉቃስ ፲፰)። በማቴዎስ 7፥7-፲፩ ላይ ኢየሱስ እንድንጠይቅ፣ እንድንፈልግና እንድናንኳኳ ይነግረናል። የግሱ የጊዜ

አመልካች፣ ጠይቁ፣ መጠየቃችሁንም ቀጥሉ፤ ፈልጉ፣ መፈለጋችሁንም ቀጥሉ፤ አንኳኩ ማንኳኳታችሁንም ቀጥሉ የሚል ነው:: ስለዚህ መጠየቅና እየጠየቅን መቀጠል ያስፈልገናል፤ እስክንቀበል ድረስ ወይም ...

**2. እንደምንቀበል ማረጋገጫ እስክናገኝ ድረስ::** በቤተ ክርስቲያናችን የጸሎት አገልግሎት በተጀመረባቸው ቀናት በየሳምንቱ ለጸሎት የሚሰባሰቡ ሴቶች ቡድን ነበር:: በአጋጣሚ ሁሉም ደንበኝነታቸው አንድ ጸጉር ቤት ሲሆን፣ ጸጉር ሠሪያቸው ክርስቲያን አልነበረችም:: ከሳምንት እስከ ሳምንት ሲጸልዩላት ቆዩ፤ አንድ ቀን ለመጸለይ ሲሰበሰቡ ግን ለልጅቱ መዳን መጸለይ አልቻሉም:: እንዲያውም ስለ መዳኗ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ራሳቸውን አገኙት፤ ስለ ጠቅላላው ጉዳይ በልባቸው ሰላም ሞላ:: በኋላ ላይ አንዲቱ ሴት ለልጅቱ የነበራት ሸክም በመጥፋቱና ለመዳና መጸለይ በማቆሟ በደለኝነት እንደ ተሰማት ተናገረች:: ከሦስት ሳምንታት በኋላ በእሁድ ማለዳ አገልግሎት ጸጉር ሠሪዋ ወደ ክርስቶስ መጣች:: ሲጸልዩላት ከነበሩት ሴቶች በቀር ሁሉ ሰው ነበር የተገረመው::

አንዳንዴ ለአንድ ነገር ስንጸልይ ሳለ እግዚአብሔር እንደ ሰማና እንደ መለሰ ማረጋገጫ እናገኛለን:: ሸክም በነበረበት ቦታ አሁን ሰላም ይሆናል::

**3. እግዚአብሔር አይሆንም እስኪል::** እግዚአብሔር አይሆንም እንዳ ለን በመንፈሳዊ መረዳት፣ በቃሉ ብርሃን፣ በሁኔታዎች ለውጥ፣ ወይም በሆነ ሌላ መንገድ እንገነዘብ ይሆናል:: በመንፈሳዊ መረዳት፣ እግዚአብሔር ለጥያቄ አችን አይሆንም የሚል መልስ ሲሰጥ በጉዳዩ ለመጸለይ ሰላም አይኖረንም ማለቱ ነው፤ ትክክል እያደረግን አይመስለንም፤ የመገታት ስሜት ይኖረናል::

በሁለተኛውና በሦስተኛው ሐሳቦች ላይ ከእግዚአብሔር ፈቃድ አኳያ እንድናገር ፍቀዱልኝ::

እኛ ፈቃዱን ለማወቅ ከምንናፍቀው በላይ እግዚአብሔር ፈቃዱን እንድናውቅ ይናፍቃል:: ለአንዳንዶች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ኩኩሉ እንደ መጫወት ነው:: "የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ነው የማገኘው?" በማለት ለሚጠይቁኝ፣ "አታገኙትም" በማለት ነው የምመልስላቸው:: የእግዚ አብሔር ፈቃድ ያገኛችኋል:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ *ማግኘት* የእናንተ ኀላፊነት አይደለም:: እግዚአብሔር ፈቃዱን እንድታውቁ ከፈለገ፣ መግለጥ የእርሱ ኀላፊነት ነው፤ ልትስቱት በማትችሉት መንገድ መግለጥ::

ለምሳሌ ሴት ልጄ እንድታደርግልኝ የምፈልገው ነገር አለ እንበል:: እንደምታደርገው ትነግረኝና ምን እንደ ሆነ ትጠይቀኛለች:: "አልነግርሽም" እላታለሁ፤ "ራስሽ ማወቅ አለብሽ:: ከተሳሳትሽ ደግሞ ችግር ይፈጠራል::"



እስቲኝ ነው አይደል? ለልጄ ያቀድኩት ተግባር ካለ፣ መግለጡ የእኔ ኀላፊነት ነው:: የእርሷ ኀላፊነት መስማትና መታዘዝ ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ማረጋገጥ እንደምንችል በሮሜ 12፥1-2 ይነግረናል፤ ሁለት ምርጫዎችን መመልከትና የትኛው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ መለየት እንችላለን:: ነገር ግን አስቀድመን ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንድናቀርብ ይነግረናል፤ *ማቅረብ* የተባለው መገዛት ወይም እጅ መስጠት ለማለት ነው::

በመሠረቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የምንፈልግ ከሆነ፣ ምን እንደ ሆነ ከማወቃችን በፊት ልንቀበለው ይገባል በማለት ነው ጳውሎስ እየተናገረ ያለው:: "ምን እንደ ሆነ ይነገረኝና ከዚያ እወስናለሁ" የሚለው አቋም በጭራሽ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ፣ ምንም ይሁን ምን፣ የተመረጠ (የተሻለ) እንደ ሆነ በማወቅ፣ ልንገዛለትና አስቀድመን ልንቀበለው ይገባል::

## እንዴት እናውቃለን?

ከመስመር ስትወጡ የሚነግራችሁ መንፈሳዊ ዳኛ በአካባቢያችሁ እንዲኖር ተመኝታችሁ ታውቃላችሁ? ጥሩ፤ እንግዲያውስ የተሰጠንም በትክክል ይኸው ነው:: ቈላስይስ 3፥15ን እናድምጥ፤

> በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ::

ይግዛ ማለት "ይዳኝ" የሚል ትርጉም ያለው የግሪክ ቃል ትርጓሜ ነው:: የዊልያምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም" "ይዳኝ" ሲለው፣ የቤክ ትርጉም ደግሞ "ይወስን" ብሎታል::

ክርስቲያን በክርስቶስ በኩል ሁለት ዐይነት ሰላሞች አሉት፤ ከእግዚአ ብሔር ጋር የሆነ ሰላምና የእግዚአብሔር ሰላም:: ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም፣ በእምነት የመጽደቅ ውጤት ነው (ሮሜ 5፥1):: በእግዚአብሔርና በክርስቲያኑ መካከል ያለው ጦርነት አብቅቶ፣ አማኙ ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ትክክለኛው ግንኙነት መጥቷል፤ ወደ ባርኮት ስፍራ:: ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ተጨ ባጭ (ነባራዊ) ነው:: ያለበት መንፈሳዊ ሁኔታ ምንም ቢሆን እያንዳንዱ አማኝ ይህ አለው:: ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ሰላም ምንም ሊረብሸው አይችልም::

የእግዚአብሔር ሰላም እግዚአብሔር ራሱ የሚደሰትበትና ከእኛ ጋር የሚጋራው ሰላም ነው:: ይህ ሰላም ኀሊናዊ (በእኛ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ)፣ እንዲሁም ውስጣዊ የልብ መረጋጋትና እርጋታ ማረጋገጫ ነው:: የእግዚ

አብሔር ሰላም የአማኙ ልብ ዕረፍት ነው:: ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ መራመድ ይህንን ሰላም ይረብሸዋል፤ ልባችን ይታወካል፤ የጸጥታ ማረጋገጫው ይሰወራል::

ጳውሎስ እየተናገረ ያለው፣ የክርስቶስ ሰላም በሕይወታችን ዳኛ እንዲሆን፣ ትክክሉንና ስሕተቱን እርሱ እንዲወስን እንድንፈቅድ ነው:: ያንን ውስጣዊ ሰላም ስናጣ፣ ልባችን ሲታወክና በቀላሉ ሲታመም፣ መንፈሳዊ ዳኛችን ፊሽካ እየነፋና ጥፋት እንደ ተፈጸመ እየተናገረ ነው::

ስለ ሆነ ጉዳይ ስጸልይ ልባዊ ማጣሪያው፣ መግቻው በድንገት ወይም በዝግታ ብቅ የሚልባቸው ጊዜአት አሉኝ:: በጉዳዩ ላይ ትክክለኝነት አይሰማ ኝም:: በሌላ አገላለጽ፣ በጉዳዩ ላይ ሰላም አይኖረኝም:: ይህንን፣ ተጫዋቹ ከመስመር መውጣቱን ዳኛው እየተናገረ እንደ ሆነ አድርጌ እወስደዋለሁ::

ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይበልጥ ንቁ በሆንን ቍጥር "እንደ እግዚአብ ሔር ፈቃድ" የሆኑትንና ያልሆኑትን ልመናዎች ይበልጥ መለየት ይቻለናል::

## ለጥበብ መጸለይ

በቤቴ ትልቅ አስፈልጎት የተነሣበትን ጊዜ አስታውሳለሁ:: ሥር የሰደደ ድብታ ምልክቶች በትልቁ ልጃችን ላይ መታየት ጀመሩ:: (በኋላ ላይ በትክክልም በሽታው እንዳለበት በሐኪም ተረጋግጧል::) ሕይወታችን በቅዠትና በጣር ውስጥ እንደ ተዘፈቀ ከመናገር በላይ ዝርዝር ውስጥ መግባት አልፈልግም:: እንደዚያን ጊዜው ዐይነት ብርቱ አለመብቃት፣ ግራ መጋባት፣ አላዋቂነት የተሰማኝ ወቅት በጭራሽ አልነበረም:: እኔና ሚስቴ ያዕቆብ 1፥5ን ለሕይወታችን ምሪት አድርገን ወሰድን፤

> ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል::

እናም ውጥንቅጣቸው የወጣ ቤተ ሰባዊ ውሳኔዎች ሲያስጨንቁን ለጥበብ መጸለይ ጀመርን:: ነገር ግን የመጣ ጥበብ አልነበረም:: የብሩኅ መረዳት ብልጭታም የለም፤ ጭንቅላቴም ጥበብ ገብቶበት መጠኑ እየጨመረ አልሄደም:: እንደሌላው ጊዜ አፌ እንደ ተያዘ ነበር የተሰማኝ::

ተስፋ መቍረጥ ውስጥ ተዘፍቄ ሳለሁ፣ አለመሳካቱ ግልጽ ቢሆንም እንኳ ራሴን ወደ ማመን ለማምጣት ጥቅሱን ደጋግሜ ማንበብ ቀጠልኩ:: "እየወደቀ ያለ የተስፋ ቃልማ አይደለም፤ ይህማ አይጠፋኝም" በማለት ነበር የማስበው:: ታዲያ ምንድን ነው መደረግ ያለበት?



ከዚያ ግን ታየኝ፤ ፊቴን በመስታዎት እንደማየው ዐይነት ቁልጭ ብሎ ነው የታየኝ:: የጥቅሱ የራሱ የመጨረሻው ሐረግ የሚለው፣ "ለእርሱም ይሰጠዋል" ነው:: አራት ነጥብ:: በቃ፤ ይኸው ነው::

እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጠኝ ከጠየቅሁት፣ ተሰማኝም አል ተሰማኝ፣ ሊኖረኝ ይገባል:: ምን እንዳደረግሁ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር ቃል የገባው ጥበብ እንደ ተሰጠኝ አመንኩና *መልካም የመሰሉኝን* ውሳኔዎች መወሰን ጀመርኩ:: እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጠኝ ከጠየቅሁ፣ የእርሱ ጥበብ በውስጤ እየሠራ እንደ ሆነ የማሰብ መብት እንዳለኝ አመንኩ::

አስፈሪ ነው:: በጊዜው ውሳኔዎቼ "ትክክለኞቹ" ስለ መሆናቸው ማወቂያ ምንም መንገድ አልነበረም:: ቢሆንም፣ ያ ጊዜ ዐልፎ፣ ወደ ኋላ ስመለከት በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ትክክለኛውን ውሳኔ ማድረጌን አስተዋልኩ:: እግዚአብሔር ለጸሎቴ መልስ የተስፋ ቃሉን ጠበቀ::

ስለ አንድ ነገር መቼና እስከ መቼ መጸለይ እንደሚያስፈልግ እንዳ ውቅ ሁለት ሐሳቦች ረድተውኛል:: አንደኛ፣ በሸክሜ አቅጣጫ እጸልያለሁ:: የምሰብክበትም መንገድ ይኸው ነው - በሸክሜ አቅጣጫ:: "በልቤ ያለውን" እሰብካለሁ:: ይህ እግዚአብሔር እኛን ከሚመራባቸው መንገዶች አንዱ በመሆኑ፣ እግዚአብሔር በዚያ እንዳደረገው በማመን በልባችን ላለው ሸክም ምላሽ መስጠትን መማር አለብን::

ሁለተኛ፣ ሸክሙ እስኪነሣልኝ እጸልያለሁ:: ልቤ በአንድ ነገር እስከ ከበደ ድረስ በጌታ ፊት አደርገዋለሁ:: ሸክሙ ሲነሣ፣ ከዚያ ጸሎት ተላቅቃለሁ::

* * *

*ተጨማሪ:: "እንዴት" እንደሚጸለይ ስለ መናገር የተቀላቀለ ስሜት አለኝ:: እግዚአብሔርን በጸሎት እንዴት መቅረብ እንዳለባቸው ለሌሎች ለመናገር በእውነቱ ማንም ብቁ አይደለም:: ምናልባት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከመለስኳቸው የሚበልጡ ጥያቄዎችን አንሥቼ ይሆናል:: "እንዴህ ከሆነስ ...?" የሚል ጥያቄ ሁልጊዜም ይኖራል፤ ነገር ግን ሁሉን ነገር በአንድ መጽሐፍ መናገር አልቻልምና አትጨነቁበት:: በዚህም ሆነ በሌላ መጽሐፍ የምታገኙት "የጸሎት ዕቅድ" እያስፈራራችሁ:: ያልተመለሰ ጸሎት የተዘለለ ሥርዐት ወይም የተጣሰ ፕሮቶኮል ውጤት ከቶ ሆኖ አያውቅም:: አድርጉት:: ዘልላችሁ ተነሡና ጸልዩ፤ መንፈስ ቅዱስ ይይዛችሁና መሄድ ወደ ሚያስፈልጋችሁ ቦታ ይወስዳችኋል::*

## ፲፱ - የቤተ ክርስቲያንን እውነተኛ ኀይል መመልከት

# የምትጸልይ ቤተ ክርስቲያን በአረማዊ ዓለም

የስኮትላንድ ንግሥት የነበረችው ሜሪ፣ "የምድር ጦር ሠራዊቶችን በሙሉ ከምፈራው በላይ የጆን ኖክስን ጸሎት እፈራዋለሁ" ማለቷ ተዘግቧል።

የቤተ ክርስቲያንን ጸሎት ሰው ሲፈራው ምናልባትም ይህ የመጨረሻ ጊዜ ነበር።

ያሲር አራፋት፣ "የእስራኤልን ዑዚዎች ከምፈራው በላይ የቅዱሳንን ጸሎት እፈራለሁ" በማለት ሲናገሩ ለማሰብ ያስቸግራል።

ዓለም ቤተ ክርስቲያንን አይፈራትም - ላመል ነው የሚያከብራት። በአጠቃላይ፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከታት በምድር ጉዳዮች ላይ በተሳታፊነቷ ሳይሆን በተመልካችነቷ ብቻ ነው፤ የምዕራቡ ዓለም አረማዊ መሪዎች የሚያቀርቡትን ሐሳብ በ"ሁሉን እሺ ባይነት" የምትቀበል አድርጎ ነው ዓለም ቤተ ክርስቲያንን የሚሥላት። ይህ የምዕራቡ ባህል ደግሞ ክርስቲያናዊው ቅድመ ግንዛቤ በዘመናዊው ኀብረተ ሰብ እሴት ቀረጻ ላይ ጠንካራ ድምፅ መሆኑን መቀበል ከተወ ረጅም ጊዜ አስቆጥሯል። ቤተ ክርስቲያን ለጎረቤቶቿ የሚሆን የተወሰነ መስህብ ያላት አስደሳች ጥንታዊ ቅርስ፣ ከትናንት ለዛሬ የተላለፈች፣ ነገር ግን ማዕበል አንድ ጥግ ወትፎ እንዳስቀረው ዓሣ ነባሪ ትልቅና ጉዳት አልባ ናት።

ለብዙዎች፣ ቤተ ክርስቲያን እየተጋፈጠች ያለችው ትልቁ አሳሳቢ ጥያቄ በሕልውና መቈየት የመቻሏ ጉዳይ ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት እችላለሁ። አዎን፣ ቤተ ክርስቲያን በሕልውና ትቈያለች። እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክር ከቶ አይተውም፤ እናም በዚህ ሁሉ ትርምስ ላይ የመጨረሻው መጋረጃ ሲገለጥ የእርሱ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው መኖሯ አይቀርም። በአሁኑ ቅርጿ በሕልውና አትገኝ ይሆናል፤ ነገር ግን የሕልውና ጉዳይ ብቻ የሚያሳስበን ከሆነ እግዚአብሔር ይርዳን። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑ ከዚህ ያለፈ ብዙ ነገር እንድትሠራ ነው የሚያስበው።



### የአረማዊነት ዘመን

"የድኅረ-ክርስትና ዘመን እነሆ።" ይህ መጽሐፍ *አዲሱ አረማዊነት (The New Paganism)* የተሰኘው የሀሮልድ ሊንድሴል መጽሐፍ መክፈቻ ዐረፍተ ነገር ነው።[1] መጽሐፉ የምዕራቡ ዓለም በአረማዊነት መሸነፉን ያሳያል። ሊንድሴል እንዲህ ብሎ ጽፏል፤

> በምዕራቡ ዓለም በአይሁድና በክርስትና ሥልጣኔ ላይ የተመሠረቱ መሠረቶች ሁሉ ወድቀዋል። በቦታውም፣ ምዕራቡ ዓለም በአጠቃላይ እንደ አረማዊ ምድር እየኖረና እየሠራ ነው።[2]

ቤተ ክርስቲያን አዲስ ኪዳናዊውን ክርስትና በሚጠላውና የማያቋርጥ ጦርነት ባወጀበት የጥላቻ ዓለም ተከብባ በአረማዊው ባህር ላይ እየቀዘፈች ነው።

በማሸነፍ ላይ ያለውን ባህል ከ"አረማዊነት"፣ "ኒዎ-አረማዊነት"፣ "ሰብአዊ-ዓለማዊነት" በየትኛውም ስም ብንጠራው አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ አብዛኛው ምዕራባዊ ዓለም በተመሠረተበት የአይሁድና የክርስትና መሠረት ላይ የመጨረሻው፣ ምናልባትም ገዳይ ቡጢ ሲያርፍ ትውልዳችን ምስክር ሆኗል።

### ቀዳሚው የአረማዊነት ዘመን

እያሸነፈ ያለው ከባቢያዊ ሁናቴ ጠባይ ለቤተ ክርስቲያን አዲስ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በአረማዊነት መካከል ሲሆን፣ አሸንፋዋለችም።

> ክርስቶስ አገልግሎቱን በይፋ ከጀመረ ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ፣ ቤተ ክርስቲያን የሮም መንግሥት መሲሑን ለማምለክ ጕልበቱ እንዲንበረከክ አድርጋዋለች።[3]

ለመሆኑ የትኛውም ወታደራዊ ኀይል ሊያደርግ ያልቻለውን ነገር በጕጕት የተሞሉ ጥቂት ደቀ መዛሙርት እንዴት ሊከውኑት ቻሉ? እኛ የሌለን፣ እነርሱ ያላቸው ነገር ነበርን? እኛ የማናውቀው እነርሱ የሚያውቁት ነገር ነበርን?

የእነዚህና የሌሎች ጥያቄዎች መልሶ እግዚአብሔር ስለ እነዚህ ፈር ቀዳጅ ክርስቲያኖች ባስቀረልን ዘገባ ውስጥ መገኘት ይችላል። በሐዋርያት

ሥራ ምዕራፍ 12 ከሚገኘው በላይ የቀዳሚዋን ቤተ ክርስቲያን ሕይወትና ጊዜ ገላጭ ምስል አይገኝም::

> ምዕራፉ የሚጀምረው በግጭት ነው፤
>
> በዚያም ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ መከራ ያጸናባቸው ዘንድ ከቤተ ክርስቲያኑ በአንዳንዶች ላይ እጁን ጫነባቸው:: የዮሐንስንም ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ ገደለው:: አይሁድንም ደስ እንዳሰኛቸው ዐይቶ ጨምሮ ጴጥሮስን ደግሞ ያዘው:: (የሐዋ. 12፥1-3)

## ጸሎት እና የጴጥሮስ መለቀቅ

ሄሮድስ ጴጥሮስን እንዲጠብቁ ዐሥራ ስድስት ወታደሮችን መደበ፤ ጴጥሮስም በሁለት ወታደሮች መካከል በሰንሰለት ታስሮ ነበር:: ለጴጥሮስ ምንም ዐይነት ማምለጫ፣ ከቅጣት መዳኛ አልነበረውም::

> ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር:: (ቍጥር 5)

ጴጥሮስ ከሚገደልበት ቀን በፊት ባለው ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ጴጥሮስ በሁለቱ ጠባቂዎቹ መካከል ተኝቶ ወደ ነበረበት ወኅኒ መጣ:: መልአኩ ጴጥሮስን ቀስቅሶ ሁለቱን የዘብ ቦታዎች አሳለፈውና ራሱ ዐውቆ በተከፈተው የብረት መዝጊያ በኩል ወደ አንዲት ስላች መንገድ አድርሶት እንደ አመጣጡ ድንገት ተሰወረ::

> ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ፣ "ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት ዐወቅሁ" አለ::
>
> ባስተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ:: (ቍጥር 11 እና 12)

ለምን አልሸሸም? ይህ ድንጋጤ የሚያጠቃው ደቀ መዝሙር ከዚህ በፊት ሸሽቷል - ጌታ ኢየሱስ ለፍርድ ሲቀርብ:: እንዲያውም አሁን የተሻለ ሰበብ አለው፤ ሕይወቱ *በትክክል* አደጋ ላይ ነው:: በመሸሸ ፈንታ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተሰበሰበችበት ወደሚያውቀው ወደ ማርያም ቤት ሄደ:: ወደ መሸሸጊያው በኋላ ይሄዳል፤ አስቀድሞ ግን እግዚአብሔር ምን እንዳደረገለት ለቤተ ክርስቲያን ማካፈል አለበት:: በጠቅላላው ታሪክ ውስጥ (ከቍጥር 1-19) ይህ የቀድሞው ከዳተኛ ነገሮችን በእርጋታ መቈጣጠሩ ያስደንቀናል::



> ፍንጩ ቍጥር 12 ላይ ይገኛል፤
>
> *ባስተዋለም ጊዜ ... ወደ ማርያም ቤት መጣ::*

ጴጥሮስ በስሷል:: ከመሮጡ በፊት ቆም ብሎ ያስባል:: ምን እንደ ተከሰተበት አጤነ፤ ከዚያም በልበ ሙሉነትና በእርጋታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደ::

## ባስተዋለ ጊዜ፤ በአንድነት ማየት

"ማስተዋል" ማለት ነገሮችን *በአንድነት ማየት* ማለት ነው:: ጴጥሮስ የቅርብ ጊዜ ክስተቶችን ወሰደና በአንድነት አስቀመጣቸው፤ እንደ ተነጣጠሉ፣ ያልተያያዙ ሁነቶች ሳይሆን እንደ አንድ ትልቅ ምስል አድርጎ ወሰዳቸው:: የያዕቆብን ሞት ብቻ ቢመለከት ይሸሽ ይሆናል፤ ሰንሰለቶቹንና ጠባቂዎቹን ብቻ ቢመለከት እንደ ከዚህ ቀደሙ ሊደነግጥ ይችል ነበር:: በሕይወት ውስጥ እያንዳንዱ ነገር ከሌላ ነገር ጋር የተሳሰረ እንደ ሆነ አሁን ተረዳ:: ምንም ነገር በተናጠል አይከሰትም:: እያንዳንዱ ክር የሸማው አካል ነው::

ይህ ዛሬም ለእኛ እውነት ነው:: የቤተ ክርስቲያንን ወቅታዊ ሁኔታ የመዓትና የጭጋግ አድርጎ የመመልከት አያሌ ድምዳሜዎች ነገሮችን ከሌሎች ነገሮች ነጥሎ የመመልከት ውጤት ናቸው:: ክርስቲያኖች በዓለማችን እየተከሰቱ ያሉትን ነገሮችን ማስተዋል፣ "አጣምረው መመልከት" እንደ ሚያስፈልጋቸው እምናለሁ:: ይህን ብናደርግ፣ ተስፈኛ (ብሩሃዊ) ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ተዋጊ ቤተ ክርስቲያን መሆን እንጀምር ነበር:: አራት እውነታዎችን እንድናስተውል፣ በአንድነት እንድናይ ሐሳብ አቀርባለሁ::

## እውነታ 1፤ ቤተ ክርስቲያንና ዓለም ደመኛ ጠላቶች ናቸው::

የድሮው የይስሐቅ ዋትስ መዝሙር፣ "ይህ ክርፋታም ዓለም ወደ እግዚአብሔር እንድቀርብ የሚያግዘኝ፣ የጸጋ ወዳጅ ነውን?" የሚል ጥያቄ ሰንዝሯል:: ያኔ መልሱ አይደለም ነበር፤ ዛሬም አይደለም ነው:: የቀደመችዋ ቤተ ክርስቲያን ይህን ታውቅ ነበር:: እኛ ስለ ማወቃችን ግን እርግጠኛ አይደለሁም:: በርካቶች ነገሮችን ማስተካከልና የተሻሉ ጓደኞች መሆን እንደምንችል፣ ወይም ቢያንስ እንደ ጥሩ ጎረቤት በሰላማዊ ሁኔታ ጎን ለጎን መኖር እንደምንችል አሁንም ተስፋ እንደሚያደርጉ አስባለሁ::

ያደግሁት በመጥምቋውያን ቤተ ክርስቲያን ሲሆን፣ በዚያን ወቅት መጥምቃውያን በዓለማዊ ደስታዎች ጕዳይ አቋማቸው ጠንካራ ነበር:: እኛ

ሕፃናቱ፣ "አላጨስም፣ አልቅምም፣ ይህን ከሚያደርጉ ሴቶችም ጋር አልሆንም" እያልን እንዘምር ነበር:: አንድ ቀን ወደ ዳንስ ቦታ ለመሄድ የእናቴን ፈቃድ ለማግኘት ሙከራ አደረግሁ፤ ይህ ትልቅ አይነኬ ጉዳይ ነበር:: በዓለማዊ ደስታና በክርስትና እምነት መካከል ያለውን ልዩነት ትልቅ ባሕረ ሰላጤ በትዕግሥት አስረዳችኝ::

ያ አምልኮተ ያህዌንና አምልኮተ በአልን ለማጣመር የመጀመሪያ ሙከራዬ ነበር:: "የምንደንሰው 'በደም የጨቀየው መስቀል' በሚለው መዝሙር ቢሆንስ?" ብዬ ጠየቅሁ::

ያሳየችኝን ፊት በፍጹም አልረሳውም::

በቤተ ክርስቲያንና በዓለም መካከል ያለው ጠላትነት በሐዋርያው ዮሐንስ በዚህ መልኩ ተገልጧል::

> ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማናቸውንም ነገር አትውደዱ፤ ማንም ዓለምን ቢወድ፣ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤ ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ፦ የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም:: ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል:: (1ዮሐ. 2፥15-17 - አ.መ.ት)

ሐዋርያው ዮሐንስ *ዓለም* የሚለውን ቃል ሌሎቹ የአዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች በአንድነት ከተጠቀሙት በላይ ተጠቅሞታል፤ በወንጌሉ ውስጥ ሰባ ዘጠኝ ጊዜና በመጀመሪያ መልክእቱ ውስጥ ሃያ ሦስት ጊዜ:: ልንርቀው የተገባው ዓለም ተፈጥሮአዊው ዓለም፣ የተፈጠረው ሥርዐት፣ ቁሳዊው አጽናፈ ዓለም አይደለም:: የሕዝቦችን ዓለም፣ የሰውን ዘር፣ የወደቀውንና ጸጋ የሚያስፈልገውን ዓለምም አይደለም:: መሪቅ ያለብን ያለ እግዚአብሔር የተዋቀረውን ሥርዐት፣ ኢአማኒውን አረማዊ ማኅበረ ሰብ ሲሆን፣ ይህም ማኅበረ ሰብ ጸረ እግዚአብሔር የሆኑትን ተጽዕኖዎችና ኀይላት ዐቅፎ የያዘ ነው::

ዮሐንስ እንድንጠበቅ የሚያስጠነቅቀን ዓለም፣ "ተለይተው ሊታወቁ ከሚችሉ ውጫዊ ቁሶች የተሠራ አይደለም፤ ከሰዎችና በዙሪያችን ካሉ ነገሮች የሚመነጩ፣ ከእግዚአብሔር የሚያርቁን ተጽዕኖዎች ድምር ነው:: ሕይወትን ወደ ታች የሚጎትት ቀፋፊ ሞገድ ነው::"[4] ዓለም በክፉው ኀይል ሥር የተደራጀና እየሠራ ያለ የሰው ሥልጣኔ ነው::



## የክርስቶስ ጠላቶች ጥምረት

ቤተ ክርስቲያንና ዓለም ደመኛ ጠላቶች የመሆናቸው እውነታ ሌላ ሊጤን የሚገባው ገጽታም አለው፤ የክርስቶስ ጠላቶች ሁልጊዜም ይተባበራሉ::

ሄሮድስ ያዕቆብን መግደሉ አይሁድን እንዳስደሰታቸው ሲያይ ጴጥሮስንም ለመግደል እርምጃ ወሰደ:: የሄሮድስ ድርጊቶች በታላላቅ መርሖች ወይም በጥልቅ አቋሞች የተነሣሡ አልነበሩም፤ በአይሁዳውያን ዘንድ ተወዳጅነትን (ተቀባይነትን) ለማትረፍ በነበረው አሳዛኝ ምኞት እንጂ:: ሄሮድሶች በአይሁዳውያን ዘንድ ተወዳጅ አልነበሩም፤ ሄሮድሶች ዙፋኑን አላግባብ ነበር የያዙት፤ በደም ሥራቸው የሚዘዋወረውም ኤዶማዊ ደም ነበር:: የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ የነበረው ይህ ሄሮድስ አግሪጳ ግን የጴጥሮስን ግድያ ፋሲካ እስኪያልፍ እስከ ማዘግየት ድረስ የአይሁድን ሕግና በዓላት በሙሉ በማክበር አይሁዳውያንን አግባባቸው:: ሄሮድስና አይሁዳውያን ከቤተ ክርስቲያን በተቃራኒ ተባበሩ:: ያዕቆብ የተገደለው በሰይፍ ብቻ ሳይሆን በሕዝብ አስተያየትም ነበር::

በቀዳማዊ ሄሮድስ አግሪጳ ዘመን የተነሣው ስደት በሐዋርያት ላይ የደረሰ ሦስተኛ ዐቢይ ጥቃት ነበር:: የመጀመሪያው በሰዱቃውያን የተሰነዘረ ሲሆን፣ ሁለተኛው በፈሪሳውያን ነበር (የሐዋርያት ሥራ 4 እና 6):: ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን አይጥና ድመት ናቸው:: ሰዱቃውያን (ጻድቃቹ ይባላሉ) በሙታን ትንሣኤና ከሞት በኋላ ባለ ሕይወት አያምኑም፤ በሕግ መምህራን የሚቀርበውን የሕጉን ትርጓሜም አይቀበሉም::

ፈሪሳውያን (የተለዩ ይባላሉ) መንጻት፣ ዐሥራትና ጥብቅ የሆነ የሕግ አጠባበቅ ግድ የሚላቸው ሕግ አጥባቂዎች ናቸው:: ግና እነዚህ ሁለት ቡድኖች እንዳቸው በሌላኛቸው ተቃራኒነት የተሰለፉ ቢሆኑም፣ በክርስቶስ ተቃራኒነት ተባብረው ተሰልፈዋል (ማቴ. 16፥11፤ 22፥15-34):: በማቴዎስ 22፥34 ላይ፣ "ፈሪሳውያንም ሰዱቃውያንን ዝም እንዳሰኛቸው በሰሙ ጊዜ አብረው ተሰበሰቡ" የሚል እናነብባለን::

ኢየሱስ ለፍርድ በቀረበበት ጊዜ ጲላጦስ ኢየሱስ ከገሊላ መሆኑን ሲያውቅ የገሊላና ጴሪያ ገዥ ወደነበረውና ከገሊላ በመጣው ሰው ላይ ሥልጣን ወዳለው ወደ ሄሮድስ አንቲጳስ ላከው:: ሄሮድስም ከኢየሱስ ጋር ከተጫወተ በኋላ፣ አፌዘበትና በንቀት አስተናግዶት ወደ ጲላጦስ መልሶ ላከው:: ሉቃስ ስለ ሁነቱ ይህን የግርጌ ማስታወሻ አከሎበታል፤

> ሄሮድስና ጲላጦስም በዚያን ቀን እርስ በርሳቸው ወዳጆች
> ሆኑ፤ ቀድሞ በመካከላቸው ጥል ነበረና:: (ሉቃ. 23፥12)

ጲላጦስ፣ "ንጉሣችሁን ልሰቀለው?" በማለት የተሰበሰበውን ሕዝብ በጩኸት ሲጠይቅ፣ "ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም" በማለት በጩኸት መልሰውለታል (ዮሐ. 19፥15)::

የዘመናችን የዚህ አቻ የተለያዩ "ዝሞች" ስብስብ በክርስትና ተቃራኒነት መተባበራቸው ነው:: ዓለማዊነት ከሂዩማኒዝም ጋር ተባብሮ ዓለማዊ ሂዩማኒዝምን ሰጥቶናል:: ለቀቅተኝነት (ሊብራሊዝም) ከብዙኀዊነት (ፕሉራሊዝም) ጋር ተጣምሯል፤ ደስታ አሳዳጅነት (ሄዶኒዝም) ከሕልውና ዊነት (ኤግዚስቴንሺያሊዝም) ጋር ተቀይጧል፤ ከሀዲነት (ኤቲዝም) ከሁሉም ጋር ጥምረት ፈጥሯል:: ለአንዳንዶች እነዚህ ሁሉ ፍልስፍናዎች ከየዕለቱ ሕይወት ጋር አንዳች ግንኙነት የሌላቸው ረቂቅ ስያሜዎች ብቻ ናቸው:: በእርግጥም ከፖስታ ቤት ሠራተኛው ጋር ስለ ሕልውናዊነት ፍልስፍና ሐሳብ አልለዋወጥም፤ ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ብዙኀዊነትና ተዛምዶአዊነት (ሪሌቲቪ ዝም) ከሰው ጋር መቼ እንደተጨዋወትኩም ማስታወስ አልችልም::

ይህ ሁሉ ሲታይ፣ በዚህ ወቅት የዓለማችንን አመለካከት እየቀረጸ ያለ እያንዳንዱ ዐቢይ ሐሳብና ፍልስፍና ሁሉ የአዲስ ኪዳናዊው ክርስትና ተቃዋሚ ሲሆን፣ ከምድረ ገጽ ተጠርጎ እንዲጠፋለትም ያስባል ማለት ነው::

ቤተ ክርስቲያን ከምትገነዘበው በላይ እነዚህን ፍልስፍናዎች መጥጣቸዋለች፤ ስለዚህም አያሌ መልእክቷ በበግ ለምድ ውስጥ የተደበቀ ፍልስፍና *(ኢ-ዝም)* እየሆነ ነው::

የማኅበረ ሰባችን እውነተኛ ተስፋ፣ ቤተ ክርስቲያን የተለየች መሆኗን እንደገና መገንዘቧ፣ በአጸፋ ሰጪነት ፈንታ ራሷ የተግባር ጀማሪ መሆኗና ዓለም አጀንዳ ቀራጭ እንዲሆን መፍቀዷን ማቆሟ ነው:: ልዩ መሆናችንን ባጣንበት መጠን በዓለም ውስጥ ለክርስቶስ ያለንን ተጽዕኖ አጥተናል:: ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ ዓለምን በመሰለች፣ እንደ ዓለም በተናገረች ወይም እንደ ዓለም በተንቀሳቀሰች መጠን ዓለም ይበልጥ ዝቅ አድርጎ እየተመለከታት ይመጣል፤ ከአንድ ነገር በቀር ዓለም ቤተ ክርስቲያንን በሁሉም ነገር ሊበልጣት ይችላል - የክርስቶስን ሕይወት በመኖር ከመግለጥ በቀር:: የተለየን የሆንንበት ነገር ይህና ይህ ብቻ ሲሆን፣ ኀይላችንም (ብርታታችንም) ያለው በዚህና በዚህ ውስጥ ብቻ ነው::



**እውነታ 2፤ የክፉ ስኬት ከስኬት መሳይነት አያልፍም::**

ለብዙ ዓመታት አንድ ታዋቂ የዜና ዘጋቢ ዘገባውን የሚደመድመው፣ "እናም ሁኔታው ይህ ነው" በማለት ነበር:: ይበልጥ ተገቢ ይሆን የነበረው ዐረፍተ ነገር ግን፣ "እናም ሁኔታው ይህን *ይመስላል"* የሚለው ነበር::

"በአንድነት ማየት" የሚለው ወሳኝነት እዚህ ጋ ነው:: የያዕቆብን ሞት እንደ ነጠላ፣ ነጻና ከሌላው ጋር ያልተያያዘ ክስተት አድርጋችሁ ከተመለከታችሁት፣ "ክፉ እንደገና አሸነፈ:: አሁንም እንደገና እግዚአብሔር በዲያብሎስ ተበለጠ" ትላላችሁ:: ነገር ግን ሁሉን ነገር በአንድነት ስትሰ በስቡና በዚያ መንገድ ስትመለከቱት በተለየ መንገድ ታውቃላችሁ:: እግዚ አብሔር ጴጥሮስን ነጻ ማውጣት ከቻለ፣ ያዕቆብን ነጻ ማውጣት ይችል ነበር:: ስለዚህ እግዚአብሔር የተበለጠ ይመስላል እንጂ አልተበለጠም::

በእርግጥ ይህ ከእምነታችን ታላላቅ ፈተናዎች አንዱ ነው፤ ሁልጊዜ የምናልፈው ዐይነትም አይደለም:: "ልባቸው ከምኞታቸው በላይ ያገኘ" (መዝ. 73፥7) የክፉዎችን ብልጽግና ስንመለከት እንደ መዝሙረኛው፣ "በውኑ ልቤን በከንቱ አጸደቅሁ፤ እጆቼንም በንጽሕና በከንቱ አጠብሁ" (ቍጥር 13) ማለት ይዳዳናል:: ለዚህ አንድ መዳኛ ብቻ ነው ያለው፤

> ዐውቅም ዘንድ አሰብሁ፤
> ይህ ግን በፊቴ ችግር ነበረ::
> *ወደ እግዚአብሔር መቅደስ እስከገባ ድረስ*
> *ፍጻሜአቸውንም እስካስተውል ድረስ::*
> (ቍጥር 16 እና 17 - አጽንኦት የተጨመረ)

ለተጨነቀው ልባችን እግዚአብሔር የሚናገረውን ስሙ፤

> ዐመፀኞችን በማየት አትሸበር
> በክፉ አድራጊዎችም አትቅና፤
> እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉና፤
> እንደ ለምለም ቅጠልም ይጠወልጋሉ:: ...
> መንገዱ በተቃናለት፣
> ክፋትን በሚሸርብ ሰው ልብህ አይሸበር:: ...
> ክፉ ሰዎች ይጠፋሉና፤ ...
> ለአፍታ እንጂ፣ ክፉ ሰው አይዘልቅም፤
> ስፍራውንም ብታስስ አታገኘውም::
> ገሮች ግን ምድርን ይወርሳሉ፤
> በታላቅ ሰላምም ሐሤት ያደርጋሉ:: (መዝ. 37፥1-11 - አ.መ.ት)

ልክ ጠባቂዎቹ ጴጥሮስን ሲፈልጉ እንዳላገኙት ሁሉ፣ እኛም ከፉ ፈልገን የማናገኝበት ቀን እየመጣ ነው:: ጻድቃን ውጥረት ውስጥ ሲገቡ ይህን ማስታወስ ያስፈልጋቸዋል፤ የዐመፅ ስኬት፣ ስኬት መሳይ ብቻ ነው::

## እውነታ 3፤ የእግዚአብሔር እጅ፣ ባይታይም እየሠራ ነው::

ያለንበትን ሁኔታ ሁልጊዜ በትክክል ልንተረጕም አንችልም፤ ውጫዊ ሁኔታዎች የምናምንበትን እያንዳንዱን ነገር የሚጣረሱበት በርካታ ጊዜ አለ:: በሚታይ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ ሁኔታውን መገምገም የሚቻል አይደለም:: ፊልጶስ አምስት ሺዎቹን ሰዎች እንዴት መመገብ እንደሚችሉ ሲጠየቅ፣ ከደቀ መዛሙርቱ ምግቡን ራሳቸው የመግዛት ዕይታ አኳያ መልሷል:: ልክ እንደ እርሱ እኛም ወደ ሀብታችን ኪስ ገብተን እንፈትሽና ባዶአችንን እንወጣለን (ዮሐ. 6፥5-7)::[5]

ብዙ ጊዜ አምላካችን ዝምተኛና ስውር አምላክ ነው:: ስውር እጁን መስከሩ:: መልአኩ በወኅኒው ተከሰተ፤ ጠባቂዎቹ አላዩትም:: ጴጥሮስ የታሰረበትን ክፍል ብርሃን ሞላው፤ ጠባቂዎቹ አላዩትም:: መልአኩ ጎኑን መታ አድርጎ ቀሰቀሰው፤ ከእጁ የወለቁት ሰንሰለቶች ድንጋይ ላይ ሲወድቁ ያሰሙትን ድምፅ ጠባቂዎቹ አልሰሙም:: ጴጥሮስ ያጠለቀውን ሰንደል ጫማ ጠፍር እየጎተተ ከወኅኒው ወጥቶ ሄደ፤ ጠባቂዎቹ አልሰሙም:: ጠባቂዎቹ መሄዱን ያወቁት ጴጥሮስ ነጻ ከወጣ ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው::

ለነገሩማ፣ ጴጥሮስም ነጻ የወጣው እርሱ ራሱ ሳያውቀው ነው:: ወደ መንገድ ሲገባ ብቻ ነው "ወደ ልቡ ተመልሶ" ነጻ መውጣቱን ያወቀው::

## እውነታ 4፤ የማይታየው የእግዚአብሔር እጅ በጸሎት ይንቀሳቀሳል::

በጴጥሮስ መታሰር የቤተ ክርስቲያን ምላሽ በሐዋርያት ሥራ 12፥5 ታትቷል፤ "ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር *ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር::"* የሐዋርያት ሥራ ጸሓፊ በጴጥሮስ ነጻ መውጣትና በቤተ ክርስቲያን ጸሎት መካከል ጥብቅ ትይይዝ መኖሩን እንድናውቅ ፈልጓል::

የእግዚአብሔር እጅ በጸሎት *ይንቀሳቀሳል* በማለት ለመናገር አመነታለሁ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ሉዐላዊነት እየጣስኩ ያለሁ ዐይነት ይመስለኛል:: ግና በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ከተመለከትነው እውነታ አኳያ ግን ቃላቱ ትክክል እንደ ሆኑ አስባለሁ:: ጸሎት በእርግጥም የእግዚ አብሔርን እጅ ያንቀሳቅሳል::



ጸሎትን በትሕትና እንደምንቀበለው ትውፊታዊ ሥርዐት፣ ከምንም ነገር ጋር ተያያዥነት እንደሌለው አንድ ሃይማኖታዊ ተግባር በመከወን ፈንታ እንደ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ኀይል ማየት አለብን:: ቀዳሚዋ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስን ነጻ ለማውጣት በቂ ተጽዕኖና ክብር አልነበራትም፤ በጸሎት ነጻ የሚያወጡበት በቂ ኀይል ግን ነበራቸው:: እነርሱ እንኳ ምን ያህል ብርቱ እንደ ነበሩ አያውቁም ነበር፤ የጴጥሮስን በር ላይ ቆሞ ማንኳኳት አላመኑምና::

ቤተ ክርስቲያን ከምታውቀው በእጅጉ የሚበልጥ ኀይል አላት:: በዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ በጆን ዌስሊ አገልግሎት በእንግሊዝ የተነሣውን ዐይነት አገር አቀፍ የወንጌል መነቃቃት (awakening) ለማግኘት ዛሬ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ አስፈልጎት መኖሩ ብዙ ይነገራል፤ ብዙ ተጽፏልም:: ፈረንሳይን ከቦጫጨቃት ዐይነቱ ደም አፋሳሽ አብዮት እንግሊዝን የጠበቃት የጆን ዌስሊና *የወንጌል ሪቫይቫል* የተባለው አገልግሎቱ ተጽዕኖ እንደ ሆነ የታሪክ ባለሞያዎች ይናገራሉ::

ጄ ኤድዊን ኦር "ዝግጁ እግሮች" *(The Eager Feet)* በተባለው አስደናቂ መጽሐፉ በሚድላንድ ከተማ በሚገኘው መጥምቃውያን ማኅበር ስለተጀመረውና የነጻዩቱ ቤተ ክርስቲያን፣ የሜተዲስት፣ የአንግሊካን አባላትና ሌሎች ሸክም ያላቸው አማኞች ስለ ተቀላቀሉት የጸሎት ጥምረት ይነግረናል:: ይህም ጥምረት ለጠቅላላው አገር አቀፍ መነቃቃት ብቻ ሳይሆን፣ በዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻው ዐሥርት ውስጥ በየቦታው ለፈነዳው ልዩ ዐይነት የሚሲዮናዊነት ጥማትም መንገድ ጠርጓል:: ኦር ሲቀጥል እንዲህ ይላል፤

> ለአጠቃላይ አገር አቀፍ መነቃቃት ሲደረግ የነበረው የጸሎት ጥምረት ከፈረንሳዩ አብዮት በድፍን ሰባት ዓመት መቅደሙ ትልቅ ትርጕም አለው:: ቀድሞ የሚከሰተው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አማኞች ሊመጣ ያለውን አደጋ ከማወ ቃቸው በፊት የከፋውን ጥቃት በብዙ ሲቀድም ይገኛል::[6]

ጄ ዌስሊ ብሬዲ "እንግሊዝ ከዌስሊ በፊትና በኋላ" *(England Before and After Wesley)* በሚለው መጽሐፉ ወደዚህ ድምዳሜ ደርሷል፤

> አገር አቀፍ ወንጌላዊ መነቃቃት የተባለው አገልግሎት በመላው እንግሊዝኛ-ተናጋሪ ዓለም ነጻ ተቋማት እንዲፈጠሩም ሆነ ጸንቶው እንዲቆሙ ምክንያት የሆኑት የመልካም መንፈስና ጠባይ እሴቶች ሖጋቢ እናት ነው::

ብሬዲ፣ "የእንግሎ ሳክሰንን ታሪክ የግብረ ገብ አቅጣጫ የቀየረ" በማለት ይጠራዋል::[7]

በአብዛኛው የአገልግሎት ዘመኔ የሪቫይቫልና የአገር አቀፍ መነቃቃት ተማሪ ነበርኩ፤ እናም አንድን የማይለወጥ እውነታ በቋሚነት ስገነዘብ ነው የኖርኩት፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚነግረን ሰዎች በሞት ሽረት ትግል ከሚያደርጉት ጽኑና ድል ነሺ ጸሎት ያልጀመረ ሪቫይቫልና አስደናቂ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ኖሮ አያውቅም:: ሪቫይቫል ሰዎች አጀንዳ ስላኖሩለት በጭራሽ መጥቶ አያውቅም:: እግዚአብሔር በልባቸው ስላኖረው ነው የሚመጣው::

### ማስታወሻ

1. Harold Lindsell, *The New Paganism* (San Francisco: Harper and Row Publishers, 1987) x.
2. *Ibid.*, 110.
3. Lindsell, *O. Cit.*, 22.
4. George C. Findlay, *Fellowship in the Life Eternal* (Grand Rapids: Wm. B. Eerdmans Publishing Company, 1955) 199.
5. For a discussion of this aspect of faith see, *The Faith Crisis* by Ronald Dunn (Wheaton, IL: Tyndale House Publishers, 1984) 77-87. ተሻሽሎ የወጣው የዚህ መጽሐፍ ቅጂ *የእምነት ኀይል* በሚል ወደ አማርኛ ተመልሷል::
6. J. Edwin Orr, *The Eager Feet* (Chicago: Moody Press, 1975) 15.
7. J. Wesley Bready, *England: Before and After Wesley* (Seven Oaks: Hodder and Stoughton, 1939) 11, 14.



## ፳ - የሪቫይቫል "ምስጢር"

# ቤተ ክርስቲያን ስትጸልይ

በሃያኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያዎቹ ዓመታት እግዚአብሔር አስደናቂ አገር አቀፍ መንፈሳዊ መነቃቃት ወደ ዌልስ አመጣ፤ ይህ ምናልባትም ክፍለ ዘመኑ ካያቸው ሃይማኖታዊ ሪቫይቫሎች ሁሉ ታላቁ ነው:: በጥቂት ወራት ብቻ በርካቶች በተአምራዊ መንገድ ተለውጠው፣ አብያተ ክርስቲያናት መቆሚያ እስኪታጣ ድረስ እስከ አፍ ገደፋቸው መሙላት ጀመሩ፤ የየሰፈሩ ግብረ ገባዊ ጠባይም ተለወጠ:: የእንግዳና ያልተለመዱ ክስተቶች ዜና በዓለም ስለ ተሠራጨ፣ በርካቶች እግዚአብሔር ሲሠራ ለማየት ወደዚህች ትንሽ አገር ጎረፉ::

የሪቫይቫሉ ይፋዊ ያልሆነ መሪ የነበረው ኢቫን ሮበርትስ አንድ ምሽት ከአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል በአንዲቱ ተገኝና ከጉባዔው መካከል ለምስክርነት ሰዎችን ጠራ:: አንድ ሰው ተነሥቶ ከሌላ አገር የመጣ ወንጌላዊ መሆኑን ተናገረ:: "የዌልስን ሪቫይቫል ምስጢር ልቃርም ነው ወደዚህ የመጣሁት" አለ::

ወዲያውኑ፣ ሮበርትስ ጣቱን ወደ ሰውዬው ጠቆመና፣ "ምንም ምስጢር የለም! ጠይቁና ትቀበላላችሁ" በማለት ጮኸ::

ወንጌላዊው በዚህ መልስ ተቀይሞ ይሆን እያልኩ እገረማለሁ:: እኔ ብሆን እቀየም ነበር:: የሆነ ሆኖ፣ ጸሎት ምስጢር አይደለም:: በእርግጥ አዲስ ነገርም አይደለም:: እኔ በየቀኑ እጸልያለሁ፤ ቤተ ክርስቲያኔም በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት የጸሎት ጉባዔ አላት:: እንደዚያ ዐይነት ነገር ግን ተከስቶ አያውቅም:: ስለዚህ የሆነ ሌላ ነገር፣ መርሓ ግብር፣ ቀመር፣ የተለመደውን ነገር ልዩ አድርጎ የሚቀይር - ምስጢር መኖር አለበት:: የኢቫን ሮበርትስን ዐረፍተ ነገር የሪቫይቫሉ እውነተኛ ማብራሪያ አድርገን ማንኛችን መቀበል እንደምንችል እጠራጠራለሁ:: አዎን፣ በጸሎት አስፈላጊነት ላይ እንስማማና፣ "ከጸሎት ባሻገርስ ምን ታደርጋላችሁ?" በማለት ወዲያውኑ እናከልበታለን::

### “ምስጢሩ”

አዎን፤ ኢቫን ሮበርትስ ትክክል ነበር። ምስጢር የለም። “ጠይቁ ትቀበላላችሁ” ነው። ያላደረግነው ይህንን ነው። ለሪቫይቫል የየራሳችንን የዝግጅት ቀመሮች እናሰባስባለን፤ እነዚህን ሰው ሠራሽ ቅመማ ቅመሞች ቀላቅለን ለማጣፈጫ በላዩ ጸሎት ጠብ እናደርግበታለን። የሰማይን ደጆች የሚከፍትን እውነተኛ ጸሎት፣ ጳውሎስ በሮሜ 15፥30 የሚናገረውን “ተጋድሎ” - ስለዚህ ዐይነቱ ጸሎት የምናውቀው ጥቂት ነገር ነው ወይም ምንም አናውቅም።

ቤተ ክርስቲያን ወደ እንብርክኳ ብትመለስና የጸሎት ኀይሏን ደግማ ብታገኝ ምን ይከሰታል ብለን መጠበቅ እንችላለን? በሐዋርያት ሥራ 12 አንድ ምስል ዐይተናል፤ አሁን በሐዋርያት ሥራ 4 ላይ በምትገኘው የምትጸልይ ቤተ ክርስቲያን ላይ ትኩረት እናድርግ።

ሐዋርያት ከአይሁድ የካህናት ሸንጎ ጋር የመጀመሪያ መላተም፣ በአካል ጉዳተኛው ሰው ፈውስ ምክንያት የተከሰተ ከረር ያለ ግጭት ገጥሟቸዋል (የሐዋ. 3)። የበፊቱ ሽባ አሁን ቆሞ ሲራመድና እየዘለለ እግዚ አብሔርን ሲያመሰግን ሲያዩ ሕዝቡ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ዙሪያቸውን ከበባቸው፤ ጴጥሮስም ክርስቶስን ለመስበክ በመልካም አጋጣሚነት ተጠቀመ በት። ኢየሱስ በመስቀል እንደ ሞተ፣ ከሙታንም እንደ ተነሣና በእውነትም ጌታና ክርስቶስ እንደ ሆነ ነገራቸው። በሐዋርያት ሥራ 4 እንደምናየው ሰዱቃውያኑ ካህናት በጴጥሮስ ስለ ትንሣኤ ማውራት ተቈጥተው ጴጥሮስን ከዮሐንስ ጋር ያዙና ወኅኒ ጨመሯቸው።

በሚቀጥለው ቀን የካህናቱ ሸንጎ አባላት ተሰበሰቡና ጴጥሮስንና ዮሐንስን ካስፈራሯቸው በኋላ በኢየሱስ ስም እንዳይናገሩም ሆነ እንዳ ያስተምሩ አዘዟቸው፤ ከዚያም ከእስር ለቀቋቸው። ወዲያውኑ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ወደ ተሰበሰቡት አማኞች ተመለሱና ታሪኩን ተናገሩ። የሊጋዪቱ ቤተ ክርስቲያን አጸፋ ምን ነበር?

ከካህናቱ ሸንጎ ጋር ውይይት ለመጀመር ወይም የተደራጀ ተቃውሞ በሃይማኖታዊ መድረክ ላይ ለማቅረብ ሙከራ አደረጉ? አላደረጉም። ያ የአማኞች ለጋ ኅብረት የመጀመሪያው ተቃውሞ ሲደርስበት ለጸሎት ተንበረከከ።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ስትጸልይ ምን እንደ ተከሰተ በሐዋርያት ሥራ 4፥31 ተዘግቧል፤



> ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፤ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።

### የህልዎተ እግዚአብሔር መታየት

“የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ።” አገላለጡ የእግዚአብሔር ህልዎት ተምሳሌት ነው። ተመሳሳይ ሐረግ በሐዋርያት ሥራ 16፥26 ይገኛል። በፊልጵስዩስ ጳውሎስና ሲላስ ተደብድበው ወደ ወኅኒ ተጥለው ነበር፤ እግራቸውም በግንድ ተጠርቆ ነበር። በመንፈቀ ሌሊት ግን እነዚህ ሁለት ሚሲዮናውያን መጸለይና መዘመር ጀመሩ፤ እናም ...

> ድንገትም የወኅኒው መሠረት እስኪናወጥ ድረስ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ፤ በዚያም ጊዜም ደጆች ሁሉ ተከፈቱ፤ የሁሉም እስራት ተፈታ።

ይህ እግዚአብሔር በዚያ መገኘቱንና እየሠራ እንደ ሆነ የሚያውጅ የህልዎተ እግዚአብሔር መገለጥ ነው።

ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች በስሙ በሚሰበሰቡበት ጊዜ ሁሉ እግዚአ ብሔር ይገኝ የለምን? ይህ እውነት ነው፤ ሆኖም እኛ ሳናውቅም ሊገኝ ይችላል። ያዕቆብ ከምድር እስከ ሰማይ በተዘረጋ መሰላል ላይ በሚወጡና በሚወርዱ መላእክት የእግዚአብሔርን መገለጥ በቤቴል ካየ በኋላ እንዲህ አለ፤

> በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው፤ እኔ አላወቅሁም ነበር። (ዘፍ. 26፥16)

ይህ ለብዙ የእሁድ ማለዳ አምልኮ መዝሙሮች ጭብጥ መሆን ይችላል።

ሁልጊዜም ህልዎተ እግዚአብሔር አብሮን አለ። የሌለን ነገር የህልዎተ እግዚአብሔር ግንዛቤ ነው። ቫንስ ሀቭነር፣ ብዙውን ጊዜ እኛ ሰባኪዎች ጉባዔ ውስጥ ጥቂት ሰዎች ብቻ መቅረታቸውን ተመልክተን፣ “ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ” የሚለውን ጥቅስ ስንጠቅስ ከእግዚአብሔር ህልዎት ይልቅ የሰዎችን መቅረት ልብ ማለታችን እንደ ሆነ መናገር ያዘወትሩ ነበር።

ህልዎተ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ለእኛ እውነት አይደለም። አንዳንዴ እርሱ የሌለ ያህል ነው ስለ እርሱ የምንናገረው። በዚያ መንገድም እንጸልያለን። ጸሎቶችን ትሰማላችሁ? የግዛ ጸሎታችሁን ማለቴ ነው።

አንዳንዴ እግዚአብሔርን በሦስተኛ መደብ እናናግረዋለን፤ ወደ እግዚአብሔር የምንጸልይ ሳይሆን ጉባዔውን እንደምናናግር ዐይነት።

ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ራሷን ለጸሎት ስትሰጥ፣ ሀልዎተ እግዚ አብሔር ይታያል። እግዚአብሔር እየሠራ፣ እየተንቀሳቀሰ፣ ጥያቄ እየመለሰ በዚያ መኖሩን ድንገት እናውቃለን።

ይህ በቂ ነው። እግዚአብሔር በትዕይንቱ መኖሩን ማወቅ በቂ ነው። የካህናት ሸንጎው መደንፋትም ሆነ መቀባጠር ይችላል፤ ካህናቱ ማስፈራራትም ይችላሉ፤ ማውገዝም መብታቸው ነው። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፤ ይህ ደግሞ በቂ ነው። በማይታለፉ ፈተናዎች ፊት የሀልዎቱ ዋስትና በቂ ነው።

## ድባባዊ ሪቫይቫል

ይህ የሚታይ ሀልዎት - እግዚአብሔር በዚያ መኖሩ ለሕዝብ በሚታወቅበት ሁኔታ በሀልዎቱ የተሞላ ድባብ - ታላላቅ ሪቫይቫሎች ተለይ ተው የሚታወቁበት ጠባይ ነው። በዌልስ ሪቫይቫል ወቅት ወደ መንደሮቹ የሚገቡ ስለ አገር አቀፉ መነቃቃት የማያውቁ እንግዶች፣ በጥልቅ የኀጢአተ ኝነት ወቀሳ ወድቀው የሚጸልይላቸው አገልጋይ ይፈልጉ ነበር። ስለ ሪቫይቫሉ የማያውቁ ዓሣ አጥማጆችም ወደ ጠረፉ ሲጠጉ ስለ ኀጢአታቸው በአስፈሪ ወቀሳ ተውጠው፣ በጀልባው ላይ ያሉት ሁሉ እግራቸው መሬት ከመንካቱ በፊት በንስሓና በእምነት ይለወጡ ነበር።

ስለ ቻርልስ ፊኔ ሲነገር፣ በሪቫይቫል ጊዜአት በእግሩ በሚጓዝበት አካባቢ የሚያልፉ መንገደኞች በኀጢአተኝነታቸው ክብደት የተነሣ በጉል በታቸው መሬት ይወድቁ እንደ ነበር ይወሳል። ፊኔ በሚሄድበት በእያንዳንዱ ከተማ አባ ናሽ የሚባል ሰው አብሮት ይሄድ ነበር፤ እርሱም ለፊኔና ለሚኖሩት ጉባዔዎች ከፍል ዘግቶ ከመማለድ በቀር ሌላ ሥራ አልነበረውም።

እኔም ይህ "ድባባዊ ሪቫይቫል" ለጥቂት ጊዜ እንዲጋጠመኝ እመሰ ክራለሁ - ሀልዎተ እግዚአብሔር በእጅ መዳሰስ እስኪቻል ድረስ የከበደባቸው ጊዜአት ገጥመውኛል። መኪናቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ መኪና ማቆሚያ እያስገቡ ሳለ ድንገት በኀጢአተኝነት ወቀሳ ሥር የሚወድቁ ሰዎች፣ እስኪነጋ መቁየት አቅቷቸው ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመጠየቅ በእኩለ ሌሊት የሚደውሉ ሰዎች፣ ከሰው የወሰዱትን ንብረት የሚመልሱና ዕርቅ የሚፈልጉ ሰዎች - እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች "ድባባዊ ሪቫይቫሉ"ን አጅበዋል።



በ1950ዎቹ መጀመሪያ ይህ ዐይነቱ ሪቫይቫል በከተማችን ተከስቶ ነበር፤ በእናት ቤተ ክርስቲያኔና በመጋቢዋ አገልግሎት። ከተማ ውስጥ የትም ቦታ ስሄድ - የከተማ አውቶብስ ውስጥ፣ መናፈሻ መኻል፣ ትምህርት ቤት - ሰዎች ሲያወሩት እሰማለሁ። ሁሉም መልካም ወሬ አይደለም፤ ሆኖም ይወራል። እንዳያገኛችሁ ልታመልጡት አትችሉም። "ድባቡን" ለማምለጥ ቢያንስ 160 ኪሎ ሜትር መራቅ አለባችሁ ሲባል ነበር። ገና በዐሥራዎቹ ዕድሜዬ ሳለሁ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ውጪ ደረጃ ላይ ቆሜ ስጸልይና ኀጢአቴን ስናዘዝ አስታውሳለሁ። ከእግዚአብሔር ጋር ነገሬን ሳላስተካክል ወደ ውስጥ አልገባም ነበር።

እነዚህን ወይም ሌሎችን ምሳሌዎች ወስዶ እግዚአብሔር የሚገለጥባቸው "የተለመዱ" መገለጫዎች ማድረግ ስሕተት ይሆናል። በእግዚአብሔር ሀልዎት ሳይሆን በስብከት ጩኸትና በአምፕሊፋየር ማምባረቅ በሚንቀጠቀጡ አብያተ ክርስቲያናት ተገኝቼ ዐውቃለሁ። ሕንጻዎችን ማንቀ ጥቀጥ ጉዳያችን አይደለም፤ የእግዚአብሔር ሀልዎትን ምልክቶች ማስገኘትም ሥራችን አይደለም። እግዚአብሔር ሕንጻውን ሲያናውጠው እናንተ ማወጅ አያስፈልጋችሁም።

ባልተለመዱ ወቅቶች እግዚአብሔር ያልተለመዱ ነገሮችን ያደርጋል፤ ነገር ግን በተለመዱትም ውስጥ የዚያኑ ያህል ነው። ኢየሱስን ከመቃብር ያስነሣው አምላክ፣ በየማለዳው ፀሐይንም የሚያወጣው አምላክ ነው።

## የኅብረት ጸሎት

ሌላ ተጨማሪ ነገር፤ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ የሚጸልዩ አማኞች፣ "በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ" ይለናል (የሐዋ. 4፥24)። ይህ በተግባራቸውና በመነሻ ሐሳባቸው ቤተ ክርስቲያኒቱ የነበራትን አንድነት የሚናገር ልብ የሚነካ ዐረፍተ ነገር ነው። የጸለዩት ሐዋርያቱ ብቻ አልነበሩም። ሁሉም ጸልየዋል። ይህ ስብስብ በአንድ ሐሳብ ተነሣሥተው አንድ ነገር ለመፈጸም በአንድ ቦታ የተሰባሰቡ አማኞች ቡድን ነበር። ይህ የኅብረት ጸሎት ምስክር ነው።

በአንድ ሰው ጸሎት ውስጥ ኀይል ቢኖርም፣ በኅብረት ጸሎት ውስጥ ልዩ ነገር መኖሩን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤

> ደግሞ እላችኋለሁ፤ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። (ማቴ. 18፥19)

ቤተ ክርስቲያን በአንድ ልብ ነበረች፤ ዳዊትን ለማንገሥ በአንድነት እንደመጡት እስራኤላውያን::

> እነዚህ ሁሉ ዳዊትን በእስራኤል ሁሉ ላይ ያነግሡት ዘንድ አርበኞችና ሰልፈኞች እየሆኑ በፍጹም ልባቸው ወደ ኬብሮን መጡ፤ ደግሞም ከእስራኤል የቀሩት ሁሉ ዳዊትን ያነግሡት ዘንድ አንድ ልብ ነበሩ:: (ዜና 12፥38)

ይኸውም የእግዚአብሔር ሕዝብ ኢየሱስን ለማንገሥ በአንድ ልብ እንደ መምጣታቸው ያለ ስፍራን የሚያናውጥ ጸሎት ዐይነት ነው:: የተለያዩ ግላዊ ሸክሞቻችን ሁሉ ወደ ጎን ተደርገው ልባችን ወደ አንድ ዋና ጅረት የሚፈስሰው፣ ያ የእግዚአብሔር ህልዎት ሲገለጥና እግዚአብሔር ስፍራውን መረከቡን ሕዝብ ሲያውቅ ነው::

## የእግዚአብሔርን ኀይል ስንቀበል

"ከጸለዩም በኋላ ... በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው" (የሐዋ. 4፥31):: *ሁሉም ተሞሉ፤* ዘገባው እንደሚናገረው:: ሐዋርያቱ ብቻ ሳይሆኑ፣ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል መንፈስ ቅዱስን የመሞላት ተሞክሮ ኖረው:: በጰንጠቆስጤ ቀን አስደናቂ መሞላት ነበር፤ ነገር ግን በፊተኛው መሞላት ብቻ ቤተ ክርስቲያኒቱ መሮጥ አትችልም:: እያንዳንዱ አዲስ ተግባር አዲስ ሙላትን ይጠይቃል::

አጋጣሚው የሆነ አስገራሚ ነገር አለው:: የጸሎታቸው ውጤት የሁላቸውም መንፈስ ቅዱስ መሞላት ነው፤ ግና እስቲ ጸሎቱን መርምሩት:: መንፈስ ቅዱስ በጸሎቱ ውስጥ አልተጠቀሰም፤ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያቀረቡት ልመና አካል አልነበረም:: በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት አልጸለዩም፤ ነገር ግን ሲጸልዩ ነበር መንፈስ ቅዱስን የተሞሉት:: ሁለት ነገሮች ትልቅ ትርጒም አላቸው::

አንድ፤ ተሞክሮ እየፈለጉ አልነበረም:: ልመናቸው ራስ ወዳድነት የሚታይበት ወይም በግል ስሜት ላይ የተመሠረተ አልነበረም:: በ"መሞላት መንቀጥቀጥ"ን ፈላጊ አልነበሩም:: በአገልግሎቴ የአስደናቂ የአቅጣጫ ለውጥ ክስተት ምስክር ነኝ:: ከዚህ በፊት ክርስቲያኑ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንዲኖረው የሚፈልገው ኀይል ለማግኘት ነበር - ክርስቶስን ለማገልገልና ለእርሱ ለመኖር የሚሆን ኀይል:: አሁን ግን እንቅስቃሴአችን ሲታይ የመሞላቱ ዓላማ የመኖር ኀይል ሳይሆን በመኖር ውስጥ ደስታን የማግኘት ይመስላል:: የሁሉ ግብ ጥሩ ስሜት እንዲሰማውና አስገራሚ የፍንደቃ ተሞክሮ እንዲኖረው



ነው:: ብዙዎቻችን በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት ይልቅ በመንፈስ ቅዱስ ጥሩ ስሜት ማግኘት ላይ ይበልጥ ትኩረት እንሰጣለን ብዬ እፈራለሁ::

ሁለት፤ መንፈስ ቅዱስን ለመሞላት ከመጠየቅ ባሻገር ሌሎችም ነገሮች መኖራቸውን እነዚህ ሁለት ቍጥሮች ያሳያሉ:: የትኛውም ሰው በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ስለ መጠየቁ አዲስ ኪዳን አይነግረንም:: ሉቃስ 11፥13 ቀረብ ይላል፤

> እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?

ለመሞላት መጠየቅ የለብንም እያልኩ አይደለም:: መጠየቅ እንችላለን፤ ግድ ግን አይደለም::

የቀዳሚዋን ቤተ ክርስቲያን ጸሎት ከመረመርን መንፈስ ቅዱስ የመሞላት ውጤት የሚያስገኘውን የጸሎት ዐይነት እንደርስበት ይሆናል::

### 1. የእግዚአብሔርን ሉዐላዊነት ተገነዘቡ::

በሐዋርያት ሥራ 4፥24 እንዲህ እናነብባለን፤

> እነርሱም በሰሙ ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ፤ እንዲህም አሉ፣ "ጌታ ሆይ፤ አንተ ሰማዩንና ምድሩን ባሕሩንም በእነርሱም የሚኖረውን ሁሉ የፈጠርህ ..."

"ጌታ" ተብሎ እዚህ የተተረጐመው የግሪክ ቃል ልዩ ነው:: "ጌታ" ተብሎ ቍጥር 29 ላይ ከቀረበው ቃል ጋር አንድ አይደለም:: የቍጥር 24 ቃል፣ "ማን አለብኝ ባይ" የሚል ትርጒም ያለው እጅግ ጠንካራ ቃል ነው:: *ማን አለብኝ ባይ* የሚለው አገላለጽ ብዙውን ጊዜ አሉታዊ ስሜት አለው፤ እዚህ ጋ ግን የእግዚአብሔርን ከሃሌ ኩሉነት (ሁሉን ቻይነት)፣ ፍጹም በሆነና ያሻውን በማድረግ ሥልጣኑ ማስተዳደሩን ይጠቁማል::

የጀመሩት ከዚህ ነው - በጠላት ማስፈራራቶች ሳይሆን፣ በእግዚ አብሔር ፍጹም ሥልጣን:: የቤተ ክርስቲያን ድል ሁልጊዜም የሚጀምረው እግዚአብሔር ሉዐላዊ ጌታችን መሆኑን ከመገንዘብ ነው::

ሉዐላዊነቱም ሁሉን ነገር በመፍጠሩ ታይቷል:: እግዚአብሔር "ሰማዩንና ምድሩን ባሕሩንም በእነርሱም የሚኖረውን ሁሉ" መፍጠሩን ገለጹ:: ለምን? ምክንያቱም "በእነርሱም የሚኖረውን ሁሉ" ከተባሉት

ከአንዳንዶች ጋር ችግር ስለ ነበራቸው ነው:: የካህናቱ ሸንጎ አባላት ፍጡራን ሲሆኑ፣ የፈጠራቸው እግዚአብሔር ነው:: የዚህ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ከፍጥረት ባሻገር ፈጣሪን፣ ከሚታየው ባሻገር የማይታየውን ተመለከቱ:: ልጆች አንዳቸው በሌላኛቸው ላይ ከሚሰነዝሯቸው ተወዳጅ ማስፈራሪያዎች አንዱ፣ "እናገርብሃለሁ!" የሚል ነው:: እነዚህ ክርስቲያኖችም ያደረጉት ይህንኑ ነው፤ የካህናት ሸንጎውን ጥፋት ለእግዚአብሔር ተናገሩበት:: የተወሰነ የፍጥረት ክፍል እያስቸገራቸው ስለ ነበር ለፈጣሪው አቤቱታ አቀረቡ::

ሉዐላዊነቱ ሁሉን ነገር በመቈጣጠሩ ውስጥም ታይቷል:: ጸሎታቸውን እንደገና ተመልከቱት:: መዝሙር 2ን በመጥቀስ ጀመሩ፤

> "የምድር ነገሥታት ተሰለፉ፤ ገዦችም በአንድነት ተሰበሰቡ፤ በጌታ ላይ፣ በተቀባውም ላይ ተከማቹ::" በእርግጥም ሄሮድስና ጳንጥዮስ ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ... አንተ በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ ላይ በኢየሱስ ላይ ለማሤር ተሰበሰቡ:: (የሐዋ. 4፥26-27 - አ.መ.ት)

በክርስቶስ ላይ የተሰባሰቡትን ኀይላት ተመልከቱ፤ ነገሥታትና ገዢዎች (አለቆች)፣ ሄሮድስና ጲላጦስ፣ አሕዛብና እስራኤል:: ይህ ግን መጨረሻው አይደለም:: ይቀጥላሉ፤

> ይህም የሆነው የአንተ ክንድና ፈቃድ ጥንት የወሰኑት እንዲፈጸም ነው::

እነዚህ ስደት የተነሣባቸው አማኞች የሕይወታቸውን እስከፊ ጨለማ፣ በክርስቶስ መሞት ተስፋዎቻቸውና ሕልሞቻቸው የተፈረካከሱበትን ቀን መለስ ብለው ተመለከቱና *እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚቈጣጠር* ተገነዘቡ:: እናም በክርስቶስ መስቀል ላይ ይህ እውነት ከሆነ፣ በደቀ መዛሙርቱ መሰደድ ላይ ምንኛ እውነት ነው! ይህ የፍጹም ሉዐላዊነቱ አስደናቂ ማሳያ ነው::

## 2. ራሳቸውን በእግዚአብሔር አገልጋይነት ተመለከቱ::

በቍጥር 29 ላይ ራሳቸውን ባሪያ በማለት ጠሩ፤

> አሁንም ጌታ ሆይ፤ ዛቻቸውን ተመልከት፤ ባሪያዎችህም *ቃልህን በፍጹም ድፍረት መናገር እንዲችሉ* አድርጋቸው:: (አ.መ.ት - አጽንኦት የተጨመረ)

ይህ የመገዛት ጸሎት ነው:: ስለ ሁኔታዎቹ ስሞታ አላቀረቡም፤ ወይም በካህናት ሸንጎው ላይ እሳት እንዲወርድ ጥሪ አላደረጉም:: ይበልጥ



ምቹ ወደ ሆነ ቦታ እንዲወስዳቸውም እግዚአብሔርን አልለመኑም:: ገና ከመነሻው ችግር ውስጥ የከተታቸውን ነገር ይበልጥ ለመፈጸም ጠየቁ - በድፍረት መናገርን፤ "ሰዎቹም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ እንዲህ በድፍረት ሲናገሩ ባዩአቸው ጊዜ ..." (የሐዋ. 4፥13 - አ.መ.ት):: እግዚአብሔር ለፈቀዳቸው ሁኔታዎች ተገዙ::

እግዚአብሔር ለሰጣቸው ተልእኮም ተገዝተዋል:: በቍጥር 29 ላይ የሚገኘው ጸሎት በእግዚአብሔር የተጠሩበትን ሥራ፣ ይኸውም ቃሉን መናገርንና ኢየሱስን ማክበርን ለመቀጠል ድፍረት እንዲያገኙ የቀረበ ልመና ነው::

አሁን እናጠቃልለው:: አዲስ የእግዚአብሔር ኀይል አቅርቦት ባስገኘላቸው ጸሎት፣ (1) የእግዚአብሔርን ሉዐላዊ ጌትነት ተቀበሉ፣ እና (2) ለእርሱና ለቤዝዎታዊ ዕቅዱ ተገዙ:: የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት የሚቀበልና ለጌትነቱ የሚገዛ የትኛውም ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ የተሞላ ነው ብሎ መናገሩ እንደሚያስማማ አምናለሁ:: እነዚህ በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ቅድመ ሁኔታዎች በእርግጥም ግላዊ የሕይወት ንጽሕናን፣ በዘላቂነት ኀጢአትን በመናዘዝ መንጻትን ይፈልጋሉ::

መንፈስ ቅዱስ እርሱ የሚፈልገውን የሚፈልግ አማኝ ሲያገኝ "አብረው ይሆናሉ::" መንፈስ ቅዱስ ትኩረቱ አንድ ነገር ነው፤ ኢየሱስ በጌትነትና በአዳኝነት ይከብር ዘንድ:: ይህን ማድረግ የሚችልን የትኛውንም ክርስቲያን ለመሙላትም ዝግጁ ነው::

## የእግዚአብሔር ዕቅድ ግብ መምታት

የሐዋርያት ሥራ 4፥33 ትኩረት የሚሹ ሁለት ሐረጎችን ይዟል፤ "ታላቅ ኀይል" እና "ታላቅ ጸጋ":: ይህ የአማኞች ቡድን እግዚአብሔር የሚፈልገውን *ለማድረግ* ታላቅ ኀይል፣ እግዚአብሔር የሚፈልገውን *ለመሆን ታላቅ ጸጋ* ተሰጥቶታል፤ አማኞቹ የበለጸገ ሕይወት ያላቸው ኀያል ምስክሮች ናቸው::

## ኀያል ምስክሮች

"የእግዚአብሔርንም ቃል በድፍረት ተናገሩ" (ቍጥር 31 - አ.መ.ት):: ሰንሰለታዊ ሂደቱን ልብ በሉ፤ ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ስትሞላ የእግዚአብሔርን ቃል በድፍረት መናገሯ አይቀሬ ነው:: የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ከመመስከር ጋር ልናፋታው አንችልም:: መንፈስ ቅዱስ መሞላት፣ መንፈስ ቅዱስ ራሱን በእኛ በኩል እንዲገልጽ፣ ተልእኮውን በሕይወታችን

እንዲፈጽም መፍቀድ ነው:: ዓላማው የሚፈጸምባቸው መሣሪያዎች ለመሆን ፈቃደኛ እስካልሆንን ድረስ ርዳታውን መጠየቅ ጥቅም የለሽ ነው::

"ምስክር" የሚለውን ቃል ስጠቀም ስለ የትኛውም የምስክርነት ዘዴ ለይቼ እየተናገርኩ አይደለም:: መንፈስ ቅዱስን ከተሞላችሁ ጎዳና ላይ ቆማ ችሁ ትሰብካላችሁ ማለቴ አይደለም፤ ልትሰብኩም ላትሰብኩም ትችላላችሁ:: እንዴት፣ መቼና የት እንደምንመሰክር መናገር የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ነው፤ ለመንፈስ ቅዱስ ስንሸነፍ (ስንገዛ) ግን ሕይወታችን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ይመሰክራል::

የዚህን ምስክርነት አንዳንድ ገጽታዎች ነጥሎ ለመመልከት ጊዜ መስጠት ጥቅም አለው::

*ግዴታ::* ሐዋርያት በትልቅ ኀይል ምስክርነት "ሰጡ":: "ሰጡ" ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል መልሶ መስጠት፣ መመለስ ማለት ነው፤ ብድርን የመክፈል ወይም ግዴታን የማሟላት ሐሳብን ያስተላልፋል:: ክርስቶስን ለሌሎች ስናካፍል ለእግዚአብሔር ውለታ እያደረግንለት አይደለም:: ብድር እየከፈልን ነው:: ይህ መወጣት ያለብን ግዴታ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ሰውን ታማኝ ያደርጋል፤ ታማኝ ሰው ደግሞ ሁልጊዜም ብድሩን ይከፍላል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮማውያን ተመሳሳይ የግዴታ ስሜት እንደ ነበረው ገልጿል፤ "ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም፣ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ" (ሮሜ 1፥14)::

*ድፍረት::* የእግዚአብሔርን ቃል በ"ድፍረት"ም ተናግረዋል:: *ድፍረት* ከአዲስ ኪዳን ታላላቅ ቃላት መካከል አንዱ ነው:: እግዚአብሔር የአዲስ ኪዳን አማኞችን ሕይወትና አገልግሎት ጠባይ ለመግለጥ ይህንን ቃል ደጋግሞ ይጠቀማል:: ድፍረት አዲስ ኪዳን ውስጥ ባለው አጠቃቀሙ *የሦስት ትርጓሜዎችን ጥላ* አዝሏል፤

(1) *የመናገር ጉብዝና* ማለት ነው፤ በተለይ በከፍተኛ ባለሥልጣናት ፊት:: ወዲያውኑ የሚመጣልን የዚህ ምሳሌ የጴጥሮስ ከፈሪ የክርስቶስ ካጂነት ወደ ፍርሀት አልባ የጰንጠቆስጤ ቀን ሰባኪነት ለውጥ ነው:: ለሚጠፉት የመመስከር ትልቁ ችግራቸው ምን እንደ ሆነ በአገሪቱ የተለያዩ ስፍራዎች በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ያሉ ክርስቲያኖችን ጠይቄአለሁ:: ሁልጊዜም ሌሎቹን የሚያስከንዳው ምላሽ ፍርሀት ነው:: ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ የመናገር ድፍረት ይሰጠናል::



(2) *የንግግር ግልጽነት፣* የክርስቶስን መልእክት ጥርት ያለና ጉልህ የማድረግ ችሎታ ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስ ራሳችንን የመግለጥ፣ ምስክርነታችንን ሰዎች እንዲረዱት የማድረግ ችሎታ ሊሰጠን ይችላል::

(3) *በምንናገረው ነገር ልበ ሙሉ መሆን* ማለት ነው:: ይህም የምንናገረው ነገር በመንፈስ ቅዱስ ግቡን እንደሚመታ የልብ ማረጋገጫ ነው:: የሚታዩ ምልክቶችን ባናይ እንኳ ቃሎቻችን ልብን ሰንጥቀው እንደ ገቡና የወንጌሉ ዘር እንደ ተዘራ እናውቃለን::

ታዲያ ሐዋርያት በታላቅ ኀይል የሰጡት ምስክርነት ምንድን ነው? "የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኀይል ይመሰክሩ ነበር" (የሐዋ. 4፥33):: መልእክታችን ኢየሱስ ሕያውና ጌታ መሆኑ ነው:: ይህም ወደ ጀመርንበት መልሶ ያመጣናል:: ቦታው ሲናወጥና የእግዚአብሔር ሀልዎት ሲታይ የኢየሱስን ሕያውነትና ጌትነት ለሰዎች ማሳመን ከባድ አይደለም::

የፊልጵስዩሱ ወኅኒ ጠባቂ በወኅኒው ፍርስራሽ መካከል ቆሞ፣ በተሰበሩ ማጠፊያዎቻቸው ላይ የሚወዛወዙትን የወኅኒ በሮች ማየቱ፣ ጳውሎስና ሲላስ ሲዘምሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ መስማቱና እስረኞቹም በሙሉ እዚያው መሆናቸውን መመልከቱ አሳመነው፤ እናም፣ "እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?" በማለት ጮኸ (የሐዋ. 16፥25-30):: የእግዚአብሔርን ሀልዎት አይቷልና የእግዚአብሔር ሞቷል ወይም የእግዚ አብሔር የለም እንቅስቃሴ ተካፋይ የመሆን ተስፋ አልነበረውም::

የሚመለከቱት እምነታችንን የሚደግፍ ማስረጃ ጥቂት ከሆነ፣ ኢየሱስ ሕያውና እየገዛ መሆኑን ላለንበት ዐይነቱ ከሀዲ (ኢአማኒ) ዘመን ማሳመን ከባድ ነው:: ጴጥሮስ፣ ኢየሱስ ጌታና ክርስቶስ ሆኖ በአብ ቀኝ ለመቀመጡ በጰንጠቆስጤ ቀን የመንፈስ ቅዱስን መገለጥ በማረጋገጫነት አመለከተ (የሐዋ. 2፥33)::

## የበለጸገ ሕይወት

"በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው" (የሐዋ. 4፥33):: ይህን የተባበረ ማኅበረ ሰብ የሚገልጥ ከዚህ የተሻለ ልብ የሚነካ ማብራሪያ ማሰብ ትችላላችሁ?

በእርግጠኝነት የዚህ ታላቅ ጸጋ ከፊሉ "አንዲትም ልብ፣ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው" (ቍጥር 32) በሚል የተገለጸው የኅብረት ስምረት ነበር:: ብዙ አማኞች ቢሆኑም፣ ነገር ግን በአንድ ልብ የሚጠቀሙ፣ በአንድ አእምሮ የሚያስቡ፣ አንድ ነፍስ ያላቸው አንድ አካል ነበሩ:: የከተማው የመጨረሻ

አላዋቂ ኀጢአተኛ እንኳ ኅብረት የክርስትና ምልክት እንደ ሆነ ያውቃል:: ኢየሱስ አብ እንደ ላከው ለዓለም የሚያሳየው በትክክልም ይህ እንደ ሆነ ተናግሯል፤

> ይህም፣ አባት ሆይ፤ አንተ በእኔ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው:: (ዮሐ. 17፥21 - አ.መ.ት)

በቤተ ክርስቲያን ላይ የነበረው ታላቅ ጸጋ ሌላኛው ከፊል ደግሞ በእነዚህ ቃላት ተገልጿል፤

> ያላቸውም ሁሉ የጋራ ነበር እንጂ የራሱ የሆነውን ሀብት እንኳ እንደ ግሉ የሚቈጥር ማንም አልነበረም:: ... ከመካከላቸውም አንድ ችግረኛ አልነበረም፤ ምክንያቱም መሬትም ሆነ ቤት የነበራቸው ሁሉ እየሸጡ ዋጋውን አምጥተው፣ በሐዋርያት እግር ሥር በማስቀመጥ ለእያንዳንዱ በሚያስፈልገው መጠን ያካፍሉት ነበር:: (የሐዋ. 4፥32-35 - አ.መ.ት)

ለምትጸልይ ቤተ ክርስቲያን የሚሆንላት ይህ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ በአዲስ እሳቤ፣ በተለወጠ ዕይታ ያጠምቃታል:: አባላቱ ለእርስ በርሳቸው አዲስ የኀላፊነት ስሜት ይኖራቸዋል፤ ንብረታቸውም በቤተ ሰብ መካከል እንዳስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ እንዲውል በእግዚአብሔር በአደራ የተሰጣቸው እንደ ሆነ ማየት ይጀምራሉ:: በዚያች ቤተ ክርስቲያን ችግረኛ ሰው የሚባል ነገር እንዳልነበር ታውቃላችሁ? "በመካከላቸውም አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረም" (ቍጥር 34)::

ቡድንተኝነት፣ በማይረባው ነገር ሁሉ የሚነሣ የይገባኛል ሙግት፣ ትንንሽ ባላባትነትና ጠባብ ድንበርተኝነት በቅዱሱ መንፈስ ፍሰት ተጠርገው ተወገዱ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለእርስ በርሳቸው ለመንፈሳዊና ለማኅበራዊ አስፈልጎት ጥንቃቄ ስትወስድ እጆችና ልቦች ተባበሩ:: በእውነቱ ሁለቱ ደግሞ ሊነጣጠሉ አይችሉም፤ የአንደኛው ምስክርነት የሌላኛውን ምስክርነት ተአማኒ ያደርገዋልና:: ወደ አብ የሚያርገው ሁለትዮሽ ጭስ፣ ጣፋጭ ሽታ ካለው አንድ መሥዋዕት የተገኘ ነው::

*ይህ በአረማዊ ምድር የምትጸልይ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ ኪዳን ምስል ነው:: ቤተ ክርስቲያን ተንበርክኮ መኖርን መማር አለባት፤ ለሪቫይቫል ለመጸለይ በቅድሚያ የጸሎት ሪቫይቫል መኖር አለበትና::*



# ምስጋና

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ በድካሜ ስላገዝከኝና መጀመርን ብቻ ሳይሆን መጨረስንም ስላስቻልከኝ ከሁሉ አስቀድሜ አመሰግንሃለሁ::

መሐሪ ታደሰ መጽሐፉን ካመጣልኝ ብዙ ዓመታት ቢቈጠሩም፣ በቀለ ወ/ኪዳን (መጋቢ) የጀመርኩትን ሌላ መጽሐፍ ትቼ ፊቴን ወደዚህ መጽሐፍ እንድመልስ ምክንያት ሆኖኛልና እነርሱን እያመሰገንኩ አንተን አከብራለሁ::

እግዚአብሔር ሆይ፤ ትርጕሙን በቅድሚያ አንብበው የማስተካከያ ሐሳብ የሚሰጡ ሰዎችንም አዘጋጅተህልኛል:: ፍቅር ፈቀደ (እኅቴ)፣ ደረጀ በላይነህ (ወዳጄ) እና ሰፋኒት ታመነ (ሚስቴ) ይህን ክፍተቴን ሞልተዋል፤ ሥራቸውንና ኑሮአቸውን ባርክ::

የመጽሐፉን ግማሽ የተረጐምኩት ሳላገባ ነው፤ ቀሪውን ግማሽ ደግሞ ካገባሁ በኋላ:: እዚያም እዚህም ያሉት ቤተ ሰቦቼ ለሥራ የተመቻቸ ሁኔታ በመፍጠር አግዘውኛል:: በተለይ ሶፊ ሌሊት ለብቻዋ ትቻት ከመኝታ ቤት ስሾልክ ቅሬታ አቅርባ አታውቅም፤ ሲነጋ፣ "ጥሩ ሠራህ?" የሚል ጥያቄ ከማቅረብ በቀር:: ሲነጋም፣ "ሻይ ላፍላልህ?" እያለች መመላለሷ አይቀርም:: ጌታ ሆይ፤ ለሰጠኸኝ መልካም ቤተ ሰብ ምስጋናውን አንተው ውሰድ፤ ሚዛኑን መጠበቅ እንድችልም አስችለኝ::

አንባቢዎችም እዚህ ውስጥ የራሳቸው ድርሻ እንዳላቸው አልዘነጋም፤ እንደቀደሙት መጻሕፍት ሁሉ ይህንንም አንብበው እንደሚጠቀሙበት ተስፋ ማድረጌ ዐቅም ሆኖኛል:: አቤቱ፤ እነርሱንም አስባቸው::

እግዚአብሔር ሆይ፤ ለመንግሥትህ ክብር፣ ለቅዱሳን ደግሞ በረከት የሚያመጣ መጽሐፍ አድርገው:: በኢየሱስ ስም፤ አሜን!

## የተርጓሚው ሌሎች ሥራዎች

ያልተንኳኩ በሮች 168 ገጽ
የብርሃን አንጓዎች 264 ገጽ

*ዋችማን ኒ*

የዘላለም ኪዳን (The Better Covenant) 144 ገጽ
የተሸነፈ ዓለም (Love Not the World) 88 ገጽ
የጸጋው ብርታት (Changed Into His Likeness) 124 ገጽ
የዕረፍት ሕይወት (Sit, Walk, Stand) 56 ገጽ

*ሮናልድ ደን*

የእምነት ኀይል (Don't Just Sit There, Have Faith) 160 ገጽ
የወዳጅ ፍላጻ (Surviving Friendly Fire) 160 ገጽ
ሰማዩ ዝም ሲል (When Heaven is Silent) 176 ገጽ

*ዴሪክ ፐሪንስ*

የጋብቻ ኪዳን (The Marriage Covenant) 64 ገጽ

## ለውጥ የሚያመጣ ጸሎት

ለጓደኞቻችሁ ወይም ለቤተ ሰባችሁ አባል "እጸልይልሃለሁ" ወይም "እጸልይሻለሁ" በማለት ተናግራችሁ፣ ከዚያ ጸሎት በእርግጥ ለውጥ ስለ ማምጣቱ ተጠራጥራችሁ ታውቃላችሁ?

ወይስ

ለግል ችግራችሁ ብትጸልዩም፣ እግዚአብሔር እንዳልሰማችሁ ተሰምቷችሁ ያውቃል?



ሮናልድ ደን አማኞች በተሻለ ውጤታማነት እንዲጸልዩ የማስተማር ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው አስተማሪ ናቸው:: የጸሎት ኀይል ለራሳችሁም ሆነ ለሌሎች አስፈልጎት እንዴት በላቀ ዓላማ እና ኀይል መጸለይ እንደምትችሉ የሚያነሣሣ ምልከታ ቀርቦበታል:: ይህ ዐይን ከፋች መጽሐፍ፣

- በውጤታማነት መጸለይ የሚችሉት "ልዕለ ቅዱሳን" ብቻ ናቸው የሚለውን አፈ ታሪክ ያስወግዳል፤
- እግዚአብሔር ጸሎትን እንዴት እንደሚመልስ አዲስ ዕይታ ይሰጣል፤
- ከ"ልመናችን" ይልቅ "ይዞታችን" ለምን አስፈላጊ እንደ ሆነ ያስረዳል፤
- ለሚጸልዩ አማኞች እግዚአብሔር ያቀረበውን "ምስጢራዊ መሣሪያ" ይገልጣል፤

ጸሎት ነገሮችን - እና እኛንም ይለውጣል:: ወደዚህ አስደናቂ መጽሐፍ ስትገቡ፣ በጸሎት ሕይወታችሁ ላይ ለሚመጣው ሥር ነቀል ለውጥ ተዘጋጁ!

ዋጋ **38.00** ብር

ርኆቦት አታሚዎች